# በማየት ሳይሆን
# በእምነት ተመላለስ

ዕብራውያን

ዋረን ደብልዩ ዌርዝቢ

ጽሑፍ፡- በዋረን ዌርዝቢ

ትርጉም፡- በግርማዊ

እርማት፡-በቁምላቸው ፋንታሁን

BIBLE BASED BOOKS

SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

Copyright © 2001 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia. Originally published in English under the title of BE CONFIDENT. Copyright © 1982 by SP Publications, Inc. Chariot Victor Publishing, 4050 Lee Vance View, Colorado Springs, Colorado 80918 U.S.A. All rights reserved.

አሳታሚ፣ የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል

Publisher – SIM Publications Department

ስልክ – 493252 የፖ.ሣ.ቁ.

Tel – 71 11 73/ 51 29 73 P.O.Box } 127

አዲስ አበባ – ኢትዮጵያ

Addis Ababa - ETHIOPIA

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት በአብዛኛው ከአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የ1954 ዓ.ም እትም ሲሆን፥ ሌሎች እትሞችን ስንጠቀም ግን በቅንፍ ውስጥ (ለምሳሌ– ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም የተወሰዱትን «አ.መ.ት» በማለት) ለማመልከት ሞክረናል።

# ማውጫ


1. የሚሰማ ሰው አለ? (ዕብ. 1፥1–3) .................... 1
2. ከመላእክት በላይ (ዕብ. 1፥4–2፥18) .................... 13
3. ከሙሴ የሚበልጥ (ዕብ. 3፥1–4፥13) .................... 24
4. ኢየሱስ ከሊቀ ካህናቱ አሮን ይበልጣል (ዕብ. 4፥14–5፥10) .................... 35
5. መጻተኞች ወደፊት በመገስገስ ዕድገት ማሳየት አለባቸው (ዕብ. 5፥11–6፥20) .................... 45
6. ምሥጢራዊው መልከ ጼዴቅ (ዕብ. 7) .................... 57
7. የሚሻል ቃል ኪዳን (ዕብ. 8) .................... 67
8. የሚበልጥ ቤተ መቅደስ (ዕብ. 9) .................... 78
9. ከፍተኛ መሥዋዕት (ዕብ. 10) .................... 89
10. እምነት – በዓለም ታላቁ ኃይል (ዕብ. 11) ....................100
11. ሩጫህን ቀጥል! (ዕብ. 12) ....................112
12. እምነታችሁ ፍሬ እያሳየ ነው (ዕብ. 13) ....................123

# መግቢያ

የዕብራውያን መልእክት ዛሬ የሚያስፈልገን መጽሐፍ ነው።

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ጊዜያቱ ይጋጩ በነበረበት፥ በኅብረተሰቡም ውስጥ የነበረው ማንኛውም ነገር የሚናጋ በመሰለበት ወቅት ነበር። የተጻፈውም እየሆነ በነበረው ሁሉ እየተደነቁ ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ለሚያስቡ ክርስቲያኖች ነበር። ጽኑ ይመስል የነበረው አሮጌው የሕይወታቸው ዘይቤ ሲያልፍ፥ እምነታቸው እየተዳከመ ይዋልል ነበር።

ከዕብራውያን ዐበይት መልእክቶች አንዱ *በእምነት ተመላለስ* የሚል ነው። በማየት ሳይሆን በእምነት መኖርን እንማር ዘንድ እግዚአብሔር ነገሮችን እያናወጣቸው ነው። እርሱም በጊዜያዊው አለመረጋጋት ላይ ሳይሆን፥ በዘላለማዊው ዘላቂነት ላይ ሕይወትህን እንድትገነባ ይፈልጋል።

ይህ በዚህ አጭር ጥናት ውስጥ ላስተላልፍ የምሞክረው መልእክት ነው። መልእክቱ ግልጽ ሆኖ ይተላለፍ ዘንድ አንዳንድ እውነቶችን በአጭሩ ለመዳሰስና ሌሎችን ለመተው ተገድጃለሁ። እንዲህ ባለ መጽሐፍ ውስጥ ዕብራውያንን የሚያህል መልእክት በዝርዝር ማቅረብ አይቻልም።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባቀረብኋቸው አተረጓጎሞችና ድርጊታዊ መርሖዎች ሁሉ ላትስማማ ትችላለህ፥ ነገር ግን ክርስቲያን ከሆንህ በሰማይ ለዘላለም የሚኖረው ሊቀ ካህናችን በእነዚህ አስቸጋሪ ዘመናት ውስጥ ሊረዳን እንደሚችል ከሚያመለክተው አሳብ ጋር ትስማማለህ ብዬ አስባለሁ። «ጻድቅ በእምነት ይኖራል!»

ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አቅንተህ በመመልከት፥ በእምነት ተመላለስ!

ዋረን ደብልዩ. ዌርዝቢ

## 1

# የሚሰማ ሰው አለ?

### ዕብራውያን 1፡1–3

ሊድስ፥ እንግሊዝ ውስጥ የሚኖር አንድ ሰው፣ ጆሮውን ለመመርመር ወደ ሐኪም ዘንድ አመራ። ዶክተሩ ለሰውዬው የማድመጥ እገዛ ይሰጥ የነበረውን መሣሪያ ከጆሮው ሲያነሣለት የበሽተኛው የማድመጥ ችሎታ ወዲያውኑ ተሻሻለ! በሽተኛው ከ20 ዓመታት በላይ መሣሪያውን ባልታመመው ጆሮው ላይ አድርጎ ይኖር ነበር!

አንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ወዳጄን፥ «በቤተ ክርስቲያናችሁ መስማት ለተሳናቸው ሰዎች አገልግሎት ትሰጣላችሁ ወይ?» ስል ጠይቄው ነበር። እርሱም ሲመልስ፡– «መላው ምእመናን መስማት ለተሳናቸው ሰዎች የሚሰጠውን አገልግሎት የሚፈልጉባቸው ጊዜያት ያሉ ይመስለኛል። የምለውን የሚሰሙ አይመስለኝም» ብሏል።

መስማትና በትክክል ማዳመጥ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ብዙውን ጊዜ ክርስቶስ፡– «ጆሮ ያለው ይስማ!» እያለ ጮሆ ይናገር ነበር። ይህም የእግዚአብሔርን ድምፅ ለመስማት ከአካላዊ ጆሮ የበለጠ ነገር እንደሚያስፈልግ ያሳያል። በተጨማሪም፥ የሚቀበል ልብ ያስፈልጋል። «ዛሬ ድምፁን ስትሰሙ፥ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ» (ዕብ. 3፡7–8)።

ብዙ ሰዎች የዕብራውያንን መልእክት ችላ በማለታቸው ተግባራዊ የሆነ መንፈሳዊ እገዛ ሳያገኙ ቀርተዋል። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ መልእክቱን «ስለፈሩት» ይህንን መጽሐፍ ከመጠቀም ተቆጥበዋል። በዕብራውያን ውስጥ የሚገኙ «ማስጠንቀቂያዎች» ያስፈራሯቸዋል። ሌሎች ደግሞ አማካይ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ላለው ሰው «የማይቀመስ» በመሆኑ ዘለል ማለቱን መርጠዋል። በእርግጥ በዕብራውያን ውስጥ የሚገኙትን አንዳንድ ጥልቅ እውነቶችን ሙሉ በሙሉ አውቃለሁ የሚል አስተማሪ ወይም ሰባኪ ሊኖር አይችልም! ነገር ግን የመጽሐፉ አጠቃላይ መልእክት ግልጽ ስለሆነ፣ እኔና እናንተ ይህንኑ በማጥናት በረከቱን የማንቋደስበት ምክንያት አይኖርም።

ምናልባት ጥናታችንን ለመጀመር ከሁሉም የሚሻለው መንገድ የዕብራውያንን መልእክት አምስት ባሕርያት መግለጽ ይሆናል።

## 1. የዕብራውያን መልእክት የግምገማ መጽሐፍ ነው።

ጸሐፊው ኢየሱስ ክርስቶስና እርሱ ያስገኘልንን ደኅንነት፤ ከዕብራውያን የሃይማኖት ሥርዓት እንደሚልቅ ለማሳየት «መሻል» ና «መብለጥ» የሚሉትን ቃላት (እና እርባታዎቻቸውን) 13 ጊዜያት ጠቅሷል። ክርስቶስ ከመላእክት ይበልጣል (1፡4)። ክርስቶስ በተሻለ የተስፋ ቃል ላይ (8፡6) የተመሠረተው የሚሻል ቃል ኪዳን መካከለኛ ስለሆነ፥ «የሚሻል ተስፋ» አምጥቷል (7፡19)። ይላል።

ሌላው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተደጋጋሚ የተጠቀሰው ቃል «ፍጹም» የሚለው ነው። በመጀመሪያው የፅርዕ (የግሪክ) አዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ ቃል 14 ጊዜያት ተደጋግሞ ተጽፎአል። ፍችውም በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም የሆነ አቋም መያዝ ማለት ነው። ይህ ፍጹምነት በሌዋውያን ክህነት (7፡11)፥ በሕግ (7፡19)፥ በእንስሳት የደም መሥዋዕትነት፥ (10፡1) የሚገኝ፡አልነበረም። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን እንደ አንድ የኃጢአት መሥዋዕት ስላቀረበ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጓቸዋል--- » (10፡14)።

ስለሆነም፥ ጸሐፊው የብሉይ ኪዳኑን የሕግ ሥርዓት ከአዲስ ኪዳኑ የጸጋ ሥርዓት ጋር ያነጻጽራል። በዚህም የአይሁድ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ጊዜያዊ በመሆናቸው፤ በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኙትን ዘላለማዊ የተሻሉ ነገሮችን ሊያቀርቡ እንዳልቻሉ ያስረዳል።

ለዕብራውያን መልእክት ሦስተኛው አስፈላጊ ቃል «*ዘላለማዊ*» ነው። ክርስቶስ የዘላለማዊ ደኅንነት ደራሲ ነው (5፡9)። በሞቱ አማካኝነት ዘላለማዊ ቤዛነትን ያስገኘ ሲሆን (9፡12)፥ የዘላለምን ርስት ተስፋ ከአማኞች ጋር ይካፈላል (9፡15)። ዙፋኑ ዘላለማዊ ከመሆኑም በላይ (1፡8)፥ እርሱ ለዘላለም ካህን ነው (5፡6፤ 6፡20፤ 7፡17፥ 21)። «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፥ ዛሬም እስከ ዘላለምም ያው ነው» (13፡8)።

እነዚህን ሦስት ጠቃሚ ቃላት በምታጣምሩበት ጊዜ፥ ኢየሱስ ክርስቶስና እርሱ የሚሰጠን ክርስቲያናዊ ሕይወት ዘላለማዊና በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም አቋም ስለሚሰጡን ከሌሎች የሚልቁ መሆናቸውን ትገነዘባላችሁ። ስለዚህ የሙሴ ሕግ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ዘላለማዊውን ቤዛነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊያከናውነው አልቻለም ነበር።

ነገር ግን ጸሐፊው እምነታቸውንና ክርስቶስ ሊሰጣቸው የሚችለውን ነገር እንዲያመዛዝኑ የጠየቃቸው ለምንድን ነው? በፈታኝ ሁኔታዎች ተከብበው ወደ አይሁዳዊ እምነታቸው ለመመለስ በማመንታት ላይ

ስለነበሩ ነው። የዕብራውያን መጽሐፍ በተጻፈበት ወቅት ቤተ መቅደሱ ገና አልፈረሰም ነበር። ክህነታዊ ሥርዓቶችም በየዕለቱ ይካሄዱበት ነበር። ለእነዚህ አይሁዳውያን አማኞች፤ ቀደም ሲል ወደሚያውቁት የአይሁድ እምነት በመመለስ ከስደት መገላገሉ ምንኛ ቀላል ነበር።

እነዚህ «ሁለተኛ ትውልድ አማኞች» ሲሆኑ፤ ወደ እምነት የመሯቸው ክርስቶስ በምድር ላይ በሚያገለግልበት ጊዜ የሚያውቁት ክርስቲያኖች ነበሩ (2፡3)። እነርሱም የአፍ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ እውነተኛ አማኞች (3፡1) ነበሩ። በእምነታቸው ምክንያት ስደት ደርሶባቸዋል (10፡32–34፤ 12፡4፤ 13፡13–14)። እንዲሁም ደግሞ ችግረኞችን ረድተዋል (6፡10)። ነገር ግን ከሐሰት አስተማሪዎች ትምህርት የተነሣ (13፡9)፥ አሁን በሕይወት የሌሉት የመጀመሪያ መሪዎቻቸው የሰጧቸውን እውነተኛ ቃል የመዘንጋቱ አደጋ አንዣበባቸው ነበር (13፡7)።

ስለ እነዚህ አማኞች አሳዛኙ ነገር በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ዕድገት ባለማሳየታቸው ወደ ኋላ በመመለሱ አደጋ ውስጥ ነበሩ (5፡ከ12 ጀምሮ)። ከእነርሱ መካከል አንዳንዶቹ መደበኛ የአምልኮ ፕሮግራም ያቋረጡ ሲሆኑ (10፡25)፥ መንፈሳዊ ዕድገትም አይታይባቸውም ነበር (6፡1)። በክርስትና ሕይወት፥ ወደፊት ካልሄዳችሁ ወደኋላ መመለሳችሁ የግድ ነው። ለዘለቄታው ባሉበት መርገጥ አይቻልም።

ጸሐፊው፥ «እንዴት ወደ ቀድሞ ሃይማኖታችሁ ትመለሳላችሁ?» ሲል ይጠይቃቸዋል። «እስኪ በክርስቶስ ያላችሁን ነገር አስቡ። እርሱ በሕግ ከምታገኙት ሁሉ የተሻለ ነው።»

የዕብራውያን መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን (የእግዚአብሔር ልጅ) ማንነትና ተግባር አግዝፎ ያቀርባል። በእርሱና በእርሱ በኩል የምታገኙትን ስትገነዘቡ ስለ ሌላ ነገር ፍላጎት አይኖራችሁም!

## 2. የዕብራውያን መልእክት የምክር መጽሐፍ ነው

ጸሐፊው ይህንን መልእክት፡– «የምክር ቃል» ይለዋል (13፡22)። «ምክር» ተብሎ የተተረጎመው የዕርዕ ቃል «ማበረታቻ፥ ማጽናኛ» የሚል ጽንሰ–አሳብ አለው። በሮሜ 15፡4 እና በ2ኛ ቆሮንቶስ በተለያዩ ክፍሎች (1፡5–7፤ 7፡7) «ማጽናኛ» ተብሎ ተተርጉሟል። ይህም በዮሐንስ 14፡16 ስለ መንፈስ ቅዱስ «አጽናኝነት» ከቀረበው ቃል ጋር ተዛማጅ ነው። የዕብራውያን መልእክት የተጻፈው ሰዎችን ለማስፈራራት ሳይሆን፤ ለማጽናናት ነው። ይህ መልእክት በየቀኑ እርስ በርሳችን እንድንጽናና ያዘናል (ዕብ. 3፡13)። በኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅ መጽናኛ እንዳለን ያስገነዝበናል (6፡18)።

በዚህ ነጥብ ላይ፡- «በዕብራውያን መልእክት ውስጥ የሚገኙት እነዚያ ብርቱ ማስጠንቀቂያዎችስ?» የሚለውን የተለመደ ጥያቄ መመለሱ ተገቢ ነው። (አምስቱን ምክሮች ከአስተዋጽኦው ውስጥ ተመልከቱ።)

በመጀመሪያ ደረጃ፤ እነዚህ አምስት ምንባቦች «ማስጠንቀቂያዎች» አይደሉም። ሦስት መሠረታዊ ቃላት በአዲስ ኪዳን ውስጥ «ማስጠንቀቅ» ተብለው የተተረጎሙ ሲሆኑ፤ በዕብራውያን ውስጥ የሚገኘው አንዱ ብቻ በ8፡5 «መጠንቀቅ» ተብሎ ተተርጉሟል። (ይህ ሙሴን የሚመለከት ሲሆን፤ በሌሎች የእንግሊዝኛ ትርጉሞች «ምክር» ተብሏል።) በ12፡25 «መናገር» ተብሎ ተተርጉሟል። በ11፡7 ብቻ ኖኅን በማመልከት «ማስጠንቀቅ» ተብሎ ተተርጉሟል። (የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ግን «እግዚአብሔርን እየፈራ» ሲል ተርጉሞታል። ስለሆነም፥ የማስጠንቀቂያ ምንባቦች ለሚባሉት አምስቱ ክፍሎች ከሁሉም የሚበልጠው መግለጫ በዕብራውያን 13፡22 «ምክር» ወይም «ማበረታቻ» የሚለው ነው። ይህም የምንባቦቹን ጠንካራነት የሚቀንስ ሳይሆን፥ ዓላማቸውን እንድንገነዘብ የሚረዳን ነው። ዓላማቸውም በእግዚአብሔር እንድንታመንና ቃሉን እንድንጠብቅ ማበረታታት ነው።

የዕብራውያን መልእክት የሚጀምረው በአንድ ዓይነተኛ እወጃ ነው፤ ይህም «እግዚአብሔር--- በልጁ በኩል ተናግሮናል» የሚል ነው (1፡1-2)። ወደ መጽሐፉ መጨረሻ ጸሐፊው፡- «ለሚናገረው እምቢ እንዳትሉ ተጠንቀቁ» ሲል ይናገራል (12፡25)። በሌላ አገላለጽ፥ የዕብራውያውን መልእክት ጭብጥ፥ «እግዚአብሔር ተናግሮናል፤ ቃሉ እኛ ዘንድ አለ። ለቃሉ የምንሰጠው ምላሽ ምንድን ነው?» የሚል ነው።

ይህንን እውነት በአእምሯችን በመያዝ በዕብራውያን ውስጥ የሚገኙትን አምስት «አስቸጋሪ ምንባቦች» በተሻለ ሁኔታ ልንረዳ እንችላለን። እነዚህ ምንባቦች እያንዳንዳቸው የእግዚአብሔርን ቃል እንድንከተል («እግዚአብሔር ተናግሮናል. . .») ያበረታቱናል። ይህንንም የሚያደርጉት ቃሉን ባንከተል የሚደርስብንን አሳዛኝ ሁኔታ በማመልከት ነው። እስኪ እነዚህን ምንባቦች በመዘርዘር በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ያላቸውን ቅደም ተከተል ለማብራራት እሞክራለሁ። ሁሉም እንዴት አንድ ላይ እንደ ሰንሰለት ተያይዘው ለእግዚአብሔር ቃል ትኩረት እንድንሰጥ የሚጠይቅ አንድ መልእክት እንደሚያቀርቡ ትገነዘባላችሁ ብዬ አስባለሁ።

ከቃሉ መውደቅ - 2፡1-14 (ቸልተኝነት)

ቃሉን መጠራጠር – 3፡7–4፡13 (የልብ ድንዳኔ)

ድንዛዜ – 5፡11–6፡20 (መዘግየት)

ቃሉን መናቅ – 10፡26–39 (ሆን ተብሎ የሚደረግ ተግባር)

ቃሉን አለመታዘዝ – 12፡14–29 (ለመስማት አለመፈለግ)

የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል የማናዳምጥ ከሆነ፥ ከቃሉ መራቅ እንጀምራለን። ቸልተኝነት ከቃሉ ወደ መራቅ ይመራል። ከቃሉ እየራቅን ስንሄድ ቃሉን መጠራጠር እንጀምራለን። እምነት የሚመጣው የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት ነውና (ሮሜ 10፡17)። የልብ ድንዳኔ ያገኘንና እርሱም በበኩሉ ወደ መንፈሳዊ ዝግምተኛነት ይመራናል። በዚህም ጊዜ ለቃሉ የሚኖረን ስሜት ዝቅ ያለ ይሆናል። ቃሉን በትኩረት መስማት ተስኖን ሰነፍ አድማጮች እንሆናለን! በዚህም ጊዜ በፈቃዳችን እግዚአብሔርን ወደማንታዘዝበት የንቀት ደረጃ እንደርሳለን። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔርን ምንም ነገር የማንጠይቅበትን የርቀት አመለካከት እናዳብራለን።

ለመሆኑ፥ እንዲህ ዓይነት መንፈሳዊ የኋልዮሽ ጉዞ በሚካሄድበት ጊዜ እግዚአብሔር የሚወስደው እርምጃ ምንድን ነው? ወደ ቃሉ እንድንመለስ ማበረታታቱን ይቀጥላል። ለመስማትና ለመታዘዝ የማንፈልግ ከሆነ መቅጣት ይጀምራል። ይህ የቅጣት ሂደት የዕብራውያን መልእክት ከፍተኛው ደረጃ (ጡዘት) የሆነው የምዕራፍ 12 ጭብጥ ነው። ከምዕራፍ 10 እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚቀጣ እንማራለን (10፡30)። እግዚአብሔር ልጆቹ ሆን ብለው ቃሉን ባለመታዘዝ «ብሏሹዎች» እንዲሆኑበት አይፈልግም። ሁልጊዜም በፍቅር መቅጣቱን ይቀጥላል።

እነዚህ አምስት ምክሮች የተሰጡት ዳግም ለተወለዱ ክርስቲያኖች ነው። ዓላማቸውም ምዕመናን ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጡ ለማበረታታት ነው። ምንም እንኳ ከእነዚህ ምንባቦች በአንዳንዶቹ ውስጥ አንዳንድ ጠንከር ያሉ ቃላት ቢኖሩም፥ ከእነዚህ ምክሮች የትኞቹም አማኞቹ ደኅንነታቸውን ሊያጡ እንደሚችሉ በመግለጽ የሚዝቱባቸው አይመስለኝም። ይህ የእኔ ግንዛቤ ነው። («እንዴትስ ይልቅ ለመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛና በሕይወት ልንኖር በተገባን? 12፡9»)። ድምዳሚው ለእግዚአብሔር ካልታዘዝን ልንሞት እንችላለን የሚል ነው። «ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ» (1ኛ ዮሐ. 5፡16)። ነገር ግን የዕብራውያን መልእክት ከማንኛውም ነገር በላይ አጉልቶ የሚሳየው ሊሞት በማይችል ሕያው ሊቀ ካህን አማካኝነት ስለሚገኘው የዘላለም ሕይወት ነው (ዕብ. 7፡22–28)።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ደኅንነትን የማጣት ወይም የክህደት ችግርን ለመግለጽ ሲሉ የዕብራውያን ጸሐፊ አንባቢያን ክርስቲያኖች ነን ይበሉ እንጂ፣ ዳግም የተወለዱ ሰዎች አልነበሩም ይሉናል። ነገር ግን ደራሲው ስለ እነዚህ ሰዎች የሚናገረው አሳብ ይህንን አመለካከት ያፋልሳል። «ከሰማያዊ ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ» ሲል ይጠራቸዋልና (3፡1)። በሰማይ ሊቀ ካህን እንዳላቸው ነግሯቸዋል (4፡14)። ይህንንም ያልዳኑ ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ አይጽፍላቸውም ነበር። በተጨማሪም፥ ከመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች ሆነዋል (6፡4)። ለማያምኑ ሰዎች የቀረበ ቢሆን ኖሮ የ10፡19–25 ተግሣጽ እርባና አይኖረውም ነበር።

የዕብራውያን መጽሐፍ የሙሴ ሕግ ሊሰጥ ከሚችለው በላይ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚሻል የሚያረጋግጥ የግምገማ መልእክት ነው። በተጨማሪም፥ የዕብራውያን መልእክት የምክር መጽሐፍ ነው። በመሆኑም አንባቢያን መንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዳያሽቆለቁልና የእግዚአብሔር ቅጣት እንዳይደርስባቸው የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙና እንዲያስተውሉ አበክሮ ይመክራቸዋል።

## 3. ዕብራውያን የምርመራ መጽሐፍ ነው

ይህንን መጽሐፍ በምታጠኑበት ጊዜ፥ «የምናምነው የእግዚአብሔርን ቃል ነው ወይስ ሊወድቁ የደረሱትን የዚህች ዓለም ነገሮች?» ስትሉ ራሳችሁን ትጠይቃላችሁ።

ይህ መልእክት የተጻፈው፣ በታሪክ ውስጥ ወሳኝ በሆነ ወቅት ለነበሩት ክርስቲያኖች ነበር። ቤተ መቅደሱ ቆሞ እንስሳት አሁንም ለመሥዋዕትነት በመቅረብ ላይ ነበሩ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ግን ከተማይቱም ቤተ መቅደሱም ይፈርሳሉ። አይሁዶችም ወደ ሌሎች አገሮች የሚበተኑ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል የአይሁድ ክርስቲያኖች ይገኙባቸው ነበር። ዘመኑ እየፈረሰ ነበር፣ እግዚአብሔርም የነገሮችን ሥርዓት እያናወጠ ነበር (12፡25–29)። ስለሆነም፥ ሕዝቡ የሚጠፉትን ነገሮች ከማመን ይልቅ በጠንካራ የእምነት መሠረት ላይ እንዲቆሙ ሊያሳስባቸው ፈለገ።

ዛሬ ያለችውም ቤተ ክርስቲያን በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ መሆንዋን አምናለሁ። በዙሪያችን ያለው ነገር ሁሉ በመፈራረስና በመለዋወጥ ላይ ይገኛል። ሰዎች በሕንጻው መሠረት ላይ ሳይሆን የሕንጻው ሠራተኞች በሚቆሙበት መወጣጫ (ስቸ ፍፍዠልድ ንግ) ላይ ሲደገፉ መኖራቸውን እየተገነዘቡ ናቸው። የእግዚአብሔርም ሰዎች ሳይቀር በዚህ ዓለም ሥርዓት ስለተያዙ የሚተማመኑት በእግዚአብሔር ሳይሆን እንደ ገንዘብ፥ ሕንጻዎችና ፕሮግራሞችን በመሳሰሉት አላፊ

ነገሮች ላይ ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን «ማራወጡን» ሲቀጥል እውነተኛ ያልሆኑ ድጋፎች ሁሉ ይወድቃሉ። በዚህም ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ ብቸኛው መተማመኛቸው የእግዚአብሔር ቃል መሆን እንዳለበት ይገነዘባሉ።

እግዚአብሔር ልባችን «በጸጋ እንዲጸና» ይሻል (13፡9)። «መጽናት» የሚለው ቃል በተለያዩ መልኮች በዕብራውያን ውስጥ 8 ጊዜያት ተጠቅሷል። ፍችውም፥ «ጸንቶ መቆም፥ አለመናወጥ» ማለት ነው። ይህ ቃል ከሚያስተላልፋቸው አሳቦች መካከል፤ ጥንካሬ፥ አስተማማኝነት፥ ማረጋገጫና ዘለቄታ የሚሉ ይገኙባቸዋል። ይህ የዕብራውያን መጽሐፍ ቁልፍ መልእክት ይመስለኛል። «በዙሪያህ ያለው ነገር ሁሉ እየፈራረሰ አንተ ግን በአስተማማኝ ሁኔታ ልትኖር ትችላለህ!» «የማይናወጥን መንግሥት ስለምንቀበል. . .» (12፡28)። የእግዚአብሔር ቃል ጽኑ ሲሆን (2፡2)፥ በእርሱ ያለን ተስፋም እንዲሁ ነው (6፡19)።

በእርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት እንደሚያድን ተቀብሎ የግል አዳኙ አድርጎ ላላመነበት ሰው ደኅንነት የለውም። በአፋቸው እናምናለን እያሉ በአኗኗራቸው እውነተኛውን ደኅንነት የማይገልጹ ሰዎችም ቢሆኑ ደኅንነት የላቸውም (ቲቶ 1፡16፤ ማቴ. 7፡21-27)። ክርስቶስ ለዘላለም የሚያድነው በእርሱ አምነው ወደ እግዚአብሔር የቀረቡትን ብቻ ነው (ዕብ. 7፡25)።

ብዙውን ጊዜ ለምእመናን የምነግራቸው የአንድ ትኬት ሻጭ ታሪክ አለ። ትኬት ሻጩ ወደ አንድ ባቡር ውስጥ ገብቶ የተሳፋሪውን ትኬት ከተመለከተ በኋላ፥ «ጌታዬ፥ የተሳሳተ ባቡር ውስጥ ነው የገቡት» ሲል መለሰለት። የሁለተኛውንም ተሳፋሪ ትኬት ተመልክቶ ተመሳሳይ ነገር ነገረው።

ተሳፋሪውም፥ «ረዳቱ እዚህ ግባ ብሎኛል» ሲል መለሰለት።

«እስኪ እንደገና ላረጋግጥ» ሲል ትኬት ሻጩ ተናገረ። በዚህም ጊዜ እርሱ ራሱ የተሳሳተ ባቡር ውስጥ መግባቱን ተገነዘበ!

በተመሳሳይ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ያልሰሙና የውሸት እምነት ያላቸው ብዙ ሰዎች ይኖራሉ ብዬ እፈራለሁ። አንዳንድ ጊዜ ሌሎች ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው በመናገር ስለሚባክኑ የራሳቸውን ሁኔታ መመርመር ይሳናቸዋል። የዕብራውያን መልእክት የምርመራ መጽሐፍ ነው፤ እምነታችሁ በትክክል የት እንዳለ እንድትመረምሩ ይረዳችኋል።

## 4. ዕብራውያን የተስፋ መጽሐፍ ነው

ይህ መጽሐፍ የሚያተኩረው በወደፊት ላይ ነው። ጸሐፊው ስለ መጭው እየተናገረ መሆኑን ያስገነዝበናል (2፡5)። ይህም አማኞች ከክርስቶስ ጋር የሚነግሡበት ጊዜ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሁሉም ነገሮች ወራሽ ሲሆን (1፡2)፥ እኛም የዘላለማዊ ውርስ ተስፋ ተካፋዮች ነን (9፡15)። በዕብራውያን 11 እንደተዘረዘሩት የእምነት አባቶች፣ እኛም የወደፊቷን የእግዚአብሔርን ከተማ ለመውረስ እንናፍቃለን (11፡10–16፥ 26)

እንደ እነዚህ ታላላቅ የእምነት ሰዎች፥ ሁሉ እኛም በምድር ላይ እንግዶችና መጻተኞች ልንሆን ይገባል (11፡13)። ለዚህም ነው እግዚአብሔር በዙሪያችን ሁሉንም ነገር እያናወጠ ያለው። እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ነገሮች ላይ መደገፋችንን እንድናቆምና፣ በመጭው ላይ ሕይወታችንን እንድንመሠርት ይፈልጋል። ይህ ማለት ግን ከሚገባው በላይ ስለ መንግሥተ ሰማይ እያሰብን ምድራዊውን ነገር ጭራሽ ችላ ማለት አለብን ማለት ሳይሆን፥ ትኩረታችንን ከዚህ ዓለም ላይ አንሥተን በዘላለማዊ እሴቶች ላይ ማድረግ አለብን ማለት ነው።

አብርሃምና የወንድሙ ልጅ የነበረው ሎጥ እነዚህን ሁለት አመለካከቶች ደህና አድርገው ያብራሩልናል (ዘፍጥ. 13–14)። አብርሃም በመረጠው ስፍራ ምቹ ቤት ሠርቶ ሊቀመጥ የሚችል ባለጸጋ ሰው ነበር። ነገር ግን አብርሃም የእግዚአብሔር ባሪያ ነበር። ይህም እንደ እንግዳና መጻተኛ በድንኳን ውስጥ መኖር እንደሚገባው የሚያመለክት ነበር። ሎጥ ግን የምነናውን ሕይወት ትቶ ክፉ ወደ ሆነች የሰዶም ከተማ አቀና። ከእነዚህ ሁለት ሰዎች ይበልጥ እውነተኛ አስተማማኝ ሕይወት የነበረው ማን ነበር? ላይ ላዩን ሲታይ በከተማ ውስጥ ይኖር የነበረው ሎጥ ድንኳን ተክሎ ከሚኖረው ከአብርሃም የተሻለ አስተማማኝ ሕይወት የነበረው ሊመስል ይችላል። ዳሩ ግን ብዙም ሳይቆይ ሎጥ የጦር ምርኮኛ ሆነ! ከዚያም አብርሃም ከምርኮኝነት አስጥሎታል።

የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ አልሰማ ብሎ ሎጥ ወደ ከተማይቱ ተመለሰ። በዚህም ጊዜ እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ሲያወድም ንብረቱን ሁሉ አጥቶ ባዶ እጁን ቀረ (ዘፍጥ. 19)። ሎጥ የዳነ ሰው ቢሆንም (2ኛ ጴጥ. 2፡7)፥ ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ በዚህች ዓለም ነገሮች ተማመነ። ሎጥ ለጊዜያዊው ነገር ስለኖረ ዘላለማዊውን ነገር ጥሎታል። ሰማዕቱ የወንጌል መልእክተኛ ጂም ኤሊየት ይህንን አሳብ

ጥሩ አድርጎ ገልጾታል፡- «የራሱ አድርጎ ሊያቆየው የማይችለውን የሚሰጥና ሊያጣው የማይችለውን ለማግኘት የሚሻ አስተዋይ ነው።»

እኔና እናንተ እንደ እግዚአብሔር ልጆች ወደፊት ሽልማት እንደምናገኝ ተስፋ ተሰጥቶናል። እንደ ቀድሞዎቹ አብርሃምና ሙሴ ዛሬ የምናሳልፋቸው ውሳኔዎች የነገዎቹ ሽልማቶች ወሳኞች ናቸው። ስለዚህም ውሳኔዎቻችን ሽልማቶችን በማግኘቱ አሳብ ሊነሣሡ ይገባል። አብርሃም የምትመጣውን ከተማ በተስፋ ይጠብቅ ስለነበር (ዕብ. 11፡10)፥ እግዚአብሔርን ታዘዘ። ሙሴ ብድራቱን ለመቀበል በተስፋ ስለተመለከተ (11፡26)፥ የግብጽን ደስታና ምቾት ለመተው ቻለ። እነዚህ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች የወደፊቱን ተስፋ እየተመለከቱ በመኖራቸው (11፡31፥ 35)፥ የዓለምንና የሥጋን ፈተናዎች ሊቋቋሙ ችለዋል።

ይኸው ተመሳሳይ የእምነት ነገር ነበር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንዲሞት ያደረገው። «እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ. . .» ይላል (12፡2)። የዕብራውያን መልእክት የሚያተኩረው፥ «ዛሬ ዓለም ተስፋ በምትሰጥህ ነገር ላይ ተመሥርተህ አትኑር! በዚህች ምድር ላይ እንግዳና መጻተኛ ሁን! በማየት ሳይሆን በእምነት ተመላለስ!» በሚሉ አሳቦች ላይ ነው።

ይህ መልክእት ጠንካራ ምግብ ሊቀበሉ ለማይችሉና ገና ብዙ እንክብካቤ ለሚፈልጉ «መንፈሳዊ ሕጻናት» የቀረበ አይደለም (5፡11–14)። በዚህ መልእክት ውስጥ «ጠንካራ አጥንት» ስለሚገኝ ይህንኑ ለመቆርጠምና ለመመመገብ «ጠንካራ ጥርሶች» ያስፈልጉናል። የዕብራውያን መልእክት የሚያተኩረው ክርስቶስ በምድር ላይ ባከናወነው ተግባር ላይ ሳይሆን (ወተት)፥ በሰማይ እያደረገ ባለው (የቃሉ አጥንት) ላይ ነው። እርሱ ጸጋውን በመስጠት የሚያበረታታን ታላቅ ሊቀ ካህናችን ነው (4፡14–16)። እንዲሁም ደግሞ ፈቃዱን እንድንፈጽም የሚያደርገን ታላቅ የበጎች እረኛ ነው (13፡20–21)። እርሱ ዓላማውን ለመፈጸም በውስጣችን በመሥራት ላይ ነው። የዚህ ታላቅ አገልግሎት አካል መሆን ምንኛ ታላቅ ነገር ነው!

ዶክተር ኤ. ደብልዩ. ቶዘር፥ «እያንዳንዱ ሰው የራሱን ዓለም መምረጥ አለበት» ይሉ ነበር። እውነተኛ አማኞች መልካሙን የእግዚአብሔርን ቃልና የመጭውን ዓለም ኃይል (6፡5) ቀምሰዋል። ይህም በኃጢአት ለተበከለው የአሁኑ ዓለም ሥርዓት ፍላጎት (አፐታይት) እንዳይኖረን ሊያደርግ ይገባል። አብርሃም ትክክለኛውን ዓለምን በመምረጥ የታማኞች አባት ሊሆን ችሏል። ሎጥ ትክክለኛ ያልሆነ ዓለም በመምረጥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች አባት ሆኗል

(ዘፍጥ. 19፡30–38)። አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ሲሆን (2ኛ ዜና 20፡7)፥ ሎጥ ግን የዓለም ወዳጅ ሆኗል። በዚህም ሎጥ ሁሉንም ነገር አጥቷል። የሎጥ ደኅንነት በእሳት እንደ መዳን ስለነበረ (1ኛ ቆሮ. 3፡15)፥ በዚህም ሽልማቱን አጥቷል።

## 5. ዕብራውያን የመክበር መጽሐፍ ነው

የዕብራውያን መልእክት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነትና ተግባር አግዝፎ ያቀርባል። በመጽሐፉ ውስጥ ከዳር እስከ ዳር የተጻፈው ይኸው ዐቢይ እውነት በመጀመሪያዎቹ ሦስት ቁጥሮች ተገልጾአል። የእነዚህ ሦስት ቁጥሮች የቅርብ ዓላማ ክርስቶስ ከነቢያት እንደሚበልጥ ማረጋገጥ ነው። ነቢያት አይሁዶች እጅግ ያከብሩዋቸው የነበሩ አገልጋዮች መሆናቸው ይታወቃል።

ክርስቶስ በማንነቱ ከነቢያት በላይ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ እንዲሁ በእግዚአብሔር የተጠራ አገልጋይ ብቻ ሳይሆን፤ የእግዚአብሔርም ልጅ ነበር። የዕብራውያን ደራሲ ስለ ክርስቶስ ያቀረበው ገለጻ ከአምላክ በቀር ለሟች ሰዎች ሊያገለግል የሚችል ባለመሆኑ (ዕብ. 1፡3)፥ በዚህ መልእክት ውስጥ የክርስቶስን አምላክነት በግልጽ እንዳመለከተ መገንዘብ ይቻላል። «የክብሩ መንጸባረቅ» በመገናኛው ድንኳንና በቤተ መቅደስ ውስጥ የነበረውን የእግዚአብሔርን «የሽክና» ክብር ያመለክታል። (ዘጸ. 40፡34–38 እና 1ኛ ነገሥት 8፡10ን ተመልከት።) («ሽክና» «ማደር» የሚል ትርጉም ያለው የዕብራይስጥ ቃል ነው።) የክርስቶስና የእግዚአብሔር አብ ግንኙነት የፀሐይና የፀሐይ ጨረር ግንኙነት ዓይነት ነው። ክርስቶስ የእግዚአብሔር የክብሩ ነጸብራቅ ነውና። ጨረሮችን ከፀሐይ መለየቱ አስቸጋሪ እንደሆነ ሁሉ፤ የክርስቶስንም ክብር ከእግዚአብሔር ባሕርይ መለየት አይቻልም።

«የባሕርዩ ምሳሌ» የሚለው (ዕብ 1፡3) «ትክክለኛ ቅጂ» የሚል መልእክት ያስተላልፋል። አሳቡን በቀጥታ ስንወስደው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ማንነት ትክክለኛ አምሳል እንደሆነ እንገነዘባለን (ቆላስይስ 2፡9 ተመልከት)። «እኔን ያየ አብን አይቷል» ሊል የሚችለው ክርስቶስ ብቻ ነው (ዮሐ. 14፡9)። ክርስቶስን ስትመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ታያለህ (ዮሐንስ 1፡14)።

በሥራውም ክርስቶስ ከነቢያት በላይ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ፥ እርሱ የአጽናፈ ዓለሙ ፈጣሪ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው በእርሱ አማካኝነት ነውና (ዕብ. 1፡2)። ክርስቶስ ሁሉንም በቃሉ መፍጠር ብቻ ሳይሆን (ዮሐ. 1፡1–5)፥ ሁሉንም ነገር የሚደግፈው በዚሁ ኃያል ቃሉ ነው (ዕብ. 1፡3)። «እርሱም ከሁሉ በፊት ነው፤ ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል» (ቆላስይስ 1፡17)።

«መጋጠም» ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጡ ቃል አንድን ነገር «ይዞ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላው መውሰድ» የሚል ፍች አለው። ይህም ክርስቶስ ፈጣሪና ለጋሽ አምላክ ከመሆኑም በላይ፥ ይህንን ዓለም በመለኮታዊ ጥበብ ወደታቀደለት ፍጻሜ እንደሚመራው ያስረዳል።

በተጨማሪም፥ ክርስቶስ ከነቢያት ሁሉ ልቆ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያውጅ ነቢይ ነው። በክርስቶስና በሌሎች ነቢያት መካከል የሚታየውን ንጽጽር በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል።

| <u>ክርስቶስ</u> | <u>ነቢያት</u> |
| --- | --- |
| እግዚአብሔር ወልድ | በእግዚአብሔር የተጠሩ አገልጋዮች |
| አንድ ወልድ | ብዙ ነቢያት |
| የፍጻሜውና የተሟላው መልእክት | የተከፋፈለና ያልተሟላ መልእክት |

በእርግጥ የብሉይ ኪዳንም ሆነ የወንጌል መገለጥ የመጣው ከእግዚአብሔር ነው። የመገለጡን ደረጃ አስመልክቶ ግን ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣው «የመጨረሻው ቃል» ነው። ክርስቶስ የእግዚአብሔር መልእክት ሁሉ ምንጭ፥ ማዕከልና ፍጻሜ ነው።

የክርስቶስ አገልግሎት እንደ ካህን አገልግሎት መሆኑ ታላቅነቱን ያሳያል። እርሱ ኃጢአታችንን በራሱ አነጻው (1፡3)። ይኼኛው የአገልግሎቱ ገጽታ ከ7 እስከ 10 ባሉት ምዕራፎች በዝርዝር ይብራራል።

በመጨረሻም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ንጉሥ ይገዛል (1፡3)። ሥራውም ስለተጠናቀቀ በእግዚአብሔር በግርማው ቀኝ ተቀምጧል። ይህም የክብር ስፍራ ነው። ይህም ወልድ ከአብ እኩል መሆኑን ያመለክታል። በመሆኑም የትኛውም ፍጡር በእግዚአብሔር ቀኝ ሊቀመጥ አይችልም።

ክርስቶስ ፈጣሪ፥ ነቢይ፥ ካህንና ንጉሥ በመሆኑ፤ ከእርሱ በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከቀረቡት አገልጋዮች ሁሉ ይበልጣል። የክርስቶስ መልክ በተለወጠበት ተራራ ላይ አብ፥ «በእርሱ ደስ የሚለኝ፥ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት» ማለቱ (ማቴ. 17፡5) አስገራሚ ሊሆን አይችልም። በዚያ ስፍራ ከታላላቅ ነቢያት ሁለቱ (ሙሴና ኤልያስ) ከእርሱ ጋር ነበሩ። እርሱ ግን ከእነርሱ በላይ ነው።

የዕብራውያንን መልእክት በምናጠናበት ጊዜ፥ ዓላማችን አእምሮአዊ ጉጉትን የሚቀሰቅሱ አስተምህሮአዊ ጉዳዮችን መመራመር እንዳልሆነ መገንዘቡ ጠቃሚ ነው።ደግሞም አንዳንድ አስተምህሮዎችን

የማጥቃትም ሆነ የመመከት ዓላማ እንደሌለን ግልጽ ሊሆን ይገባል። ስለዚህ ዓላማችን. እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል የሚያስተላልፈውን መልእክት መስማትና ማስተዋል ነው። ስለሆነም፥ «ኢየሱስን ልናይ እንወዳለን!» (ዮሐ. 12፡21) የሚለውን የግሪኮች ጸሎት ልናስተጋባ ይገባል። እንግዲያውስ ዓላማችን ክርስቶስን በሚገባ አውቆ የበለጠ ከፍ ከፍ አድርጎ ማክበር ከሆነ፥ ስለ መጽሐፉ ያለን የአመለካከት ልዩነት ሁሉ እርሱን በምናመልክበት ጊዜ ይዘነጋል።

የዚህን አስደሳች መጽሐፍ አጠቃላይ አሳብ ለመጨበጥ እንችል ዘንድ የሚከተለውን አስተዋጽኦ እንመልከት፡-

## አስተዋጽኦ

1. ከሌሎች የሚበልጥ ማንነት – ክርስቶስ (ምዕ. 1–6)
   ሀ. ከነቢያት በላይ (1፡1–3)
   ለ. ከመላእክት በላይ (1፡4–2፡18)
   (ምክር፡- ከቃሉ ስለ መውደቅ፤ 2፡1–4)
   ሐ. ከሙሴ በላይ (3፡1–4፡13)
   (ምክር፡- ቃሉን ስለ መጠራጠር፤ 3፡7–4፡13)
   መ. ከአሮን በላይ (4፡14–6፡20)
   (ምክር፤ ስለ ድንዛዜ፤ 5፡11–6፡20)
2. ከሌሎች የሚበልጥ ክህነት – መልከ ጼዴቅ (ምዕ. 7–10)
   ሀ. የሚበልጥ ሥርዓት (ምዕ. 7)
   ለ. የሚበልጥ ቃል ኪዳን (ምዕ. 8)
   ሐ. የሚበልጥ መቅደስ (ምዕ. 9)
   መ. የሚበልጥ መሥዋዕት (ምዕ. 10)
   (ምክር፡- ቃሉን ስለ መናቅ፤ 10፡26–39)
3. የሚበልጥ መርሕ – እምነት (ምዕ. 11–13)
   ሀ. ታላቅ የእምነት ምሳሌዎች (ምዕ. 11)
   ለ. በእምነት መታገሥ – ቅጣት (ምዕ. 12)
   (ምክር፡- ቃሉን ስላለመታዘዝ፤ 12፡14–29)
   ሐ. የማጠቃለያ ተግባራዊ ምክሮች (ምዕ. 13)
   «ስለዚህ--- ወደ ፍጻሜ (ብስለት) እንሂድ» (6፡1)።

# 2

# ከመላእክት በላይ

ዕብራውያን 1፥4–2፥18

በአይሁድ ሃይማኖት ውስጥ መላእክት ዐቢይ ስፍራ ይሰጣቸው ነበር። ለዚህም ቀዳሚው ምክንያት፥ ለሙሴ ሕግ በተሰጠበት ወቅት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ መላእክት በማጀባቸው ነበር። ይህም በዘዳግም 33፥2፤ መዝሙር (68)፥17፤ የሐዋርያት ሥራ 7፥53 እና በገላትያ 3፥19 ተገልጾአል። የዕብራውያን መልእክት ፍሬ ነገር ክርስቶስና በእርሱ በኩል የሚገኘው ደኅንነት ከሙሴ ሕግ እንደሚበልጥ ማሳየት በመሆኑ፥ ደራሲው ስለ መላእክት መጥቀሱ አስፈላጊ ነበር።

ይህ ስለ መላእክት የተነገረው ረዥም ክፍል በሦስት የተከፈለ ነው። በመጀመሪያ፥ ክርስቶስ ከመላእክት እንደሚበልጥ ተገልጾአል (ዕብ. 1፥4–14)። ይህንኑ ለማረጋገጥ ከብሉይ ኪዳን ሰባት ጥቅሶች ቀርበዋል። ሁለተኛ፥ አንባቢዎቹ (እኛንም ጨምሮ) በልጁ በኩል ለተገለጸው የእግዚአብሔር ቃል ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጡ ተመክረዋል (2፥1–4)። በመጨረሻም፥ የሰውን አካል የለበሰው ክርስቶስ፥ መናፍስት ከሆኑት መላእክት እንዴት እንደሚበልጥ የሚያስረዱ ማብራሪያዎች ቀርበዋል (2፥5–18)።

## 1. ክርስቶስ ከመላእክት እንደሚበልጥ ማረጋገጫ (1፥4–14)

በዚህ ክፍል የቀረቡት ሰባት የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች፥ ክርስቶስ ከመላእክት እንደሚበልጥ ያረጋግጣሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ደራሲው እነዚህን ጥቅሶች ሴፕቱዋጂንት ከተባለ የግሪክ ብሉይ ኪዳን ትርጉም እንደወሰደ ይናገራሉ። (ሴፕቱዋጂንት በግሪክ 70 ማለት ነው። 70 ምሁራን/ ሊቃውንት በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈውን ብሉይ ኪዳን በግሪክ ቋንቋ እንደተረጎሙ ከትውፊት እንረዳለን። ሴፕቱዋጂንት በእንግሊዝኛ መጻሕፍት ውስጥ 70 ቁጥርን በሚወክሉ ሮማን ቁጥሮች «LXX» የሚገለጽበትም ጊዜ አለ።) ይሁንና፥ በእስትንፋሱ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲጻፍ ያደረገው መንፈስ ቅዱስ፥ እርሱ እንደወደደ ጥቅሶችን ሊመርጥና እውነትን እንደገና ሊገልጽ ይችላል።

እስኪ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመላእክት እንደሚበልጥ የቀረበውን ገለጻና ይህንኑ ለማረጋገጥ ከብሉይ ኪዳን የተጠቀሱትን ምንባቦች እንመልከት።

ሀ. <u>እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው</u> (1፡4–5)። ከመላእክት እንደሚበልጥ የተነገረለት የክርስቶስ ማዕረግ (ስም) «ልጅ» የሚለው ነው። ምንም እንኳ መላእክት ጠቅለል ባለ መልኩ «የእግዚአብሔር ልጆች» ሊባሉ ቢችሉም (ኢዮብ 1፡6)፥ በግሉ ይህን ማዕረግ የተቀበለ መልአክ የለም። ይህ ሙሉ በሙሉ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ማዕረግ ነው። ይህን አሳብ ለማጠናከር የቀረበው የመጀመሪያው ጥቅስ መዝሙር 2፡7 ነው። «አንተ ልጄ ነህ፤ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ።» ጳውሎስ ይህ «ልደት» የትንሣኤው ወቅት እንደነበር ያስረዳል (የሐዋ. 13፡33)። ከዘላለም ዘመናት ጀምሮ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ወልድ ነበር። ከዚያም ራሱን በማዋረድ ሰው ሆነ (ፊልጵ. 2፡5–6)። በትንሣኤው ግን ከአብ የተቀበለውን ያንኑ ስብእና ከፍ ከፍ በማድረግ ወደ ጎን ትቶት የነበረውን ዘላለማዊ ክብር ተቀበለ (ዮሐ. 17፡1፥ 5)። ትንሣኤ፥ «ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው!» ሲል ያውጃል (ሮሜ 1፡4)።

ሁለተኛው ጥቅስ 2ኛ ሳሙኤል 7፡14 ነው። በዳዊት ሕይወት የዚህ ጥቅስ የቅርብ ተዛምዶ እግዚአብሔር ልጁ ሰሎሞንን እንደሚወደውና እንደ ልጅ እንደሚቀጣው የሚያሳይ ነው [መዝ. (89)፡27 አንብብ]። ዋንኛ ተዛምዶው ግን ከሰሎሞን በሚልቀው የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት የሚንጸባረቅ ይሆናል (ማቴ. 12፡42)።

ለ. <u>እርሱ አምልኮን የሚቀበል በኩር ነው</u> (ዕብ. 1፡6) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «በኩር» ሁልጊዜም መጀመሪያ መወለድን አያመለክትም። ምንም እንኳ ሰሎሞን በይፋዊ የዘር ሐረግ ዝርዝር ውስጥ አሥረኛው ልጅ ቢሆንም (1ኛ ዜና 3፡1–5)፥ እግዚአብሔር ግን በኩር አድርጎታል። በኩሩ ልጅ የመውረስና የተለየ በረከት የመቀበል መብት ስላለው፥ ይህ ቃል ደረጃንና ክብርን የሚያመለክት ነው። ክርስቶስ «የፍጥረት ሁሉ በኩር ነው» (ቆላስይስ 1፡15)። ለዚህም ምክንያቶቹ ሁሉንም ነገር መፍጠሩና ከሙታን ከተነሡት ሁሉ ቀዳሚ መሆኑ ናቸው (ቆላስይስ 1፡18)። ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ መላእክት ሰግደውለታል። (ይህ ጥቅስ የተወሰደው ከሮሜ 32፡43 የሴፕቱዋጂንት ትርጉም ነው። ይህም፥ «ሰማያት ከእርሱ ጋር ደስ ይበላቸው። የእግዚአብሔርም ልጆች ያክብሩት!» የሚል ነው።) ይህ እግዚአብሔር እንዲያደርጉት ያዘዛቸው በመሆኑ፥ የክርስቶስን አምላክነት ያረጋግጣል። የእግዚአብሔር መላእክት ፍጡር የሆነን አካል አያመልኩምና።

ሐ. <u>መላእክት አገልግለውታል</u> (ዕብ. 1፡7)። ይህ ከመዝሙር (104)፡4 ላይ የተወሰደ ምንባብ ነው። «መንፈስ» የሚለው ቃል የተተረጎመባቸው የዕብራይስጥና የዕርዕ ቃላት «ነፋስ» ተብለውም

ተተርጉመዋል። መላእክት በምድር ላይ በሚያገለግሉበት ጊዜ በሰው አምሳል ሊገለጹ ቢችሉም እንኳ፥ ሥጋዊ አካል የሌላቸው ፍጡራን መናፍስት ናቸው። ጌታችን በምድር ላይ በነበረ ጊዜ መላእክት አንዳንድ ጊዜ ያገለገሉት ሲሆን (ማቴ. 4፡11፤ ሉቃስ 22፡43)፥ አሁንም እርሱንና እኛን ያገለግላሉ።

መ. ክርስቶስ በዙፋን ላይ የተቀመጠና የተቀባ አምላክ ነው (ዕብ. 1፡8–9)። አንዳንድ የሐሰት አስተማሪዎች ይህንን ከመዝሙር (45)፡6–7 የተወሰደውን ጥቅስ፥ «መለኮታዊ ዙፋንህ--- » ብለው ይተረጉማሉ። ይህንንም የሚያደርጉት የክርስቶስን አምላክነት የሚያሳይ አሳብ ለመቀበል ስለሚቸገሩ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው ትርጉም ግን፥ «አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ ከዘላለም እስከ ዘላለም ጸንቶ ይኖራል» ተብሎ መነበብ አለበት። መላእክቱ በዙፋኑ ፊት ያገለግሉታል እንጂ በዙፋኑ ላይ አይቀመጡም። ከመዝሙረ ዳዊት (110) ዐበይት አስተምህሮዎች አንዱ እግዚአብሔር የቀባው መሢሕ አሁኑኑ በክብር ዙፋን ላይ የተቀመጠ መሆኑ ነው። ክርስቶስ ራሱ ይህንን ትርጉም አዘል መዝሙር የጠቀሰ ሲሆን (ማርቆስ 12፡35–37፤ 14፡62)፥ ጴጥሮስም በበዓለ ኀምሳ ቀን ጠቅሶታል (የሐዋ. 2፡34–36)። ጌታችን ገና ወደ ምድራዊ መንግሥቱ ባይገባም፥ በክብር ነግሦ አል (ኤፌ. 1፡20)።

ክርስቶስ ወደ ሰማይ ዐርጎ በከበረ ጊዜ፥ ለሰማያዊ አገልግሎቱ በደስታ ዘይት ተቀብቷል (ዕብ. 1፡9)። ይህ ምናልባትም ጴጥሮስ በበዓለ ኀምሳ ዕለት የጠቀሰውን መዝሙር 16፡11ን ያመለክት ይሆናል። «. . . በፊትህም በሐሤት ትሞላኛለህ» (የሐዋ. 2፡28)። ይህ እንዴት ያለ አስደሳች ትእይንት ሊሆን እንደሚችል መገመት ትችላላችሁ! መዝሙር 45 የሠርግ መዝሙር ሲሆን፥ ጌታችን ዛሬ በፊቱ ያለውን እየተካፈለ ሰማያዊ የሙሽራነት ሕይወት ይኖራል (ዕብ. 12፡2)። መላእክት ያወድሱታል፤ ነገር ግን የእርሱን ሥልጣን ወይም ደስታ ሊጋሩ አይችሉም። የጌታችን ዙፋን ዘላለማዊ መሆኑ ዘላለማዊ አምላክ መሆኑን ያመለክታል።

ሠ. እርሱ ዘላለማዊ ፈጣሪ ነው (1፡10–12)። ይህ ረዥም ጥቅስ የተገኘው ከመዝሙር (102)፡25–27 ነው። መላእክት ራሳቸውም የፍጥረታት አካል በመሆናቸው ምድርን አልመሠረቷትም። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ፈጣሪ አምላክ በመሆኑ አንድ ቀን አሮጌውን ፍጥረት አስወግዶ አዲሱን ይጀምራል። በዙሪያችን ያለው ሁሉ ሲለወጥ፥ እርሱ ግን ያው ነው። «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፣ ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው» (ዕብ. 13፡8)። አሮጌው ፍጥረት አንድ ቀን ለአዲሱ ስፍራ በመልቀቅ እንደ ሸማ ተጠቅልሎ ያልፋል።

ሰ. *ክርስቶስ ገዥ ሲሆን፥ መላእክት ግን አገልጋዮች ናቸው* (1፡13–14)። እዚህ ላይ ደራሲው መዝሙር (110)፡1ን ይጠቅሳል። ክርስቶስ አሁን በአብ ቀኝ በክብር መቀመጡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ ስፍራዎች ተመልክቷል፤ (ማቴ. 22፡43–44፤ 26፡64፤ ማር. 16፡19፤ የሐዋ. 2፡33–34፤ ሮሜ 8፡34፤ ቆላስይስ 3፡1፤ ዕብ. 1፡3፥ 13፤ 8፡1፤ 10፡12፤ 12፡2፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡22 አንብብ።) መላእክት በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውን ጌታ የሚያገለግሉ መናፍስት ናቸው። እንዲሁም ደግሞ በክርስቶስ በማመን የደኅንነት ወራሾች የሆንነውን እኛንም ያገለግሉናል። ታዲያ የእግዚአብሔር መላእክት እኛን ማገልገላቸው እግዚአብሔር እንዴት እንዳከበረን አያሳይምን?

በእነዚህ ጥቅሶች አማካኝነት የቀረቡትን ማስረጃዎች ችላ ማለት የሚቻል አይሆንም። ኢየሱስ ክርስቶስ ከመላእክት ይበልጣል። እንዲሁም በመላእክት አጃቢነት ለእስራኤል ሕዝብ ከተሰጠው ሕግም ክርስቶስ እንደሚበልጥ ይመሰክራል።

## 2. ተግሣጽ– ቃሉን አስተውሉ እንጂ ወደ ኋላ አትበሉ (ዕብ. 2፡1–4)

ይህ በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ከሚገኙ አምስት ተግሣጾች የመጀመሪያው ነው። የእነዚህ ተግሣጾች ዓላማ አንባቢያኑ ለእግዚአብሔር ቃል ትኩረት እንዲሰጡና እንዲታዘዙ ማበረታታት ነው። በምዕራፍ አንድ ውስጥ እንደተመለከትነው፥ እነዚህ ተግሣጾች እየጠነከሩ በመሄድ ከእግዚአብሔር ቃል በማፈንገጥ የእግዚአብሔርን ቃል ወደ አለመታዘዝ ያድጋሉ (12፡14–29)። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ልጆቹ በእርሱ ላይ ሲያምፁ ዝም ብሎ እንደማያልፍም ተመልክተናል። እግዚአብሔር መገሠጹን የሚቀጥል ሲሆን፥ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜም የእርሱ የሆኑትን መቅጣቱ የማይቀር ነው።

ደራሲው በሚጽፍበት ጊዜ ራሱንም በመጨመር «እኛ» ስለሚል፥ ተግሣጹ የተጻፈው ለአማኞች እንደሆነ እንረዳለን። በዚህ ስፍራ የተመለከተው አደጋ መዳናችንን ችል ማለት ነው። ደራሲው «ብንተው» ሳይሆን፥ «ቸል ብንል» እንዳለ ልብ በሉ። ዓላማው ኃጢአተኞች ወደ ጌታ እንዲመጡ ማበረታታት ሳይሆን፥ ክርስቲያኖች ከጌታ የተቀበሉትን ታላቅ መዳን አክብረው እንዲይዙ ለማሳሰብ ነው።

ደራሲው በ2፡1፥ «ከሰማነው ነገር ስተን እንዳንወድቅ» ሲል ያቀረበውን አሳብ፥ በ6፡19 በመልሕቅ ምሳሌ አድርጎ ያብራራዋል። ይህንንም ያደረገው በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ላይ ለመደገፍ ምን ያህል ጽኑ ዋስትና እንዳለን ለማሳየት ነው። ምናልባትም ከየትኛውም ነገር በላይ ለብዙ መንፈሳዊ ክንቱነቶች የሚዳርገን ቸልተኝነት ሳይሆን

አይቀርም። የእግዚአብሔርን ቃል፥ ጸሎት፥ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መሳተፍ ስንተው (10፡25 አንብብ) እና ሌሎችም ለመንፈሳዊ ዕድገት የሚጠቅሙንን ዕድሎች ሁሉ ቸል ስንል ያን ጊዜ ወደ ውድቀት እናመራለን። የምንሸራተተው እኛ ነን እንጂ መልሕቁ አይደለም።

በብሉይ ኪዳን ዘመን፥ የእግዚአብሔርን ቃል ያላከበሩ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ይቀጡ ነበር። ይህ የቅጣት ቃል በመላእክት አማካይነት ይተላለፍ ነበር። ይልቁንም በዚህ ዘመን ላለነው ከእግዚአብሔር ልጅ ለተሰጠን ቃል ምን ያህል የከበደ ኃላፊነት እንደተቀበልን አስተውለናል? በቁጥር 2፥ ላይ በ«መተላለፍ» የምንፈጽማቸውን ኃጢአቶች ሲያመለክት፥ «አለመታዘዝ» ደግሞ ቃሉ የሚያዘንን መልካም ተግባር ከሥራ ላይ ሳናውል መቅረታችንን ያስረዳል።

አንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ «ቅዱሳን የሚፈጽሟቸው ኃጢአቶች» በሚል ርእስ ተከታታይ ስብከቶችን ያቀርብ ነበር። የመጋቢው ተግሣጽ ጠንከር በማለቱ መለዘብ እንዳለበት የተሰማው አንድ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል፥ «የቅዱሳን ኃጢአት ከሌሎች ኃጢአቶች ጋር እኩል መታየት አለበት?» ሲል ጠየቀ። መጋቢውም፥ «ልክ ነህ ከሌሎች ጋር በእኩል መታየት የለበትም። የቅዱሳኑ ኃጢአት የከፋ ነው» ሲል መለሰ።

ዛሬ አማኞች «ከጸጋ በታች» በመሆናቸው «ከሕግ በታች» በነበሩት ላይ ይደርስ ከነበረው የእግዚአብሔር ቅጣት ነፃ እንደሚሆኑ እናስባለን። ነገር ግን ብዙ ከተሰጠው ብዙ እንደሚጠበቅ መገንዘብ ይኖርብናል። እግዚአብሔር በልጁ በኩል የተናገረን መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ የተነገረን ቃል በሐዋርያዊ ተምአራትም አማካይነት ተረጋግጧል (2፡4)። «ምልክቶችና ድንቆች» የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ አሥራ አንድ ጊዜያት ተጠቅሷል። በዚህ ስፍራ ለቃሉ ምስክርነት በመስጠት ያጸኑትን ተአምራት ያመለክታል። እነዚህም ተአምራት በሐዋርያት በኩል የተፈጸሙ ነበሩ (ማር. 16፡17-20፤ የሐዋ. 2፡43 አንብብ)። ዛሬ የተሟላ የእግዚአብሔር ቃል ስላለን፥ ሐዋርያዊ ተአምራት አያስፈልጉንም። በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ለቃሉ ምስክርነት የሚሰጠው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው (ሮሜ 8፡16፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡1-3)። እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያገለግሉ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተለያዩ የጸጋ ስጦታዎችን ያድላል። (ኤፌ. 4፡ከ11 ጀምሮ፤ 1ኛ ቆሮ. 12)።

ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል በቸልታ ይመለከታሉ። በግልም ሆነ በጋራ የእግዚአብሔርን ቃል ከማንበብና ከጸሎት መራቁ የብዙ መንፈሳዊ ውድቀቶች መንሥኤ እንደሆነ ከመጋቢነት

አገልግሎቴ ተረድቻለሁ። እያንዳንዱ አማኝ የዚህን አሳብ እውነትነት ስለሚያውቅ ምሳሌዎችን ማብዛት አያስፈልገኝም። እያንዳንዱ በራሱ ወይም በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ የዚህ ዓይነቱን መንፈሳዊ ውድቀት እንደሚታዘብ የተረጋገጠ ነው።

«የበረከት ሁሉ ምንጭ ሆይ፥ ና» (Come, Thou Fount of Every Blessing) የሚለውን ተወዳጅ መዝሙር የደረሰው ሮበርት ሮቢንሰን፥ ወደ ክርስቶስ የመጣው በጆርጅ ዋይትፊልድ ታላቅ የወንጌል ስብከት አገልግሎት ወቅት ነበር። ይህ ሰው ጌታ በመጋቢነት አገልግሎት በከፍተኛ ደረጃ ከተጠቀመበት በኋላ መንፈሳዊ ነገሮችን ችላ በማለቱ ወደ ዓለም ተመለሰ። በዚህም ጊዜ ሰላም ለማግኘት በመሻት ወደ ተለያዩ አገሮች ይጓዝ ጀመር። ከጉዞዎቹ በአንደኛው ላይ ግሩም መንፈሳዊ ሕይወት ከነበራት አንዲት ወጣት ጋር ተገናኘ።

«ስለዚህ ስለማነበው መዝሙር ምን ታስባለህ?» ስትል ለሮቢንሰን የመዝሙር ደብተሩን ሰጠችው። መዝሙሩ ራሱ የደረሰው ነበር! ጥያቄዋን ለመሸሽ ቢፈልግም የሚቻል ሆኖ አላገኘውም። የሚናገረው ራሱ ጌታ ነበርና። በመጨረሻም፥ ማንነቱን በመግለጽ ከጌታ እንዴት እንደኮበለለ ገለጸላት።

«ግን እነዚህ የምሕረት ምንጮች እኮ አሁንም እየፈሰሱ ናቸው» ስትል ወጣቷ የእግዚአብሔርን ምሕረት አረጋገጠችለት። በመጨረሻም፥ በወጣቷ ማበረታቻ ሮቢንሰን ልቡ ተሰብሮ በንሥሐ ወደ ጌታ ሊመለስ ችሏል።

በቀላል በወጀብ መገፋት ይቻላል፥ ግን ትልቁን ማዕበል መቋቋሙ አስቸጋሪ ነው። ደኅንነታችን ከፍተኛ ዋጋ የተከፈለበት ታላቅ ደኅንነት ነው። ወደ ሕይወታችንም ታላላቅ የተስፋ ቃሎችንና በረከቶችን ያመጣልናል። ወደ ከበረው ታላቅ የክብር ውርስም ይመራናል። ይህንን ደኅንነት እንዴት ችል ልንለው እንችላለን?

## 3. ማብራሪያ– ክርስቶስ በሰብአዊነቱ ምክንያት ለምን ከመላእክት እንዳነሰ (ዕብ. 2፡5–18)

መላእክት ሥጋዊ አካል ሳይኖራቸው የሚያገለግሉ መሆናቸው፥ በምድር ላይ በሚያገለግልበት ጊዜ ሥጋዊ አካል ለብሶ ከነበረው ክርስቶስ የሚያስበልጣቸው ይመስላል። (አሁን ግን በአንዳች ውስንነት ያልተከለለ የከበረ አካል አለው።) ደራሲው የጌታችን ሰብአዊነት መሰናከል ወይም የበታችነት ምልክት ያልሆነባቸውን ምክንያቶች አብራርቷል።

ሀ. <u>ሰብአዊነቱ ሰው መጀመሪያ ተቀብሎ ሳይጠቀምበት የቀረውን የአገዛዝ ብቃት እንዲጎናጸፍ አስችሎታል</u> (2፡5–9)። ይህ አሳብ የተደገፈበት ጥቅስ ከመዝሙር 8፡4–6 የተወሰደ ሲሆን፥ በጥንቃቄ ብታነበው መልካም ነው። እግዚአብሔር የመጀመሪያዎቹን ወንድና ሴት በፈጠረ ጊዜ፥ በፍጥረቱ ላይ እንዲገዙ ሥልጣን ሰጣቸው (ዘፍጥ. 1፡26–31)። ዳዊት እግዚአብሔር ሥልጣኑንና ኃይሉን ለደካማ ሰው በማጋራቱ ይደነቃል! ሰው ከመላእክት ትንሽ ዝቅ ብሎ የተፈጠረ (እናም ከመላእክት ያነሰ) ቢሆንም፥ ከመላእክት የበለጠ የመልካም ዕድሎች ተጠቃሚ ሊሆን በቅቷል። እግዚአብሔር መላእክት የመጭው ዓለም ወራሾች እንደሚሆኑ ቃል አልገባላቸውም (ዕብ. 2፡5)።

ነገር ግን ዛሬ ሰው በተሰጠው ሥልጣን ፍጥረታትን እየገዛ ባለመሆኑ ሰው ዓሦችን፥ ወፎችንና እንስሳትን ሊቆጣጠር አይችልም። ራሱንም እንኳ ለመቆጣጠር እየቸገረው ነው! «ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ነገር ተገዝቶለት አናይም» (2፡8)።

ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን እናየዋለን! (2፡9)። እርሱ ለሰው ልጅ ግራ መጋባት እግዚአብሔር ያዘጋጀው መልስ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ለሰው ኃጢአት መከራ ተቀብሎ ሊሞትና ሰው በኃጢአት ምክንያት ያጣውን የገዢነት ሥልጣኑን ለመመለስ ነው። ጌታችን በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ይህንኑ ሰው በኃጢአቱ ምክንያት ያጣውን ሥልጣን ተግባራዊ አድርጓል። በዓሦች (ሉቃስ 5፡1–11፤ ማቴ. 17፡24–27፤ ዮሐ. 21፡1–11)፥ በዶሮ (ሉቃስ 22፡34፤ 60)፥ በዱር እንስሳት (ማር. 1፡12–13) እና በቤት እንስሳት ላይ (ማር. 11፡1–7) ሥልጣኑን አሳይቷል። ኢየሱስ ክርስቶስ የኋለኛው አዳም በመሆን (1ኛ ቆሮ. 15፡45)፥ ሰው በኃጢአቱ ምክንያት ያጣውን ሥልጣን መልሷል። ዛሬ ሁሉም ነገር ከእግሮቹ በታች ናቸው (ኤፌ. 1፡20–23)።

ሰው የክብርና የምስጋና ዘውድ ተጭኖለት ነበር (ዕብ. 2፡7)። ነገር ግን ዘውዱን ጥሎ የኃጢአት ባሪያ ሆነ። አሁን ኢየሱስ ክርስቶስ ያንን «ክብር» መልሶ በእጁ ስላስገባ (2፡9)፥ አማኞች ዛሬ የንጉሣዊ አገዛዙ ተካፋዮች ናቸው (ራእይ 1፡5–6)። ጌታ አንድ ቀን መንግሥቱን ሲመሠርት ከእርሱ ጋር አብረን በክብር እንነግሣለን። ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ሁሉ ያደረገው ለእኛ ሲሆን፥ ያደረገውም ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ነው (ዕብ. 2፡9)። የሰውን ሥጋ ባይለብስ ኖሮ፥ ለሰዎች ሁሉ ሲል ባልሞተ ነበር (2፡9)። መላእክት እንደማይሞቱ እውነት ነው። እንዲሁም ደግሞ መላእክት ኃጢአተኞችን እንደማያድኑና ሰው ያጣውን ሥልጣን እንደማይመልሱለት እውነት ነው።

ለ. <u>ሰብአዊነቱ ብዙ ልጆችን ወደ ክብር እንዲያመጣ አስችሎታል</u> (2፡10-13)። ክርስቶስ የመጨረሻው አዳም ብቻ ሳይሆን የደኅንነት መሪም /ካፒቴን (በኩር) ነው። «ካፒቴን» የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በቀጥታ ሲተረጎም «ፊር ቀዳጅ - ሌሎች ይከተሉ ዘንድ መንገዱን የሚከፍት» የሚል ፍች ይሰጣል። (በ1954 የታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስም «ራስ» ሲል ይህንኑ ተመሳሳይ መልእክት ያስተላልፋል።) ክርስቶስ ሰው ይሆን ዘንድ ክብሩን ተወ። ነገር ግን ከሞት ተነሥቶ ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ ክብሩ ተመልሶለታል። አሁንም ያድናቸው ዘንድ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ የእዚያ ክብር ተቋዳሾች ናቸው (ዮሐ. 17፡22-24)። በዚህ ዓይነት ብዙ ልጆችን ወደ ክብር በማምጣት ላይ ነው!

ክርስቶስ ከእኛ ጋር አንድ ሆኗል፥ እኛም ከእርሱ ጋር አንድ ሆነናል። በመንፈስም ከእርሱ ጋር አንድ ነን። እንዲያውም እኛ ወንድሞቹ ነን (ዕብ. 2፡12)። ደራሲው መሢሐዊ መልእክት የያዘውን መዝሙር (22)፡22ን ይጠቅሳል። በዚህ መዝሙር ውስጥ ክርስቶስ፥ ክርስቲያኖች ወንድሞቹ እንደሆኑ ያስረዳል። ይህም እኛ የእግዚአብሔርን ልጅ ባሕርይ እንደምንጋራና የአንድ ቤተሰብ አባላት መሆናችንን ያሳያል። ይህ እንዴት የሚያስደንቅ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው!

የዕብራውያን ጸሐፊ ከሴፕቱዋጀንት ውስጥ ኢሳይያስ 8፡17-18ንም ጠቅሷል። ይህ በቁሙ የሚያመለክተው ተጠቃሾች ኢሳይያስና ትርጉም አዘል ስሞች የተሰጧቸው ልጆቹ መሆናቸው ይታወቃል። (ኢሳ. 7፡3፤ 8፡1-4 አንብብ)። ነገር ግን ምንባቡ በዋንኛነት የሚያመላክተው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። አማኞች ወንድሞቹ ብቻ ሳንሆን ልጆቹም ጭምር ነን (ዕብ. 2፡13)። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መጥቶ ሰው ባይሆን ኖሮ ክብሩን እንካፈል ዘንድ ከምድር ሊወስደን አይችልም ነበር። ትስእብት/ ተሰግዎ፥ ስቅለትና ትንሣኤ ጎን ለጎን የሚሄዱ ነገሮች ናቸው። እነዚህም ሁሉ ወደ ክብር የሚመሩ ናቸው።

ወደፊት ከመቀጠላችን በፊት በ2፡10 ውስጥ በምትገኝ አንዲት ሐረግ ላይ መነጋገር ይኖርብናል። «የመዳናቸውን ራስ በመከራ ይፈጽም ዘንድ» የሚለው ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ፍጹም እንዳልነበረ አያመለክትም። «ፍጹም» ሲል ቃሉ «ሙሉ፥ ውጤታማ፥ ብቁ» በሚሉ ቃላት ሊተካ ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ሥጋ ባይለብስና መከራ ተቀብሎ ባይሞት ኖሮ፥ ብቁ አዳኝና ሊቀ ካህን ሊሆን አይችልም ነበር።

ሐ. <u>ሰብአዊነቱ ሰይጣንን ትጥቅ እንዲያስፈታና እኛን ከሞት እንዲያድን አስችሎታል</u> (2፡14-16)። መላእክት የማይሞቱ ስለሆኑ።

ክርስቶስ መላእክትን ለማዳን አልመጣም (ቁ. 16ን ተመልከት)። እርሱ የመጣው የሰውን ልጆች ለማዳን ነው ይህን ለማድረግ የሰውን ሥጋና ደም ወስዶ ሰው መሆን ነበረበት ማለት ነው ይህን ሲያደርግ ብቻ ነበር ሊሞትና በሞቱም ሰይጣንን ድል ሊነሳ የሚችለው። ሰይጣን አሁንም በእንቅስቃሴና በሥራ ላይ ስለሚገኝ፥ «ይሽር ዘንድ» የሚለው ሐረግ የዲያብሎስን የህልውና ማክተም አያመለክትም። እንዲተላለፍ የተፈለገው መልእክት ክርስቶስ የሰይጣንን ክፉ ተግባር እንዳሰናከለ ነው። ሰይጣን ትጥቁን እንዲፈታ ተደረገ እንጂ ሙሉ በሙሉ አልተደመሰሰም።

ሰይጣን የሞት ሥልጣን የነበረው እንዴት ነው? የመጨረሻው የሞት ሥልጣን በአምላካችን እጅ ነው (ዘዳግ. 32፡39፤ ማቴ. 10፡28፤ ራእይ 1፡18)። ሰይጣን ሊያደርግ የሚችለው እግዚአብሔር የፈቀደለትን ብቻ ነው (ኢዮብ 1፡12፤ 2፡6)። ነገር ግን ሰይጣን የኃጢአት ቀዳሚ ጠንሳሽ ስለሆነ (ዮሐ. 8፡44) እና ኃጢአት ሞትን ስለሚያስከትል (ሮሜ 6፡23)፥ ሰይጣን በሞት ላይ ሥልጣን የሚኖረው በዚህ አኳኋን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰይጣንን ነፍሰ ገዳይ ብሎታል (ዮሐ. 8፡44)። ሰይጣን የሞትን ፍርሃት በሰዎች ላይ በማስፈን አገዛዙን ይቀጥላል። መንግሥቱ የጨለማና የሞት ነው (ቆላስይስ 1፡13)። በኢየሱስ ክርስቶስ የምናምን እኛ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከሰይጣን ሥልጣንና ከሞት አስጨናቂ ፍርሃት ነፃ ወጥተናል። የክርስቶስ ሞት፥ ቀብርና ትንሣኤ ድልን አጎናጽፎናል! (1ኛ ቆሮ. 15፡55–58)።

ኢየሱስ ክርስቶስ የወደቁትን መላእክት ለማዳን የመላእክትን ባሕርይ አልያዘም (ራእይ 12፡7–9፤ 2ኛ ጴጥ. 2፡4)። ነገር ግን ሰው ይሆን ዘንድ ከመላእክት ዝቅ አለ! ሰውም ብቻ ሳይሆን የአብርሃም ዘር አይሁዳዊ ሆነ (ዕብ. 2፡16)። አይሁዶች የተናቁና የተጠሉ ሕዝቦች ሆነው ሳለ፥ ጌታችን አይሁዳዊ በመሆን ከእነርሱ እንደ አንዱ ሆነ።

መ. <u>ሰብአዊነቱ ለሕዝቡ የሚራራ ሊቀ ካህን እንዲሆን አስችሎታል</u> (2፡17–18)። መላእክት መከራ ተቀብለው የማያውቁ ንጹሐን መናፍስት በመሆናቸው፥ ድካማችንንና ጉድለታችንን ሊረዱልን አይችሉም። ክርስቶስ ግን በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ከኃጢአት በቀር የሰውን ድክመቶች በመቀበሉ ወንድሞቹን መስሏል። ምስኪን ሕጻን፥ ልጅ፥ በሳል ጎልማሳ መሆን ምን እንደሚመስል ያውቃል። የድካምን፥ የረሃብንና የጥማት ስሜቶችን ያውቃል (ዮሐ. 4፡6–8)። መናቅና መጣል፥ እንዲሁም በውሸት መከሰስ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚያሳድር ይረዳል። ሥጋዊ መከራና ሞትም በሕይወቱ ውስጥ አልፎአል። ይህ ሁሉ ለሰማያዊው የሊቀ ካህንነት አገልግሎቱ የወሰደው «ሥልጠና» አካል ነበር።

ምሕረትና ታማኝነት ለሌለው ሊቀ ካህን ምሳሌ የሚሆን አገልጋይ ከፈለግህ የኤሊን ታሪክ አንብብ (1ኛ ሳሙ. 1፥9–18)። ኤሊ ልጆቹን በታማኝነት በእግዚአብሔር ፊት መመላለስን ያላስተማረ ሰው ነበር። ሌላው ቀርቶ ልቧ የተሰበረባትንም ሐናን እንደ ሰካራም ከመቁጠር ወደ ኋላ አላለም (1ኛ ሳሙ. 1፥9–18)።

ኢየሱስ ክርስቶስ መሐሪም ታማኝም ነበር። ለሕዝቡ መሐሪ፥ ለእግዚአብሔር ደግሞ ታማኝ ነበር። በክህነት አገልግሎቱ ከቶውንም ስሕተት አልነበረበትም። ከእግዚአብሔር ጋር እንታረቅ ዘንድ ለኃጢአታችን አስፈላጊውን መሥዋዕት አቅርቧል። ኃጢአት ያልነካው ቅዱስ በመሆኑ ለራሱ መሥዋዕት ማቅረብ አያስፈልገውም ነበር።

ነገር ግን የዳንን ሰዎች ኃጢአት ለማድረግ ብንፈተንስ? ክርስቶስ ሊረዳን ከጎናችን ይቆማል! በምድር ላይ በነበረ ጊዜ የተገዳደሩትን ፈተናዎች በድል ተወጥቷል። የትኛውንም ጠላት ረትቷልና ለእኛም ፈተናን ለማሸነፍ የሚያስፈልገንን ጸጋ ሊሰጠን ይችላል። በዕብራውያን 2፥18 ስለ ክርስቶስ እርዳታ የሚናገረው «መርዳት» የሚለው ቃል ቃል በቃል ሲተረጎም የሚያለቅስ ልጅን የጩኸት ጥሪ ሰምቶ ለመታደግ መሮጥን የሚያመለክት ነው። ፍችውም፥ «በሚያስፈልግበት ጊዜ እርዳታን መስጠት» የሚል ነው። መላእክት ቢረዱንም (1፥14)፥ በፈተናችን ጊዜ ክርስቶስ የሚሰጠንን ዓይነት እርዳታ ሊሰጡን አይችሉም። ክርስቶስ ሰው ሆኖ መከራን ስለ ተቀበለና ስለ ሞተልን፥ ይህንን ሊይደርግ ይችላል።

እዚህ ጋ ጌታችን እንደ ሊቀ ካህንና እንደ ጠበቃ የሚያከናውናቸውን አገልግሎቶች ልዩነት መግለጹ አስፈላጊ ይሆናል (1ኛ ዮሐ. 2፥1)። ክርስቶስ ሊቀ ካህናችን እንደ መሆኑ፥ በምንፈተንበት ጊዜ ኃጢአት ከመፈጸም የሚጠብቀንን ጸጋ ይሰጠናል። ኃጢአትን ብናደርግ ግን ጠበቃችን እንደ መሆኑ በእግዚአብሔር ፊት በመቅረብ ከልባችን ይቅርታን በምንጠይቅበት ጊዜ ይምረናል (1ኛ ዮሐ. 1፥5–2፥2)። እነዚህ ሁለቱም አገልግሎቶች አሁን ስለ እኛ እየቀረበ ባለው የምልጃ ተግባር ውስጥ ይካተታሉ። ለዘላለም ደኅንነታችን ዋስትና የሚሆነውም ይኸው የእርሱ የአማላጅነት አገልግሎት ነው። (በዕብራውያን 7፥25 «ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና» የሚለውን ተመልከት።)

ይህንን ክፍል በክለሳ በምታነብበት ጊዜ የእግዚአብሔር ጸጋና ጥበብ እጅግ አስደናቂ መሆኑን ትገነዘባለህ። ከሰብአዊ እይታ አንጻር፥ የአምላክ ሰው መሆን ሞኝነት ሊመስል ይችላል። ነገር ግን ደኅንነታችንና ከዚያ ጋር የተያያዙትን ነገሮች ሁሉ ያስገኘልን ይኸው

የጸጋ ሥራ ነው። ክርስቶስ ሰው በሆነ ጊዜ በሰብአዊ አካሉ መላእክት ሊያደርጉ ያልቻሉትን አድርጓልና ከመላእክት በለጠ እንጂ አላነሰም። የክብሩ ተካፋዮች ለመሆን የምንችልበትን መንገድ አዘጋጅቷል!

ክርስቶስ፥ እኛን ወንድሞቼና እኅቶቼ ብሎ ለመጥራት አያፍርም።

እኛስ፥ «ጌታችን» ብለን ልንጠራው እናፍር ይሆን?

## 3

# ከሙሴ የሚበልጥ

ዕብራውያን 3፡1–4፡13

አይሁዶች ከአብርሃም ቀጥሎ እጅግ አድርገው የሚያከብሩት ሙሴን መሆኑ ጥርጥር የለውም። የዕብራውያን መልእክት የተጻፈላቸው ሰዎች ወደ ሕግ የመመለስ ብርቱ ፈተና ገጥሟቸው ስለነበር፥ ጸሐፊው ወደ ሕግ መመለስ ማለት ወደ ሙሴ መመለስ መሆኑን ይገልጽላቸዋል። ጠቅላላው የአይሁድ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ከሙሴ የመጣ በመሆኑ፥ ጸሐፊው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙሴ እንደሚበልጥ ለአንባቢዎቹ ማሳመን ነበረበት። በዚህ ክፍል፥ ቢያንስ በሦስት ምክንያቶች ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙሴ እንደሚበልጥ ተገልጾአል።

## 1. ክርስቶስ በማንነቱ ከሙሴ ይበልጣል– (3፡1–2)

ጸሐፊው መልእክቱ የተላከላቸውን ሰዎች የሚገልጽባቸው ሁለት ስሞች ዳግም የተወለዱ መሆናቸውን ያሳያሉ። «ቅዱሳን ወንድሞች» የሚለው ሐረግ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለውና የሚያገለግለው በእግዚአብሔር ጸጋ ተለይተው በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች ብቻ ነው። ጸሐፊው «ከሰማያዊ ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ» ሲል የክርስቶስ አካል ለሆኑት የቤተ ክርስቲያን አባላት እንደሚናገር ያስረዳል። ዳግም ያልተወለዱ አሕዛብ ወይም አይሁድ ይህንን በረከት ሊቀበሉ አይችሉም! በዚህ ስፍራ «ተካፋዮች» ተብሎ የተተረጎመው ቃል በሉቃስ 5፡7 «ጓደኞች» (በሌሎች ትርጉሞች «አጋሮች») ተብሏል። ይህ በአራት ዓሣ አጥማጆች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ ያገለገለው ቃል አብረው በመሥራት ላይ መሆናቸውን ያሳያል።

እውነተኛ ክርስቲያኖች በሰማዩ ጥሪ ብቻ ሳይሆን፥ በኢየሱስ ክርስቶስም ዘንድ ዕድል ፈንታ አላቸው (ዕብ. 3፡14)። በመንፈስ ቅዱስ በኩል፥ እኛ የአካሉ፥ የሥጋውና የአጥንቱ ክፍሎች ነን (ኤፌ. 5፡30)። እውነተኛ አማኞች የመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ናቸው (ዕብ. 6፡4)። «የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም» (ሮሜ 8፡9)። የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን፥ የእግዚአብሔርን የፍቅር ቅጣትም እንካፈላለን (ዕብ. 12፡8)። አለመቀጣት የእግዚአብሔር ልጅ አለመሆንን ያሳያል።

እነዚህ ሰዎች ቅዱሳንና የሰማያዊ ጥሪ ተካፋዮች በመሆናቸው፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ ስላላቸው እምነት ሊመሰክሩ ይችሉ ነበር።

ምስክርነት የሚለው ቃል «ተመሳሳይ ነገር መናገር» የሚል ፍች ያለው ነው። ደኅንነታቸውን አስመልክቶ እውነተኛ ክርስቲያኖች ሁሉ ተመሳሳይ ነገር ይናገራሉ። በዚህ መልእክት ውስጥ፥ ጸሐፊው አንባቢያኑ ይህንኑ እምነታቸውን እንዲጠብቁ ሁለት ጊዜ አሳስቧቸዋል (4፡14፤ 10፡23)። ቀደም ባሉት ዘመናት ሁሉ የእምነት ጀግኖች «እንግዶችና መጻተኞች» ሆነው እንዲኖሩ ያደረጋቸው ይኸው እምነታቸው ነበር (11፡13)።

የዕብራውያን መልእክት ለተጻፈላቸው ሰዎች ይህንን ሁሉ ያደረገላቸው ሙሴ ሳይሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር! ጸሐፊው ሙሴን ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲያስቡ ነበር የመከራቸው። ክርስቶስን ስለ ማሰብ (መመልከት) የሚያስረዳው ቃል «በጥንቃቄ ማጤን፥ ሙሉ በሙሉ መገንዘብ» የሚል ፍች አለው። ይህ ክርስቶስን በቅጽበት የማየት ጉዳይ አይደለም። ይልቁንም ስለ ማንነቱና ስላደረጋቸው ነገሮች በአንክሮ የማጤን ጉዳይ ነው።

ክርስቶስ ከሙሴ መብለጡ ግልጽ ጉዳይ ነው። ሙሴ ነቢይና መሪ እንዲሆን የተጠራ ሰው ሲሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አብ ወደ ዓለም የላከው ውድ ልጁ ነው። «ሐዋርያ» ማለት «ለአንድ ዓላማ የተላከ» ማለት ነው። ሙሴ በእግዚአብሔር ተጠርቶ የተላከ ሲሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የእግዚአብሔር የመጨረሻ ቃል ሆኖ ወደ ኃጢአተኛ ሰው ዘንድ የመጣ ነው። በወንጌላት ውስጥ ክርስቶስ ከአብ እንደ ተላከ ተደጋግሞ ተነግሯል፥ (ዮሐ. 3፡17፥ 34፤ 5፡36፥ 38፤ 6፡29፥ 57፤ 7፡29፤ 8፡42፤ 10፡36፤ 11፡42፤ 17፡3 እና 13፡3)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ብቻ ሳይሆን፥ ሊቀ ካህናትም ነው። ሙሴ እንደ ካህን ያገለገለ ነቢይ ቢሆንም [መዝ. (99)፡6 አንብብ]፥ ሊቀ ካህናት አልነበረም። ያ የወንድሙ የአሮን ማዕረግ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን «ታላቅ ሊቀ ካህናት» ነው (ዕብ. 4፡14)።

ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሐዋርያ እግዚአብሔርን ለሰዎች ወክሏል፤ እንደ ሊቀ ካህናት ሰዎችን በሰማይ ለእግዚአብሔር ይወክላል። ሙሴ ለእስራኤል የእግዚአብሔርን እውነት በማስተማሩና ከእግዚአብሔር ጋር በተራራ ላይ በተገናኘ ጊዜ ለእስራኤል በመማለዱ (ዘጸ. 32፡30–32 አንብብ) ተመሳሳይ አገልግሎቶችን አካሂዷል። ሙሴ በቀዳማይነት የሕግ ነቢይ ሲሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የእግዚአብሔር ጸጋ መልእክተኛ ነበር (ዮሐ. 1፡17 አንብብ)። ሙሴ ወደ ዓለም ለሚመጣው አዳኝ መንገድ በመጥረግ አገልግሏል።

የዕብራውያን ጸሐፊ ግን ሙሴም ሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ተልዕኮ በታማኝነት እንደተወጡ ያስረዳል።

ሙሴ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት ያነፃው ባይሆንም፥ በታማኝነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽሟል (ዘኍ. 12፡7)። ይህም የመጀመሪያው ምእተ ዓመት አይሁዳውያን ክርስቲያኖች በዚያ አስከፊ መከራ ውስጥ በታማኝነት ክርስቶስን እንዲከተሉ አበረታቷቸዋል። ወደ ሙሴ ከመመለስ ይልቅ ሙሴን መስለው ለጥሪያቸው በታማኝነት መቆም ይጠበቅባቸው ነበር።

## 2. ክርስቶስ በአገልግሎቱ ከሙሴ ይበልጣል (ዕብ. 3፡3–6)

በዚህ ክፍል ውስጥ «ቤት» የሚለው ቃል ስድስት ጊዜ ተጠቅሷል። ቃሉ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንጂ ሕንጻውን አይደለም። ሙሴ ከአሮጌው ቃል ኪዳን በታች ሆኖ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለነበሩት አይሁዶች አገልግሎቱን አበርክቷል። ዛሬ ደግሞ ክርስቶስ በአዲሱ ቃል ኪዳን ሥር የእግዚአብሔር ሕዝብ ለሆኑት ክርስቲያኖች አገልግሎቱን በማበርከት ላይ ይገኛል። እኛም «ቤቱ» ነን (ቁ.6)። ይህንን የቤትን «መንትያ» አጠቃቀም በ2ኛ ሳሙኤል 17 ውስጥ ልትመለከት ትችላለህ። ዳዊት እግዚአብሔር ይኖርበት ዘንድ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለመሥራት ፈልጎ ነበር። እግዚአብሔር ግን ራሱ የዳዊትን ቤት (ቤተሰብ) እንደሚሠራና ከዘሮቹ ጋር ቃል ኪዳን እንደሚገባ ገለጸለት።

በሙሴና በክርስቶስ መካከል የሚታየው ንጽጽር ግልጽ ነው። ሙሴ በቤቱ ውስጥ ባሪያ ሲሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የቤቱ ልጅ ነው። ሙሴ የቤተሰቡ አባል ሲሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ቤተሰቡን መሥርቷል! በነገራችን ላይ፥ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ለክርስቶስ አምላክነት የቀረበው ማስረጃ የጠነከረ ነው። እግዚአብሔር ሁሉንም ካዘጋጀና ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ቤት ከሠራ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙሴ ለመብለጡ ሌላም ምክንያት አለ። ነቢዩ ሙሴ ወደፊት ስለሚመጡት ነገሮች የተናገረ ሲሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እነዚህን ነገሮች ከፍጻሜ አደረሳቸው (ቁ. 6)። ሙሴ በጥላ ውስጥ ሲያገለግል (8፡5 እና 10፡1 አንብብ)፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚያውጀውን ወንጌል ሙሉና የመጨረሻ ብርሃን ፈነጠቀ።

በቁጥር 5 «ሎሌ» ተብሎ የተተረጎመው የፅርዕ (የግሪክ) ቃል አገልጋይ ወይም ባሪያ የሚለውን አሳብ ለማስተላለፍ የሚያገለግለው የተለመደ ቃል አይደለም። ቃሉ የሚያሳየው በራሱ ፈቃድ በፍቅር ተነሣሥቶ የሚሠራውን አገልጋይ ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ቃሉ ያገለገለው ለሙሴ ብቻ ነው። በአገልግሎቱ መጀመሪያ አካባቢ ሙሴ

እያመነታ የእግዚአብሔርን ጥሪ ላለመቀበል አሻፈረኝ ብሎ ነበር። ነገር ግን ለመታዘዝ ከወሰነበት ጊዜ አንሥቶ ሁሉንም ተግባር ያከናወነው በፍቅርና በመሰጠት ልብ ነበር።

በቁጥር 6 «እኛም--- እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ» የሚለው ሐረግ ከአጠቃላይ ዓውዱ አንጻር ሊታይ ይገባል። ዓውዱም ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ወደ ተስፋይቱ ምድር መምራቱ ነው። ጸሐፊው እኛ እንደ ክርስቲያኖች ደኅንነታችንን በራሳችን መጠበቅ እንዳለብን ማስገንዘቡ አይደለም። ይህ የተፈጸመው የክርስቶስ ሥራና ሰማያዊ አገልግሎቱ ለደኅንነታችን ዘላለማዊ ዋስትና መሆኑን ከሚያስረዳው የመጽሐፉ ጭብጥ ያፈነገጠ አሳብ ነው። (7፡ከ14 ጀምሮ)። ይልቁንም ጸሐፊው ድፍረታቸውንና ተስፋቸውን አጽንተው የሚይዙ ወገኖች በትክክል መዳናቸውን እንደሚያረጋግጡ ያስረዳል።

«ድፍረት» የሚለው ቃል በቀጥታ ሲወሰድ «በነጻነት መናገር፥ ግልጽነት» የሚል መልእክትን ያስተላልፋል። የመናገር ነጻነት ካለህ የሚያስፈራህ ነገር ስለሌለ ደፋር ትሆናለህ። አንድ አማኝ ያለፍርሃት በግልጽና በነጻነት ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ሊቀርብ ይችላል (4፡16)። እኛም ከፈሰሰልን የክርስቶስ ደም የተነሣ ይህ ድፍረት አለን (10፡19)። ስለሆነም፥ ሁኔታዎች የፈለገውን ዓይነት መልክ ቢይዙም ይህን መታመናችንን መጣል የለብንም። ወደ ውድቀት የምናዘነብል መሆናችንን በመገንዘብ በራሳችን ላይ ከመተማመን መቆጠብ አለብን። ነገር ግን ከቶውንም በማይወድቀው በኢየሱስ ክርስቶስ ልንተማመን ይገባል።

በክርስቶስ በማመናችንና ይህንንም በመመስከራችን ምክንያት ደስታንና ተስፋን ልናገኝ እንችላለን (ቁ. 6)። ጸሐፊው እነዚህ መከራ የሚቀበሉ ቅዱሳን መጽናት ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲደሰቱም ይፈልጋል። በቤቱ ውስጥ የተወደደ ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ለእያንዳንዱ የቤተሰቡ አባል የሚያስፈልገውን እንክብካቤ ያደርጋል። እርሱ ታማኝ ሊቀ ካህናት ስለሆነ፥ በምናልፍባቸው የሕይወት ፈተናዎች ሁሉ የሚያስፈልገንን ያሟላል። ታላቅ እረኛ በመሆኑ (13፡19-20)፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ የሚከሰቱትን ገጠመኞች በመጠቀም እርሱን የሚያስከብር አገልግሎት እንዲያበረክቱ ያስታጥቃቸዋል።

በሌላ አገላለጽ፥ በክርስቶስ ያመኑ ሰዎች በጽናታቸው፥ በድፍረታቸውና ደስታ የተሞላበትን የተስፋ ሕይወት በመኖራቸው የእምነታቸውን እውነተኛነት ያረጋግጣሉ። የድሮው ሸክም ወይም

የአሁኑ ስጋት ሳያውካቸው፥ የተባረከውን የጌታን የመመለስ ተስፋ እየተጠባበቁ «በወደፊት ሕይወት ይመላለሳሉ»። ጉዞው ፈታኝ በሚሆንበት ጊዜ ሳይቀር መንገዳቸውን በጽናት እንዲቀጥሉ የሚያነሣሣቸው «ሰማያዊው ጥሪ» ነው።

በዚህ ክፍል የእስራኤላውያን የምድረ በዳ ጉዞ በዋናነት ተጠቅሷል። ከእስራኤል ሕዝብ መካከል ሁለት ሰዎች (ካሌብና ኢያሱ) በ3፡6 የተገለጸውን ሁኔታ ያብራራሉ። ከ20 ዓመት በላይ የሆነ ሰው ሁሉ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሳይገባ መሞት ነበረበት (ዘኍ. 14፡26–28 አንብብ)። ካሌብና ኢያሱ ግን በእግዚአብሔር በማመናቸው፥ እግዚአብሔር እምነታቸውን አከበረላቸው። ካሌብና ኢያሱ ለ40 ዓመታት ዘመዶቻቸውና ጓደኞቻቸው ሲሞቱ እየተመለከቱ ኖረዋል። እነዚህ ሁለቱ ሰዎች ግን አንድ ቀን ወደ ተስፋይቱ ምድር እንደሚገቡ በመገንዘብ በእግዚአብሔር ቃል ተማመኑ። ሌሎች ሞትና ኀዘን ሲገጥማቸው ካሌብና ኢያሱ ግን በመታመን ተስፋ ደስ ተሰኙ። አማኞች እንደ መሆናችን፥ እግዚአብሔር ወደ መንግሥተ ሰማያት እየወሰደን እንደሆነ እናውቃለን። ስለሆነም፥ የእነ ካሌብን ዓይነት በደስታ የፈካ መተማመንና ተስፋ ልናሳይ ይገባል።

## 3. ክርስቶስ በሚሰጠው ዕረፍት ከሙሴ ይበልጣል (ዕብ. 3፡7–4፡13)

ይህ ረዥም ክፍል በዚህ መልእክት ውስጥ ከሚገኙ አምስት ማስጠንቀቂያዎች ሁለተኛው ነው። በመጀመሪያው ማስጠንቀቂያ (2፡1–4) ጸሐፊው ከቸልታ የተነሣ ከእግዚአብሔር ቃል ተለይተው እንዳይወድቁ አስጠንቅቋቸዋል። በዚህ ክፍል ደግሞ በልብ ድንዳኔ ምክንያት የእግዚአብሔርን ቃል መጠራጠር የሚያስከትለውን አደጋ ያብራራል። የዚህን ምክር አሳብ ለመረዳት የክፍሉን ዳራ መመልከቱ ጠቃሚ ነው። ይህም እስራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው ወደ ተስፋይቱ ምድር በሚጓዙበት ጊዜ በበረሃ ውስጥ የነበራቸውን ጥርጣሬ የሚያሳይ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ፥ ከዚሁ የእስራኤላውያን የጉዞ ገጠመኝ የምንማራቸው መንፈሳዊ ትምህርቶች እንዳሉ መገንዘብ ይኖርብናል። የእስራኤላውያን የግብጽ ባርነት ኃጢአተኛ የሆነ ሁሉ የዚህ ዓለም እስረኛ መሆኑን ያስረዳል። እስራኤላውያን ከግብጽ ምድር በበጎች ደምና በእግዚአብሔር ኃይል ነፃ እንደ ወጡ ሁሉ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ኃጢአተኛም ነፃ ይወጣል (ቆላስይስ 1፡13–14)። የእግዚአብሔር በግ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከኃጢአት ነፃ ወጥተናል።

የእስራኤላውያን በግብጽም ሆነ በምድረ በዳ መቅረት የእግዚአብሔር ፈቃድ አልነበረም። የእርሱ ፍላጎት ሕዝቡ በክብር ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲገቡ ነበር። ነገር ግን እስራኤላውያን ከሚወርሷት ምድር ዳርቻ ሲደርሱ፥ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ስለተጠራጠሩ እየተቅበዘበዙ ለመቆየት ተገደዋል (ዘኁ. 13–14)። አሥሩ ሰላዮችና ሕዝቡ «አንችልም» ብለው ለቅሶ ተቀመጡ። ሙሴ፥ ኢያሱና ካሌብ፥ ግን «በእግዚአብሔር እርዳታ እንችላለን!» ሲሉ መለሱ። ሕዝቡ በእምነት ወደፊት እንደ መሄድ ባለማመን የኋሊት ስለ ተጓዙ፥ ርስታቸውን አጥተው በበረሃ ውስጥ ሞቱ። ወደ ምድሪቱ ገብቶ ያረፈው አዲሱ ትውልድ ነበር።

ዛሬ ለእኛ ለክርስቲያኖች ከነዓን በኢየሱስ ክርስቶስ ያለንን መንፈሳዊ ርስት ትወክልልናለች (ኤፌ. 1፡3፥ 11፥ 15–23)። አንዳንድ መዝሙሮቻችን ከነዓንን የመንግሥተ ሰማይ፥ ዮርዳኖስን መሻገር ደግሞ የሞት ተምሳሌት አድርገው ማቅረባቸው አሳዛኝ ነው። ከነዓን የጦርነትና የሽንፈት ስፍራ ስለነበረች፥ መንግሥተ ሰማይን በጥሩ ሁኔታ ልታንጸባርቅ አትችልም! እስራኤላውያን ወንዙን በእምነት መሻገር ነበረባቸው (ይህ አንድ አማኝ ለዓለምና ለኃጢአት መሞቱን ያመለክታል። ሮሜ 6) እና ርስታቸውንም በእምነት መውረስ ነበረባቸው! በእምነት ወጥተው (ኢያሱ 1፡3) ምድሪቱን መውሰድ ይጠበቅባቸው ነበር። ይህም ዛሬ አማኞች ሊያደርጉት የሚገባው ነው።

አሁን የምድረ በዳ መቅበዝበዝ ምንን እንደሚወክል ሳንገነዘብ አልቀረንም። ምድረ በዳው የሚወክለው በክርስቶስ ያላቸውን መንፈሳዊ ርስት ሳይጨብጡ የእግዚአብሔርን ቃል እየተጠራጠሩ በዕረፍት የለሽነት የሚኖሩትን አማኞች ሁኔታ ነው። እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር እንደነበረው ከእነዚህም አማኞች ጋር መሆኑ እርግጥ ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔርን የበረከት ሙላት ተቀብለው ሊደሰቱ አይችሉም። ከግብጽ ቢወጡም፥ ገና ወደ ከነዓን አልገቡም።

ይህንን ጸራ ልብ ስንል መረጃ በመያዝ፥ በዚህ ክፍል ውስጥ ከሚገኙት ቁልፍ ቃላት *«ዕረፍት»* የሚለውን በተሻለ መንገድ ልንረዳ እንችላለን (ዕብ. 3፡11፥ 18፤ 4፡1፥ 3፥ 4፥ 5፥ 8፥ 9፥ 10፥ 11)። ጸሐፊው በብሉይ ኪዳን ታሪክ ውስጥ የሚታወቁትን ሁለት ዕረፍቶች ጠቅሷል። (1) እግዚአብሔር የፍጥረት ሥራውን በፈጸመ ጊዜ *ያረፈበት የሰንበት ዕረፍት* (ዕብ. 4፡4፤ ዘፍጥ. 2፡2)። (2) *እስራኤላውያን በከነዓን ያገኙት ዕረፍት* (ዕብ. 3፡11፤ ዘዳግ. 12፡9፤ ኢያሱ 21፡43–45)። እነዚህ ዕረፍቶች ለዛሬው የክርስቲያኖች ሁኔታዎች ሥዕላዊ ማብራሪያ ይሰጡናል። የሰንበት ዕረፍት በክርስቶስ ያገኘነው ደኅንነት ተምሳሌት ሲሆን (ዕብ. 4፡3 እና ማቴ. 11፡28

እንብብ)። የከነዓን ዕረፍት ደግሞ በክርስቶስ ያለንን ዕረፍት ስንቀበል ዛሬ የምንኖረውን ሕይወት ያመለክታል (ዕብ. 4፡11–13፤ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተሰጠውን አጽንኦት አስተውል)። የመጀመሪያው የደኅንነት ዕረፍት ሲሆን፥ ሁለተኛው የመታዘዝ ዕረፍት ነው።

ከዚህም በላይ ጸሐፊው ስለ ሦስተኛው የዕረፍት ዓይነት ይናገራል። ይህም ወደፊት አማኞች ሁሉ ከእግዚአብሔር የሚያገኙትና ደስ የሚሰኙበት ዕረፍት ነው። «እንግዲያስ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ቀርቶላቸዋል» (4፡9)። ይህ በዕርዕ (በግሪክ) «ሳባቲስሞስ» የሚል ቃል ሲሆን፥ «ሰንበትን መጠበቅ» ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ ቃል የተጠቀሰው በዚህ ስፍራ ብቻ ነው። ቅዱሳን ወደ መንግሥተ ሰማይ በሚገቡበት ጊዜ ታላቅ የእግዚአብሔር የሰንበት ዕረፍት ይሆናል። በዚህ ጊዜ ጦርነቶችና ሥራዎች ሁሉ ያበቃሉ (ራእይ 14፡13)።

እነዚህን ዕረፍቶች እንደሚከተለው ልናመለክት እንችላለን።

| <u>የበፊት</u> | <u>የአሁን</u> | <u>የወደፊት</u> |
|---|---|---|
| የእግዚአብሔር የሰንበት ዕረፍት | የደኅንነት ዕረፍት | መንግሥተ ሰማያት |
| እስራኤላውያን በከነዓን ያገኙት ዕረፍት | የመታዘዝ ዕረፍት (በክርስቶስ የሚገኝ ድል) | |

ስለ እስራኤል ታሪክና «ዕረፍት» ከቀረበው ከዚህ ዳራ በመነሣት፥ ምንባቡን እንደሚከተለው ልንመረምር እንችላለን። ጸሐፊው በዚህ ክፍል ሦስት ተግሣጾችን ያቀርባል፡–

ሀ. <u>እናስተውል</u> (ዕብ. 3፡7–19)። ምን እናስተውል? አሳዛኙን የእስራኤል ታሪክና የሚያስተላልፈውን መልእክት አስተውለን እንመልከት። ጸሐፊው እግዚአብሔር ለእስራኤል አሳዛኝ ሁኔታ ምላሽ የሰጠበትን መዝሙር (95)፡7–11 ይጠቅሳል። እግዚአብሔር ሕዝቡን በማውጣት፥ በብዙ ምልክቶችና ድንቆች ኃይሉን እየገለጸ የሚያስፈልጋቸውን በማሟላት ሲንከባከባቸው ቆይቷል። እስራኤላውያን የዚህ ሁሉ በረከት ተጠቃሚዎች ሆነውም እንኳ ወደ እግዚአብሔር ይበልጥ ሲቀርቡ ወይም ሲታመኑ አናይም። እግዚአብሔር ያደረገላቸው ሁሉ መንፈሳዊ በረከትን አላጎናጸፋቸውም። እንዲያውም የዚህ ተገላቢጦሽ ነበር የሆነው። በእግዚአብሔር ላይ ልባቸውን አደነደኑ! እግዚአብሔርን ተፈታተኑት። እርሱ ባይከዳቸውም እነርሱ ከዱት።

የችግሮች ሁሉ ምንጭ በልብ ውስጥ የሚኖር ችግር ነው። የእስራኤል ሕዝብ (ከሙሴ፥ ከኢያሱና ከካሌብ በስተቀር) የተቀሩት በልባቸው ሳቱ። ልባቸው ከእግዚአብሔርና ከቃሉ አፈነገጠ። እንዲሁም ደግሞ የማያምን ክፉ ልብ ነበራቸው (ቁ. 12)። እግዚአብሔር በከነዓን ድልን ይሰጠናል ብለው ሊያምኑ አልቻሉም ነበር። ምንም እንኳ እግዚአብሔር በግብጽ ታላላቅ ምልክቶችን ሲያደርግ ቢመለከቱም፥ በከነዓን ለሚጠብቃቸው ተግዳሮት ብቃት ይኖረዋል ብለው አላሰቡም።

አንድ ሰው የሚስትና የማይታዘዝ ልብ ሲኖረው ውጤቱ የልብ ድንዳኔ ይሆናል። ይህም ለእግዚአብሔር ሥራና ቃል ምላሽ የማይሰጥ የደነዘዘ ልብ ነው። የሕዝቡ ልብ እጅግ ከመደንደኑ የተነሣ ወደ ግብጽ ለመመለስ ፈለጉ! እግዚአብሔር የሰጣቸውን ነጻነት በግብጽ ባርነት ለመለወጥ ሲፈልጉ አያስገርምም! የዕብራውያን መልእክት አንባቢያንም «ወደ ኋላ በመመለሱ» አደጋ ውስጥ ስለነበሩ፥ ይህ ታሪክ የሚያስተላልፍላቸው መልእክት ቀላል አልነበረም።

እስራኤላውያን በበረሃ ውስጥ በሚገኘው ቃዴስ በርኔ በተባለ ስፍራ ሲደርሱ የእግዚአብሔር ፍርድ ወረደባቸው። ያ ሁሉ ሕዝብ ምድረ በዳ ውስጥ ወድቆ አዲሱ ትውልድ ብቻ ወደ ተስፋይቱ አገር መግባት ቻለ። «ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ብዬ በቁጣዬ ማልሁ» ብሏል (3፡11)። ነገር ግን ይህ ዛሬ ለአማኞች ወይም ለአንድ አማኝ የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድን ነው? ቤተ መቅደሱና ክህነቱ ስለ ፈረሰ ዛሬ አይሁዳዊም ሆነ አሕዛብ ወይም ክርስቲያን ወደ ሙሴ ሕግ ሊመለስ አይችልም። ነገር ግን አማኞች ሁሉ በክርስቶስ ላይ ያለውን እምነት ትተው ማመቻመችና እስራት ወዳለበት የዓለም ሥርዓት ለመመለስ መፈተናቸው አይቀርም። ይህ በተለይ በስደትና መከራ ጊዜ እውነት ነው። መከራ እውነተኛ ክርስቲያኖችን ከአስመሳዮቹ ስለሚለይ፥ ሁልጊዜም የስደት እሳት ቤተ ክርስቲያንን ሲያጠራ ቆይቷል። እውነተኛ አማኞች ስለ ክርስቶስ መከራ ለመቀበል ፈቃደኞች ሲሆኑ፥ እምነታቸውን አጽንተው ይይዛሉ፤ (ዕብ. 3፡6 እና 14 አንብብ)። ምንም እንኳ የምንድነው እምነታችንን በመጠበቅ ባይሆንም፥ እምነታችንን መጠበቃችን ለመዳናችን ማረጋገጫ ነው።

በሕይወታችን ዙሪያ የሚያንዣብቡትን መንፈሳዊ አደጋዎች መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። እንዲሁም ደግሞ ለጌታ ታማኞች እንሆን ዘንድ አንዳችን ሌላውን ልናበረታታ ይገባል (3፡13)። የዕብራውያን መልእክት ከተጻፈላቸው አማኞች መካከል አንዳንዶቹ በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በትጋት የማይሳተፉ ይመስላሉ፤ (10፡23–25 አንብብ)። ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ሳይደጋገፉ ሊኖሩ

አይችሉም። ሕዝቡ ወደ ከነዓን ላለመግባት በወሰነ ጊዜ ሙሴ፥ ካሌብና ኢያሱ ያበረታቷቸው ነበር። ሕዝቡ ግን አልሰሟቸውም ነበር።

ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው፥ እስራኤላውያን በምድረ በዳ ውስጥ በተቀበዘበዙባቸው አርባ ዓመታት ውስጥ እግዚአብሔር አዝኖባቸው ነበር። እነርሱም ገና ከግብጽ ከመውጣታቸው እግዚአብሔርን ያስቆጡት ጀመር (ዘጸ. 16፡ከ1 ጀምሮ)። እንጀራ ከሰጣቸው በኋላ ስለ ውኃ አጉረመረሙ (ዘጸ. 17፡1-7)። ሙሴ ያንን ስፍራ «ማሳህ መሪባ» ብሎ ጠርቶታል። ትርጉሙም «ማስቆጣትና መፈታተን» ማለት ነው። በዕብራውያን 3፡10 ጥቅም ላይ የዋሉት እነዚሁ የተጠቀሱ ቃላት ናቸው።

የእስራኤላውያን ኃጢአት በቁጥር 12 ላይ ተጠቅሷል። ይኸውም ከሕያው አምላክ መለየት ነው። «ክህደት» የሚለው የአማርኛ ቃል ይህንን አሳብ ከሚያመለክተው የፅርዕ (የግሪክ) ቃል የተተረጎመ ነው። በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ይህ ቃል ያገለገለው በዚህ ስፍራ ብቻ ነው። ክህደት ማለት እምነትን መተውና ለዘላለም መኮንን ይሆን? ይህ አሳብ በዚህ ዓውድ ውስጥ ተስማሚ አይደለም። እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ባለመሻትና በልበ ደንዳናነት ወደ ግብጽ ለመመለስ በመፈለግ ከሕያው አምላክ ተለይተዋል። እግዚአብሔር ግን ወደ ግብጽ እንዲመለሱ አልፈቀደላቸውም። ነገር ግን በበረሃ ውስጥ ቀጥቷቸዋል። እግዚአብሔር ሕዝቡ ወደ ባርነት እንዲመለስ አልፈቀደም።

የዕብራውያን መልእክት ትኩረት እውነተኛ አማኞች አለማቋረጥ ለእነርሱ በሚማልድ ሕያው አዳኝ ስለሚያምኑ፥ ዘላለማዊ ደኅንነት እንዳላቸው ማመልከት ነው። ይሁንና ጸሐፊው ይህ መተማመኛ ለኃጢአት ምክንያት ሊሆን እንደማይገባ ያስረዳል። እግዚአብሔር ልጆቹን ይቀጣል። ከነዓን የመንግሥተ ሰማይ ሳይሆን አማኞች ዛሬ በክርስቶስ ያገኙት መንፈሳዊ ርስት ተምሳሌት እንደሆነች እናስታውስ። የእግዚአብሔርን ቃል የሚጠራጠሩና በእግዚአብሔር ላይ የሚያምፁ ክርስቲያኖች መንግሥተ ሰማይ መግባታቸው አይቀርም። ነገር ግን የዛሬውን ርስት በማጣት ለእግዚአብሔር ቅጣት ራሳቸውን ያጋልጣሉ።

ለ. *እንፍራ* (4፡1-8)። አማኞች ዛሬ በክርስቶስ ባገኙት ርስት ደስ ሊሰኙ መብት አላቸው። የእግዚአብሔርን ቃል ከማመን እንዳንስት መጠንቀቅ አለብን። ቃሉ ዓላማውን ሊያሳካ የሚችለው በእምነት ሲዋሃድ ነውና። በዚህ ክፍል የቀረበው ሙግት በአያሌ አሳቦች ላይ የተመሠረተ ነው። (1) እግዚአብሔር *ሥራውን* ጨርሶ ስላረፈ፥ ከዚያ

ጊዜ ጀምሮ ወደ ዕረፍቱ መግባት እንችላለን። (2) አይሁዶች ወደ ዕረፍታቸው ለመግባት አልቻሉም። (3) ከብዙ ዓመታት በኋላ [መዝ. (95)]፥ እግዚአብሔር አሁንም ወደ ዕረፍቱ መግባት እንደምንችል ገልጾአል። ዛሬም ይህ ዕድል ተሰጥቶአል። ይህም ማለት ኢያሱ እስራኤላውያንን ወደ እውነተኛ ዕረፍት አላገባቸውም ማለት ነው። ገና ዕረፍቱ ቀርቶልናል።

እስራኤላውያን በከነዓን ያገኙት ዕረፍት፣ እኛም ሕይወታችንን ለክርስቶስ አሳልፈን በምንሰጥበት ጊዜ የምናገኘው ዓይነት ዕረፍት ነው። በእምነት ወደ ክርስቶስ በምንመጣበት ጊዜ፣ የደኅንነትን ዕረፍት እናገኛለን (ማቴ. 11፡28)። ራሳችንን ለእርሱ አሳልፈን በመስጠት በእምነት በምንታዘዝበት ጊዜ፣ የመታዘዝን ዕረፍት እናገኛለን (11፡29–30)። የመጀመሪያው ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን ማድረግ ሲሆን፣ (ሮሜ 5፡1)፥ ሁለተኛው የእግዚአብሔርን ሰላም መቀበል ነው (ፊልጵ. 4፡6–8)። ወደ ዕረፍት የምንገባው በእምነት ነው (ዕብ. 4፡3)። ዕረፍቱ ወደ እኛ የሚገባው ደግሞ እግዚአብሔርን በእምነት ስንታዘዝና ራሳችንን ለፈቃዱ ስናስገዛ ነው።

ሐ. <u>እንትጋ</u> (4፡9–13)። ትጋት የመንሸራተት (የመወሰድ) የኩብለላ (ውድቀት) ተቃራኒ ነው (2፡1–3)። ለመሆኑ፥ እንዴት ነው የምንተጋው? ለእግዚአብሔር ቃል ትኩረት በመስጠት ነው። እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ቃል ባለማመናቸው በዓመፀኛነት ምድረ በዳ ላይ ወድቀው ቀርተዋል። «እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው፤ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» (ሮሜ 10፡17)።

ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ቃል ከሰይፍ ጋር ሲያመሳስል እግዚአብሔር ቅዱሳንን ለመቅላት ይጠቀምበታል ማለት አይደለም! ይልቁንም ቃሉ የኃጢአተኞችን ልብ እንደሚነካ (የሐዋ. 5፡33፤ 7፡54) እና ሰይጣንን እንደሚያሸንፍ (ኤፌ. 6፡17) ለማሳየት ፈልጎ ነው። በዚህ ክፍል ትኩረት የተሰጠው፤ ቃሉ ወደ ውስጥ ጠልቆ ብርሃኑን በመፈንጠቅ፥ በሰው ልብ የተሰወረውን ሊገልጥ እንደሚችል በማስገንዘቡ ላይ ነው። ቃሉ «መርማሪ» ወይም «ሃያሲ» ነው። እስራኤላውያን ቃሉ በእነርሱ ላይ እንዲፈርድ መፍቀድ ሲገባቸው፤ ራሳቸው የእግዚአብሔርን ቃል ለመተቸት ይፈሩ።

እግዚአብሔር ልባችንን ያያል (መዝ. 4፡13)። እኛ ግን ሁልጊዜም በልባችን ውስጥ ምን እንዳለ ላናስተውል እንችላለን (ኤር. 17፡9)። እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ ያለውን ኃጢአትና አለማመን እናይ ዘንድ ቃሉን ይጠቀማል። ቃሉ ልባችንን ያጋልጠዋል። እግዚአብሔርን ካመንን፤ ቃሉ እግዚአብሔርን እንድንታዘዝና የተሰፋ ቃሎቹን

ገንዘባችን ለማድረግ ያስችለናል። እያንዳንዱ አማኝ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማትና ለማስተዋል መትጋት የሚኖርበትም ስለዚህ ነው። በቃሉ ውስጥ እግዚአብሔርን እናያለን። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያየንም እናያለን። ትክክለኛውን የማንነታችንን ምስል ከቃሉ እናገኛለን። ይህም ግንዛቤ ከንብንባችንን አውልቀን ለእግዚአብሔር ልባችንን እንድንከፍት፥ ፈቃዱን እንድንተማመንና እንድንታዘዘው ያስችለናል።

ይህ ተግባር የተቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ በተፈጸመው የማዳን ሥራ ሳቢያ ነው። እግዚአብሔር የፍጥረትን ሥራ በፈጸመ ጊዜ አርፎአል። የእግዚአብሔር ልጅም የአዲሱን ፍጥረት ሥራ በፈጸመ ጊዜ አርፎአል። እኛም ቃሉን በማመንና ፈቃዱን በመቀበል ወደ ዕረፍቱ እንገባለን። ይህንንም ልናደርግ የምንችለው ቃሉን በመስማት፥ በመረዳት፥ በማመንና በመታዘዝ ነው። በክርስቶስ ያለንን ርስት ልናሳውቅ የምንችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው።

ኢያሱ ኢያሪኮን ከመያዙ በፊት ሁኔታውን ለመሰለል ወደዚያው ሄዶ ነበር። እዚያም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ተገናኘው (ኢያሱ 5፡13–15)። በዚህ ጊዜ ኢያሱ ሁለተኛው አዛዥ መሆኑን ተገነዘበ! ጌታ ሰይፍ ይዞ ስለነበር፥ ኢያሱ በሙሉ ተገዥነት ከፊቱ ወደቀ። እንግዲህ ይህ የግል ልምምድ ነበር ለኢያሱ የአደባባይ ድል የሰጠው።

እኛም መንፈሳዊ ርስታችንን የምናውጀው ራሳችንን ለእርሱ በማስገዛትና ቃሉን በመታመን ነው። ከዚህ የመስጠት ሕይወት ሊመልሰን የሚችል ክፉና የማያምን ልብ እንዳይኖረን መጠንቀቅ ይኖርብናል።

# 4

# ኢየሱስ ከሊቀ ካህናቱ አሮን ይበልጣል

ዕብራውያን 4፡14–5፡10

ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ተስፋ ወደተገባላቸው ዕረፍት አላደረሳቸውም። እንዲያውም እርሱ ራሱ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዳይገባ ተከልክሏል። ሙሴ ወደ አካላዊው ዕረፍት ያስገባቸው ቢሆንም፥ ተስፋ ወደተገባላቸው መንፈሳዊ ዕረፍት ግን አልደረሱም (4፡8 አንብብ)። የመጀመሪያው ሊቀ ካህናት የነበረው አሮንስ? የአሮን ክህነት ከእነዚያ ሁሉ መሥዋዕቶቹና ሥርዓቶቹ ጋር የተጨነቀችውን ነፍስ ወደ ዕረፍት ሊመራት ይችላል?

ይህ መልእክት የተጻፈላቸው የዕብራውያን ክርስቲያኖች በሚያሳዝን ሁኔታ ወደ ቀድሞው የአባቶቻቸው ሃይማኖት ለመመለስ ከጅለው ነበር። ማንኛውም አይሁዳዊ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዞ ቤተ መቅደሱንና ካህናት በመሠዊያ ላይ የሚያካሂዱትን አገልግሎት የመመልከት ዕድሉ ነበረው። ይህም ሊያዩና ሊዳስሱ የሚችሉት ተጨባጭ ነገር ነበር። እንደ እነዚህ የዕብራውያን ክርስቲያኖች ሰው በስደት ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ፥ በእምነት ሳይሆን በማየት መመላለሱ እንደሚቀለው እሙን ነው። ብዙዎቻችን እነዚህ ሰዎች ከተጋፈጡዋቸው ላነሱ ችግሮች እንኳን ጌታን ተጠራጥረን የለምን?

የዕብራውያን መልእክት ማዕከላዊ ጭብጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናትነት ነው። ይህም አሁን በመንግሥተ ሰማይ ለሕዝቡ በሚያደርገው ምልጃና የክህነት አገልግሎት ላይ ያተኩራል። የክርስቶስ የክህነት አገልግሎት ከአሮንና እርሱን ተከተው ከተሾሙት ሁሉ በላይ ነው። ጸሐፊው አራት ነጥቦችን በማቅረብ አሳቡን ያዳብራል።

## 1. ኢየሱስ ክርስቶስ ከሌሎች የሚበልጥ የማዕረግ ስም አለው (4፡14–16)

«ትልቅ ሊቀ ካህናት. . . ስላለን» (4፡14)። አሮን ሊቀ ካህናት ሲሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ትልቅ (ታላቅ) ሊቀ ካህናት ነበር። ይህንን ማዕረግ የያዘ የብሉይ ኪዳን ካህን አልነበረም። ነገር ግን ጌታችን ታላቅ የሆነው በምንድን ነው?

በመጀመሪያ ደረጃ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውም አምላክም ነው። እርሱ «የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ» ነው። «ኢየሱስ» የሚለው ስም «አዳኝ» የሚል ፍች ሲኖረው፥ ሰብአዊነቱንና ምድራዊ አገልግሎቱን

ያመለክታል። «የእግዚአብሔር ልጅ» የሚለው አምላክነቱንና እግዚአብሔርነቱን ያሳያል። በልዩ ማንነቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰብአዊነትንና አምላክነትን አጣምሮ ይዟል። ይህም ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር፥ ለሰዎች ደግሞ እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን ሁሉ ለማምጣት ያስችለዋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በማንነቱ ብቻ ሳይሆን፥ በሥልጣኑም ታላቅ ነው። አሮንና ከእርሱ በኋላ የተሾሙ ካህናት ወደ መገናኛው ድንኳንና የቤተ መቅደሱ ቅድስተ ቅዱሳን በዓመት አንድ ጊዜ እየገቡ አገልግለዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን «በሰማያት ያለፈ» ሊቀ ካህናት ነው (4፡14፥ ቀጥተኛ አተረጓጎም)። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አባቱ በሚሄድበት ጊዜ ከባቢያዊ ሰማያትንና ፕላኔታዊ ሰማያትን አልፎ እግዚአብሔር ወደሚገኝበት ወደ ሦስተኛው ሰማይ ዐርጓል (2ኛ ቆሮ. 12፡2)። ከምድራዊው ይልቅ በሰማያዊ ድንኳን ውስጥ የሚያገለግል ሊቀ ካህናት ምንኛ የላቀ ነው!

ነገር ግን የክርስቶስ ሥልጣን ሌላም ገጽታ አለው። ይኸውም በመንግሥተ ሰማያት ውስጥ መኖሩ ብቻ ሳይሆን፥ ከዙፋን ላይ የተቀመጠ መሆኑ ነው። ዙፋኑም «የጸጋ ዙፋን» ነው (ዕብ. 4፡16)። በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ የሚገኘው የምሕረት መቀመጫ በእስራኤል የእግዚአብሔር ዙፋን ነበር (ዘጸ. 25፡17-22)። ያ ግን «የጸጋ ዙፋን» ተብሎ ሊጠራ አይችልም። ጸጋ በመጋረጃ ተከልሎና በድንኳን ውስጥ ተሸሽጎ የሚቀመጥ አይደለም።

በተጨማሪም፥ ተራ ሰዎች ወደ መገናኛው ድንኳንም ሆነ ቤተ መቅደስ ውስጥ ሊገቡ የማይችሉ ሲሆን፥ ካህናት እስከ መጋረጃው ድረስ መቅረብ ይችሉ ነበር። ከመጋረጃው አልፎ ሊሄድ የሚችለው ሊቀ ካህናት ብቻ ሲሆን፥ ይህንንም የሚያደርገው በስርየት ቀን ብቻ ነበር (ዘሌ. 16)። የአዲስ ኪዳን አማኞች ግን በድፍረት ወደ ጸጋው ዙፋን እንዲቀርቡ ተጋብዘዋል! ይህ ሊቀ ካህናታችን የሚያገለግልበት እንዴት ያለ ታላቅ ዙፋን ነው!

ታላቁ ሊቀ ካህናታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማያት በዙፋን ላይ ተቀምጧል። እዚህ ላይ ሊቀ ካህናችንን ታላቅ የሚያደርግ ተጨማሪ ገጽታ እንዳለ መገንዘቡ አስፈላጊ ነው። ይኸውም ለእርዳታ ወደ እርሱ ለሚመጡት የምሕረትና የጸጋ አገልግሎት እያበረከተ መሆኑ ነው። ምሕረት ማለት የሚገባንን ቅጣት ሳንቀበል ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን መቀበል ማለት ነው። ጸጋ ማለት ደግሞ ብቁ ያልሆንለትንና የማይገባንን መቀበል ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ ምሕረትንና ጸጋን ሊያገለግል የሚችል የብሉይ ኪዳን ካህን አልነበረም። አንድ

እስራኤላዊ በኃጢአት በሚፈተንበት ጊዜ፥ በቀላሉ የሊቀ ካህናቱን እርዳታ ሊያገኝ አይችልም ነበር። እግዚአብሔር እንዲረዳው እንኳ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሊገባ አይችልም ነበር። በጸጋ ዘመን ያለነው ግን የኢየሱስ ክርስቶስ አማኞች እንደ መሆናችን መጠን፥ በየትኛውም ጊዜ፥ በየትኛውም ሁኔታ ወደ ሊቀ ካህናቱ ልንቀርብና የሚያስፈልገንን እርዳታ ልናገኝ እንችላለን።

ታላቁ ሊቀ ካህናችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከአሮን የበለጠ በመሆኑ በጸጋ ዘመን ላለነው አማኞች ሁሉ ማስተማመኛዎችን ሊሰጠን ይችላል። በመጀመሪያ ደረጃ፥ በመከራ ውስጥ በማለፋችን ብቻ ሃይማኖታችንን የምንተውበት ምክንያት የለም (ዕብ. 4፡14)። እነዚህ ዕብራውያን ክርስቲያኖች በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የነበራቸውን እምነትና ድፍረት ለመተው ተፈትነው ነበር (3፡6፥ 14 ተመልከት)። በክርስቶስ የሚገኘው ደኅንነት ዘላለማዊ ስለሆነ፥ ይህ ደኅንነታቸውን የመተው ጉዳይ አይደለም (5፡9)። ይልቁንም እምነታቸውን በይፋ የመመስከር ጉዳይ ነበር። ወደ ብሉይ ኪዳን ሥርዓት ቢመለሱ፥ ለሁሉም የሚያስተላልፉት መልእክት በኢየሱስ ክርስቶስ እንደማያምኑ ነበር (ገላ. 2፡11-21)። የዚህ ዓይነቱ አለማመን ደግሞ የክርስቶስን ስም ያሰድባል።

የደኅንነት ትልቁ ዓላማ የእግዚአብሔር መክበር ነው (ኤፌ. 1፡6፥ 12፥ 14)። እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ሕግ ጥሰው የጥጃ ጣዖት በሠሩ ጊዜ፥ ሙሴን እጅግ ያሳሰበው የእግዚአብሔር ክብር ጉዳይ ነበር (ዘጸ. 32)። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን አጥፍቶ ከሙሴ አዲስ ሕዝብ ለመጀመር ቢፈልግም፥ ሙሴ ፈቃደኛ አልነበረም። ነገር ግን ሙሴ በእግዚአብሔር ክብርና የተስፋ ቃል ላይ ተመሥርቶ ለሕዝበ እስራኤል ማለደ። ስለዚህም እግዚአብሔር ሕዝቡን ለኃጢአታቸው ቀጥቶ ከጥፋት አዳናቸው (ዘጸ. 32፡11-13)።

ሁለተኛው ማስተማመኛ፥ በድፍረት ወደ እግዚአብሔር ቀርበን የሚያስፈልገንን እርዳታ ልናገኝ ስለምንችል፥ ወደ ኋላ መመለስ የለብንም የሚል ነው (ዕብ. 4፡16)። ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስፈልገንን ምሕረትና ጸጋ ስለሚሰጠን፥ የትኛውም መከራም ሆነ ፈተና ከአቅማችን በላይ አይሆንም። «እርሱ ግን ከእኛ የራቀ ነው!» ብለን ልንከራከር እንችላለን። «እርሱ ፍጹም የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ፥ እንደ እኛ ስላሉት ደካማ ኃጢአተኞች ችግር ምን ሊያውቅ ይችላል?» ብለንም ልንጠይቅ እንችላለን።

ነገር ግን ይህ የታላቅነቱ አካል እንደሆነ መገንዘብ አለብን! ጌታችን የሰውን ሥጋ ለብሶ በምድር ላይ በሚያገለግልበት ጊዜ ዛሬ እኛ

በምናልፍባቸውና በሌሎችም ችግሮች ውስጥ አልፎአል። እንዲሁም፥ ኃጢአትን ሠርቶ የማያውቅ ሰው ከእኔና ከእናንተ በላይ የፈተናና የመከራ ጥልቀት እንደሚሰማው መገንዘብ አለብን። ክርስቶስ በኃጢአት ባይወድቅም ተፈትኗል። ስለሆነም፥ እኛም በምንፈተንበት ጊዜ ሊረዳን ይችላል። እኛ እምነታችንን ለመጠበቅ ሳንችል ብንቀር፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቃት እንደ ጎደለው ወይም እኛን መርዳት እንደ ተሳነው ከቶውን አያሳይም። ይልቁንም ጸጋውና ምሕረቱ በነፃ ቀርቦልን ሳለ ለመጠቀም አለመቻላችንን ለዓለም እየተናገርን ነው።

## 2. ኢየሱስ ክርስቶስ ከአሮን የበለጠ ሹመት ተቀብሏል (5፡1፥4–6)

በኬንታኪ ግዛት፥ ኮቪንግተን የምትገኝ የካሊቨሪ መጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያን መጋቢ በሆንሁ ጊዜ፥ ወደ ከተማው ማዘጋጃ ቤት ሄጄ የቃል ኪዳን ውል መፈጸም ይጠበቅብኝ ነበር። ይህንን ካላደረግሁ ሙሽሮችን የማጋባት ሕጋዊ ሥልጣን አይኖረኝም። የሹመት የምስክር ወረቀቴን በማሳየት የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ መሆኔን ማረጋገጥ ነበረብኝ።

አንድ ቀን ከአባሎቻችን አንዱ መረበሹን የሚገልጽ ስልክ ደወለልኝ። በቀጣዩ ዕለት ለመጋባት ያቀዱ ክርስቲያን ወገኖች ሊያጋባቸው ከሚቹገን በመጣ አንድ ዘመዳቸው አማካኝነት የጋብቻ ሥነ ሥርዓታቸውን ሊያከናውኑ አስበው ሳለ ሰውዬው የማጋባት ሥልጣን እንዳልተሰጠው ተረዱ። እንግዳው መጋቢ የጋብቻ ቃል ኪዳኑን ሊያነብ መቻሉ ግልጽ ነው። በተጨማሪም፥ ከእኔ በላይ ተጋቢዎቹን ደህና አድርጎ ያውቃቸዋል። ነገር ግን ይህ ብቻ ሙሽሮቹን የማጋባት ሥልጣን ሊያሰጠው አልቻለም። ሕጋዊ ፈቃዱ አልነበረውምና።

ማንም ራሱን እንደ ሊቀ ካህናት ቀርቶ እንደ ካህንም ሊሾም አይችልም። ንጉሥ ሳዖል ያለ ሹመቱ መሥዋዕት ለማቅረብ ሲሞክር የገጠመው ዕጣ መንግሥቱን ማጣት ነበር (1ኛ ሳሙ. 13)። ቆሬና ከእርሱ ጋር የተባበሩ ዓማፅያን ራሳቸውን ካህናት አድርገው ሊሾሙ ሲሞክሩ እግዚአብሔር ፈርዶባቸዋል (ዘኁል. 16)። ንጉሥ ዖዝያን ወደ ቤተ መቅደሱ ገብቶ ዕጣን ለማጠን ሲሞክር እግዚአብሔር በለምፅ መቶታል (2ኛ ዜና 26፡16–21)።

አሮን ሊቀ ካህናት ይሆን ዘንድ በእግዚአብሔር የተመረጠ አገልጋይ እንደ መሆኑ፥ በአግባቡ ተሹሞ ሥልጣን እንዲይዝ ተደርጓል (ዘጸ. 28)። አሮን ያገለግል ዘንድ የተመረጠ ሊቀ ካህናት ነበር። ዋና ተግባሩም እግዚአብሔር ያዘዛቸውን መሥዋዕቶች በመሠዊያው ላይ

ማቅረብ ነበር (ዕብ. 8፡3-4፤ 9፡14)። መሥዋዕቶቹ በትክክለኛ ስፍራ፥ በትክክለኛ አገልጋይ ካልቀረቡ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አይኖራቸውም ነበር።

የክህነትና የመሥዋዕቶች ሥርዓት መኖር፥ ራሱ ሰው ከእግዚአብሔር እንደ ራቀ ያመለክት ነበር። እግዚአብሔር የሌዊን ሥርዓት የመሠረተው በጸጋው ነበር። ዛሬ ያ ሥርዓት በኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ተፈጽሟል። እርሱ በመስቀል ላይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ባቀረበው መሥዋዕት የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያገለግል መሥዋዕትም ሊቀ ካህናት ነው።

በዕብራውያን 5፡1 የተገለጸው የሹመት ርእስ ጉዳይ በ5፡5-6 ይበልጥ ተስፋፍቶ ቀርቧል። ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ተሾመ እንጂ ራሱን እንደ ሊቀ ካህናት አልሾመም። በ5፡5 የቀረበው ጥቅስ ከመዝሙር 2፡7 የተወሰደ ነው። ይህ ጥቅስ ቀደም ሲል ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማረጋገጥ በ1፡5 ቀርቦ ነበር። በ5፡5 ግን ትኩረት የተሰጠው በኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ላይ ሳይሆን፥ በክህነቱ ላይ ነው። እንደዚያ ከሆነ፥ ይህ ጥቅስ ለክፍሉ የሚሰጠው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚሆነውን አሳብ ከሐዋርያት ሥራ 13፡33-34 እናገኛለን። በዚህ ስፍራ ሐዋርያው ጳውሎስ መዝሙር 2፡7ን በመጥቀስ ምን ማለት እንደሆነ አብራርቷል። «ዛሬ ወልጄሃለሁ» የሚለው ዐረፍተ ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣቱን እንጂ በቤተልሔም መወለዱን አያመለክትም። የእግዚአብሔር ልጅ በትንሣኤው ወደ ከበረ አዲስ ሕይወት «ተወልዷል»! በጸጋው ዙፋን ሊቀ ካህናታችን ይሆን ዘንድ በከበረ አካል ወደ ሰማይ ዐረገ። አሮን የሊቀ ካህናትነትን ሹመት ባገኘ ጊዜ፥ የእንስሳትን መሥዋዕት ያሳርግ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሊቀ ካህናታችን ይሆን ዘንድ ራሱን ሠውቷል። ከዚያም ከሞት ተነሥቷል!

እግዚአብሔር አብ፥ «አንተ ልጄ ነህ» ብቻ ሳይሆን፥ «አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ»ም ብሎታል ዕብ. 5፡6፤ ከመዝሙር (110)፡4 የተወሰደ ። ይህ መዝሙር ቀደም ብሎም (1፡3) ኢየሱስ ክርስቶስ በጠላቶቹ ላይ ድልን እንደ ተቀዳጀ ለማረጋገጥ ተጠቅሶ ነበር። አሮን በተሾመ ጊዜ እግዚአብሔር በቀጥታ ለእርሱ በመናገር ክህነቱን አላወጀም። ነገር ግን እግዚአብሔር ስለ ልጁ ይህንን ልዩ አወጃ አድርጓል።

የክርስቶስን ክህነት ልዩ የሚያደርጉና በዚህም ምክንያት፥ ሹመቱን ከአሮን የሚያልቁ ሁለት ምክንያቶች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ፥ እርሱ

*ለዘላለም* ሊቀ ካህናት ነው። የሰው የሕይወት ዘመን የተጣለበትን የጊዜ እገዳ ማለፍ ስለማይችል በብሉይ ኪዳን ለዘላለም ካህን ሆኖ ያገለገለ ማንም የለም። «ዘላለም» የሚለው ቃል በዚህ መልእክት ውስጥ በጣም አስፈላጊ ነው። ቢያንስ ስድስት ጊዜያት ያህል ጸሐፊው የክርስቶስ ክህነት ዘላለማዊ መሆኑን አመልክቷል (5፡6፤ 6፡20፤ 7፡17፥ 21፥ 24፥ 28)። እርሱ ዘላለማዊ ካህን ስለሆነ፥ ለሕዝቡ ዘላለማዊ ደኅንነትን ይሰጣል።

የክርስቶስን ሹመት ልዩ የሚያደርገው ሁለተኛው ምክንያት፥ ሹመቱ ከብሉይ ኪዳን ካህናት *የተለየ* መሆኑ ነው። የእነርሱ የአሮን ዓይነት ሲሆን፥ የክርስቶስ ግን የመልከ ጼዴቅ ዓይነት ነው። ይህ በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ቁልፍ አሳብ ስለሆነ፥ ጊዜ ወስደን ልንመረምርና ልንረዳው ይገባል።

መልከ ጼዴቅ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰው ሁለት ጊዜ ብቻ ነው [ዘፍጥ. 14፡17–24 እና መዝ. (110)፡4]። የስሙ ትርጉም፥ «የጽድቅ ንጉሥ» የሚል ሲሆን፥ «የሳሌም (ሰላም) ንጉሥ»ም ተብሎ ተጠርቷል። ነገር ግን ስለ መልከ ጼዴቅ የሚያስገርመው በድርቡ ካህንም ንጉሥም መሆኑ ነው! ንጉሥ *ያዝያን* ንጉሥም ካህንም ለመሆን ፈልጎ በእግዚአብሔር ተቀጥቷል። እነዚህን ሁለት ሥልጣናት አንድ ላይ አጣምረው ሊይዙ የቻሉት ኢየሱስ ክርስቶስና፥ ሕግ ከመሰጠቱ በፊት የነበረው መልከ ጼዴቅ ብቻ ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ *በዙፋን ላይ የተቀመጠ* ሊቀ ካህናት ነው!

ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለም ካህን ሊሆን የቻለበት ምክንያት፥ «እንደ መልከ ጼዴቅ ካህን» በመሆኑ ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ መልከ ጼዴቅ መሞት የሚናገር ክፍል የለም (ዕብ. 7፡1–3 አንብብ)። በእርግጥ ሰው በመሆኑ አንድ ወቅት ላይ መሞቱ የማይቀር ነው። ነገር ግን መሞቱ አልተገለጸም። በዚህም ምክንያት ይህም መልከ ጼዴቅ *የዘላለም* ካህን ለሆነው ለኢየሱስ ክርስቶስ ተስማሚ ተምሳሌት ሊሆን በቅቷል።

ነገር ግን መልከ ጼዴቅ እንደ *ሰማያዊ* ሊቀ ካህናትም ጌታችንን በተምሳሌትነት ይወክለዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሌዊ ነገድ ስላልተወለደ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት እንደ ካህን ሊያገለግል አይችልም ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው የዳዊት ዘር ከሆነው ከይሁዳ ነገድ ነበር። በሰማይ ሊቀ ካህናት ይሆን ዘንድ በምድር መሥዋዕት ሆነ። እነዚህ ሁሉ እውነቶች በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ከምዕራፍ 7–10 የቀረቡ ሲሆኑ፥ እዚህ በመግቢያነት ቀርበዋል።

### 3. ኢየሱስ ክርስቶስ ከአሮን የበለጠ ይራራል (5፡2፥ 7–8)

እያንዳንዱ የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት አገልግሎቱን የሚያበረክተው ላልተማሩትና ለሳቱት ነበር (ዕብ. 5፡2)። እግዚአብሔር ለዓመፃ ኃጢአቶች ፍርድን ከመበየን ውጭ ያዘጋጀው ችሮታ አልነበረም (ዘጸ. 21፡12–14፤ ዘኁ. 15፡27–31 አንብብ)። ነገር ግን ሰዎች በድካምና በስሕተት ኃጢአትን በሚሠሩበት ጊዜ የመውጫ ቀዳዳ አዘጋጅቶላቸው ነበር። የብሉይ ኪዳን ካህን እርሱ ራሱም ሰው ስለሆነ፥ የኃጢአተኞች ችግር ሊገባው ይችል ነበር። እንዲያውም በስርየት ቀን ለሕዝቡ ኃጢአት መሥዋዕት ከማቅረቡ በፊት ለራሱ ኃጢአት መሠዋት ነበረበት! (ዘሌ. 16፤ ዕብ. 9፡7)።

ኃጢአተኛ የሆነ ሰው ለሌሎች ኃጢአተኞች የሚራራ ሊመስለን ይችላል። ይህ ግን ሁልጊዜም እውነት አይደለም። ሰዎችን ራስ ወዳድ ስለሚያደርግ፥ በራሳችን ጉዳይ ተውጠን የሌሎችን ሰዎች ጉዳቶች እንዳንመለከት ሊያሳውረን ይችላል። ኃጢአት ልባችንን በማደንደን ከመራራት ይልቅ እንድንፈርድ ሊያደርገን ይችላል። ሊቀ ካህኑ ኤሊ ሐናን ሰክረሻል ባላት ጊዜ፥ ልጅ ለማግኘት ስትጸልይ የነበረችው ሐና እንዴት ልቧ እንደተሰበረ ማስተዋል ይበቃል (1ኛ ሳሙ. 1)።

ስለሆነም፥ ለኃጢአተኛ የሚራራውና ለመርዳት የሚፈልገው ንጹሕ ልብ ያለው መንፈሳዊ ሰው ነው (ገላ. 6፡1 አንብብ)። እኛ ኃጢአተኞች ስለሆንን፥ ኃጢአተኞችን ለመርዳት እንቸገራለን። ክርስቶስ ግን ፍጹም ስለሆነ፥ በኃጢአት ከወደቅን በኋላ ጉድለታችንን ሊያስተካክል ይችላል።

ጌታችን በምድር ላይ የአገልግሎቱ ዘመን ለሊቀ ካህናዊ አገልግሎቱ ይዘጋጅ ነበር (ዕብ. 5፡7–8)። «በሥጋው ወራት» የሚለው ሐረግ «የሰውን ሥጋ ለብሶ በምድር ላይ ይመላለስ በነበረ ጊዜ» ማለት ነው። ጌታችን ከልደቱ እስከ ሞቱ ድረስ ኃጢአት ባይሠራም፥ የሰብአዊ ባሕርይን ድክመቶች ተጋፍጧል። ማደግና ወደ በሳልነት መሸጋገር ምን እንደሆነ ያውቅ ነበር (ሉቃስ 2፡52)። መራብን፥ መጠማትን፥ መድከምን በሥጋዊ ሕይወቱ ውስጥ ተለማምዷል (ዮሐ. 4፡6–8፥ 31)። ለኃጢአት ከመፈተኑም በላይ (ማቴ. 4፡1–11)፥ በኃጢአተኞች ስደት ደርሶበታል።

የእግዚአብሔር ልጅ «መታዘዝን የሚማረው» እንዴት ነው? ክርስቶስ ይህንን የተማረው ማንኛውም ልጅ መታዘዝን ሊማር በሚገባው መንገድ ሲሆን፥ ይህም የሕይወትን ልምዶች የሚመለከት ነው። ጌታችን በምድራዊ ሕይወቱ የአብን ፈቃድ በማመን እንደኖረ ማስታወስ አለብን። አምላክ እንደ መሆኑ፥ ምንም መማር

አያስፈልገውም። ነገር ግን የሰውን ሥጋ ለብሶ እንደ መጣ የእግዚአብሔር ልጅ፥ በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ የሚያልፈውን ነገር ሁሉ መለማመድ ነበረበት። ይህም ያስፈለገው እንደ ሊቀ ካህናት ለማገልገል ይችል ዘንድ ነው። እግዚአብሔር በባሕርዩ ዓመፀኛ ሊሆን ስለማይችል፥ እንዴት መታዘዝ እንዳለበት መማር አያስፈልገውም። ነገር ግን የሰውን ሥጋ እንደ ለበሰ ሰው–አምላክ በታዛዥነት ውስጥ የሚካተቱትን ነገሮች ማወቅ ያስፈልገው ነበር። በዚህ መንገድ የእኛን ትክክለኛ ሁኔታ ሊገነዘብ ችሏል።

ይህ ዝግጅት ሞትንም ያካተተ ነበር። የዕብራውያን ጸሐፊ ጌታችን በጌቴሰማኒ ያሳለፈውን ሰቆቃ ገልጾአል (ማቴ. 26፡36–46)። ወደ መስቀሉ ሲቀርብ ክርስቶስን ያሳሰበው ሥጋዊ ሞት ሳይሆን በኃጢአት ምክንያት ከአብ መለየቱ ነበር። ሌሎች የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሲሞቱ እንዲህ ባለ ከፍተኛ የጭንቅ ስሜት አላለፉም ነበር። ምክንያቱም በሥጋው የመላውን ዓለም ኃጢአት የተሸከመ ሌላ አገልጋይ አልነበረም።

በጌቴሴማኒ ጸሎቱ፥ ጌታችን አብን አልተቃወመም። ይልቁንም የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይፈጸም ሲል ጸልዮአል (ሉቃስ 22፡42)። የጸለየው ከሞት ለማምለጥ ሳይሆን፥ ከሞት ለመዳን ነበር። የጸለየው ከሞት ለመነሣት በመሆኑ፥ እግዚአብሔር ያንን ጸሎት መልሷል። ስለ ሞቱ አስቀድሞ የተነበየ ሲሆን፥ ነፍሱን በገዛ ፈቃዱ እንደሚሰጥም ተናግሯል። ይህም በዕብራውያን 5፡5 ከቀረበው እና ከሞት መነሣቱን ከተነበየው የመዝሙር 2፡7 ጥቅስ ጋር ይስማማል።

የዕብራውያን ጸሐፊ አብ የክርስቶስን ጸሎት እንደመለሰ ገልጾአል (5፡7)። በመስቀል ላይ መሞቱ እውነት በመሆኑ፥ የጸለየው ከዚህ ሞት ለመዳን አልነበረም ማለት ነው። እንዳይሞት ጸልዮ አብ ቢመልስለት ኖሮ ክርስቶስ በመስቀል ላይ አይሞትም ነበርና። የጸለየው አብ ከሞት እንዲያመልጥ እንዲያደርገው ሳይሆን ከሞት (ከመቃብር) እንዲታደገው ነበር። ስለዚህም አብ ኢየሱስን ከሙታን በማስነሣት ጸሎቱን መለሰለት።

ማንም ሰው የኢየሱስ ክርስቶስን ዓይነት ሞት አልሞተም። እርሱ ለእኛ ኃጢአት ሆኗል (2ኛ ቆሮ. 5፡21፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡24)። ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት ሲሞቱ፥ ክርስቶስ ግን ለዓለም ኃጢአት ሞቷል። ከሁሉም የሚበልጠውን ሥቃይ ስለተቀበለ ሕዝቡ በመከራ ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ ሊራራ ይችላል። የዚህ መልእክት አንባቢዎች በአስቸጋሪ ጊዜ ውስጥ በማለፍ ላይ ነበሩ። ነገር ግን «ደምን እስከማፍሰስ ድረስ አልተቃወሙም» (ዕብ. 12፡4)። ንብረቶቻቸው

ይወረሱባቸውና ለመሳለቂያነት ይዳረጉ የነበሩ ቢሆኑም (10፡32–34)፥ በመስቀል ላይ ተሰቅለው በአብ የመተው መሪር ፅጣ ግን አልገጠማቸውም።

የትኛውም ዓይነት መከራ ቢደርስብን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ችግሮቻችንን ተገንዝቦ ሊረዳን ይችላል። የክርስቶስን የመራራትና የማበረታታት ብቃት ልንጠራጠር አይገባም። እንዲሁም ደግሞ የሌሎችን ችግሮች እንድንገነዘብና በተሻለ መንገድ እንድንረዳቸው ለማስቻል አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ሆን ብሎ በፈተና ውስጥ እንደሚያሳልፈንም ማወቅ አለብን (2ኛ ቆሮ. 1 ከቁጥር 8 ጀምሮ)።

ቻርልስ ስፐርጀን በለንደን ወጣት ሰባኪ በነበሩ ጊዜ፥ የስመረ አገልግሎታቸው አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ሰዎችን አስቀንቷቸው ነበር። በዚህም ምክንያት የተለያዩ ሐሜቶችና የስፐርጀንን ዝና ለማጉደፍ የሚዛመቱ ወሬዎች ነበሩ። ስብከቶቻቸው «ፍሬ ቢሶች» ሲባሉ፥ እርሳቸውም «ቲያትረኛ» እና «የአትሮኖስ ዱልተኛ» በሚሉ ቅጽሎች ይዘለፉ ጀመር። አገልግሎታቸው ሥር ከሰደደ በኋላ እንኳ ስለ ስፐርጀን የሚናገሩ የውሸት ጽሑፎች ጋዜጦች ላይ መውጣታቸው አላቋረጠም። ሃይማኖታዊ ጋዜጦች ሳይቀሩ ስፐርጀንን ተስፋ ለማስቆረጥ ታጥቀው የተነሡ ይመስል ነበር።

በተለይ አንድ ትችት ጋዜጣ ላይ ከወጣ በኋላ ስፐርጀን በጌታ ፊት ወድቀው፥ «ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ አንተ ለእኔ ስትል ዝናህን ጥለሃል። እኔም በፈቃዴ ለአንተ ዝናዬን እጥላለሁ» ሲሉ ጸለዩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስፐርጀን የልብ ሰላም አገኙ። ታላቅ ሊቀ ካህናቸው ችግራቸውን እንደሚረዳላቸውና እያንዳንዱ ሰዓት የሚያስፈልጋቸውን ጸጋ እንደሚሰጣቸው ተገንዝበዋል።

## 4. ኢየሱስ ክርስቶስ ከአሮን የሚበልጥ መሥዋዕትን አቅርቧል (ዕብ. 5፡3፥ 9–10)

ይህ አሳብ ቀደም ብሎ የተነሣ ሲሆን፥ ጸሐፊው በምዕራፍ 9 እና 10 በዝርዝር ያብራራዋል።

በዚህ አሳብ ውስጥ ሁለት አስፈላጊ ነገሮች ተካተዋል። ከእነዚህም የመጀመሪያው ኢየሱስ ክርስቶስ ለራሱ መሥዋዕት ማቅረብ እንዳላስፈለገው ነው። በዓመታዊው የስርየት በዓል ላይ ሊቀ ካህኑ ለሕዝቡ ሊሠዋ የሚችለው መጀመሪያ ለራሱ መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ብቻ ነበር (ዘሌ. 16)። ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአት የሌለው የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ፥ ለራሱ መሥዋዕት የሚያቀርብበት ምክንያት አልነበረውም። ከአብ ጋር ፍጹማዊ ግንኙነት ስለነበረው፥ ከኃጢአት ለመንጻት የሚደረግ ሥርዓት ለእርሱ አስፈላጊ አልነበረም።

ሁለተኛው ልዩነት የብሉይ ኪዳን መሥዋዕት በተደጋጋሚ የሚደረግ ሲሆን፥ የጌታችን ግን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የቀረበ መሆኑ ነው። በተጨማሪም፥ እነዚያ መሥዋዕቶች ኃጢአትን የመሸፈን እንጂ የማንጻት ብቃት አልነበራቸውም። ኃጢአትን ለማንጻትና ለማስወገድ እንከን የሌለበትን የእግዚአብሔርን በግ መሥዋዕት ይጠይቅ ነበር።

ክርስቶስ ኃጢአት የሌለው ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑና ፍጹም መሥዋዕት ሊያቀርብ በመቻሉ፥ የዘላለም ደኅንነት መሥራች ነው (ዕብ. 5፡9) ። ይህ የትኛውም የብሉይ ኪዳን ካህን ሊያደርግ ያልቻለውና ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ያስገኘልን መሥዋዕት ነው። «ከተፈጸመ በኋላ» የሚለው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ «ፍጹም አልነበረም» የሚል መልእክት አያስተላልፍም። ይህ አሳብ በዕብራውያን 2፡10 ጥናታችን የተብራራ ሲሆን፥ የአገልግሎቱን ከፍጻሜ መድረስ የሚያመለክት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በተቀበላቸው መከራዎች ምክንያት በሰማይ ለሚያከናውነው የሊቀ ካህናትነት አገልግሎት ብቁ ሆኗል። እርሱ ሕዝቡን ለማዳን፥ ለመጠበቅና ለማበርታት ይችላል።

«ለሚታዘዙት» (5፡9) የሚለው ባንታዘዘው የዘላለምን ደኅንነት እናጣለን የሚል መልእክት ያስተላልፍ ይሆን? እግዚአብሔርን መታዘዝ በእግዚአብሔር መተማመን እንደ ማለት ነው። «የሚታዘዙለት» የሚለው ቃል በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑትን ሰዎች የሚገልጽ ነው። በሐዋርያት ሥራ 6፡7 ከካህናት ብዙዎች ለእምነት መታዘዛቸው ተገልጾአል። «ነገር ግን ሁሉም የምሥራቹን ቃል አልታዘዙም» (ሮሜ 10፡16)። «ለእውነት እየታዘዛችሁ. . . ነፍሳችሁን አንጽታችሁ» (1ኛ ጴጥ. 1፡22)። በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ጥሪውን ከታዘዝን በኋላ፥ ዘላለማዊው ደኅንነቱን እንቀበላለን።

በዚህ ክፍል ውስጥ የቀረቡት አራት ነጥቦች፥ ታላቅ ሊቀ ካህናት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከአሮን እንደሚበልጥ ለማስገንዘብ ብርቱ ማረጋገጫዎች ናቸው። በሚበልጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ደስ መሰኘት ሲቻል፥ ወደ ሕግ የበታችነት መመለሱ ለማንም ቢሆን ሞኝነት ነው። እንግዲህ፥ እነዚህ የዕብራውያን አማኞች ወደ ሕጉ ለመመለስ የተፈተኑት ለምን ነበር? *ምክንያቱም በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባላቸው እምነት አድገው አልበሰሉም ነበር!* ስለሆነም፥ ጸሐፊው ለአንድ አፍታ ቆም ብሎ በጌታ እንዲያድጉ ይመክራቸዋል። ይህም የቀጣዩ ምዕራፍ ጭብጥ ይሆናል።

## 5

# መጻተኞች ወደፊት በመገስገስ ዕድገት ማሳየት አለባቸው

ዕብራውያን 5፥11–6፥20

«በእምነትና በትዕግሥት የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንድትሆኑ. . . [አንፈልግም]» (6፥12)።

ይህ ጥቅስ አስቸጋሪና ብዙውን ጊዜ ሰዎች በተሳሳተ መልኩ የሚረዱትን ክፍል ዋና መልእክት ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል። እስራኤላውያን ወደ ኋላ ለመመለስ በመፈለጋቸው እግዚአብሔር ቃል የገባላቸውን ተስፋ ሳይወርሱ ቀርተዋል። ምንም አደጋ ሳያገኛቸው ከግብጽ ምድር ቢወጡም፥ የተስፋይቱን ምድር ወርሰው ደስ ሊሰኙ አልቻሉም። ዛሬም አማኞች ተመሳሳይ ስሕተት ሊፈጽሙ ይችላሉ።

ይህ ክፍል በመንፈሳዊ ዕድገት ላይ እንደሚያተኩር ከተገነዘብን በደኅንነታችን ዋስትና ላይ ጥያቄ ሊያስከትሉ የሚችሉትን የተሳሳቱ አተረጓጎሞች ልንለይ እንችላለን። በዚህ ክፍል፥ ጸሐፊው ከመንፈሳዊ ዕድገት ጋር በሚዛመዱ ሦስት ርእስ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል።

## 1. በመንፈሳዊ ሕይወት ያለማደግ ምልክቶች (5፥11–14)

ጸሐፊው ስለ ክርስቶስ ሰማያዊ ክህነት ለመጻፍ ሲዘጋጅ አንባቢያኑ ለዚህ ትምህርት ዝግጁዎች ለመሆናቸው እርግጠኛ አልነበረም። ችግሩ እርሱ የተማሪዎቹን ሁኔታ ለመረዳት የሚቸገር አስተማሪ መሆኑ ሳይሆን፥ የእነርሱ የግንዛቤ ማነስ ነበር በ5፥11። «ጆሮቻችሁ ስለ ፈዘዙ» ተብሎ የተተረጎመው ሐረግ፥ በ6፥12 «ዳተኛ» ተብሎ ተተርጉሟል። ይህም መንፈሳዊ ዕድገትን የሚገታ መንፈሳዊ ስልቹነት ወይም ስንፍናን የሚያመለክት ነው።

ለመሆኑ፥ አራቱ በመንፈሳዊ ሕይወት ያለማደግ ምልክቶች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. <u>ለቃሉ የተሰላቸ ስሜት ማሳየት</u> (5፥11)። እነዚህ አማኞች የኋሊት ጉዟቸውን የጀመሩት ከቃሉ በመንሸራተት (2፥1–4) እና ቃሉን በመጠራጠር (3፥7–4፥13) ነበር። ከዚህም የተነሣ አሁን ለመስማት እስከማይችሉ ድረስ ጆሮዎቻቸው ፈዝዘዋል። ይህም ቃሉን ለመቀበልና ተግባራዊ ለማድረግ እንዳይችሉ አድርጓቸዋል። እነዚህ አማኞች በተሰሎንቄ ክርስቲያኖች የነበረው ቃሉን በየዋሕነት ወደ

ልባቸው የመቀበል ፈቃደኝነት አልነበራቸውም። «ስለዚህ የመልእክትን ቃል እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከእኛ በተቀበላችሁ ጊዜ፥ በእውነት እንዳለ በእናንተ በምታምኑ ደግሞ እንደሚሠራ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርጋችሁ ስላልተቀበላችሁት፥ እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ሳናቋርጥ እናመሰግናለን» (1ኛ ተሰ. 2፡13)።

በመንፈሳዊ ሕይወት ወደ ኋላ የመሄድን ሁኔታ ከሚያሳዩ ምልክቶች አንዱ ለመጽሐፍ ቅዱስ የተሰላቸ ስሜት ማሳየት ነው። ሰው ለእግዚአብሔር ነገር ስልቹ መሆን ሲጀምር የሰንበት ትምህርቱ፥ ስብከቱ፥ የትኛውም መንፈሳዊ ተግባር አሰልቺ ይሆንበታል። ችግሩ ብዙውን ጊዜ የሰንበት ትምህርት አስተማሪው ወይም የመጋቢው ሳይሆን፥ የአማኙ ነው።

ለ. <u>ለማካፈል አለመቻል</u> (ዕብ. 5፡12)። መንፈሳዊ እውነትን ለሌሎች ማካፈል የብስለት ምልክት ነው። ሁሉም ክርስቲያኖች የማስተማር ስጦታ ባይኖራቸውም፥ ከቃሉ የተማሩትን ለሌሎች ሊያካፍሉ ይችላሉ። ልጆች ሊማሩ ከሚያቅቷቸው ነገሮች አንዱ ለሌሎች ማካፈል ነው። የዚህ መልእክት ተቀባዮች ከረዥም ጊዜ በፊት በክርስቶስ ያመኑ በመሆናቸው የእግዚአብሔርን እውነት ለሌሎች ማካፈል መቻል ነበረባቸው። ከተቀበሉት አንፃር ሌሎች እንዲያድጉ መርዳት ሲችሉ፥ እንደገና ቀላል መንፈሳዊ ነገሮችን ሌሎች እንዲያስተምሯቸው ይፈልጉ ነበር። እነዚህ ሰዎች «በከርሞ ጥጃነት» ሕይወት ውስጥ ነበሩ!

ሐ. <u>የልጆች ምግብ</u> (5፡12-13)። ወተት እንደ ሌላው ምግብ የሆድን ብዙ የማድቀቅ ሂደት ሳይጠይቅ ከሰውነታችን ጋር በቀላሉ ስለሚዋሃድ፥ በተለይ ለልጆች ተስማሚ ነው። ጠንካራ ምግብ ግን ጥርሰ ጠንካሮች ብቻ ሊመገቡ ይችላሉ። ጸሐፊው «ወተት»ን «በእግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለው የሕፃንነት ትምህርት» ሲል ይገልጸዋል (5፡12)። ከቃሉ «አጥንት» ተብሎ ሊገለጽ የሚችለው ክፍል፥ ጌታችን አሁን ስላለበት ሰማያዊ የሊቀ ካህናትነት አገልግሎት የሚያስረዳው ነው። ጸሐፊው ይህንን ሥጋ ሊሰጣቸው ቢፈልግም፥ እነርሱ ግን ለመቀበል የተዘጋጁ አልነበሩም።

የቃሉ ወተት ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ያደረጋቸውን ነገሮች ያመለክታል። እነዚህም መወለዱ፥ በምድር ላይ ያሳለፈው ሕይወት፥ ትምህርቱ፥ ሞቱ፥ መቀበሩና መነሣቱ ናቸው። የቃሉ አጥንት አሁን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ የሚያካሂደውን ተግባር ያመለክታል። የክርስትና ሕይወትን በምድር ላይ በተጠናቀቀ ሥራው

ላይ እንጀመርና በሰማይ ባልተጠናቀቀ ሥራው መሠረት ማደጋችንን እንቀጥላለን።

እንደ እውነቱ ከሆነ፥ እጅግ ያደገ ክርስቲያንም ቢሆን ወተት አያስፈልገውም ሊባል የሚችልበት ደረጃ ሊደርስ ከቶውንም አይችልም። አማኞች እንደ መሆናችን መጠን አሁንም ጌታችን በምድር ላይ ካከናወናቸው ተግባራት ብዙ ነገሮችን ልንማር እንችላለን። ነገር ግን እዚያው ማቆም የለብንም! በመንፈሳዊ ሕይወታችን ማደግ ይጠበቅብናል። የምናድገውም ክርስቶስ ለእኛ በሰማይ ስለሚያደርገው የክህነት አገልግሎት ስናውቅ ነው። (ጌታ አሁን ለሕዝቡ ምን ለማድረግ እንደሚፈልግ በዕብራውያን 13፡20–21 ጠቅለል ብሎ የቀረበውን አሳብ ተመልከት።)

መ. <u>በቃሉ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል አለማወቅ</u> (5፡14)። በቃሉ በምናድግበት ጊዜ፥ በዕለታዊ ሕይወታችን እንዴት እንደምንጠቀምበት እናውቃለን። ቃሉን ከሥራ ላይ በምናውልበት ጊዜ «በመንፈሳዊ ሕዋሳቶቻችን» በመጠቀም፥ መንፈሳዊ መመራመርን እናሳድጋለን። ለመመርመር አለመቻል የትናንሽ ልጆች ባሕርይ ነው። ሕፃን ልጅ ያገኘውን ሁሉ ወደ አፉ ይከታል። ያልበሰለ አማኝ ከሬድዮ፥ ከቴሌቪዥንና ከጋዜጣ ያገኘውን ስብከት ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አስተያይቶ ሳይገመገም እንዲሁ ይቀበላል።

ሥጋዊ አካላችን የስሜት ሕዋሳት እንዳሉት ሁሉ፥ ውስጣዊ መንፈሳዊ ክፍላችንም «መንፈሳዊ የስሜት ሕዋሳቶች» አሉት። ለምሳሌ፥ «እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ፤ እዩም» [መዝ. (34)፡8]። «የእናንተ ግን ዓይኖቻችሁ ስለሚያዩ፥ ጆሮቻችሁም ስለሚሰሙ ብፁዓን ናቸው» (ማቴ. 13፡16)። የእግዚአብሔርን ቃል ስንመገብና በዕለታዊ ሕይወታችን ላይ ስንጠቀም፥ ውስጣዊ «መንፈሳዊ የስሜት ሕዋሳቶቻችን» እየተለማመዱና እየተጠናከሩ በመሄድ ንቃትን ያዳብራሉ። ጳውሎስ ይህንን ሂደት እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ ይለዋል (1ኛ ጢሞ. 4፡7–8)።

መልካሙን ከክፉ መርምሮ መለየት የክርስቲያናዊ ብስለት ወሳኝ ክፍል ነው። በሙሴ ዘመን እስራኤላውያን ይህንን የመመርመር ብቃት በማጣታቸው ተስፋ የተሰጣቸውን ምድር ለመውረስ አልቻሉም። የዚህ መልእክት ተቀባዮችም በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ነበሩ። በክርስትና እምነት ባሉበት መርገጥ አይቻልም። አንድም ወደ ፊት በመግፋት የእግዚአብሔርን በረከት እንቀበላለን፤ አሊያም ወደ ኋላ ተመልሰን በዓላማ–ቢስነት እንቅበዘበዛለን።

አንድ ጊዜ አንድ ሰባኪ፥ «ብዙ ክርስቲያኖች በመሀል ሰፋሪነት ቤት ውስጥ ይዋኙ ቃሉ» ሲል ሰማሁት። «ይህን ስትል ምን ማለትህ ነው?» ብዬ ጠየቅሁት።

«በግብጽና በከነዓን መካከል ይዋኙ ቃሉ። ከአደገኛ ስፍራ ቢወጡም፥ ወደ ዕረፍትና የርስት ባለጸግነት አይደርሱም። በስቅለተ ዓርብና በእሑድ ፋሲካ መካከል ይውተረተራሉ። በክርስቶስ ደም ቢድኑም፥ በትንሣኤው ሕይወት አዲስነት ደስ አይሰኙም» ሲል አብራራልኝ።

## 2. ለመንፈሳዊ ብስለት ጥሪ (6፡1–12)

ማንም ሰው ወደዚህች ዓለም ሊመጣ የሚችልበት ብቸኛ መንገድ እንደ ሕፃን ልጅ ተወልዶ ነው! ከዚህ የተለየ አማራጭ የለም። ነገር ግን አንድ ሕፃን አላድግ ብሎ እዚያው ቢቀር የሚያሳዝን ነገር ነው። ወላጆች ምንም ያህል ሕፃኑን ልጃቸውን ለመንከባከብ ቢወዱም፥ አድጎ እንደ በሳል ሰው ሙሉ በሙሉ በሕይወት እንዲደሰት መፈለጋቸው እውነት ነው። እግዚአብሔርም ለልጆቹ ተመሳሳይ ፍላጎት አለው። ለዚህም ነው ጸሐፊው «ወደ ብስለት እንሂድ» የሚለን (6፡1፣ ከአ.መ.ት.)።

ሀ. <u>ይህ ለመንፈሳዊ ዕድገት የቀረበ ጥሪ ነው</u> (6፡1–3)። እንድናድግ ከተፈለገ የልጅነት ነገሮችን ወደ ኋላ ትተን፥ በመንፈሳዊ ነገሮች ወደ ፊት መሄድ አለብን። የቁጥር 1 ቀጥተኛ ትርጉም፥ «የክርስቶስን ትምህርት የመጀመሪያ ነገሮች (ሀ ሁ) ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አቁመን. . .» የሚል መልእክት ያስተላልፋል። በመዋለ ሕፃናት በነበርሁ ጊዜ አስተማሪያችን ፊደል አስቆጥራናለች። ልጆች ፊደልን የሚማሩት ቃላትን፥ ዓረፍተ ነገሮችን፥ መጻሕፍትንና በጽሑፍ የሰፈረውን ሁሉ ለማንበብ እንዲችሉ ከፍ ወዳሉ ደረጃዎች እንዲሸጋገሩና የላቁ ትምህርቶችን እንዲማሩ ነው። ስለሆነም ሁልጊዜ ሀሁ ሲማሩ አይኖሩም። እነዚህን መሠረታዊ ነገሮች የሚማሩት ወደ ሌሎች የተሻሉ ነገሮች ለመሸጋገር ነው።

«እንሂድ» የሚለው ቃል «በእርሱ ብርታት ወደ ፊት እንገስግስ» የሚል አሳብ አለው። ራሳችንን ለእርሱ አሳልፈን ስንሰጥ፥ ቃሉን ስንቀበልና በቃሉ ላይ ተደግፈን እርምጃዎችን ስንወስድ ወደ ፊት እንድንሄድ የሚያስችለን እግዚአብሔር ነው። ሕፃን ልጅ የሚያድገው፥ ሲመገብ፥ ሲተኛ፥ ሲጫወትና ሰውነቱን ሲያንቀሳቅስ ነው። ተፈጥሮ ራሱ እግዚአብሔር በወሰነለት ሥርዓት መሠረት ቀን በቀን እያሳደገው በመጨረሻም ልጁ ወደ ብስለት እንዲደርስ ያደርጋል። ለክርስቲያኖች ማደግ ተፈጥሯዊ ሲሆን፥ አለማደግ ግን እንግዳ ነገር ነው።

ጸሐፊው ስድስት የክርስትና ሕይወት መሠረታዊ እውነቶችን ዘርዝሯል። እነዚህ ለአይሁድ እምነትም መሠረታዊ እውነቶች ናቸው። የክርስትና እምነታችን በአይሁድ እምነት ላይ የተመሠረተና ከዚያ ባሻገርም ለአይሁድ እምነት ተፈጻሚነትን የሚሰጥ ነው። መዳን ከአይሁድ ነውና (ዮሐ. 4:22)። የዚህ መልእክት ተቀባዮች ከስደት ለመሸሽ ብለው ወደ ይሁዲነት ቢሄዱ፥ የኋልዮሽ ተመልሰው ፍጹሙን ፍጹም ባልሆነው፥ በሳሉን በሳል ባልሆነው መለወጣቸው ነበር።

የመጀመሪያዎቹ ሁለት ነገሮች (ንስሐና እምነት) ወደ እግዚአብሔር የመመለስ ሁኔታዎች ሲሆኑ፥ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት የመግቢያ የጅማሬ መንገዶች ናቸው። ንስሐ መግባት ማለት አስተሳሰብን መቀየር ማለት ነው። ይህ ኃጢአትን መጥላት ብቻ ወይም የኋላውን እያሰቡ መጸጸትና መቆጨት አይደለም። ነገር ግን ስለ ኃጢአት የነበረንን የቀድሞ አስተሳሰብ መቀየርና ከእርሱም ፊታችንን መመለስ ማለት ነው። አንድ ኃጢአተኛ ንስሐ ከገባ በኋላ (ይህም ራሱ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው የሐዋ. 5:31 እና 11:18)፥ በእግዚአብሔር ሊያምን ይችላል። ንስሐ መግባትና ማመን ጎን ለጎን የሚሄዱ ነገሮች ናቸው (የሐዋ. 20:21)።

ቀጣዮቹ ሁለት ነገሮች (ጥምቀትና እጅ መጫን) አንድ ሰው ከአጥቢያ ማኅበረ ምእመናን ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያመለክቱ ናቸው። በአዲስ ኪዳን አንድ ሰው ንስሐ ገብቶ በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ፥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ይሆናል (የሐዋ. 2:41–47)። በዕብራውያን 6:2 «ጥምቀቶች» ተብሎ በብዙ ቁጥሮች የተገለጸው አሳብ «እጥበቶች» ሊባል ይችላል (9:10)። ውኃ በራሱ ኃጢአትን ሊያነጻ ባይችልም (1ኛ ጴጥ. 3:21)፥ ጥምቀት የመንፈሳዊ እጥበት ተምሳሌት ነው። («ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ፤ ከኃጢአትህም ታጠብ» (የሐዋ. 22:16)። እንዲሁም ደግሞ ጥምቀት ከክርስቶስ ሞት፥ መቀበርና ትንሣኤ ጋር መተባበራችንን የሚያሳይ ምሳሌ ነው (ሮሜ 6:1–4)። እጅ መጫን (ዕብ. 6:2) አንዳንድ በረከቶችን መካፈልን (ሉቃስ 24:50፤ የሐዋ. 19:6) ወይም የአንድን ሰው ለአገልግሎት መለየት ያመለክታል (1ኛ ጢሞ. 4:14)።

የመጨረሻዎቹ ሁለቱ የሙታን ትንሣኤ (የሐዋ. 24:14–15) እና የመጨረሻው ፍርድ (የሐዋ. 17:30–31) የወደፊትን ዘመን የሚያመለክቱ ናቸው። አይሁዶችም ሆኑ ክርስቲያኖች በእነዚህ አስተምህሮዎች ያምናሉ። ብሉይ ኪዳን ስለ አጠቃላይ ትንሣኤ ቢያስተምርም፥ ትምህርቱ ግልጽ ሆኖ አልተቀመጠም። አዲስ ኪዳን

የዳኑትም ሆኑ ያልዳኑት በመጨረሻው ዘመን ከሙታን የሚነሡ መሆናቸውን ያስተምራል (ዮሐ. 5፡24-29፤ ራእይ 20፡4-6፥ 12-15)።

የዕብራውያን 6፡1-3 መልእክት ግልጽ ነው። ይህም፥ «መሠረት ጥላችኋል። ሀሁን ታውቃላችሁ። አሁን ወደ ፊት ተራመዱ! እግዚአብሔር ወደ ብስለት እንዲያደርሳችሁ ራሳችሁን ለእርሱ ተዉለት!» የሚል ነው።

ለ. <u>ይህ ዕድገት ከደኅንነት ጋር የሚገናኝ አይደለም</u> (6፡4-6)። እነዚህ ቁጥሮች በ10፡6-39 ከቀረበው ማስጠንቀቂያ ጋር ብዙ ክርስቲያኖችን ሲያሳስቡና ሲያስጨንቁ ይታያል። ለዚህም ምክንያቱ ሰዎች እነዚህን ጥቅሶች በተሳሳተ መንገድ መተርጎማቸውና ከአገልግሎት ላይ ማዋላቸው ነው። እነዚህን ጥቅሶች ካነበቡ በኋላ የማይሰረይ ኃጢአት እንደሠሩ በማመን (ወይም ሰይጣን ስላሳመናቸው) ተረብሸው ከሩቅ አገር ስልክ የደወሉልኝ ሰዎች አጋጥመውኛል። ዳግም ላልተወለደ ክርስቲያን የውሸት ዋስትና ለመስጠት እንደማልፈልግ ሁሉ፥ እውነተኛ አማኞችም ተሰናክለው እግዚአብሔር ካዘጋጀላቸው መልካም በረከት እንዲጎድሉ አልሻም።

የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች የዚህን ከባድ ምንባብ ትርጉም በውል ለመረዳት የተለያዩ መላምቶችን አቅርበዋል። ከእነዚህም መካከል አንደኛው አመለካከት፥ ጸሐፊው በፈቃዳችን ጀርባችንን ለክርስቶስ ሰጥተን ወደ አሮጌው ሕይወታችን በመመለስ የክህደት ኃጢአት እንዳንፈጽም እያስጠነቀቀን ነው የሚል ነው። ይህ አመለካከት እንደሚለው፥ እንዲህ ዓይነት እርምጃ የወሰደ ሰው ለዘላለም ይጠፋል። እኔ ግን ከዚህ አመለካከት ጋር የማልስማማባቸው አያሌ ምክንያቶች አሉኝ። በመጀመሪያ ደረጃ፥ «አፖስቴሲያ» የሚለው የፅርዕ (የግሪክ) ቃል በዚህ ምንባብ ውስጥ አላገለገለም። በ6፡6 «የካዱ» የሚለው «ፓራፒፕቶ» ከሚለው የፅርዕ (የግሪክ) ቃል የተተረጎመ ሲሆን፥ ቀጥተኛ ፍችውም «መውደቅ» ማለት ነው። ሁለተኛ፥ ሁልጊዜም ግልጽ ያልሆነውን የምንተረጉመው ግልጽ በሆነው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እውነተኛ አማኝ ሊጠፋ እንደማይችል የሚያስረዱ በርካታ ምንባቦች አሉ። እንዲያውም፥ ለዘላለማዊ ደኅንነት ዋቢ ከሚቆሙ ጠንካራ ሙግቶች መካከል አንዱ የዚህ ምዕራፍ የመጨረሻው ክፍል ነው! (6፡13-20)። በተጨማሪም ዮሐንስ 5፡24፤ 10፡26-30፤ ሮሜ 8፡28-39 ተመልከት።

ደኅንነታችንን ልናጣ እንችላለን ብለው የሚያስተምሩ ሰዎች በዚህ መልኩ የወደቀ ሰው እንደገና ወደ ደኅንነት ሊመጣ ይችላል ብለው ያስተምራሉ። ነገር ግን ይህ ምንባብ (ዕብ. 6፡4-6) የሚያስተምረው

የዚህን ተገላቢጦሽ ነው! «እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው።» በሌላ አገላለጽ፥ ይህ ክርስቶስን ስለ መካድ የሚናገር ከሆነ፥ የካደ ሰው እንደገና ወደ ደኅንነት ሊመጣ አይችልም ማለት ነው። ስለሆነም፥ ክህደትን የፈጸመ ሰው ለዘላለም ይጠፋል ማለት ነው።

ሌሎች ደግሞ እነዚህ ሰዎች እውነተኛ አማኞች አልነበሩም ይላሉ። ምንም እንኳ እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተባበሩ ቢሆንም፥ ዳግም አልተወለዱም ነበር ብለው ያስባሉ። ለማንኛውም እነዚህ ሰዎች የተገለጹበትን ሁኔታ በመመልከት ዳግም መወለድ አለመወለዳቸውን ልንረዳ እንችላለን።

ብርሃን በርቶላቸው ነበር (6:4)። «አንድ ጊዜ» የሚለው «ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ» ማለት ነው። ይህ ግሥ በዕብራውያን 10:32 ያገለገለበት ሁኔታ እውነተኛ ደኅንነት ማግኘትን ያመለክታል (2ኛ ቆሮንቶስ 4:4-6)።

«ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን» (ዕብ. 6:4) እና «መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን» (6:5)። እነዚህ ሰዎች «ቀምሰዋል እንጂ በልተው አላጣጣሙም» ማለት አተረጓጎምን በአንድ ቃል ላይ መመሥረት ነው። እግዚአብሔር ልጁ ሞትን ለሰዎች ሁሉ እንዲቀምስ ፈቅዷል (2:9)። ይህ ማለት ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሞትን ፍሙና አይቷል ማለት አይደለም! «መቅመስ» በተጠቀሰው ሂደት ውስጥ ማለፍን ያመለክታል። ስለሆነም፥ እነዚህ የዕብራውያን ክርስቲያኖች የደኅንነትን ስጦታ፥ የእግዚአብሔርን ቃልና የእግዚአብሔርን ኃይል በሕይወታቸው ውስጥ ተለማምደዋል። ይህ እውነተኛ ደኅንነት ማግኘታቸውን አያመለክትም?

«ከመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን» (4:5)። እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ነበሩ ማለቱ የግሡን ቀላል ፍች ለመቀበል አለመፈለግ ይሆናል። ይህም ማለት በትክክል እንደተገለጸው፥ «ተካፋዮች» ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን፥ የሰማያዊ ጥሪ (3:1) እና የክርስቶስ ተካፋዮች (3:14) ናቸው።

እነዚህን ነገሮች ሳገናዝብ፥ የተጠቀሱት ሰዎች አማኞች ነን የሚሉ ብቻ ሳይሆኑ፥ እውነተኛ አማኞች መሆናቸው በግልጽ ይታየኛል። ከዚህም በላይ፥ ደኅንነትን ያላገኘ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያስድበው እንዴት ነው?

ሦስተኛው አመለካከት፥ ይህ (ያልተጠቀሰው ኃጢአት) ገና ቤተ መቅደሱ ሳይፈርስ የነበሩት የዕብራውያን ክርስቲያኖች ብቻ ሊፈጽሙት የሚችሉት እንደሆነ ያስረዳል። እንደዚያ ከሆነ፥ ጸሐፊው ይህንን ጉዳይ ከጌታችን ሰማያዊ ክህነትና ከመንፈሳዊ ብስለት አስፈላጊነት ጋር ያዛመደው ለምንድን ነው? እርሱ የጻፈው ጉዳይ ከዛሬው ዘመን ጋር የማይዛመድ ከሆነ፥ የምክሩ ዓላማ ምንድን ነው? እነዚህን ቁጥሮች ለመጀመሪያው ምእተ ዓመት የአይሁድ ክርስቲያኖች የተወሰኑ ናቸው ካልን፥ ማስጠንቀቂያው ፋይዳ ቢስ የሚሆን ይመስለኛል።

እንደዚያ ከሆነ፥ ጸሐፊው ለእኛ ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ምንድን ነው? ምናልባትም እውነተኛ አማኝ ሊጠፋ አይችልም የሚለውን አመለካከት ለማረጋገጥ አንድ የፈጠራ (ልብ ወለዳዊ) ሁኔታ እየተጠቀመ ይሆናል። ቁጥር 9 ይህንን አተረጓጎም የሚደግፍ ይመስላል። «ስለ እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ምንም እንኳ እንዲሁ ብንናገር፥ አብልጦ የሚሻለውና ለመዳን የሚሆነው እንዲሆንላችሁ ተረድተናል።» የጸሐፊው ሙግት የሚከተለውን አቅጣጫ ይይዛል።

«እንበልና ወደ ብስለት ሳታድጉ ትቀራላችሁ። ይህ ማለት ግን ደኅንነታችሁን ታጣላችሁ ማለት ነው? አታጡም! ደኅንነታችሁን ካጣችሁ እንደገና መልሳችሁ ልታገኙት አትችሉም። ይህ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን ማሰደብ ይሆናል። እንደገና ለእናንተ መሰቀል አለበት ማለት ነው። ይህ ደግሞ አይቻልም።»

በቁጥር 4፥ ጸሐፊው ተውላጠ ስሞችን ከ«እኛ» ወደ «እነርሱ» ለውጧል። ይህ ለውጥ ደግሞ በአእምሮው የነበረው መላምታዊ ሁኔታ እንደሆነ ያመለክታል።

ይሁንና፥ መላምታዊ ሁኔታን የግድ አስፈላጊ የሚያደርግ ሌላም አማራጭ አተረጓጎም አለ። በቁጥር 6 ስለ «መስቀል» እና «ማዋረድ» የሚናገሩ ግሦች የአሁን ጊዜ ቀጣይ ድርጊቶችን የሚያመለክቱ ናቸው። «እየሰቀሉትና. . . እያዋረዱት. . .» ጸሐፊው እነዚያ ሰዎች በፍጹም ወደ ንስሐ ሊመጡ አይችሉም አላለም። ጸሐፊው በክርስቶስ ላይ እንዲህ ያለ አሳፋሪ ተግባር እየፈጸሙ ሳሉ ወደ ንስሐ ሊመጡ አይችሉም ነው የሚለው። በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንዲህ ዓይነት እርምጃ መውሰዳቸውን ካቆሙ ንስሐ ገብተው ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ኅብረት ሊያድሱ ይችላሉ።

የትኛውንም አመለካከት ብንከተል፥ የጸሐፊው ዓላማ አንባቢዎችን ማስፈራራት ሳይሆን ማረጋገጫ መስጠት እንደሆነ እንገንዘብ። ሊያስፈራራቸው ቢፈልግ ኖሮ ክርስቶስን እንዲያዋርዱት ያደረጋቸውን

ኃጢአት ይጠቅስ ነበር። ጸሐፊው ግን እንደዚህ አላደረገም። «ክህደት» የሚል ፍች ያለውን የዕርዕ (የግሪክ) ቃል መጠቀም ሲችል፥ «መውደቅ» የሚለውን መርጧል። (ገላ. 6፡1 ላይም ተመሳሳይ ቃል ይገኛል።)

ክርስቲያኖች «ለሞት የሚያደርስ ኃጢአት» ሊፈጽሙ ይችላሉ (1ኛ ዮሐ. 5፡16-17፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡30-32)። ይህ የዕብራውያን ጸሐፊ በምዕራፍ 12 ውስጥ የሚያነሣው የእግዚአብሔር ቅጣት ነው።

ሐ. <u>ይህ ዕድገት ፍሬያማነትን ያስከትላል</u> (6፡7-10)። ይህ ስለ እርሻ መሬት የሚናገረው ምሳሌ ጌታችን ስለ ዘሪው ምሳሌ (ማቴ. 13፡1-9 እና 18-23)፥ ጳውሎስ ደግሞ ሥራችን በእሳት ስለሚፈተንበት ሁኔታ ከሚናገረው አሳብ ጋር ይመሳሰላል (1ኛ ቆሮ. 3፡6-23)። የእርሻ መሬት ጠቃሚነቱን የሚያሳየው ፍሬ በመስጠት ነው። እውነተኛ ክርስቲያንም መንፈሳዊ ዕድገት በማሳየት ለእግዚአብሔር ክብር ፍሬ ያፈራል። የሚቃጠለው «እሾህና አሜኬላው» እንጂ እርሻው እንዳልሆነ እንገንዘብ። እግዚአብሔር «የራሱ የሆነን ነገር አይረግምም»

በዕብራውያን 6፡7 የእግዚአብሔርን በረከት የምታመለክተው እርሻ በቁጥር 9 ከደኅንነት ጋር ተያይዘው የሚሰጡንን ነገሮች እንደምታሳይ ተገልጾአል። ሁሉም አማኝ እኩል ፍሬ ሊሰጥ አይችልም። አንዳንዶች 100፥ ሌሎች 60 እና 30 እጥፍ ይሰጣሉ (ማቴ. 13፡23)። ነገር ግን ሁሉም አማኝ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያረጋግጠውን አንድ ዓይነት ፍሬ ያፈራል (ማቴ. 7፡15-20)። ይህም በክርስቶስ እየበሰልን ስንሄድ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ የሚሠራው የክርስቲያናዊ ባሕርይና አካሄድ ፍሬ ነው (ገላ. 5፡22-26)።

ጸሐፊው በሕይወታቸው እንደሚገኙ የሚያውቃቸውን አንዳንድ ፍሬዎች ዘርዝሯል (ዕብ. 6፡10)። እነዚህ ሰዎች ከፍቅራቸው የተነሣ ለጌታና ለሌሎች ቅዱሳን አገልግለው ነበር። አሁንም ይህንኑ አገልግሎት አላቋረጡም ነበር (1ኛ ተሰ. 1፡3-10፤ ራእይ 2፡2 አንብብ።) እነዚህ ደኅንነትን ከሚያጅቡ ነገሮች አንዳንዶቹ ናቸው።

ነገር ግን ጸሐፊው አንባቢዎቹ በአገልግሎታቸው ላይ በማተኮር እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን የተሟላ ርስት ወደሚያገኙበት የበሳልነት ደረጃ ሳይደርሱ እንዳይቀሩ ይሰጋል።

መ. <u>ይህ ዕድገት ትጋትን ይጠይቃል</u> (ዕብ. 6፡11-12)። ምንም እንኳ ወደ ብስለት የሚወስደን ራሱ እግዚአብሔር ቢሆንም (ዕብ. 6፡1፥ 3)፥ አማኙ የራሱን ድርሻ መወጣት እንዳለበት ግልጽ ነው። እግዚአብሔር

የሰጠንን መንፈሳዊ ሀብት መጠቀም እንጂ ሰነፎችና ዳተኞች መሆን የለብንም። (በግሪኩ ቋንቋ፥ ዳተኛ በ5፡11 ከቀረበው ፈዛዛነት ጋር አንድ ነው።) እግዚአብሔር የተስፋ ቃሎችን ገብቶልናል። ስለሆነም፥ በእምነትና በትዕግሥት እነዚህን የተስፋ ቃሎች መቀበል አለብን! እንደ ካሌብና ኢያሱ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ልናምንና ርስታችንን ልንወርስ ይገባል! የእርሻ መሬቱ ምሳሌ (ዕብ. 6፡–8) እና እንድንተጋ የሚያሳስበው ምክር ሁልጊዜም የሰሎሞንን ማስጠንቀቂያ ያስታውሰኛል (ምሳሌ 24፡30–34)።

## 3. የመንፈሳዊ ዋስትና መሠረት (ዕብ. 6፡13–20)

አንባቢዎቹ ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ ያቀረበውን ማሳሰቢያ በሌላ መልኩ እንዳይረዱት በማሰብ፥ ጸሐፊው ይህንን ክፍል በግሩም የደኅንነት ዋስትና ደምድሞታል። ሁላችንም የሚገባንን ያህል መንፈሳዊ ዕድገት እያሳየን ባንሆንም፥ እግዚአብሔር ይኮንነናል ብለን መፍራት የለብንም። ጸሐፊው የአማኙ ደኅንነት የተረጋገጠ መሆኑን ለማሳየት ሦ ስት ነጥቦችን አቅርቧል፡

ሀ. <u>የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል</u> (6፡13–15)። እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ዋንኛ የተስፋ ቃል በዘፍጥረት 22፡16–17 ተመዝግቧል። ከአብርሃም ውድቀቶችና ኃጢአቶች በተቃራኒ፥ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ስለ ጠበቀ ይስሐቅ ሊወለድ ችሏል። ብዙዎቹ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች የሚደገፉት በእኛ ባሕሪ ጥንካሬ ላይ ሳይሆን በእርሱ ታማኝነት ላይ ነው። መታገሥ (ዕብ. 6፡15) የዳተኝነት (6፡12) ተቃራኒ ነው። የጸሐፊው መልእክት፥ «በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ ተግታችሁ ብታድጉ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል አግኝታችሁ ትደሰታላችሁ» የሚል ነው።

ዛሬ ያለን ክርስቲያኖች ከአብርሃም ይልቅ ብዙ የተስፋ ቃሎች አሉን! እንግዲያው ወደ መንፈሳዊ ሕይወት እንዳናድግ የሚይዘን ምንድን ነው? በእምነት አለመሰማራታችን ነው። ወደ እርሻው ምሳሌ ብንመለስ፥ ገበሬው መከሩን የሚሰበስበው ዘሩን ቁጭ ብሎ በመመልከት አይደለም። ማረስ፥ መዝራት፥ አረም መንቀል፥ መኮትኮትና ምናልባትም መሬቱን ውኃ ማጠጣት ሊኖርበት ይችላል። የቤተ ክርስቲያንን ኅብረት፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ጸሎት ቸል የሚል አማኝ ብዙ መንፈሳዊ መከር ሊሰበስብ አይችልም።

ለ. <u>የእግዚአብሔር መሀላ</u> (6፡16–18)። እግዚአብሔር ለአብርሃም የተስፋ ቃል በመስጠት ሳይወሰን፥ የተስፋ ቃሉ እንደሚፈጸም በመሀላ ጭምር አረጋግጦለታል። አንድ ምስክር በፍርድ ቤት መሀላ በሚፈጽምበት ጊዜ በእግዚአብሔር ስም እንዲምል ይደረጋል። ለትንሹ

ለመመስከር የታላቁን ስም እንጠራለን። ነገር ግን ከእግዚአብሔር የሚበልጥ ስለ ሌለ በራሱ ስም ማለ!

እግዚአብሔር ይህንን ያደረገው ለአብርሃም ብቻ አይደለም። የተስፋ ቃሉ ወራሾች ለሆኑትም ሁሉ የተስፋ ቃሉንና መሀላውን ሰጥቷል (ቁ. 17)። አብርሃምና ዘሮቹ የዚህ ውርስ ቀዳሚ ወራሾች ናቸው (11፥19 አንብብ)። ነገር ግን አማኞች ሁሉ የአብርሃም መንፈሳዊ ዘር መሆናቸው ተገልጾአል (ገላ. 3፥29)። ስለሆነም የደኅንነት ዋስትናችን በእግዚአብሔር የተስፋ ቃልና በእግዚአብሔር መሀላ ተረጋግጧል ማለት ነው። ይህም በሁለት በማይለወጡ ነገሮች ተመልክቷል (6፥18)። በፊታችን ስላለው ተስፋ ታላቅ ማበረታቻ አለን! የዕብራውያን መልእክት አበረታች እንጂ ተስፋ አስቆራጭ መጽሐፍ አይደለም!

መጠለያን ለማግኘት ስለመሸሽ የሚናገረው አሳብ (6፥18) በዘኍልቁ 35፥9 እና በኢያሱ 20 የተጠቀሱትን የብሉይ ኪዳን «የመማፀኛ ከተሞች» የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር በድንገት ሰው የገደለ ሰው መጠለያ ሊያገኝ የሚችልባቸውን ስድስት ከተሞች አዘጋጅቶ ነበር። ሰውዬው ከዮርዳኖስ ወንዝ ወዲያና ወዲህ ከተከለሉት ሦስት ሦስት ከተሞች በአንደኛው ውስጥ ተጠልሎ ሳለ ሽማግሌዎች ጉዳዩን ይመረምራሉ። ሽማግሌዎቹ ግድያው የታሰበበት ሳይሆን በድንገት የተከሰተ መሆኑን ከገለጹ፥ በደለኛው በዘመኑ የነበረው ሊቀ ካህናት እስኪሞት ድረስ በመማፀኛ ከተማ ውስጥ በሰላም እንዲኖር ይፈቅዱለታል። ሊቀ ካህናቱ ከሞተ በኋላ ወደ ቤቱ ሊመለስ ይችላል። ሰውዬው በመማፀኛ ከተማ ውስጥ እስከኖረ ድረስ የሟቹ ዘመዶች ሊበቀሉት አይችሉም ነበር።

እኛም ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሸሽተናል። እርሱ ዘላለማዊ መጠለያችን ነው። እርሱ ከቶውንም ሊሞት የማይችል ሊቀ ካህናት በመሆኑ (ዕብ. 7፥23-25)፥ ዘላለማዊ ደኅንነታችን የተረጋገጠ ነው። አስቀድሞ ሞቶ ስለ ተነሣ፥ ማንም ተበቃይ ሊነካን አይችልም።

ሐ. <u>የእግዚአብሔር ልጅ</u> (6፥19-20)። በክርስቶስ ላይ ያለን ተስፋ እንደ ነፍስ መልሕቅ ነው። መልሕቅ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተወዳጅ ምሳሌ ነበር። በካታኮምቦች ውስጥ ቢያንስ 66 የመልሕቅ ሥዕሎች ተገኝተዋል። የግሪክ ስቶይክ ፈላስፋ የነበረው ኤፒክቴተስ፥ «መርከብን በአንድ መልሕቅ ብቻ፥ ነፍስን በአንዲት ተስፋ ማሰር አይገባም» ሲል ጽፎአል። ክርስቲያኖች ግን ተስፋችን በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ መልሕቅ አለን (ቆላስይስ 1፥5፤ 1ኛ ጢሞ. 1፥1)።

ይህም ሆኖ፥ ይህ መንፈሳዊ መልሕቅ ከመርከቦች መልሕቅ የተለየ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ፥ የእኛ መልሕቅ ያለው በምድር ላይ ሳይሆን ሰማይ ላይ ነው። ከመልሕቁ ጋር የታሰርነው ባለንበት እንድንቆም ሳይሆን ወደ ፊት እንድንሄድ ነው። መልሕቃችን ሊበላሽ የማይችል ጽኑና የተረጋገጠ ነው። የትኛውም ምድራዊ መልሕቅ ያንን ዓይነት ዋስትና ሊሰጠን አይችልም!

ከዚያም ጸሐፊው አሳቡን በመቋጨት፥ ይህ አዳኝ አንድ ቀን እንከተል ዘንድ ቀዳሚያችን ሆኖ ወደ ሰማይ እንደገባ ያስረዳል (ዕብ. 6፡20)። የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት ቀዳሚ አልነበረም። ምክንያቱም ማንም እርሱን ተከትሎ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሊገባ አይችልም ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አንድ ቀን እንከተለው ዘንድ ወደ ሰማይ ሄዷል።

ዶክተር ኤች. ኤ. አይረንሳይድ «በመጋረጃ ውስጥ» (6፡19) እና «ከሠፈር ውጭ» (13፡13) የሚሉ ሁለት ሐረጎች የዕብራውያንን መልእክት አሳብ ጠቅለል አድርገው እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናችን እንደ መሆኑ በመጋረጃ ውስጥ ነው። ስለሆነም፥ ወደ ዙፋኑ በመቅረብ የሚያስፈልገንን እርዳታ ልናገኝ እንችላለን። ይሁንና፥ «የምሥጢር ቅዱሳን» መሆን የለብንም። ራሳችን የክርስቶስ መገለልን በመጋራት ነቀፌታውን ተሸክመን ከሠፈር ውጭ ልንወጣ ይገባል (13፡13)። ይህ መልእክት የተጻፈላቸው የዕብራውያን ክርስቲያኖች ነቀፌታውን ላለመሸከምና ከራሳቸው ለማራቅ ተፈትነው ነበር። ነገር ግን በመጋረጃው ውስጥ ካለን ከሠፈር ውጭ ለመውጣት አንቸገርም።

በዚህ ክፍል ለቀረበው ምክር የትኛውንም አመለካከት እንውሰድ። ዋናውን መልእክት እንዳንስት ያስፈልጋል። ዋናው መልእክት አማኞች እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላቸው የብስለት ጎዳና እንዲያመሩ የሚጋብዝ ነው። ከቃሉ ብንንሸራተት (2፡1-4)፥ ቃሉን መጠራጠር እንጀምራለን (3፡7-4፡13)። ብዙም ሳይቆይ ቃሉን መስማት ይሰለቸናል (5፡11-6፡20)። ይህም ስልቹና ዳተኛ አማኞች ያደርገናል። ላለመንሸራተት ከሁሉም የሚሻለው መንገድ መልሕቁን አጥብቆ መያዝ ነው!

መልሕቁን ይዘን ወደ ሰማይ እናዝግም! ከዚህ የበለጠ ምን አስተማማኝ ነገር ይኖራል?

## 6

# ምሥጢራዊው መልከ ጼዴቅ

### ምዕራፍ 7

አንድ የቤተ መጻሕፍት ሠራተኛ፥ የሸርሎክ ሆልስ መደብሮች ታሪኮችን ካስተዋወቀኝ ጊዜ ጀምሮ ልብን የሚሰቅሉ ወንጀል ነክ ልቦለዶችን ሳነብ ቆይቻለሁ። አንዳንድ ጊዜ መጽሐፉን አንብቤ ከመጨረሴ በፊት፥ የጭብጡን ምሥጢር አስቀድሜ ለመገመት እሞክራለሁ። አንዳንዴም እንዳሰብሁት ሆኖ አገኘዋለሁ። ከዚህ የልቦለድ ድርሰት ንባብ የተማርሁት ነገር ቢኖር፥ የትኛውንም ገጸ ባሕሪ መናቅ እንደሌለብኝ ነው። ከጉዳዩ ጋር የማይገናኙ የሚመስሉ ገጸ ባሕርያት ሳይቀሩ ወንጀለኞች ሆነው ሊገኙ ይችላሉ።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን ዐበይት ሰዎች ስም ዝርዝር ብንጠየቅ መልከ ጼዴቅን የምንጨምር አይመስለኝም። መልከ ጼዴቅ ለአንድ ጊዜ ብቻ በዘፍጥረት 14፡17–24 የተጠቀሰ ሲሆን፥ በመዝሙር 110፡4 እንደገና ተጠቅሶአል። ምንም እንኳ ይህ ከፍተኛ እውቅና ሊያስገኝ የሚችል ባይመስልም፥ መንፈስ ቅዱስ ከብሉይ ኪዳን እነዚህን ሁለት ምንባቦች በመጠቀም ታላቅ እውነት ሊያስተላልፍ ችሏል። ይህም እውነት የመልከ ጼዴቅ ክህነት ከሌዊ ክህነት የሚበልጥ ሲሆን፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት ደግሞ ከአሮን ክህነት እንደሚበልጥ የሚያስረዳ ነው።

በአስተዋጽኦው ውስጥ እንደተመለከተው፥ ምዕራፍ 7 የዕብራውያንን መልእክት ሁለተኛ ዐቢይ ክፍል የሚያስተዋውቅ ነው። ይህም ክርስቶስ የበለጠ የክህነት ሥልጣን እንዳለው የሚያስረዳ ክፍል ነው (7–10)። በምዕራፍ 7 ላይ ጸሐፊው የክርስቶስ ክህነት እንደ መልከ ጼዴቅ ክህነት በሥርዓት የሚበልጥ እንደሆነ ገልጾአል። በምዕራፍ 8 ትኩረት የተሰጠው በክርስቶስ ልዩ ቃል ኪዳን ላይ ሲሆን፥ በምዕራፍ 9 ላይ በሚሻል ቤተ መቅደሱ፥ በምዕራፍ 10 ደግሞ በሚሻል መሥዋዕቱ ላይ አጽንኦት ተሰጥቷል።

የሌዊ ነገድ ለክህነት አገልግሎት የተለየ መሆኑ ለአይሁድ ሕዝብ የታወቀ ነበር። ይህ ነገድ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ እንዲያገለግል እግዚአብሔር የመረጠው ሲሆን (ዘጸ. 29፤ ዘኁል. 18)፥ አሮን የመጀመሪያው በእግዚአብሔር የተሾመ ሊቀ ካህናት ነበር። ካህናቱ ጉድለቶች ቢኖሩዋቸውም እግዚአብሔርን ለብዙ መቶ ዓመታት አገልግለዋል። አሁን ግን ጸሐፊው የክህነት አገልግሎታቸው እንዳበቃ

ገልጾአል! ይህን አሳብ ለማጠናከርና የመልከ ጼዴቅ ክህነት ከአሮን እንደሚበልጥ ለማሳየት፥ ሦስት የመከራከሪያ ነጥቦችን ያቀርባል።

## 1. ታሪካዊ ክርክር፡ መልከ ጼዴቅና አብርሃም (ዕብ. 7፡1–10)

እዚህ ላይ የቀረበው በዘፍጥረት 14፡17–24 የተገለጸው ታሪክ ነው። ከመልከ ጼዴቅ ጥሩ ግንዛቤ ለማግኘት ጊዜ ወስዳችሁ አንብቡት። የዚህ መልእክት ጸሐፊ መልከ ጼዴቅ ስለተባለው ምሥጢራዊ ሰው አያሌ ነጥቦችን እንድንገነዘብ ይፈልጋል።

ሀ. <u>መልከ ጼዴቅ የተወለደው ንጉሥና ካህን ሆኖ ነበር</u> (ዕብ. 7፡1)። በብሉይ ኪዳን ዘመን በዙፋን መቀመጥና መሠዊያ ማገልገል የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን ቀደም ብለን ተመልክተናል። እግዚአብሔር በጉልበት የክህነት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልጉ ሰዎችን ይቀጣ ነበር። መልከ ጼዴቅ ግን ሁለቱንም ሥልጣናት ይዞ ነበር! አሮን ይህ ሥልጣን አልነበረውም። እዚህ ላይ መልከ ጼዴቅ «አስመሳይ ካህን» እንዳልሆነ መገንዘብ አለብን። እርሱ የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር (ዘፍጥ. 14፡18፥ 22 አንብብ)። አገልግሎቱም ሕጋዊ ነበር።

ለ. <u>ዓይነተኛ ስሙም ትርጉም ያለው ነው</u> (ዕብ. 7፡2)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ስሞችና ፍችዎቻቸው አስፈላጊዎች ናቸው። ዛሬ ስለ ትርጉማቸው ሳንጨነቅ ለልጆቻችን ደስ ያሉንን ስሞች እንሸልማለን። በብሉይ ኪዳን ዘመን ግን ሁኔታው እንደዚህ አልነበረም። አንዳንድ ጊዜ ከትልቅ መንፈሳዊ ክስተት ሳቢያ ስሞች ይቀየራሉ (ዘፍጥ. 32፡14–32፤ ዮሐ. 1፡35–42)። «መልከ ጼዴቅ» የሚለው ስም በዕብራውያን ቋንቋ «የጽድቅ ንጉሥ» ማለት ነው። «ሳሌም» (በዕብራይስጥ «ሻሎም») የሚለው ደግሞ ሰላምን ያመለክታል። ይህም መልከ ጼዴቅ የጽድቅም የሰላምም ንጉሥ እንደሆነ ያስረዳል።

ጽድቅና ሰላም ብዙውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አብረው የሚገለጹ አሳቦች ናቸው። «የጽድቅም ሥራ ሰላም፥ የጽድቅም ፍሬ ለዘላለም ጸጥታና መታመን ይሆናል» (ኢሳ. 32፡17)። «ምሕረትና እውነት ተገናኙ፤ ጽድቅና ሰላም ተስማሙ» [መዝ. (85)፡10]። «በዘመኑም ጽድቅ ያብባል፥ ጨረቃም እስኪያልፍ ድረስ ሰላም ብዙ ነው» መዝ. (72)፡7 ። «ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፥ በኋላም ታራቂ. . . የጽድቅም ፍሬ ሰላምን ለሚያደርጉት ሰዎች በሰላም ይዘራል» (ያዕ. 3፡17–18)። በርግጥም እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያስበው «የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን» እንዲያፈሩ ነው (ዕብ. 12፡10–11)።

እውነተኛ ሰላም ሊገኝ የሚችለው በጽድቅ አማካኝነት ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀን በሰላም ለመኖር ከፈለግን መጀመሪያ በክርስቶስ አምነን ጽድቅን ልናገኝ ይገባል (ሮሜ 5፡1)። ሰው የብሉይ ኪዳንን ሕግ በመጠበቅ ሊጸድቅ አይችልም (ገላ. 2፡21)። ጽድቅና ሰላም ሊስማሙ የሚችሉት ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባከናወነው ሥራ ላይ ብቻ ነው።

ሐ. <u>ከአብርሃም አሥራትን ተቀብሏል</u> (ዕብ. 7፡2)። ይህ አስፈላጊ አሳብ ከቁጥር 4–10 ተብራርቷል። አሥራት ማለት ከአሥር አንድ እጅ ማለት ነው። አይሁዶች ከእህሎቻቸውና ከከብቶቻቸው አንድ አሥረኛውን ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ የብሉይ ኪዳን ሕግ አዟቸዋል (ዘሌዋ. 27፡30–32)። እነዚህ የአሥራት ገቢዎች በመገናኛው ድንኳን (ዘኁል. 18፡ከ21 ጀምሮ) እና በኋላም በቤተ መቅደስ ውስጥ ለሚያገለግሉ ሌዋውያን ይሰጡ ነበር (ዘዳግ. 12 ከ5 ጀምሮ)። እህል፥ ፍሬፍሬ ወይም እንስሳት ይዞ ለመሄድ መንገዱ በጣም ከራቀ አሥራቱ በገንዘብ ተለውጦ ይከፈል ነበር (ዘዳግ. 14፡22–27)።

ይሁንና፥ አሥራት መከፈል የተጀመረው በሙሴ ዘመን አይደለም። ሕግ ከመሰጠቱ ከረዥም ጊዜ በፊት አብርሃም አሥራት ይሰጥ ነበር። እንዲያውም የከርሰ ምድር ተመራማሪዎች በጥንት ዘመን በሚኖሩ አገሮች ዘንድ አሥራት መስጠት የተለመደ እንደነበር ተረድተዋል።

መ. <u>የቤተሰብ ታሪኩ የተለየ ነው</u> (ዕብ. 7፡3)። መልከ ጼዴቅ ሰው ስለሆነ አባትና እናት ሊኖሩት የግድ ነው (ቁ.4 ተመልከት)። ነገር ግን በብሉይ ኪዳን ውስጥ የዘር ሐረጉ አልተጠቀሰም። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የብዙዎቹ ታላላቅ ሰዎች የዘር ሐረግ ተገልጾአል። በተለይ ካህናት የዘር ሐረጋቸው የግድ መታወቅ ነበረበት (ዕዝራ 2፡61–63፤ ነህ. 7፡63–65 አንብብ)። እዚህ ላይ ጸሐፊው የዘር ሐረጉን አለመጠቀስ አስመልክቶ የሚያቀርበው ክርክር ልብ ሊባል የሚገባው ነው።

መልከ ጼዴቅ መልአክ ወይም ልዕለ ሰብአዊ ፍጡርም አልነበረም። ወይም ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተገለጸበት መልክ አልነበረም። መልከ ጼዴቅ በማያጠራጥር ሁኔታ በምድር ይኖር የነበረ ሰው፥ ንጉሥና ካህን ሲሆን፥ በምድር ባለች ከተማ ለመኖሩም ጥርጥር የለም። የትውልድ ሐረጉን ዘገባ አስመልክቶ ግን ስለ መወለዱም ሆነ መሞቱ የተጻፈ ነገር የለም። ይሁን እንጂ፥ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተምሳሌት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ቢሞትም፥ ኅልኅታ የእርሱ ሕይወትና አገልግሎት ፍጻሜ አልነበረም። ከሞት ተነሥቶ አሁን «በማያልፍ ሕይወት ኃይል» ይኖራልና ነው (ዕብ. 7፡16)። ስለ መልከ ጼዴቅ ሞት

የሚናገር መረጃ ስለሌለ፥ አሁንም መልከ ጼዴቅ በክህነት የሚያገለግል ይመስላል። ይህም ከዘላለማዊ የእግዚአብሔር ልጅ ጋር የሚመሳሰልበት ሌላው መንገድ ነው።

የመልእክቱ ተዛማጅነት ግልጽ ነው። አሮንም ሆነ ዘሮቹ ያለ ዘር ሐረግ አወራረድ በክህነት ሊያገለግሉና (7፡3) ዘላቂ አገልግሎትም ሊሰጡ አይችሉም ነበር። እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ነገሥታትና ካህናት ሊሆኑም ባልቻሉ ነበር።

ሠ. <u>አሥራትን የመቀበልና አብርሃምን የመባረክ ሥልጣን ነበረው</u> (7፡4-10)። አብርሃም ከአንስተኛ ጦርነት ያገኘውን ምርኮ በአሥራትነት መስጠቱ የመልከ ጼዴቅን ታላቅነት ያመለክታል። አብርሃም ይህን ያደረገው የመልከ ጼዴቅን ሥልጣን በመገንዘቡ ነበር። በተጨማሪም፣ መልከ ጼዴቅ በተለየ መንገድ አብርሃምን ባርኮታል። «ትንሹም በታላቁ እንዲባረክ ክርክር የሌለበት ነገር ነው» (7፡7)። አብርሃም አሥራት በመስጠትና ቡራኬውን በመቀበል የዚህን ንጉሥ-ካህን ታላቅነት መስክሯል።

ነገር ግን ይህ ከአሮን ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው? ተዛማጅነቱ አስገራሚ ነው። ስለሆነም፥ አባታቸው አብርሃም የመልከ ጼዴቅን ታላቅነት ተገንዝቦ ሲያከብረው፥ የሌዊም ወገን በጊዜው በሕይወተ ሥጋ ባይኖሩም በቅድመ አያታቸው አማካይነት በወገቡ ውስጥ ሆነው አብረው ተሳትፈዋል። የአይሁድ ሕዝብ በዘር አንድነት ላይ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡ ሲሆን፥ ይህም ለዚህ ዓይነቱ ተግባር አንድ ምሳሌ ነው። አሥራት የከፈለው አብርሃም ብቻ ሳይሆን ገና ሳይወለዱ ከወገቡ ውስጥ ያሉት እስራኤላውያን ሁሉ ነበሩ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብርሃም ዘር ስለመጣ (ዕብ. 2፡16)፥ እርሱም አሥራት ከሰጡት ውስጥ ነው ማለት ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ በዚህ ምድብ ውስጥ አይካተትም። ከአብርሃም ጋር አንድ የሆነው ሰው ሆኖ በምድር በኖረበት ጊዜ ብቻ ነበር። በሥጋው ወራት ብቻ (5፡7)። ክርስቶስ ዘላለማዊ አምላክ በመሆኑ፥ እንደ አሮንና ቤተሰቡ በአብርሃም ውስጥ አልነበረም።

## 2. አስተምህሮአዊ ክርክር፡ ክርስቶስና አሮን (ዕብ. 7፡11-25)

በዚህ ክፍል፥ ጸሐፊው ክርክሩን በአንድ ደረጃ ወደፊት አራምዶታል። መልከ ጼዴቅ ከአሮን መብለጥ ብቻ ሳይሆን አሮንን ተክቷል። «እንደ አሮን» ወይም «እንደ ሌዊ» የሚባለው ክህነት

ቀርቶ፥ «እንደ መልከ ጼዴቅ ክህነት» ሆነ። እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት ሥር ነቀል ለውጥ ያመጣው ለምንድን ነው?

ሀ. <u>ምክንያቱም ክህነቱም ሆነ ሕጉ ፍጹም አልነበሩም</u> (7፡11–14)። «ፍጹም» እና «ፍጹምነት» ተብለው የተተረጎሙት ቃላት በዚህ መልእክት ውስጥ ቁልፍ አሳቦችን ይዘዋል (2፡10፤ 5፡9፤ 6፡1፤ 7፡11፥ 19፤ 9፡9፤ 10፡1፥ 14)። ትርጉማቸውም «መሟላት፥ መጠናቀቅ» ማለት ነው። የብሉይ ኪዳን ካህናት በአገልግሎታቸው የእግዚአብሔርን ሥራ በአምላኪው ልብ ውስጥ ሊፈጽሙ አይችሉም ነበር። «ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና» (7፡19)። የእንስሳት መሥዋዕቶች የትኛውም አማኝ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹማዊ ሕሊና እንዲኖረው ሊያደርጉ የማይችሉ ስለነበሩ (10፡1–3)፥ በሙሴ ሥርዓት ይካሄድ የነበረው ቅዱስ ሕግ ዘላቂ ሥርዓት አልነበረም። ለክርስቶስ መምጣት መንገድ ለመጥረግ እንደ «ሞግዚት» የሚያገለግል ነበር (ገላ. 3፡19–4፡7)።

ካህናት ሥልጣናቸውን የተቀበሉት ከብሉይ ኪዳን ሕግ ስለሆነ (ዕብ. 7፡28) እና ክህነቱም ስለተለወጠ፥ በሕጉም ላይ ለውጥ ተካሂዷል። ለምሳሌ የአሜሪካ ሕግ ስለ ንጉሣዊ አገዛዝ የሰጠው ምንም ዓይነት የሕግ አንቀጽ ስለሌለ፥ አንድ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የአሜሪካ ንጉሥ ነኝ ሊል አይችልም። ይህንን ለማድረግ ከተፈለገ፥ መጀመሪያ ሕጉ መለወጥ አለበት።

የሙሴ ሕግ የይሁዳ ነገድ በክህነት ስለሚያገለግልበት ሁኔታ የተናገረው ነገር አልነበረም (7፡14)። ሊቀ ካህናችን በሥጋዊ የትውልድ ሐረጉ ከይሁዳ ነገድ ስለሆነ፥ የሙሴ ሕግ መለወጥ ነበረበት። እናም ለውጥ ተካሂዷል! ጠቅላላው የብሉይ ኪዳን ሕግ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለተፈጸመ ጠቀሜታው አብቅቷል (ቆላስይስ 2፡13–14)። አማኙ ከሕግ ነፃ ወጥቷል (ገላ. 5፡1–6)፤ ለሕግ ሞቷል (ሮሜ 7፡1–4)።

ይህ አዲስ መዋቅር ክርስቲያን ሕገ–ወጥ የመሆን መብት እንደሰጠው ተደርጎ አይታይም። ከሕግ ነፃ ነን ማለት ኃጢአት ለመፈጸም ነፃ ነን ማለት አይደለም። ይልቁንም፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም «መረን» ተለቀናል ማለት ነው። የምንታዘዘው ከውጫዊ ጫና ሳቢያ ሳይሆን፥ ከውስጣዊ ፍላጎታችን ነው (2ኛ ቆሮ. 5፡14፤ ኤፌ. 6፡6)። ራሳችንን ለእርሱ በምንሰጥበት ጊዜ በውስጣችን የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ «የሕግን ጽድቅ» እንድናሟላ ያስችለናል (ሮሜ 8፡1–4)።

ለ. <u>ክሕነቱና ሕጉ ፍጹም ባለመሆናቸው ለዘላለም ሊቀጥሉ አይችሉም</u> (ዕብ. 7፡15–19)። በቁጥር 15 «ሌላ» የሚለው «ሌላው

ዓይነት» ማለት ነው። የሌዊ ካህናት የተሾሙት ጊዜያዊና ፍጹም ባልሆነው ሕግ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ለክህነት የተሾመው በእግዚአብሔር አዋጅ ነበር። ሕጉ ደካማና የማይጠቅም ስለሆነ (7:17)፥ ለዘላለም ሊቀጥል አይችልም። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ፥ በማያልፍ ሕይወት ኃይል ይኖራል (7:16)። ይህ ጠቃሚ ባልሆነው ሕግና ዘላለማዊ በሆነ ሕይወት መካከል የተካሄደ ምንኛ ታላቅ ልዩነት ነው!

ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለም ካህን ስለሆነና ለዚሁ ዘላለማዊ ክህነት ብቁ የሚያደርግ ባሕርይ ስላለው፥ ከቶውንም በሌላ ሊተካ አይችልም። ሕግ ተሻረ ማለት (ቁ. 18) ክህነቱም አብሮ ተሻረ ማለት ነው። ነገር ግን ማንም የማያልፈውን የሕይወት ኃይል ሊሽር አይችልም! ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለም ካህን ሆኖ እንደሚኖር የሚያስረግጠውን አመክንዮ እውን ያደርገዋል።

ጸሐፊው የመልእክቱ ተደራሲያን ወደ ቀድሞው የቤተ መቅደስ ሥርዓት ለመመለስ የመፈለጋቸውን ፈተና አልዘነጋም። ለዚህም ነው (ቁ. 19) ሕጉ ሊፈጽም ያልቻለውን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደፈጸመ የገለጸላቸው። ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ የተሻለ ተስፋ እንዳመጣልንና ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ እንዳስቻለን ነው። ወደ ይሁዲነት መመለስ ማለት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የማድረግን ብፅዕና እንደሚያሳጣቸው አበክሮ ያስረዳል። የአይሁድ ሃይማኖት የሚሰጠው ብቸኛው ተስፋ የክርስቶስ ምጽአትን ነበር። ይህን ደግሞ አማኞችም ያገኙት በረከት ነበር።

ሐ. <u>የእግዚአብሔር መሐላ ሊሻር ስለማይችል</u> (7:20-22)። በአሮን ሥርዓት ከተሾሙት ካህናት መካከል እግዚአብሔር የግል መሐላ የገባለት አንድም ሰው አልነበረም። የአሮን ካህናት ያገለገሉት በሥጋዊ ሕግ አማካኝነት ነበር (7:16)። የሚያገለግሉት ግብረገባዊ ወይም መንፈሳዊ ብቃታቸው ተፈትኖ አልነበረም። በአሮን የክህነት ሥርዓት ዋናው ነገር ካህኑ ከትክክለኛው የዘር ግንድ መምጣቱና አንዳንድ ሥጋዊና ሥርዓታዊ መስፈርቶችን ማሟላቱ ብቻ ነበር (ዘሌ. 21:16-24)።

የኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት የተመሠረተው በመስቀል ላይ ሥራው፥ በባሕርዩ (ዕብ. 2:10፤ 5:5-10) እና በእግዚአብሔር መሐላ ላይ ነበር «አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ» ይላል [7:21፤ መዝ. (110):4]። ይህ ዓረፍተ ነገር የሚጀምረው፥ «ጌታ. . . ብሎ ማለት አይጸጸትም» በማለት ነው። ይህ የማይለወጥ ጉዳይ ነው።

ይህ መሐላ ለጌታችን ክህነት የበለጠ ዘላቂነትና ማረጋገጫን ይሰጣል። ኢየሱስ ክርስቶስ «ለሚሻል ኪዳን ዋስ» ነው (7፡22)። ዋስ ስምምነቱ ተግባራዊ እንደሚሆን የሚያረጋግጥ አካል ነው። ይሁዳ ወንድሙ ቢንያም በሰላም ወደ ቤት እንደሚመለስ ለአባቱ ዋስ ለመሆን ፈቃደኛ ነበር (ዘፍጥ. 43፡1-14)። ጳውሎስ ባሪያ ለነበረው ለአናሲሞስ ዋስ ለመሆን ፈቃደኛ ሆነ (ፊልሞና 18-19)። በአሁኑ ጊዜ ምናልባት ለዚህ ጽንሰ አሳብ አቻ የሚሆንልን በፍርድ ቤት የተከሰሰን ሰው በተፈለገ ጊዜ ለማቅረብ ቃል ገብተው የሚዋሱ ሰዎች ይሆናሉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል አማላጅ በመሆኑ (1ኛ ጢሞ. 2፡5)፥ የእግዚአብሔር ታላቅ ዋስ ነው። እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባው ቃል ኪዳን ሙሉ በሙሉ እንደሚፈጸም ከሞት ተነሥቶ ለዘላለም በመኖር ላይ ያለው አዳኛችን ዋስትና ይሆናል። እግዚአብሔር ሕዝቡን አይጥልም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን እንደሚፈጽምልን ዋስትና የገባልን ብቻ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ፊት ወኪላችን እንደ መሆኑ መጠን፥ በእኛ ምትክ ለቃል ኪዳኑ መሟላት የሚገቡትን ነገሮችም ያሟላል። እኛ ራሳችን እነዚህን ነገሮች ልናሟላቸው አንችልም። ነገር ግን በእርሱ ስላመንን አድኖናል፤ እንደሚጠብቀንም ደግሞ ዋስትና ሰጥቶናል።

በ7፡22 «ኪዳን» የሚል በጣም ጠቃሚ የዕብራይስጥ ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠቅሶ እናገኛለን። ይህ ቃል በዚህ መልእክት ውስጥ 21 ጊዜ ተጠቅሷል። ቃሉ «የመጨረሻ ኑዛዜና ኪዳን» የሚል ፍች አለው። በምዕራፍ 8 ይህንን ቃል ጠለቅ ብለን እናጠናለን።

እግዚአብሔር የክህነትን ሥርዓት ለምን ከአሮን ወደ መልከ ጼዴቅ እንደ ለወጠ ጸሐፊው ሦስት ምክንያቶችን አቅርቧል። (1) ክህነቱና ሕጉ ፍጹም አልነበሩም። (2) ፍጹም ሳይሆኑ ለዘላለም ሊቀጥሉ አይችሉም ነበር። (3) አዲስ ሥርዓት እንደሚመሠርት እግዚአብሔር ምሏል። ከዚያም ጸሐፊው ይህንን ክፍል በአራተኛው ምክንያት ደምድሟል።

መ. <u>ካህናቱ ሰዎች እንደ መሆናቸው ሁሉ ይሞቱ ነበር</u> (7፡23-25)። ክህነታቸው ፍጹም አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ በሞትም ይቋረጥ ነበር። ለዘላለም የሚኖር ካህን ስላልነበር ብዙ ሊቀ ካህናት ተፈራርቀዋል። ከዚህ በተቃራኒ፥ የቤተ ክርስቲያን ሊቀ ካህናት አንድ ብቻ ሲሆን፥ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውና ለዘላለም የሚኖረው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው! ካህኑ ካልተለወጠ ክህነቱም ዘላለማዊ ይሆናል። ይህም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ዋስትናንና

መተማመንን ያጎናጽፋል። «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፥ ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው» (13፡8)። «አንተ ለዘላለም ካህን ነህ» [መዝ. (110)፡4]።

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ኑዛዜአቸውን ሰጥተው ከሞቱ በኋላ ኑዛዜዎችን ሕገ ወጥ በሆነ መልኩ ለመጠምዘዝ ሲሞከር በጋዜጦች ላይ ሳናነብ አልቀረንም። ይህ የሚሆነው አንዳንድ ግብረ ገባዊነት የጎደላቸው ዘመዶች ወይም የንግድ ሸሪኮች ኑዜዛውን ለግል ጥቅማቸው ለማዋል በሚሞክሩበት ጊዜ ነው። ይህ ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ ባስተላለፈልን «የመጨረሻ ኑዛዜና ኪዳን» ላይ ይፈጸማል የሚል ስጋት ከቶውንም ሊያድርብን አይችልም። ኑዛዜውን ከጻፈ በኋላ ኑዛዜው ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ሞቷል። ነገር ግን ከሞት ተነሥቶ ወደ ሰማይ በማረግ ኑዛዜውን ለእኛ የጸና አድርጎልናል።

የማይለወጠው ክርስቶስ የሊቀ ካህንነቱን አገልግሎት ይቀጥላል ማለት «የማይለወጥ ክህነት» እንዳለ ያመለክታል (7፡24)። «የማይለወጥ» የሚለው ቃል የተተረጎመበት የፅርዕ (የግሪክ) ቃል «ዋጋ ያለው፥ ለውጥ የማይደረግበት» የሚል አሳብ ይዟል። ይህ ቃል በሕጋዊ ውሎች መጨረሻ ላይ የሚጻፍ ነበር። የጌታችን ክህነት በሰማይ «ዋጋ ያለውና ለውጥ የማይደረግበት» ነው። ከዚህም የተነሣ፥ በዚህ ተለዋዋጭና እርጋታ በሌለበት ዓለም ውስጥ በልበ ሙሉነት ልንመላለስ እንችላለን።

የጉዳዩ መደምደሚያ ምንድን ነው? በቁጥር 25 እንደተጻፈው፥ «ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና፤ ስለዚህ ደግሞ የማይለወጥና ለዘላለም የሚኖር ሊቀ ካህናት ስለሆነ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሙሉ ለሙሉ፥ ለዘላለም ሊያድናቸው ይችላል።» የዚህ ጥቅስ አሳብ ክርስቶስ ፈጽሞ ማዳን መቻሉ እንጂ ከፍጹም አዘቅት እንደሚያድን አይደለም። ክርስቶስ የትኛውንም ኃጢአተኛ ከየትኛውም ዓይነት የከፋ ሁኔታ ሊያድን እንደሚችል ቢታወቅም፥ የዚህ ምንባብ አሳብ ግን ይኼ አይደለም። ምንባቡ የሚያተኩረው ክርስቶስ በእርሱ የሚያምኑትን ሙሉ በሙሉ፥ ለዘላለም እንደሚያድን በመግለጹ ላይ ነው። እርሱ ለዘላለም ሊቀ ካህናችን ስለሆነ፥ ለዘላለም ሊያድነን ይችላል።

ለዚህ ሙሉ መዳን መሠረቱ የአዳኛችን ሰማያዊ ምልጃ ነው። «ሊያማልድ» የሚለው ቃል «መገናኘት፥ መቅረብ፥ መለመን፥ መማፀን» የሚሉትን አሳቦች ያካተተ ነው። እዚህ ላይ እግዚአብሔር አብ ከእኛ ጋር ስለተጣላ እግዚአብሔር ወልድ ሁልጊዜም በፊቱ እየቀረበ እንዳይፈርድብን ይለምነዋል ብለን ልናስብ አይገባም!

የደኅንነት ዕቅድ አብና ወልድ የሚለያዩበት ሳይሆን በፍጹም ስምምነት የሚያካሂዱት ነው (13፡20–21)። ወይም ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ በእኛ ፈንታ እንደሚጸልይ ወይም በተደጋጋሚ ደሙን ለመሥዋዕት እንደሚያቀርብ አድርገን ልናስብ አይገባም። ያ ተግባር በመስቀል ላይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተፈጽሟል።

ምልጃ ስንል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሕዝቡ ሆኖ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት መወከሉን ያካትታል። ስለዚህ በክርስቶስ አማካኝነት አማኞች ወደ እግዚአብሔር በጸሎት ሊቀርቡና መንፈሳዊ መሥዋዕቶችን ሊያቀርቡ ይችላሉ (4፡14–16፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡5)። የክርስቶስ ሕይወት በራሱ በሰማይ ለእኛ የሚቀርብ ጸሎት ነው ሲል አንድ ሰው ተናግሯል። ተግባሩን የሚወስነው ማንነቱ ነው።

በዚህ ረዥም ክፍል ውስጥ የቀረበውን አሳብ በምንከልስበት ጊዜ (ዕብ. 7፡11–25)፥ የጸሐፊው አመክንዮ ያስገርመናል። የመልከ ጼዴቅን ሥርዓት የያዘው የኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት ከአሮን እንደሚበልጥና የአሮንን ክህነት እንደተካው ገልጾአል። ታሪካዊም ሆነ አስተምህሮአዊ ክርክሮቹ አሳማኝነት ያላቸው ናቸው። አሁንም ጸሐፊው ሦስተኛ ክርክሮችን ያቀርባል።

## 3. ተግባራዊ ክርክር፡ ክርስቶስና አማኙ (7፡26–28)

አሮናውያን ካህናት ምንም ያህል ትጉዎችና ታዛዦች ቢሆኑ እንኳ፥ ሁልጊዜም የሰዎችን ሁሉ ፍላጎቶች ሊያሟሉ አይችሉም ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሁላችንንም ፍላጎቶች ሙሉ በሙሉ ያሟላል። «እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባናል» ሲል «ለእኛ ተስማሚያችን ነው፤ ፍላጎታችንን ሙሉ በሙሉ ያሟላልናል» ማለቱ ነው። እዚህ ላይ ትኩረት የተሰጠው ኃጢአት–የሌለበት በመሆኑ ላይ ነው። እርሱም ፍጹም በመሆኑ፥ ለሕዝቡ ፍጹም የሆነ አገልግሎት ሊሰጣቸው ይችላል። አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ካህናት ከኃጢአታቸው የተነሣ ሕዝቡን ለማገልገል አለመቻላቸው ብቻ ሳይሆን፥ በድለዋቸዋልም። ይህ ግን በኢየሱስ ክርስቶስና በሕዝቡ መካከል ሊከሰት አይችልም።

የብሉይ ኪዳን ካህናት ለአገልግሎታቸው «የተለዩ» በመሆናቸው በዚህ በኩል «ቅዱሳን» ናቸው። ነገር ግን ሁልጊዜም በባሕርያቸው ቅዱሳን አልነበሩም። እንደሚያገለግሏቸው ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞችም ነበሩ። «ያለ ተንኮል» (ቁ.6) እንከን የሌለው መሆኑን ያስረዳል። የትኛውም የአይሁድ ካህን እንከን የሌለው ነው ሊባል አይችልም። «ነውር የሌለበት» ማለት «ያልተበላሸ» ማለት ነው። አሁንም እነዚህን ባሕርያት የተቀዳጀው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ጌታችን በምድር

ላይ በሚያገለግልበት ጊዜ፥ የኃጢአተኞችና የቀራጮች ወዳጅ ነበር (ማቴ. 9፡10፤ 11፡19)። ይህ ግን ባሕርዩን አላጎደፈበትም። ጌታ የራሱን ንጽሕና ሳያጎድፍ ከሰዎች ጋር መኖር ይችል ነበር። ክርስቶስ ከሰዎች ተነጥሎ ለብቻው ባይኖርም፥ ከኃጢአት የተለየ ንጹሕ ሕይወት ነበረው። ካለበት ስፍራ የተነሣ (ከሰማያት ከፍ ስላለ) ከኃጢአተኞች የተለየ ነው። ነገር ግን ከሚያገለግላቸው ሰዎች አልተለየም። ሁልጊዜም በጸጋው ዙፋን ፊት ስንቀርብ እናገኘዋለን።

ሌላው ክርስቶስ ኃጢአት እንደሌለበት የሚያሳየው፥ እንደ ሌሎቹ ካህናት ለራሱ ኃጢአት መሥዋዕትን ማሳረግ ያላስፈለገው መሆኑ ነው። በዓመታዊ የስርየት በዓል ዕለት ሊቀ ካህናቱ ለሕዝቡ ኃጢአት ከመሠዋቱ በፊት ለራሱ ኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ ነበረበት (ዘሌ. 16)። እንዲሁም ደግሞ እንደ ቤተ መቅደስ ሥርዓት በየቀኑ የሚቀርቡ መሥዋዕቶች ነበሩ። አንድ ካህን ኃጢአት ከሠራ ለራሱ መሥዋዕት ማቅረብ ነበረበት (ዘሌ. 4 ከቁጥር 3 ጀምሮ፤ ዘጸ. 29፡38-46)። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አንድ መሥዋዕት ብቻ ለኃጢአታችን በማቅረብ ዘላለማዊ እልባት ሰጥቷል (ዕብ. 9፡23-28 አንብብ)።

ለእኛ የሚያስፈልገን ሊቀ ካህናት እንዲህ ያለው ነው! እኛም በየቀኑና በየሰዓቱ ወደ ኃጢአት የምናዘነብል ደካሞች በመሆናችን ለመንፈሳዊ እርዳታ ወደ እርሱ መቅረብ አለብን። ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናችን እንደ መሆኑ መጠን፥ ከኃጢአት የምንቆጠብበትን ጸጋና ምሕረት ይሰጠናል። ኃጢአትን ብናደርግ ግን በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት እርሱ ጠበቃችን ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡1-2)። ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ይቅርታን በማድረግ ወደ ቀድሞው መንፈሳዊ ሕይወታችን ይመልሰናል (1ኛ ዮሐ. 1፡9)።

የዚህ ትምህርት ነጥብ ግልጽ ነው። ከእንዲህ ዓይነቱ ሊቀ ካህናት ለምን ፊታችሁን ትመልሳላችሁ? የሚል ነው። በሙሴ ሕግ ያገለገሉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ከሥጋዊ ድካማቸው የተነሣ ይወድቁ ነበር። ነገር ግን ሊቀ ካህናችን ለዘላለም የተሾመ (ፍጹም የተደረገ) ሲሆን፥ እርሱም አንድም እንከን ወይም ግድፈት የሌለበት ነው (7፡28)። እንዲህ ዓይነቱ ሊቀ ካህናት ሙሉ በሙሉ ይስማማናል!

ለእኛ የታቀደውን ይህን የጸጋ አገልግሎት እየተጠቀምንበት ነው?

## 7

# የሚሻል ቃል ኪዳን

### ዕብራውያን 8

አንድ ጊዜ በሃይማኖታዊ የመገናኛ ብዙኃን አዘጋጅ ስብሰባ ላይ ስብከት ሳቀርብ ሳለሁ አንድ ወዳጄ ሙዚቃ በመጫወት አገልግሎ ነበር። ይህ ዘማሪ የተዋጣለት የፒያኖ ተጫዋች ከመሆኑም በላይ የቆዩ ክርስቲያናዊ ሙዚቃዎችን በዘመናዊ ዘይቤ የማቅረብና የመተርጎም ስጦታም ነበረው። ሁልጊዜም የእርሱን ሙዚቃ መስማት ያስደስተኝ ነበር። በዚያን ዕለት ግን እንዲጫወትበት የተሰጠው የተበላሸና ከጥቅም ውጪ ለመሆን ምንም ያህል ያልቀረው ፒያኖ ስለነበረ በጣም አዘንሁለት። ፒያኖው ከአንድ የከሰረ ኩባንያ በእርዳታ የተሰጣቸው ሳይሆን አይቀርም። ሆኖም ሙዚቃ ተጫዋቹ የሚችለውን ጥረት አድርጎ ለመጫወት ሞክሯል፥ ይሁንና የተሻለ መሣሪያ ቢሰጡት ኖሮ የተሻለ ይጫወት ነበር።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁሉም የሚበልጥ የእግዚአብሔር ካህን ነው። ይህንን የበላይነቱን የሚቀንስ አንዳችም ነገር የለም! ለዚህም ምክንያቱ በሚሻል ቃል ኪዳን (ዕብ. 8)፥ በሚሻል ቤተ መቅደስ ውስጥ (ምዕ. 9)፥ እንዲሁም በሚሻል መሥዋዕት (ምዕ. 10) የሚያገለግል መሆኑ ነው። የዚህ ምዕራፍ ጭብጥ የላቀ ቃል ኪዳን ነው። ጸሐፊው ለዚህ ቃል ኪዳን ከፍተኛነት ሦስት ምክንያቶችን አቅርቧል።

### 1. አገልግሎቱ የሚካሄደው በከፍተኛ ሊቀ ካህናት ነው (8፡1–2)

የጸሐፊው ክርክር ዙሪያ ጥምጥም ይሆን? መጀመሪያ ክርስቶስ ከሌሎች እንደሚበልጥ ካሳየ በኋላ፥ «እርሱ ከቀደሙት አገልጋዮች የሚበልጥ ከሆነ፥ የሚያገለግለው ቃል ኪዳን መብለጥ አለበት» ሲል ይናገራል። ይህ ዙሪያ ጥምጥም ክርክር አይደለም። ምክንያቱም ድምዳሜው አመክኒዮአዊ ነው። የበላይ የሆነ ካህን ዝቅ ባለ ቃል ኪዳን ሊያገለግል አይችልም። ሌላው ማብራሪያ መጠቀም ካስፈለገ፥ አንድ ትልቅ ችሎታ ያለው ጠበቃ የሚከራከርለት የውርስ ኑዛዜ ብቁ ካልሆነ ብዙም ለውጥ ሊያመጣ እንደማይችል መገንዘብ ይቻላል። ጌታችንም በዝቅተኛ «የመጨረሻ ኑዛዜና ኪዳን» ላይ ተመሥርቶ ያገለግላል ማለት የማይታሰብ ነው።

«ከተናገርነው ዋና ነገሩ ይህ ነው» የሚለው የቀረበው አሳብ የርእሰ ጉዳዩ ጭብጥ እንደሆነ ያመለክታል። ከዚያም ጌታችን እውነትም

ከሌሎች የሚበልጥ ሊቀ ካህናት መሆኑን ለማረጋገጥ አያሌ «የማጠቃለያ ሙግቶችን» አቅርቧል።

ሀ. <u>ግብረገባዊ ብቃቱ</u> (8፡1)። «እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን» (8፡1)። ይህ ዓረፍተ ነገር ወደ ዕብራውያን 8፡22–28 ይመልሰናል። «እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባናል» (7፡26)። ኢየሱስ ክርስቶስ ሥነ ምግባራዊ ፍጹምነትን ይዞ በችግሮቻችንና በፈተናዎቻችን ከእኛ ጋር መተባበሩ ከቀደሙትም ሆነ ካሉት ካህናት ያልቀዋል። ስለሆነም፥ ወደ ብሉይ ኪዳን ክህነት ለመመለስ የሚፈልጉ አንባቢዎቹ ይህንን ተስማሚ(ተገቢ) ሊቀ ካህናት ማጣታቸው ነው።

ለ. <u>የተፈጸመ ሥራ</u> (8፡1)። ዛሬ ጌታችን ሥራው ስለተፈጸመ (በዙፋኑ) ላይ ተቀምጧል። በብሉይ ኪዳን የካህናቱ ሥራ ባለመጠናቀቁ የሚቀመጡባቸው ወንበሮች አልነበሩም። ተደጋግመው የሚያቀርቡዋቸው መሥዋዕቶች ሁሉ ኃጢአትን የሚያስገነዝቡ በመሆናቸው፥ የትኞቹም የተፈጸሙ ደኅንነቶችን ሊያስገኙ አልቻሉም። የእንስሳት ደም ኃጢአትን ሊያስወግድ ወይም ሕሊናን ሊያነጻ አይችልም ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን ኃጢአት ለማስወገድ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ እነዚህ መሥዋዕቶች ኃጢአትን ከመሸፋፈን ያለፈ ሚና አልነበራቸውም (ዮሐ. 1፡29)።

ሐ. <u>ከዙፋን ላይ መቀመጡ</u> (8፡1)። ለኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ሥራ ክብርን የሚጨምረው መቀመጡ ብቻ ሳይሆን የተቀመጠበት ስፍራ ነው። የተቀመጠውም በሰማይ በአብ ቀኝ ነው። ይህ ታላቅ እውነት ቀደም ሲል የተገለጸ ሲሆን (1፡3)፥ ወደፊትም እንደገና ይጠቀሳል (10፡12፤ 12፡2)። ኢየሱስ ከዙፋን ላይ በመቀመጡ አብ ለወልድ፥ «ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ» [መዝ. (110)፡1] ሲል የሰጠው የተስፋ ቃል ተፈጽሟል። የእስራኤል ሊቀ ካህናት አለመቀመጡ ብቻ ሳይሆን በዙፋን ላይ አለመቀመጡም እውነት ነው። በዙፋን ላይ ሊቀመጥ የሚችለው እንደ መልከ ጼዴቅ ያለ ካህን ብቻ ነውና። መልከ ጼዴቅ ደግሞ ንጉሥም ካህንም ነበር (ዕብ. 7፡1)።

መ. <u>ከሁሉም በላይ ከፍ ከፍ ማለቱ</u> (8፡1)። ኢየሱስ ክርስቶስ ያለው በሰማያት ነው። እርሱም በዕርገቱና በመከበሩ በሰማያት አልፎአል (4፡14)። አሁን ከማንም በላይ ከፍ ብሏል (ኤፌ. 1፡20–23፤ ፊልጵ. 2፡5–11)። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለቀረበው ሙግት የክርስቶስ በሰማያዊ ቤት መቅደስ ውስጥ ማገልገል መጠቀሱ ጠቃሚ ነው።

እነዚህን አራት የማጠቃለያ ሙግቶች በምንከልስበት ጊዜ፥ ጌታችን በላቀ ቃል ኪዳን ማገልገሉ ምን ያህል አመክንዮአዊ እንደሆነ እንገነዘባለን። በሥነ ምግባሩ ፍጹም የሆነ ሊቀ ካህናት፥ የሰዎችን ልብ ሊለውጥ በማይችል ቃል ኪዳን ላይ ተመሥርቶ ያገለግላል ብሎ ማሰብ ይቻላል? ሥራውን የፈጸመ ሊቀ ካህናት ምንም ሊፈጽም በማይችል ቃል ኪዳን ያገለግላል ብለህ ትገምታለህ? በሰማይ ያለ ንጉሥ–ካህን ምንም ነገር ፍጹም ሊያደርግ በማይችል አሮጌ ቃል ኪዳን ይገደባል ብለን ልናስብ እንችላለን? (ዕብ. 7፡19)። ከዚህ አንጻር፥ የጸሐፊው ድምዳሜ ተገቢ ይመስላል፤ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ፍሬያማ አገልግሎት እንዲያበረክት ከተፈለገ በሰማይ የሚኖር የላቀ ሊቀ ካህናት የሚያገለግልበት ቃል ኪዳንም የላቀ መሆን አለበት።

## 2. አገልግሎቱ የሚሰጠው በከፍተኛ ስፍራ ነው (8፡3–5)

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ጸሐፊው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በአሁኑ ጊዜ በሰማያዊት ቤተ መቅደስ ውስጥ እንደሚያገለግል የሚያስረዳውን ግሩም እውነት ገልጾአል። ለዚህም ምክንያቱ ምን እንደሆነ መረዳት አይከብድም። በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ መኖሩንና በቤተ መቅደሱ ውስጥ ካህናት ስጦታዎችንና መሥዋዕቶችን ያቀርቡ እንደነበር የጸሐፊው አንባቢያን ያውቃሉ። በትውፊት ወደ ተረኩበት የሙሴ ሥርዓት መመለሱ ምንኛ ቀላል ነበር! ለመሆኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ መቅደስ ውስጥ እያገለገለ መሆኑን የምናውቀው እንዴት ነው? የሊቀ ካህናትነት አገልግሎቱን ሲያበረክት ያየው ሰው አለን? እነዚህ ጥሩ ጥያቄዎች ናቸው። ጥሩ መልሶችም ተሰጥተዋቸዋል!

ሀ. <u>አመክኒዮአዊ ምላሽ</u> (8፡3)። ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናት መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጾአል። ነገር ግን ሁሉም ሊቀ ካህናት ሌሎችን የሚያገለግሉ ናቸው። ማዕረጉም የአገልግሎት እንጂ የክብር አይደለም። እያንዳንዱ የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህን የተሾመው ስጦታዎችንና መሥዋዕቶችን ያቀርብ ዘንድ ነው። ስለሆነም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ስጦታዎችንና መሥዋዕቶችን ማቅረብ አለበት (5፡1 እና 7፡27 አንብብ)። ነገር ግን እነዚህ መሥዋዕቶች እግዚአብሔር በወሰነው ስፍራ እንጂ የተገኘ ቦታ ላይ ሊቀርቡ አይችሉም (ዘዳግ. 12፡13–14)። ያ የተወሰነው ስፍራ ቤተ መቅደስ ነው። ይህም ድምዳሜውን አመክኒዮአዊ ያደርገዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ስጦታዎችንና መሥዋዕቶችን የሚያቀርብ ሊቀ ካህናት ከሆነ፥ ይህንኑ የሚያካሂድበት ቤተ መቅደስ ሊኖረው ይገባል። ክርስቶስ ያለው በሰማይ ስለሆነ፥ ይህም ቤተ መቅደስ በሰማይ መኖር አለበት።

ይህም ሆኖ፥ ጌታችን የብሉይ ኪዳንን የሚመስሉ መሥዋዕቶችን እያቀረበ ነው ብለን ልናስብ አይገባም። «የሚያቀርበው» የሚለው በ8፡3 የሚገኘው ቃል በፅርዑ (በግሪኩ) ቋንቋ «ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ» የሚል አሳብ ይዟል። በመስቀል ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን እንደ አንድ መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቧል (9፡24–28)። በሌላ አባባል፥ ጌታችን በሰማይ የሚኖር ሕያው መሥዋዕት ነው። ስለዚህም ራሱን ደጋግሞ መሥዋዕት ማድረጉ አስፈላጊ አልሆነም።

ለ. <u>በዘር ሐረግ ላይ የተመሠረተ ምላሽ</u> (8፡4)። ቀደም ሲል ይህ እውነት በ7፡11–14 ተገልጾአል። ሰብአዊ የዘር ሐረጉን አስመልክቶ፥ ጌታችን ከይሁዳ ነገድ እንደመጣ ይታወቃል። እግዚአብሔር መሲሑ ከይሁዳ ንጉሣዊ የዘር ሐረግ እንደሚመጣ ቃል ገብቶ ነበር (ዘፍጥ. 49፡8–10)። ስለሆነም ኢየሱስ ክርስቶስ አሁንም በምድር ላይ ቢሆን ኖሮ፥ እንደ ካህን አያገለግልም ነበር። በሰማይ ግን ሥርዓቱ የአሮንን ሳይሆን የመልከ ጼዴቅን የሚከተል በመሆኑ፥ በክህነት ሊያገለግል ይችላል።

አሁንም ክርክሩ የሚያስኬድ ነው። ዳዊት ኢየሱስ ክርስቶስ ካህን እንደሚሆን ተንብዮ ነበር [መዝ. (110)፡4]። ኢየሱስ ከይሁዳ ነገድ መወለዱ ካህን ለመሆን አያስችለውም። ስለሆነም በሰማይ ለዘላለም ካህን መሆን ነበረበት። በምድራዊ ቤተ መቅደስ ተቀባይነትን ስለማያገኝ፥ በሰማያዊ ቤተ መቅደስ ማገልገል ነበረበት።

ሐ. <u>ምስያዊ ምላሽ</u> (ዕብ. 8፡5)። «ምስያ» ለአዲስ ኪዳን እውነት የቆመ የብሉይ ኪዳን ተምሳሌት ነው። እያንዳንዱ ምስያ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተገለጸ ስለሆነ፥ እያንዳንዱን የብሉይ ኪዳን ገጸ ባሕርይ ወይም ክስተት ምስያ ለማድረግ መሞከር የለብንም። በዚህ ክፍል ውስጥ «ምሳሌ» የሚለው ቃል በግሪኩ «ቱፖስ» የሚባል ነው።

ካህናት ያገለገሉባት ቤተ መቅደስ የሰማያዊቷ ቤተ መቅደስ ቅጂ (ምሳሌ) ነበረች። ጥቅሱ የተወሰደው ከዘጸአት 25፡40 ሲሆን፥ ይህም በጠቅላላው ሰማያዊቷን ቤተ መቅደስ የሚጠቁም ነበር። ሙሴ ይህንን ምሳሌ በተራራው ላይ ተመልክቶ መሠረታዊ ክፍሎቹን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ አካትቷል። ይህ ማለት ግን ሰማያዊቷ የመገናኛ ድንኳን ከቆዳና ከሸማ የተሠራች ናት ማለት አይደለም። እዚህ ላይ አጽንኦት የተሰጠው ለቤተ መቅደሱ መሠረታዊ ትርጉምና አሠራር ነው። እውነተኛይቱ ቤተ መቅደስ የምትገኘው በሰማይ ነው። በምድር ላይ የተሠሩት የመገናኛው ድንኳንና ቤተ መቅደሱ ግን ቅጂዎች ብቻ ናቸው።

ይህ አማኞቹ ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኞች ሆነው እንዲኖሩና ወደ ይሁዲነት (አይሁዳዊነት) እንዳይመለሱ ለመርዳት የቀረበ ክርክር ነው። ምድራዊዎቹ የመገናኛው ድንኳንና ቤተ መቅደስ እውነተኛና ቋሚዎች ቢመስሉም፥ የእውነተኛው ድርጊት ቅጂዎች ናቸው! የብሉይ ኪዳን ሥርዓት ከጥላነት ያለፈ ሚና አልነበረውም (ቆላስይስ 2፥17 አንብብ።) ሕጉ ወደፊት የሚመጡ ነገሮች ጥላ ነበር (ዕብ. 10፥1)። እውነተኛውና የተሟላው ብርሃን የተገለጠው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እንግዲህ ወደ ጥላው መሄድ ለምን ያስፈልጋል?

ሰማያዊ ትእይንት የተገለጸበት የዮሐንስ ራእይ ከብሉይ ኪዳን የመገናኛ ድንኳን ጋር የሚመሳሰሉ ነገሮችን ያቀርባል። ዮሐንስ በሰማይ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንዳለ ይነግረናል (ራእይ 11፥19)። በዘላለሙ መንግሥት መላዋ የእግዚአብሔር ከተማ ቤተ መቅደስ ስለምትሆን የተለየ ቤተ መቅደስ አያስፈልግም (21፥22)። ለምሳሌ የነሐስ መሠዊያ (6፥9–11) እና የዕጣን ማጠኛ (8፥3–5) ተገልጸዋል። «የብርጭቆ ባሕር» (4፥6) የመታጠቢያ ሰሐን፥ ሰባቱ የእሳት መብራቶች (4፥5) ደግሞ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የነበረውን ባለ ሰባት ቅርንጫፍ መቅረዝ ያስታውሰናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በቅጂዋ ሳይሆን በመጀመሪያዋ ቤተ መቅደስ ውስጥ እያገለገለ ስለሆነ፥ በሚሻል ስፍራ እንደሚያገለግል ግልጽ ነው። ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊቷ ቤተ መቅደስ ውስጥ ኅብረት ልናደርግ ስንችል ለምን በቅጂዋ ቤተ መቅደስ ውስጥ ከካህናት ጋር ኅብረት እናደርጋለን? ይህ ከሕንጻው ይልቅ በሕንጻው ንድፍ ውስጥ ለመኖር እንደ መፈለግ ነው!

ጸሐፊው አሁን ስለ አዲስ ኪዳን የበላይነት ሁለት ማረጋገጫዎችን ሰጥቶናል። እነዚህም የአዲስ ኪዳን አገልግሎት በሚበልጠው በኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት፥ በሚበልጥ ሰማያዊ ቤተ መቅደስ ውስጥ እንደሚካሄድ የሚያስረዱ ናቸው። ከዚያ በመቀጠል ሦስተኛውን ማረጋገጫ ያቀርባል።

## 3. የተመሠረተውም በሚሻል ቃል ኪዳን ላይ ነው (8፥6–13)

በአሮጌው ኪዳን ሕግ በተሰጠበት ወቅት፥ ሙሴ ለሰዎች የእግዚአብሔር እንደራሴ ሆኖ ያገለግል ነበር (ገላ. 3፥19–20)። የእስራኤል ሕዝብ በሲና ተራራ ላይ እጅግ ከመፍራታቸው የተነሣ፥ የእግዚአብሔርን ድምፅ ላለመስማት ፈልገው ሙሴ እንዲናገራቸው ለመኑት (ዘጸ. 20፥18–21)። የሚያሳዝነው ይህ ፈሪሃ-እግዚአብሔር

ብዙም አብሯቸው አልቆየም። ወዲያው እንጠብቃለን ያሉትን ሕግ መጣስ ጀመሩ። የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን፥ እርሱ ብቸኛው መካከለኛ ነው (1ኛ ጢሞ. 2፡5)። የክርስቶስ አገልግሎት በሚሻል ቃል ኪዳን ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፥ ከብሉይ ኪዳን ካህናት የተሻለ ነው። የክርስቶስ ቃል ኪዳን ደግሞ በሚሻሉ ተስፋዎች ላይ የተመሠረተ ነው።

በዚህ አንቀጽ ውስጥ የተጠቀሰው «የሚሻል ቃል ኪዳን» ነቢዩ ኤርምያስ በትንቢቱ የተናገረለት ነው (ኤር. 31፡31–34)። ትንቢቱ የተሰጠው ለአይሁዶች የወደፊቱን ሕይወት አስተማማኝነት ለመግለጽ ነበር። ኤርምያስ ያገለገለው ሕዝቡ ወደ ባቢሎን ምርኮ ሊሄድ በቀረበበት የእስራኤል ታሪክ ፍጻሜ አካባቢ ነበር። በዚህ የሕዝቡ የወደፊት ሕይወት የጨለመ በሚመስልበት ወቅት እግዚአብሔር ወደ ቀድሞው ሕይወታቸው እንደሚመለሱና በረከትንም እንደሚያገኙ ተስፋ ሰጣቸው።

ጌታችን ወደ ጎልጎታ ከመሄዱ በፊት፥ በሰገነት ላይ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን በዓል አከበረ። በዚህም ጊዜ «ቅዱስ ቁርባን» የምንለውን ሥርዓት መሠረተ። ጽዋውን በማንሣት፥ «ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው» ብሏል (ሉቃስ 22፡20፤ ማር. 14፡22–24)። ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን ቃላት ከቤተ ክርስቲያን ጋር አዛምዷቸዋል (1ኛ ቆሮ. 11፡23–27)። የዕብራውያን ጸሐፊም ኢየሱስ ክርስቶስ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ እንደሆነ ገልጾአል (ዕብ. 9፡15፤ 12፡24)።

ለመሆኑ፥ ይህ ለእስራኤል ቃል የተገባውና ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምበት አዲስ ኪዳን የሚሠራው እንዴት ነው? በሌላ አገላለጽ፥ እግዚአብሔር እነዚህን በረከቶች ለመስጠት ለአይሁዶች ተስፋ ገብቶ ሲያበቃ ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው እንዴት ነው?

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ይህንን ችግር የሚፈቱት ቤተ ክርስቲያን «አዲሷ እስራኤል» እንደሆነችና የአዲስ ኪዳን የተስፋ ቃሎች «የአብርሃም መንፈሳዊ ዘር» እንደሆኑ በመግለጽ ነው። አማኞች ዛሬ የአብርሃም መንፈሳዊ ዘር መሆናቸው በገላትያ 3፡13–29 የተገለጸ ቢሆንም፥ ይህ ግን ቤተ ክርስቲያን «መንፈሳዊት እስራኤል» ነች ከሚለው አሳብ የተለየ ነው። በዕብራውያን 8፡8 የተጠቀሰው የተስፋ ቃል የእስራኤልን ቤትና የይሁዳን ቤት ለይቶ ይናገራል። «እስራኤል» እና «ይሁዳ» የሚሉትን ግልጽ ቃላት በሌላ ከለወጥን በኋላ፥ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እንደምንተረጉም ለመወሰን የሚቻልበት መንገድ መቋጫ ሊኖረው አይችልም።

ሌሎች ደግሞ ይህ «አዲስ ኪዳን» በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳልተፈጸመና ጌታችን በክብር በሚመለስበት ጊዜ፥ አይሁዶች ተሰብስበው መንግሥታቸውን በሚመሠርቱበት ጊዜ ወደፊት የሚፈጸም መሆኑን ያስረዳሉ። ይህንንም አቋም ከወሰድን፥ በዕብራውያን 9፡15 እና 12፡24 ኢየሱስ ክርስቶስ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ እንደሆነ የተገለጸውን አሳብ ለማብራራት እንቸገራለን። ሁለት አዲስ ኪዳናት እንዳሉና አንዱ ለቤተ ክርስቲያን አንዱ ደግሞ ለእስራኤል እንደሚሠራ መናገሩ ተጨማሪ ጥያቄዎችን መፍጠር ይሆናል።

ምናልባትም መፍትሔ የሚገኘው «መጀመሪያ አይሁዶች» በሚለው የእግዚአብሔር መርህ ውስጥ ይሆናል (ሮሜ 1፡16)። እግዚአብሔር ለሕዝቡ አዲስ ኪዳን ለመስጠት ቃል የገባ ቢሆንም፥ የዚህ ቃል ኪዳን በረከቶች የሚገኙት የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ነው። እርሱ የአዲሱ ኪዳን መካከለኛ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን በጀመረ ጊዜ መጀመሪያ የሄደው የእርሱ ወደሆኑት ነበር (ማቴ. 15፡24)። ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት የላከውም ወደ አይሁዶች ብቻ ነበር (10፡5-6)። ቤተ ክርስቲያን የምስክርነት አገልግሎት እንድትሰጥ ሲልክ፥ ከኢየሩሳሌም እንድትጀምር አደረገ (ሉቃስ 24፡46-48፤ የሐዋ. 1፡8)። ጴጥሮስ በዕለተ በዓለ ኀምሳ ስብከቱን ያቀረበው ለአይሁዶችና ወደ አይሁድነት ለተለወጡ አሕዛብ ብቻ ነበር (የሐዋ. 2፡14፥ 22፥ 36)። በዚህ ስብከት ውስጥ ጴጥሮስ የወንጌሉ የምሥራች መጀመሪያ ለአይሁዶች እንደሆነ ገልጾአል (የሐዋ. 3፡25-26)።

ነገር ግን ሕዝቡ መልእክቱንና መልእክተኞችን አልተቀበሉም። በሺህ የሚቆጠሩ አይሁዶች በክርስቶስ አምነው መዳናቸው ባይካድም፥ አብዛኛው ሕዝብ ቃሉን አልተቀበለም፤ የሃይማኖት መሪዎችም ቤተ ክርስቲያንን ተቃውመዋል። ይህ ሁኔታ ካስከተላቸው መዘዞች አንዱ የእስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ መሞት ነበር (የሐዋ. 7)። ለዚህ ሁኔታ የእግዚአብሔር ምላሽ ምን ነበር? ወንጌሉ ከኢየሩሳሌምና ይሁዳ ወደ ሰማርያ (የሐዋ. 8)፥ ከዚያም ወደ አሕዛብ ተሻገረ (የሐዋ. 10)።

ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ዳግም ተወልደው በክርስቶስ አንድ የሆኑ አይሁዶችና አሕዛብ የሚገኙባት አካል ነች (ኤፌ. 2፡11-22፤ ገላ. 3፡27-29)። «በክርስቶስ» የሆኑ ሁሉ በመስቀል ላይ ዋጋ የተከፈለበት የአዲስ ኪዳን ተካፋዮች ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ እስራኤልን ለመዋጀት በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ፥ የአዲስ ኪዳን በረከቶች በጭንቀት ተከበው ለሚገኙት እስራኤላውያን ይደርሳሉ። እግዚአብሔር

ሕዝቡ ለሆኑት እስራኤላውያን ምን እንዳቀደ ለማወቅ ኤርምያስ ምዕራፍ 31ን በሙሉ አንብበው።

የአዲስ ኪዳንን የሚሻሉ የተስፋ ቃሎች ከመመርመራችን በፊት፥ ሌላም እልባት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ አለ። የአዲስ ኪዳን መኖር የብሉይ ኪዳንን ስሕተትነት ወይም ሕጉ ዛሬ ምንም አገልግሎት እንደማይሰጥ የሚያመለክት አድርገን መውሰድ የለብንም። ሁለቱም ኪዳናት እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጣቸው ናቸው። ሁለቱም ኪዳናት ተያያዥ በረከቶችን ያስገኛሉ። እስራኤላውያን አሮጌውን ኪዳን ታዘው ቢሆን እግዚአብሔር ይባርካቸውና ለመሲሑ መምጣት ይዘጋጁ ነበር። ጳውሎስ ብሉይ ኪዳን የራሱ የክብር ድርሻ እንዳለው አመልክቷል (2ኛ ቆሮ. 3፡7–11)። ስለሆነም፥ ብሉይ ኪዳንን ማጣጣልም ሆነ ማዋረድ አይገባም።

ምንም እንኳ አዲሱ የጸጋ ቃል ኪዳን ከሙሴ ሕግ ነፃ ቢያወጣንም (ገላ. 5፡1)፥ እግዚአብሔርን ካለመታዘዝ ወይም ኃጢአትን ካለመሥራት ነፃ አላወጣንም። እግዚአብሔር አሁንም በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት «የሕግ ጽድቅ» በእኛ ሕይወት ተፈጻሚ እንዲሆን ይፈልጋል (ሮሜ 8፡1–4)። ሕጉን በሕጋዊ መንገድ ልንጠቀም እንችላለን (1ኛ ጢሞ. 1፡8–11)።

አሁን የአዲስ ኪዳንን የሚሻሉ ተስፋዎች ልንመለከት እንችላለን።

ሀ. <u>የእግዚአብሔር ጸጋ ተስፋ</u> (ዕብ. 8፡7–9)። አዲስ ኪዳን ትኩረት የሚሰጠው «እኔ አደርጋለሁ» በሚለው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ ነው። በሲና ተራራ የእስራኤል ሕዝብ፥ እግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃላት ሁሉ እንደሚፈጽሙ ተናግረው ነበር (ዘጸ. 24፡3)። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል አልታዘዙም። እናደርጋለን ማለቱና አድርጎ መገኘቱ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ነገር ግን አዲሱ ቃል ኪዳን ሰው ለእግዚአብሔር ባለው ታማኝነት ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ለሰው በሰጠው የታመነ ተስፋ ላይ የሚመሠረት ነው። የዕብራውያን ጸሐፊ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑት የገባውን ተስፋ ተግባራዊ እንደሚያደርግ ያስረዳል (8፡10)። እንዲያውም «አደርጋለሁ» የሚለው የእግዚአብሔር ተስፋ በዚያች አንዲት ቁጥር ውስጥ ሦስት ጊዜያት የተደጋገመ ሲሆን፥ ከቁጥር 8–12 ስድስት ጊዜ ተደጋግሟል።

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብጽ ያወጣቸው አንድ አባት የልጆቹን እጆች ይዞ በሚመራበት መንገድ ነበር። እግዚአብሔር ቅዱስ ሕጉን ለእስራኤላውያን የሰጣቸው ለራሳቸው ጥቅም ነበር። ይኸውም ከሌሎች አገሮች በመለየት ከአረማውያን ክፉ ልማዶች ለመጠበቅ

ነበር። ሕዝቡ ግን በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አልጸኑም (8፡9)። ለዚህም እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ተደጋጋሚ ቅጣቶችን በማምጣትና በመጨረሻም ለምርኮኛነት አሳልፎ በመስጠት የጨከነ ምላሽ ሰጥቷል።

እግዚአብሔር ጥፋትን ያገኘው፥ ከቃል ኪዳኑ ሳይሆን ከሕዝቡ ዘንድ ነበር። «ስለዚህ ሕጉ ቅዱስ ነው፤ ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት» (ሮሜ 7፡12)። ችግሩ ያለው ከሕጉ ሳይሆን ከራሳችን የኃጢአተኛነት ተፈጥሮ ነው። ምክንያቱም በራሳችን የእግዚአብሔርን ሕግ ልንጠብቅ አንችልም። ሕጉ ምንም ነገር ፍጹም አላደረገም (ዕብ. 7፡19)። ለዚህም ምክንያቱ የየትኛውንም ሰው ልብ ሊለውጥ የማይችል መሆኑ ነው። ይህንን ሊያደርግ የሚችለው የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው።

አዲሱ ኪዳን ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። የትኛውም ኃጢአተኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ሳያምን የዚህ ኪዳን አካል ሊሆን አይችልም። ሕግና ሥራ አብረው እንደሚሄዱ ሁሉ፥ ጸጋና እምነትም አብረው የሚሄዱ ናቸው (ሮሜ 11፡6)። ሕጉ፥ «እነዚህን ነገሮች (በሕጉ የተደነገጉትን) የሚያደርግ ሰው በእነርሱ ይኖራል» ይላል (ገላ. 3፡12)። ጸጋ ግን፥ «ሥራው ስለተጠናቀቀ፥ እመንና በሕይወት ኑር!» ይላል።

ለ. <u>የውስጣዊ ለውጥ ተስፋ</u> (ዕብ. 8፡10)። የሙሴ ሕግ የእግዚአብሔርን ቅዱስ መመዘኛዎች ሊያውጅ ቢችልም፥ ለመታዘዝ የሚያስፈልገውን ኃይል አይሰጥም ነበር። ኃጢአተኛ ሰዎች አዲስ ልብና ውስጣዊ ለውጥ ያስፈልጋቸዋል። አዲስ ኪዳን የሚያደርገውም ይህንኑ ነው። (ተመሳሳይ አሳብ ከሕዝቅኤል 36፡26-27 አንብብ።) አንድ ኃጢአተኛ በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ፥ መለኮታዊ ባሕርይን ይቀበላል (2ኛ ጴጥ. 1፡1-4)። ይህ መለኮታዊ ባሕርይ ደግሞ እግዚአብሔርን ለመውደድና ለመታዘዝ የሚችልበትን ፍላጎት ይሰጠዋል። ኃጢአተኞች በተፈጥሯቸው በጥላቻና ባለመታዘዝ የታሰሩ ናቸው (ቲቶ 3፡3-7)። አዲሱ ባሕርይ ግን እያንዳንዱ አማኝ እግዚአብሔርን የሚታዘዝበትን ፍላጎትና ኃይል ይለግሰዋል።

ሕጉ ውጫዊ ሲሆን፥ እግዚአብሔር ከሕዝቡ የሚፈልጋቸው ነገሮች በድንጋይ ጽላት ላይ ተጽፈው ይገኙ ነበር። በአዲስ ኪዳን ግን የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች አእምሮና ልብ ውስጥ ተጽፎአል (2ኛ ቆሮ. 3፡1-3)። ራሱን አሳልፎ የሰጠው አማኝ ይበልጥ ኢየሱስ ክርስቶስን እየመሰለ ይሄድ ዘንድ የእግዚአብሔር ጸጋ በእርሱ ውስጥ ውስጣዊ ለውጦችን ያካሂዳል (3፡18)።

ብዙ ክርስቲያኖች በጸጋ እንደዳኑና ዳሩ ግን የክርስትና ሕይወታቸውን በብሉይ ኪዳን ሕግ ማሟላት እንደሚገባቸው ማሰባቸው አሳዛኝ ነገር ነው። በአዲስ ኪዳን ድነው በብሉይ ኪዳን ለመቀደስ ይፈልጋሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህ ወገኖች ከጸጋ እንደወደቁ ያስረዳል (ገላ. 5፡4)። እነዚህ ሰዎች የወደቁት ከደኅንነት ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በጸጋ ከሚባርክበት ክልል ነው። ቅዱሳን የምንሆነው በራሳችን ኃይል የእግዚአብሔርን ቃል ለመጠበቅ በመሞከር አይደለም። የሕግን ጽድቅ የምንፈጽመው ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ አሳልፈን በመስጠት ሲሆን (ሮሜ 8፡1–4)፥ ይህም ሙሉ በሙሉ የጸጋ ሥራ ነው።

ሐ. <u>ለሁሉም ይቅርታ እንደሚደረግላቸው የተሰጠ የተስፋ ቃል</u> (ዕብ. 8፡11–12)። በሕግ ይቅርታ የለም። ሕጉ የተሰጠው ለዚያ ዓላማ አይደለምና። «ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤ ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና» (ሮሜ 3፡20)። ሕግ እንኳንስና ለሰው ልጆች በሙሉ ለእስራኤላውያንም ይቅርታን እንደሚያደርግ አይናገርም። በስሙ የሚያምኑ ሁሉ ይቅርታን የሚያገኙት በኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕት ብቻ ነው። ስለዚህ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች ኃጢአትን የማስታወስ እንጂ የማስወገድ ሚና አልነበራቸውም (ዕብ. 10፡1–3፥ 18)።

ዕብራውያን 8፡11 ከትንቢተ ኤርምያስ 31፡34 የተወሰደ ነው። ይህ ጥቅስ እስራኤል ከይሁዳ ጋር የምትዋሃድበትን (ዕብ. 8፡8) እና ተስፋ በተገባው መንግሥት ደስ የምትሰኝበትን ጊዜ ያመለክታል (ኤር. 31፡1–14)። በዚያን ጊዜ ወንጌሉን ለሌሎች ማካፈሉ አስፈላጊ አይሆንም፤ እያንዳንዱ በግሉ ጌታን ያውቃልና። እስከዚያን ጊዜ ድረስ ግን የወንጌሉን መልእክት ለጠፋው ዓለም ማካፈሉ መልካም ዕድልም ኃላፊነታችንም ነው።

እግዚአብሔር ኃጢአታችንንና በደላችንን ከእንግዲህ አያስታውስም ማለት ምን ማለት ነው? (ዕብ. 8፡12)። ይህ አስፈላጊ አሳብ እንደገና በዕብራውያን 10፡16–17 ተጠቅሷል። ይህ ሁሉን የሚያውቀው አምላካችን ያደረግነውን ይረሳዋል ማለት ይሆን? እግዚአብሔር አንድን ነገር የሚረሳ ከሆነ፥ አምላክ ሊሆን አይችልም። «ከእንግዲህ አያስታውስም» ማለት «ከእንግዲህ በኃላፊነት አይጠይቀንም» ማለት ነው። እግዚአብሔርን ሁሉንም ነገር እያስታወሰ፥ ከእኛ ጋር ያለውን ግንኙነት በሕግና ሥራ ላይ ሳይሆን በጸጋና ምሕረት ላይ ይመሠርተዋል። የኃጢአት ይቅርታ ካገኘን በኋላ እንደገና አንጠየቅበትም። ነገሩ ለዘላለም ይዘጋል።

መጋቢ እንደመሆኔ መጠን የማማከር አገልግሎት በምሰጥበት ወቅት ሰዎች፥ «ይቅር ልል እችላለሁ፤ ልረሳ ግን አልችልም» ሲሉ እሰማለሁ።

እኔም ብዙውን ጊዜ፥ «በርግጥ ልትረሳው አትችልም። ከአእምሮህ ለማውጣት በምትሞክርበት ጊዜ የበለጠ እያስታወስኸው ትሄዳለህ። ነገር ግን መርሳት ማለት ይኼ አይደለም» እላቸዋለሁ። ከዚያም መርሳት ማለት በበደለን ሰው ላይ ቂም አለመያዝ መሆኑን አብራራላቸዋለሁ። ሌሎች ሰዎች ያደረጉብንን እያስታወስን፥ ምንም ነገር እንዳልበደሉን አድርገን እናስተናግዳቸዋለን።

ይህ እንዴት ይቻላል? ይህ የሚቻለው ከመስቀሉ የተነሣ ነው። በመስቀሉ ላይ እግዚአብሔር ልጁን እንደ ኃጢአተኛ ቆጥሮታልና! ከእግዚአብሔር ይቅርታን ማግኘታችን ሌሎችን ይቅር እንድንል ያስችለናል።

መ. <u>የዘላለም በረከት ተስፋ</u> (8፡13)። ይህ መልእክት በተጻፈበት ወቅት እስራኤል አሁንም በብሉይ ኪዳን ደንብ ትተዳደር ነበር። ቤተ መቅደሱ ገና ያልፈረሰ ሲሆን፥ ካህናትም መሥዋዕቶችን ያቀርቡ ነበር። ምናልባትም በእምነታቸው የዳኑት አይሁዶች ክርስቲያን ወዳጆቻቸው ተጨባጭ ለማይመስለው እምነት ይህንን «ጽኑ መሠረት ያለው ሃይማኖት» በመተዋቸው እንደ ሞኞች ሳይቆጥሯቸው አልቀሩም። ክርስቲያን ያልሆኑ አይሁዶች ያልተረዱት ነገር ቢኖር «ጠንካራ ሃይማኖታቸው» እንዳረጀና ሊጠፋ እንደተቃረበ ነበር። በ70 ዓ.ም. የኢየሩሳሌም ከተማና ቤተ መቅደሱ በመደምሰሳቸው፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አይሁዶች የማምለኪያ ቤተ መቅደስም ሆነ ካህናት ሊያገኙ አልቻሉም (ሆሴዕ 3፡4 አንብብ።)

ነገር ግን አዲሱ ኪዳን ዘላለማዊ በረከትን ያመጣል። ኢየሱስ ክርስቶስ የዘላለም ደኅንነት (ዕብ. 5፡9) እና የዘላለም ቤዛነት (9፡12) ምንጭ ነው። «አዲስ» ተብሎ የተተረጎመው የዕርዕ (የግሪክ) ቃል የጊዜን ሳይሆን የጥራትን አዲስነት ያመለክታል። ይህ አዲስ ኪዳን እንዲህ ያለ ጥራት ስላለው ለመቼውም ተተኪ ሳያስፈልገው ይኖራል!

አዎን፥ ጌታችን በአዲስ ኪዳን መሠረት እያገለገለ ነው። ይህም ክርስቶስ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን አዲስ ባሕርይና እጅግ የተዋበ አዲስ ሕይወት እንድንካፈል የሚያደርግ አዲስ ኪዳን ነው።

# 8

# የሚበልጥ ቤተ መቅደስ

**ዕብራውያን 9**

ክርስቲያን የሁለት ዓለማት፥ ማለትም የሰማይና የምድር ዜጋ ነው (ማቴ. 22፡21) ይህም በመሆኑ፥ የቄሣርን ለቄሣር፥ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር መስጠት ይኖርበታል (ማቴ. 222፡21) የሁለት ዓለማት ዜጋ ስለሆነ፥ በእይታ በሚገዛው ዓለም ውስጥ እንዴት በእምነት መኖር እንዳለበት ማወቅ አለበት። አንድ ክርስቲያን የዓለምን ስበት ለማሸነፍ የማይታየውን መመልከት ይኖርበታል (ዕብ. 11፡24–27) «ማየት ማመን ነው!» ለሚለው የተግባራዊ ሰው አባባል፥ መንፈሳዊ ሰው የሚሰጠው ምላሽ፥ «ማመን ማየት ነው!» የሚል ነው።

ይህ የእምነት መርህ ከሰማያዊ ቤተ መቅደስ ጋር ካለን ግንኙነት ሊዛመድ ይገባል። መቼም ይህንን ቤተ መቅደስ በዓይናችን አላየነውም። ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚነግረን እናውቀዋለን። ዛሬ እግዚአብሔር በእጆች በተሠራች ቤተ መቅደስ ውስጥ እንደማይመለክ እናውቃለን (የሐዋ. 7፡46–50)። በምድር ላይ እግዚአብሔር የሚያድርበት ልዩ ስፍራ የለም (ዮሐ. 4፡19–24፤ ኢሳ. 57፡15፤ 6፡1–2 አንብብ።) አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን «ቤተ እግዚአብሔር» ብለን ልንጠራ ብንችልም፥ እግዚአብሔር እዚያ እንደማይኖር እናውቃለን። እግዚአብሔር በሕንጻው ውስጥ የሚመለክ ቢሆንም፥ በዚያ ግን አያድርም።

ይህ ምዕራፍ (ዕብ. 9) የብሉይ ኪዳንን ቤተ መቅደስ (የመገናኛውን ድንኳን) ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን ከሚያገለግልበት ሰማያዊ ቤተ መቅደስ ጋር ያነጻጽራል። ከንጽጽሩ እንደምንገነዘበው፥ የአዲስ ኪዳን ቤተ መቅደስ ከድሮው የበለጠ ነው።

## 1. የሚያንሰው የብሉይ ኪዳን ቤተመቅደስ (9፡1–10)


የዕብራውያን መልእክት የመገናኛው ድንኳን ደንቦችና ተግባራት በእግዚአብሔር የተመሠረቱ መሆናቸውን ያስረዳል። የመገናኛው ድንኳን አገልግሎት ከአዲሱ ዝቅ ያለው ሥርዓቶቹን እግዚአብሔር ስላልመሠረታቸው አይደለም። አሮጌው ኪዳን በሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ የካህናት አገልግሎት በእግዚአብሔር የተቋቋመ ከመሆኑም በላይ ፍጹም አግባብነት ያለው ነበር።

እንዲህ ከሆነ፥ የመገናኛውን ድንኳን የሚያሳንሰው እንግዲህ ምንድነው? ለዚህ ጥያቄ አምስት መልሶች አሉ።

ሀ. የመገናኛው ድንኳን ምድራዊ ቤተ መቅደስ ነበር (9፡1-10)። ይህም ማለት የመገናኛው ድንኳን በሰው የተሠራ (9፡11) እና በሰው የተተከለ (8፡2) ነው ማለት ነው። ቤተ መቅደሱ የተሠራው የአይሁድ ሕዝብ በለጋስነት ለሙሴ ካመጧቸው ስጦታዎች ነበር። ከዚያም እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን ይሠሩ ዘንድ ለባስልኤልና ኤልያብ መንፈሳዊ ጥበብና እውቀትን ሰጣቸው (ዘጸአት 35-36 አንብብ።) ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ፥ ቤተ መቅደሱ ለእግዚአብሔር ተሰጠ (ዘጸ. 40)። ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ክብር ቤተ መቅደሱን ቢሞላውም፥ ይህ ሰዎች ከምድራዊ ቁሳቁሶች የሠሩት ምድራዊ ሕንጻ መሆኑን አላስቀረውም።

ምድራዊ ሕንጻ በመሆኑ፥ አያሌ ድክመቶች ነበሩት። ከእነዚህም ድክመቶች አንዱ ጥገና የሚያስፈልገው መሆኑ ነው። እንዲሁም ደግሞ በቦታ የተከለለ ነበር። አንድ ቦታ ከተተከለ ሌላው ዘንድ ሊገኝ አይችልም ነበር። ወደ ሌላ ስፍራ ለመውሰድ ከተፈለገ ማፈራረስና የተለያዩ ክፍሎችን ለየብቻ ማንቀሳቀስ ያስፈልግ ነበር። ከዚህ በላይ የሚገለገልበት የእስራኤል ሕዝብ ብቻ እንጂ ሌሎች የዓለም ሕዝቦች አልነበሩም።

ለ. ከርሱ ለሚበልጠው ነገር ምስያ ነበር (ዕብ. 9፡2-5)። ጸሐፊው የመገናኛውን የተለያዩ ክፍሎች ዘርዝሯል። ይህንንም ያደረገው እነዚህ ሁሉ መንፈሳዊ ትርጉም ስላላቸው ነው። እነዚህም በሰማያት ያሉትን ነገሮች የሚመስሉ ናቸው። (ዕብ. 9፡23)። የመገናኛው ድንኳን አጠቃላይ ገጽታ በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ ተመልክቷል።


ቅድስተ ቅዱሳን
የቃል ኪዳኑ ታቦት
መጋረጃ
የዕጣን መሠዊያ
የዕጣን
መሠውያ
መቅረዝ
የኅብስት ገበታ
ቅድስት ስፍራ
መጋረጃ

«የመጀመሪያይቱ» (9፡2) እና «ሁለተኛይቱ» (9፡7) የሚሉት ቃላት የመገናኛውን ድንኳን የመጀመሪያና ሁለተኛ ክፍሎች ያመለክታሉ። የመጀመሪያይቱ ቅድስት ስፍራ ስትባል፥ ሁለተኛይቱ ግን ቅድስተ ቅዱሳን በመባል ትታወቃለች። እነዚህ ሁሉ የየራሳቸው ዕቃዎች የነበሯቸው ሲሆኑ፥ ዕቃዎቹም ልዩ ፍች ነበራቸው።

ሰባት ቅርንጫፎች ያሉት መቅረዝ ከቅድስት ስፍራ ይቆም ነበር። (ዘጸ. 25፡31-40፤ 27፡20-21፤ 37፡17-24)። መቅረዙ የሚበራው በሻማ ሳይሆን በዘይት ነበር። በመገናኛው ድንኳን ውስጥ መስኮቶች ስላልነበሩ፥ ይህ መቅረዝ ካህናት በቅድስት ስፍራ ለሚያከናውኑት አገልግሎት ብርሃን በመስጠት ያገለግላል። እስራኤል ለአሕዛብ ብርሃን እንድትሆን ነበር የተጠራችው (ኢሳ. 42፡6፤ 49፡6)። ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ሲሆን (ዮሐ. 8፡12)፥ አማኞች በዓለም ውስጥ እንዲያበሩ ተጠርተዋል (ፊልጵ. 2፡14-15)።

በተጨማሪም፥ በቅድስቲቱ ውስጥ 12 ኅብስቶች የተቀመጡበት ጠረጴዛ ይገኝ ነበር። ይህም የኅብስት ጠረጴዛ ተብሎ ይታወቃል (ዘጸ. 25፡23-30፤ 37፡10-16፤ ዘሌ. 24፡5-9)። በየሰንበቱ ካህኑ ጠረጴዛው ላይ የቆዩትን ኅብስቶች አንሥቶ በአዲስ ይተካቸዋል። እነዚህ ኅብስቶች «የመገኛ ኅብስቶች» ሲባሉ፥ ጠረጴዛውም «የመገኛ ጠረጴዛ» ተብሎ ይጠራል። ኅብስቶቹን ሊበሉ የሚችሉት ካህናት ብቻ ሲሆኑ፥ በቤተ መቅደስ ውስጥ የመብላት ግዴታ ነበረባቸው። ይህም ለ12ቱ ነገዶች ያቆማቸው እግዚአብሔር በመካከላቸው እንደሚገኝ ያስገነዝባቸዋል። ለኛም ዛሬ እንደ «የሕይወት እንጀራ» ለዓለም አልፎ ስለተሰጠው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተምሳሌታዊ መልእክት ያስተላልፋል (ዮሐ. 6)።

የወርቅ መሠውያው ሁለቱን የመገናኛ ድንኳን ክፍሎች ከሚለየው መጋረጃ ፊት ይገኛል። በዕብራውያን 9፡4 «ማዕጠንት» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «መሠውያ» ሊባል ይገባል። የወርቅ መሠውያ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ባይቀመጥም፥ አገልግሎቱ ከቅድስተ ቅዱሳን ጋር የተገናኘ ነው። ይህ የሚሆነው በምን መንገድ ነው? በዓመታዊው የስርየት ዕለት ሊቀ ካህናቱ ከመጋረጃው ውስጥ ባለው የምሕረት መከደኛ ፊት ዕጣን ለማጠን የሚጠቀምበትን ከሰል የሚወስደው ከዚህ መሠውያ ነው (ዘሌ. 16፡12-14)። ሙሴ የወርቁን መሠውያ ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር ያዛምደዋል። (ዘጸ. 40፡5)። የመጽሐፈ ነገሥት ጸሐፊም እንደዚሁ ያዛምዳቸዋል (6፡22)። በየጠዋቱና ማታው ካህኑ በዚህ መሠውያ ላይ ዕጣን ያጥናል። ዳዊት ይህ ወደ እግዚአብሔር የሚያርግ ጸሎት ተምሳሌት እንደሆነ ገልጾአል (መዝ. 141፡2)። ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚማልድልን የሚያስገነዝበንም ሊሆን ይችላል

(ሮሜ 8፡33-34)። ስለዚህ የዕጣን መሠውያ ዝርዝር አሳቦችን ከዘጸአት 30፡1-10፤ 37፡25-29 ልታነብ ትችላለህ። ዕጣኑ ራሱ በዘጸአት 30፡34-35 ተገልጾአል።

ቅድስተ ቅዱሳኑ በውስጡ የሚይዘው የቃል ኪዳኑን ታቦት ብቻ ነው። ታቦቱ ከእንጨት የተሠራ ሲሆን፥ ርዝመቱ 3/4ኛ ጫማ፥ ስፋቱ 2 1/4ኛ ጫማ፥ ቁመቱ ደግሞ 2 1/4ኛ ጫማ ነው። ከዚህ ታቦት ላይ ከወርቅ የተሠራ ውብ «የምሕረት መቀመጫ» ሲደረግ፥ ከእያንዳንዱ ጫፍ ላይ አንዳንድ ኪሩቤል ይቀመጣል። ይህ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የእግዚአብሔር ዙፋን ነበር (መዝ. 80፡1፤ ዘጸ. 25፡10-22)። በስርየት ቀን ከታቦቱ ውስጥ ያሉትን የሕግ ጠረጴዛዎች ለመሸፈን ከምሕረት መቀመጫው ላይ ደም ይረጫል። ይህም እግዚአብሔር ሰዎች የተላለፉትን ሕግ ሳይሆን፥ የተረጨውን ደም እንዲመለከት ያደርገዋል። ክርስቶስ የምሕረት መቀመጫችን ነው (ይህም 1ኛ ዮሐንስ 2፡2 እና ሮሜ 3፡25 ውስጥ ተመልክቷል።) ነገር ግን የእርሱ ደም ኃጢአትን መሸፈን ብቻ ሳይሆን፥ የማስወገድም ብቃት አለው።

በእነዚህ የቤተ መቅደስ ዕቃዎች ውስጥ አያሌ መንፈሳዊ እውነቶች የሚገኙ ሲሆኑ፥ ሁሉም ዋጋ ያላቸው ናቸው። ከሁሉም የሚበልጠው እውነት ግን ይህ ነው፤ ሁሉም በተምሳሌት እውነታውን የሚወክሉ እንጂ መንፈሳዊ እውነታ አይደሉም። የብሉይ ኪዳንን ቃል ኪዳን የበታች የሚያደርገውም ይኼ ነው።

ሐ. ሰዎች ሊደርሱበት አይችሉም ነበር (ዕብ. 9፡6-7)። አይሁዶች ለአምልኮ በመገናኛ ድንኳን ውስጥ መሰብሰብ ይችሉ እንደነበር ካሰብን ተሳስተናል። ወደ መገናኛው ድንኳን መግባት የሚችሉት ካህናትና ሌዋውያን ብቻ ነበሩ። በተጨማሪም፥ ምንም እንኳ ካህናት በቅድስት ውስጥ በየዕለቱ ቢያገለግሉም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚገባው ሊቀ ካህናቱ ብቻ ነበር። ይህንንም የሚያደርገው በዓመት አንድ ጊዜ በስርየት ቀን ብቻ ነበር። ሊቀ ካህናቱ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በሚገባበት ጊዜ መጀመሪያ ለራሱ ኃጢአት፥ ከዚያም ለሕዝቡ ኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ ይኖርበታል። ከዚህ በተቃራኒ፥ ሰማያዊቷ የመገናኛ ድንኳን ሁልጊዜም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ክፍት ነች! (10፡19-25)።

መ. ጊዜያዊ ነበር፥ (9፡8)። የውጭው አደባባይ (የመጀመሪያው ድንኳን፥ 9፡6) ቆሞ መገኘቱ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያዘጋጀው የደኅንነት ሥራ አለመፈጸሙን ያመለክታል። የውጭው አደባባይ በሕዝቡና በቅድስተ ቅዱሳን መካከል የሚገኝ ነው! ካህናት በቅድስት ስፍራ በሚያገለግሉበት ጊዜ እግዚአብሔር ወደሚገኝበት ስፍራ

የሚወስደው መንገድ ገና አልተከፈተም ነበር። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ፥ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከታች ለሁለት በመከፈሉ (ማቴ. 27:50-51) ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚወስደው መንገድ ሊከፈት ችሏል። ከዚህ በኋላ በክርስቶስ የሚያምኑ ኃጢአተኞች ወደ እግዚአብሔር ሊቀርቡ ስለሚችሉ፥ ቅድስትም ሆነች ቅድስተ ቅዱሳን አስፈላጊዎች አልሆኑም።

ሠ. አገልግሎቱ ውጫዊ እንጂ ውስጣዊ አልነበረም (ዕብ. 9:9-10)። የሚቀርቡት መሥዋዕቶችም ሆኑ ከምሕረት መቀመጫው ላይ የሚረጨው ደም የአምላኪውን ልብም ሆነ ሕሊና ሊለውጡ አይችሉም ነበር። የመገናኛው ድንኳን ሥርዓቶች ሁሉ ሥርዓታዊ ንጽሕና ጽዳትን እንጂ ግብረገባዊ ንጽሕናን የሚያመለክቱ አልነበሩም። ስለሆነም የሰውን ልብ የሚለውጡ ሳይሆኑ ሜዳዊ የሥጋ ሥርዓቶች ብቻ ነበሩ።

## 2. የሚበልጥ ሰማያዊ ቤተ መቅደስ (9:11-28)

ከላይ የዘረዘርናቸው አምስቱ የብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደስ ድክመቶች፥ የአዲስ ኪዳን ቤተ መቅደስን የበላይ ከሚያደርጉ አምስት ነጥቦች ጋር ይዛመዳሉ። በሁሉም ረገድ፥ የአሁኑ ቤተ መቅደስ የበላይ ነው።

ሀ. ሰማያዊ ነው (9:11)። ጸሐፊው በዚህ ጉዳይ ላይ ቀደም ብሎ አጽንኦት ሰጥቶ ገልጾአል። ይህንንም ያደረገው አንባቢዎቹ ከምድራዊው ይልቅ በሰማያዊ ነገሮች ላይ እንዲያተኩሩ ስለፈለገ ነው። የአይሁድን ውብ ቤተ መቅደስ ጨምሮ ምድራዊ ነገሮች መውደማቸው የማይቀር ነበር፤ ሰማያዊ ነገሮች ግን ለዘላለም ይኖራሉ።

የብሉይ ኪዳን የመገናኛ ድንኳን የተበጀው በሰዎች እጅ ነበር (ዘጸ. 35:30-35)። የአዲስ ኪዳን ቤተ መቅደስ ግን በሰው እጆች የተሠራች አይደለችም። በዕብራውያን 9:11 እንደተገለጸው፥ ይህች ቤተ መቅደስ የዚህ ፍጥረት አይደለችም። የሙሴ የመገናኛ ድንኳን የተሠራችው በዚህ ፍጥረት ቁሳቁሶች ነበር። ሰማያዊቷ ድንኳ እንዲህ ዓይነት ነገሮች አያስፈልጓትም ነበር (ዕብ. 9:24)። ሰማያዊቷ ቤተ መቅደስ ምድራዊ ፍጥረት ስላልሆነች፥ በጊዜ ሂደት ከሚደርስ ውድቀት ነፃ ነች።

«ይመጣ ዘንድ ያለው መልካም ነገር» የተባለለት እነሆ አሁን መጥቷል! በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በምስያ ጥላነት የተገለጸው ሁሉ በክርስቶስ ሰማያዊ የክህነት አገልግሎት እውን ሆኗል። የመገናኛው

ድንኳን የተሠራው በሰማያዊቷ ቤተ መቅደስ ምሳሌ ነበር። አሁን ግን ምሳሌው አያስፈልገንም። ዘላለማዊ እውነት አለን!

ለ. አገልግሎቱ ኃጢአትን ለማስወገድ ብቁ ነው (9፡12-15)። በዚህ ስፍራ የሰማያዊውን አገልግሎት የበላይነት የሚያሳዩ ተከታታይ ንጽጽሮች ቀርበዋል።

የእንስሳት መሥዋዕቶችና የክርስቶስ መሥዋዕት (9፡12)። ጸሐፊው በምዕራፍ 10 የእንስሳት መሥዋዕትን የበታችነት የሚገልጽ ቢሆንም፥ በዚህ ስፍራ ለዚያ አሳብ መሠረት ይጥላል። የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከእንስሳት መሥዋዕት እንደሚበልጥ መረጃ መጠየቅ የሚያስፈልግ አይደለም። የእንስሳት ደም እንዴት የሰውን የኃጢአት ችግር ሊፈታ ይችላል? ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ሥጋ የለበሰው ለኃጢአተኞች ለመሞት እንዲችል ነው። የሞተው በፈቃዱ ነበር። የትኞቹም የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች በገዛ ራሳቸው መቅረባቸው አጠራጣሪ ነው። የእንስሳቱን ደም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይዞ የሚገባው ሊቀ ካህናቱ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እንደ መጨረሻና የተሟላ መሥዋዕት እግዚአብሔር ባለበት ስፍራ ራሱን አቀረበ። የእንስሳት መሥዋዕቶች በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ሲሆኑ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በማያዳግም ሁኔታ ራሱን አንድ ጊዜ ሠውቷል። በመጨረሻም፥ የትኛውም የእንስሳት መሥዋዕት ዘላለማዊ ቤዛነት ሊያስገኝ አይችልም። ደማቸው የክርስቶስ ደም ኃጢአትን የሚያስወግድበት ጊዜ እስኪመጣ ድረስ ለጊዜው ኃጢአትን ከመሸፈን ያለፈ ሚና አልነበረውም (ዮሐ. 1፡29)። እኛ ግን የዘላለም ቤዛነት አለን። ይህ በመልካም ተግባራችን ላይ የሚመሠረት ሳይሆን፥ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በተፈጸመው የኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ በአስተማማኝነት የተከናወነ ተግባር ነው።

ሥርዓታዊ መንጻትና የሕሊና መንጻት (ዕብ. 9፡13-14)። የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶች የሰውን ልብ ሊለውጡ አይችሉም። ይህ ማለት ግን አምላኪው ልቡ በእግዚአብሔር ካመነ መንፈሳዊ ልምምድ አይኖረውም ማለት ሳይሆን፥ ነገር ግን ትኩረት የሚደረገው በውጫዊ የመንጻት ሥርዓቶች ላይ መሆኑን ለማመልከት ነው። አምላኪው የታዘዘውን ደንብ ተግባራዊ ካደረገ፥ «ነፅተሃል!» ይባል ነበር። ይህም ሥጋን የማንጻት እንጂ ሕሊናን የማንጻት ተግባር አልነበረም። (ስለ ጊደር አመድ ዘኍልቁ 19ን አንብብ።)

የአዲስ ኪዳን አገልግሎት ውስጣዊ መሆኑን ከዕብራውያን 8 ላይ ተምረናል። «ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ» (ዕብ. 8፡10)። ይህ የተከናወነው በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው (2ኛ ቆሮ. 3፡1-3)። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ

የኃጢአታችንን ዋጋ ባይከፍል ኖሮ፥ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን አያድርም ነበር። በውጫዊ ሥርዓቶች ሕሊናችን ሊጸዳ አይችልም። ይህ ውስጣዊ ኃይልን የሚጠይቅ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ነቀፋ የሌለበት በመሆኑ ፍጹም መሥዋዕት ሊያቀርብ ችሏል።

ጊዜያዊና ዘላለማዊ በረከቶች (ዕብ. 9፡15)። የብሉይ ኪዳን በረከቶች በእግዚአብሔር ሕዝብ ታዛዥነት ላይ የተመሠረቱ ነበሩ። እግዚአብሔር ከታዘዙት ይባርካቸው ነበር፤ ካልታዘዙት ደግሞ አይባርካቸውም። እነዚህ በረከቶች ጊዜያዊ ብቻ ሳይሆኑ፥ ዘላለማዊ ረብ የማያስገኙም ነበሩ። ዝናብ፥ ጥሩ አዝመራ፥ ከጠላትና ከበሽታ መጠበቅና የመሳሰሉትን የሚያካትቱ ነበሩ። የእስራኤላውያን የከነዓን ርስት ቁሳዊ በረከቶችን የሚያስቀድም ነበር። ዘላለማዊ ርስታችን በባሕርዩ በቀዳሚነት መንፈሳዊ ነው (ኤፌ. 1፡3)። የተተከረባቸው ዘላለማዊ እሴቶች እንደሆኑ ልብ እንበል። - ዘላለማዊ ቤዛነት፥ (ዕብ. 9፡12) እና ዘላለማዊ ርስት፥ (ቁ. 15)። አማኝ በክርስቶስ ያገኘው በረከት ሁሉ ዘላለማዊ እሴት ስላለው ልበሙሉነት ሊሰማው ይችላል።

በብሉይ ኪዳን የተሟላ ደኅንነት እንዳልነበረ ከ9፡15 በግልጽ እንገነዘባለን። በዚያን ጊዜ የተፈጸሙት በደሎች ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እስከተሰዋበት ጊዜ ድረስ ሳይወገዱ ተሸፍነው ቆይተዋል። (ሮሜ 3፡24-26)። ክርስቶስ ዘላለማዊ ደኅንነትን ስለመሠረተ፥ የዘላለማዊ ርስት ተካፋዮች ልንሆን እንችላለን።

እነዚህን ሦስት ንጽጽሮች በምንከልስበት ጊዜ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ኃጢአታችንን የማስወገድ ብቃት እንዳለው ሳንገነዘብ አልቀረንም። በምድር ላይ የተፈጸመውና በሰማይ ላይ በመካሄድ ላይ ያለው የምልጃ አገልግሎቱ ብቁ ና ውጤታማ ናቸው።

ሐ. አገልግሎቱ የተመሠረተው ክቡር በሆነ መሥዋዕት ላይ ነው (ዕብ. 9፡16-23)። «ቃል ኪዳን» የሚለው ቃል «ስምምነት» ብቻ ሳይሆን፥ «የመጨረሻ ኑዛዜና ኪዳን» የሚል ፍችም አለው። አንድ ሰው ኑዛዜ ከሰጠ፥ ኑዛዜው ተግባራዊ የሚሆነው ከሞተ በኋላ ብቻ ነው። ስለሆነም፥ አዲስ ኪዳን ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ መሞት ነበረበት። «ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈስሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው» አለ (ሉቃስ 22፡20)።

ቃል ኪዳን በብሉዩም ሳይቀር የተመሠረተው በደም ላይ ነበር። ዕብራውያን 9፡19-21 የተወሰደው ሙሴና እስራኤላውያን ብሉይ ኪዳንን ስላጸኑበት ሁኔታ ከሚተርከው ከዘጸአት 24፡3-8 ነው። የሕጉ መጽሐፍ፥ ሕዝቡ፥ የመገናኛው ድንኳንና በውስጡ የሚገኙ የአምልኮ

ዕቃዎች ሁሉ በደም ተረጭተዋል። ይህ የእግዚአብሔር ፍርሃት በተለየ ሁኔታ በእነርሱ ላይ የወደቀበት ጊዜ መሆኑን መገመት እንችላለን።

ብሉይ ኪዳን በተጀመረበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን የመገናኛ ድንኳን አገልግሎት በሚካሄድባቸው ጊዜያት ሁሉ ደም ይረጭ ነበር። በብሉይ ኪዳን ሰዎችና ዕቃዎች የሚነጹት በደም፥ በውኃ ወይም በእሳት ነበር (ዘኁል. 31፡21–24)። ይህም ሥርዓታዊ መንጻት እነዚህ ዕቃዎችና ሰዎች አሁን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳገኙ የሚያሳይ ነበር። መንጻቱ የዕቃውን ወይም የሰውዬውን ባሕርይ አይለውጥም። የእግዚአብሔር መርህ ደም ሳይፈስ ኃጢአት አይሰረይም የሚል ነው (ዘሌዋ. 17፡11)።

እግዚአብሔር ኃጢአት በደም እንደሚሰረይ ስለደነገገና ከኃጢአት መንጻት የሚቻለው በደም መርጨት ስለሆነ፥ አዲስ ኪዳንም ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ደም መፍሰሱ ወሳኝ ነበር። «ምሳሌዎቹ» (ማለትም የብሉይ ኪዳን የመገናኛ ድንኳን) በደም መርጨት ይነጹ ነበር። እነርሱ ብቻ ሳይሆን «ኦሪጂናሎቹም» እንዲሁ በደም ሊነጹ ግድ ነበር! ብቻ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም የአማኙን ሕሊና ብቻ ሳይሆን (ዕብ. 9፡14)፥ ሰማያዊ ነገሮችንም ሳይቀር ያነጻል (9፡23)።

ቀድሞ ነገር፥ ሰማያውው ቤተ መቅደስ እንዴት ሊረክስ ይችላል? ምድራዊ ቤተ መቅደስ ኃጢአተኛ ሰዎች የሚገለገሉበት በመሆኑ ሊረክስ እንደሚችል ማሰብ እንችላለን። በመሆኑም በታላቁ የስርየት ቀን የመገናኛው ድንኳን በደም መርጨት ይነጻ ነበር። (ዘሌዋ. 16፡12–19)። ነገር ግን ሰማያዊው ቤተ መቅደስ እንዴት ርኩሰት ሊገኝበት ይችላል? ምክንያቱም ኃጢአት ሰማያዊትዋን ቤተ መቅደስ ሊያረክሳት አይችልም። ለነገሩማ ምድራዊቱም ቤተ መቅደስ በዚሁ ሁኔታ በኃጢአት ባልረከሰች ነበር። ይህ ሰዎች ከእግዚአበሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚመለከት ነው። በአምልኮ ዕቃ ላይ የተረጨው ደም የሚለውጠው የዕቃውን ባሕርይ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ከዚያ ነገር ጋር ያለውን ግንኙነት ነው ለውጠዋል። ከተረጨው ደም የተነሣ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ኅብረት ማድረግ ይችላል።

በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ኃጢአተኞች የሆንን እኛ ወደ ሰማያዊቷ ቅድስተ ቅዱሳን ልንገባ እንችላለን (ዕብ. 10፡19–22)። በአካላዊ ይዞታችን በምድር ላይ ብንገኝም፥ በመንፈሳዊ ሁኔታ በሰማያዊቷ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እናደርጋለን። እግዚአብሔር ወደ ሰማያዊ ኅብረቱ ይቀበለን ዘንድ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም መረጨት አለበት። ስለዚህ እግዚአብሔር ወደሚገኝበት ስፍራ የምንገባው በኢየሱስ ደም ነው (10፡19)።

አሁን የጸሐፊውን አሳብ ጠቅለል አድርገን ልንመለከት እንችላለን። ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን የተመሠረተው በደም ላይ ነው። ነገር ግን አዲስ ኪዳን የተመሠረተው በከፍተኛ ስፍራ በሚያገለግል ከፍተኛ መሥዋዕት ላይ ነው! ምሳሌዎቹ በእንስሳት ደም ሲነጹ፥ የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ደም ይነጻል። ይህም እጅግ ታላቅ ዋጋ የተከፈለበት ሁኔታ ነው።

መ. አገልግሎቱ ሲጠበቅ የነበረው ተስፋ መከናወኑን ያሳያል (9፡24)። የአዲስ ኪዳን ክርስቲያን ጥላ የሆነውን ሳይሆን እውነተኛውን ነገር ይዟል! የምንደገፈው በጊዜያዊ ቤተ መቅደስ ውስጥ በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ በሚገባ ሊቀ ካህናት ላይ ሳይሆን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ዘላለማዊት ቤተ መቅደስ በገባው ሊቃ ካህናት ላይ ነው። በዚያም በእግዚአብሔር ፊት እኛን ይወክለናል። ዘወትር ይህንኑ ያደርጋል።

ለመንፈሳዊ ሕይወትህ በእጆች በተሠራ ነገር ላይ እንዳትተማመን ተጠንቀቅ (9፡24)። እንዲህ ዓይነቱ መታመኛ ዘለቄታዊነት የለውም። የመገናኛው ድንኳን በሰሎሞን ቤተ መቅደስ የተተካ ሲሆን፥ እሱም ቢሆን በባቢሎናውያን ተደምስሷል። አይሁዶች ከምርኮ በኋላ ወደ አገራቸው ሲመለሱ ቤተ መቅደሳቸውን እንደገና ሠርተውታል። በኋላም ንጉሥ ሄሮድስ ይህንኑ ቤተ መቅደስ አስፋፍቶ አስውቦታል። ይኸው ቤተ መቅደስ በሮማውያን ከፈራረሰ በኋላ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ–አልባ ለመሆን ተገደደች። በተጨማሪም፥ የዘር ሐረግ ዘገባዎች ስለጠፉ፥ አይሁዶች ማን በክህነት ሊያገለግል እንደሚችል እርግጠኞች አይደሉም። ይህም በሰው እጆች የተሠሩት ነገሮች ጊዜያዊ ሲሆኑ፥ በሰው እጆች ያልተሠሩት ነገሮች ዘላለማዊ መሆናቸውን ያመለክታል።

ሠ. <u>አገልግሎቱ የተሟላና ፍጻሜው ለዘላለም የተቋጨ ነው</u> (9፡25–28)። ጌታችን በሰማይ ከሚያካሂደው አገልግሎት ውስጥ ያልተሟላ ወይም ጊዜያዊ የሆነ ምንም ነገር የለም። ጸሐፊው አሁንም በብሉይ ኪዳን አገልግሎትና በአዲስ ኪዳን አገልግሎት መካከል ያለውን ግልጽ ንጽጽር እንደሚከተለው አመልክቷል።

| <u>ብሉይ ኪዳን</u> | <u>አዲስ ኪዳን</u> |
|---|---|
| ተደጋጋሚ መሥዋዕቶች | የማያዳግም መሥዋዕት |
| የሌሎች ደም | የራሱ ደም |
| ኃጢአትን መሸፈን | ኃጢአትን ማስወገድ |
| ለእስራኤላውያን ብቻ | ለኃጢአተኞች ሁሉ |
| ከቅድስተ ቅዱሳኑ ተለይቷል | ወደ መንግሥተ ሰማይ ገብቶ እዚያው ይኖራል |

| | |
|---|---|
| ሕዝቡን ለመባረክ ይመጣል | ሕዝቡን ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመውሰድ ይመጣል |

በአጭሩ የክርስቶስ *ሥራ* የተፈጸመ፥ የመጨረሻና ዘላለማዊ ነው። በዚህ የተሟላ *ሥራ* ላይ ተመሥርቶ አሁን በሰማይ ስለ እኛ ሆኖ እያገለገለ ነው።

በዕብራውያን 9፡24-28 «ይታያል» የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ እንደተጠቀሰ አስተውለሃል? (በቁጥር 26 «ተገልጦአልና» የሚለውም «ታይቷልና» የሚል ፍች አለው።) እነዚህ ሦስቱ የጌታችንን ሥራ ጠቅለል ባለ መልኩ ያቀርቡልናል። በመስቀል ላይ በመሞት ኃጢአትን ሲያስወግድ ታይቷል (ቁ. 26)። አሁን በሰማይ ስለ እኛ በእግዚአብሔር ፊት ይታያል (ቁ.24)። አንድ ቀን ክርስቲያኖችን ወደ ሰማያዊው ቤት ለመውሰድ ይገለጣል (ቁ.28)። እነዚህ ሦስቱም የደኅንነት የጊዜ ገጽታዎች በአገልግሎቱ ተዳስሰዋል።

የዕብራውያን ክርስቲያኖች ይህንን መልእክት ካነበቡ በኋላ መሀል ቤት የሚባል ነገር እንደሌለ እንደሚገነዘቡ ይጠበቅባቸው ነበር። ምድራዊውን ወይም ሰማያዊውን፥ ጊዜያዊውን ወይም ዘላለማዊውን፥ ያልተሟላውን ወይም የተሟላውን የመምረጥ ግዴታ ተጥሎባቸዋል። *ግን ከዚህ ሁሉ ወደ ቤተ መቅደስ ተመልሰው ከክርስትና እምነታቸው ጋር አስማምተው ለምን አይቀጥሉም?* ከሁለቱም ኪዳኖች ለምን ምርጥ ምርጡን አይወስዱም? ይህ ነቀፌታውን ይዞ ከከተማ ውጭ ላለመውጣት ማምለጫ ጥረት እንደሚሆን ግልጽ ነው (13፡13)። ስለሆነም፥ መሀል ቤት የሚባል ነገር የለም።

የአማኙ ቤተ መቅደስ በሰማይ ነው። አባቱና አዳኙ ያሉት በሰማይ ነው። ዜግነቱም (ፊልጵ. 3፡20)፥ እንዲሁም መዛግብቱም በሰማይ ሊሆኑ ይገባል። (ማቴ. 6 ከቁጥር 19 ጀምሮ)። ተስፋውም በሰማይ ስለሆነ እውነተኛ አማኝ የሚመላለሰው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም። በምድር ላይ ምንም ነገር ቢከሰት፥ ሁሉም ነገር በሰማይ አስተማማኝ ስለሆነ፥ አማኝ በእምነት ሊመላለስ ይገባል።

9

# የሚበልጥ መሥዋዕት

ዕብራውያን 10

አንድ ታዳጊ ወጣት እናቱ ለጉብኝት ወደ አንድ ስፍራ በሄደችበት ወቅት፥ በቤት ውስጥ ካሉት መጻሕፍት አንድ መንፈሳዊ መጽሐፍ ወስዶ ለማንበብ ወሰነ። እናቱ የተሰጠች ክርስቲያን ስለነበረች ወጣቱ በመጽሐፉ መጀመሪያ ስብከት፥ በመጽሐፉ መጨረሻ ደግሞ ከሕይወት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ተግባራዊ ምክሮች እንዳሉት ያውቅ ነበር። በእነዚህ መካከል ደግሞ ምክሮች ሊኖሩ ይችላሉ።

መጽሐፉን በሚያነብበት ወቅት «የተፈጸመው የክርስቶስ ሥራ» የሚል ሐረግ አጋጠመው። ይህ ሐረግ የወጣቱን ትኩረት ጠፍንጎ ያዘው።

«ደራሲው ለምን በዚህ አገላለጽ ተጠቀመ?» ሲል ራሱን ጠየቀ። «ለምን የክርስቶስ የማስተሰረይ ሥራ አላለም?» (ወጣቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላትን በትክክል ያውቅ ነበር። አዳኙን ብቻ ነበር ያላወቀው!) ከዚያም «ተፈጸመ» የሚባል ቃል በአእምሮው ውስጥ በድንገት ቦግ አለ። በዚህም ጊዜ የደኅንነት ሥራ ሙሉ በሙሉ የተከናወነ መሆኑን ለመገንዘብ ቻለ።

«ሥራው በሙላት ካለቀና ጠቅላላው ዋጋ ከተከፈለ፥ እኔ ላደርገው የሚገባኝ ቀሪ ተግባር ምንድነው?» ሲል ራሱን ጠየቀ። ለጥያቄው መልሱን ያውቅ ነበርና አዳኙንና የኃጢአቱን ሙሉ ይቅርታ ይቀበል ዘንድ በጉልበቱ ተንበረከከ። የቻይና ኢንላንድ ሚሽን መሥራች የነበሩት ጄ. ሃድሰን ቴይለር ደኅንነትን ያገኙት ይህን በመሰለ ሁኔታ ነበር።

ዕብራውያን ምዕራፍ 10 ፍጹም ካልሆኑት የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች በተለየ ሁኔታ የበለጠ ክብደት ፍጹም ለሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕት ይሰጣል። የጌታችን ከሁሉ በላይ የሆነ የክህነት ሥልጣን፥ እንደ አሮን ሳይሆን እንደመልከ ጸዴቅ ዓይነት ክህነት ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ የክህነት አገልግሎት በበለጠው የአዲስ ኪዳን ሥርዓት ላይ የተመሠረተና ብልጫ ባለው ሰማያዊ ቤት መቅደስ ውስጥ የሚከናወን ነው። ይህ ሁሉ ከፍ ባለው የመሥዋዕት መሠረት ላይ የተደገፈ ነው። የዕብራውያን ምዕራፍ 10 ጭብጥም ይኸው ነው።

ጸሐፊው የኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕቶች ለምን ከብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች የበለጡ እንደሆኑ የሚያብራሩ ሦስት ፍሬ ነገሮችን እንደሚከተለው ዘርዝሮአል።

## 1. የክርስቶስ መሥዋዕት መሆን ኃጢአትን ያስወግዳል (10፥1–10)

ኃጢአት ትልቁ የሰው ልጅ ችግር እንደሆነ ግልጽ ነው። ሰው የትኛውንም ሃይማኖት ይከተል፥ ሃይማኖቱ ለኃጢአት ችግር የማያነሳ ከሆነ ፋይዳ ቢስ ነው። ሰው በባሕርዩ ኃጢአተኛ ሲሆን፥ በተግባርም ደግሞ የባሕርዩን ኃጢአተኝነት ያረጋግጣል። «ኃጢአተኞች የሆንነው ኃጢአትን ስለምንሠራ አይደለም፤ ኃጢአተኞች ስለሆንን ኃጢአትን እናደርጋለን» የሚለው አባባል ትክክለኛ ነው።

ሀ. የሚሻል መሥዋዕት አስፈላጊነት (10፥1–4)። የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች ዝቅተኞች የሆኑት ለምንድን ነው? በጌታ ትእዛዝ ሥራ ላይ ውለው ለብዙ መቶ ዓመታት ሲያገለግሉ አልነበረምን? አንዳንድ ጊዜ አይሁዶች እነዚህን ትእዛዛት ተግባር አልባ ቢያደርጉዋቸውም (ኢሳ. 1፥11–15)፥ በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ ሰዎች መሥዋዕቶቻቸውን በእግዚአብሔር ፊት ከልባቸው በማቅረብ በረከትን እንዳገኙ ይታወቃል።

የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች ሁነኛ ባሕርያቸው በራሳቸው ኪዳኑን ዝቅተኛ (የበታች) የሚያደርጉ ናቸው። ሕጉ የሚመጡ መልካም ነገሮች «ጥላ» እንጂ በራሱ እውነተኛ ነገር አልነበረም። የመሥዋዕት ሥርዓት ጌታችን በመስቀል ላይ የሚፈጽመው ሥራ ምስያ ወይም መግለጫ ነበር። ይህም ሥርዓቱ ጊዜያዊና ዘለቄታዊ ተግባር ሊያከናውን የማይችል እንደነበር ያስገነዝበናል። የመሥዋዕቶቹ በየቀኑ መደጋገምና የስርየት ዕለቱ በየዓመቱ መካሄድ ራሱ የሥርዓቱን ደካማነት ያመለክታል።

የእንስሳት መሥዋዕቶች ከቶውንም የሰውን የበደለኝነት ስሜት ሊያስወግዱ አይችሉም። እግዚአብሔር በእምነት የሚያመልኩትን ሰዎች ኃጢአት ይቅር እንደሚል ቢናገርም (ዘሌ. 4፥20፥ 26፥ 31፥ 35)፥ ይህ ሕጋዊ ይቅርታ እንጂ ከሰዎች ልብ ውስጥ የበደለኝነትን ስሜት የሚያስወግድ አልነበረም። ሰዎች የተሟላ ይቅርታ እንዳገኙ ለልባቸው የሚመሰክር ዋስትና የሚሰጣቸው አልነበረም። «አሁን የኃጢአት ክስ ሕሊናዬን አያስጨንቀኝም» ለማለት አይችሉም ነበር። የአምላኪዎቹ ሕሊና በሚያቀርቡት መሥዋዕት አማካኝነት ከኃጢአት ነጻ ወጥቶ ቢሆን ኖሮ ሌላ መሥዋዕት ማቅረብ ባላስፈለጋቸው ነበር።

ስለሆነም፥ ዓመታዊው የስርየት ቀን ኃጢአትን የሚያስወግድ ሳይሆን፥ ኃጢአትን የሚያስገነዝብ ነበር። መሥዋዕቶች በየዓመቱ መደጋገማቸው ያለፈው ዓመት መሥዋዕቶች ተግባራቸውን እንዳላከናወኑ የሚያመለክት ማስረጃ ነበር። የሕዝቡ ኃጢአቶች መሸፈናቸው እውነት ቢሆንም፥ ሰዎቹ ከኃጢአታቸው አልነጹም ነበር። በልባቸው ውስጥ እርሱ ይቅር እንዳላቸውና እንደተቀበላቸው የሚያረጋግጥ የእግዚአብሔር ውስጣዊ ምስክርነት አልነበራቸውም።

የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን ሊያስወግድ ባለመቻሉ ምክንያት የተሻለ መሥዋዕት እጅግ ያስፈልጋቸው እንደነበር ግልጽ ነው። የእንስሳት ደም ኃጢአትን በመሸፈን ፍርድን ለጊዜው ቢያስተላልፍም፥ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ደኅንነትን አያጎናጽፋቸውም ነበር። ይህንን ሊያደርግ የሚችለው ከሁሉ በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ መሥዋዕት ብቻ ነበር።

ለ. <u>የተሻለ መሥዋዕት የሚያጎናጽፋቸው በረከቶች</u> (ዕብ. 10፡5-9)። መሥዋዕቱን ያቀረበው ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ነው። በዚህ ስፍራ የቀረበው ጥቅስ የተገኘው ከመዝሙር 40፡6-8 ሲሆን፥ ከኢየሱስ ክርስቶስ ትስእብት (ተሰግዎ) ጋር የሚዛመድ ነው። («ወደ ዓለም ሲገባ. . .»)። ይህ ጥቅስ ኢየሱስ ክርስቶስ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች ፍጻሜ መሆኑን ያስረዳል።

*መሥዋዕት* የሚለው ቃል የማንኛዎቹን የእንስሳት መሥዋዕት ያመለክታል። *መባ* የምግብና የመጠጥ መሥዋዕቶችን ያመለክታል። የሚቃጠል መሥዋዕትና የኃጢአት መሥዋዕትም በዚህ ክፍል ውስጥ ተጠቅሰዋል (ቁ. 5፥ 8)። የበደል መሥዋዕት፥ መስዋዕት በሚለው ቃል ውስጥ ተካቷል (ቁ. 5)። እነዚህ መሥዋዕቶች እያንዳንዳቸው የኢየሱስ ክርስቶስን መሥዋዕት በምስያነት የሚያመለክቱ ሲሆኑ፥ የመስቀል ላይ *ሥራውን* የተወሰኑ ገጽታዎች ያሳያሉ። (ዘሌ. 1-7 አንብብ)።

«ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ» (ዕብ. 10፡5) የሚለው ዐረፍተ ነገር በዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ምንባብ ውስጥ አልተጠቀሰም። መዝሙር 40፡6፥ «ጆሮቼን ግን ከፈትህ» ይላል (አ.መ.ት.)። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ የብሉይ ኪዳን የዕርዕ ትርጉም ከሆነው ከሴፕቱዋጂንት ነበር ጥቅሱን የወሰደው። እንግዲህ፥ ይህንን ልዩነት እንዴት እናስታርቃለን? አንዳንድ ሰዎች «ጆሮቼን ግን ከፈትህ» የሚለውን ዐረፍተ ነገር ከዘጸአት 21፡1-6 ጋር ያዛምዱታል። ይህም ባሮቹ ነፃ ለመውጣት ባይፈልጉ የባሮቹ ጌታ ምን ማድረግ እንዳለበት የሚናገር ምንባብ ነው። ባሪያው ነፃነቱን ካልፈለገ ጌታው ጆሮውን ይበሳል። ይህም ባሪያው ከጌታው ጋር ለመኖር እንደፈቀደ የሚያሳይ

ምልክት ነበር። የመልእክቱ ፍሬ ነገር ጌታችን ጆሮውን እንደተበሳ ፈቃደኛ ባሪያ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

ይህ ማብራሪያ አስቸጋሪ የሚሆነው ነፃ ለመውጣት የፈለገ ባሪያ አንድ ጆሮውን ብቻ የሚበሳ ሲሆን፥ በመዝሙር 40:6 ውስጥ የሚናገረው ግን ስለ ሁለት ጆሮዎች መሆኑ ነው። በተጨማሪም፥ የመዝሙር 40:6 ግስ «መውጋት» የሚል ፍች ሲኖረው፥ የዘጸአት ግስ ግን «መብሳት» የሚል ነው። ጌታችን እንደ ባሪያ ያገለገለ መሆኑ ቢታወቅም፥ የዕብራውያን ጸሐፊ ይህን አሳብ ይዞ የሚናገር አይመስልም። ምናልባትም የጆሮዎቹ መከፈት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመስማትና ለመታዘዝ መፍቀዱን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። (ኢሳ. 50:4-6 አንብብ።) እግዚአብሔር እሱንና ፈቃዱን በምድር ላይ ያገለግል ዘንድ ለልጁ የተዘጋጀ ሥልጣን ሰጥቶታል። ጌታችን ብዙውን ጊዜ ስለዚህ ነገር ተናግሯል (ዮሐ. 4:34፤ 5:30፤ 6:38፤ 17:4)።

በእርግጥ በዕብራውያን 10 ውስጥ የሚገኘውን ቃል የመተርጎም መብት ያለው መዝሙር 40 እንዲጻፍ በእስትንፋሱ የመራው መንፈስ ቅዱስ ነው። «የተከፈቱ ጆሮች» ለአገልግሎት የተዘጋጀ ሰውነትን የሚያመለክቱ ናቸው።

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች ደስ አለመሰኘቱን ጸሐፊው ሁለት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ውስጥ ገልጾአል። (10:6፥ 8 አንብብ።) ይህ ግን የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች ትክክል አለመሆናቸውን ወይም እውነተኛ አምላኪዎች የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቃቸው እንዳልተጠቀሙ አያመለክትም። ይልቁንም እግዚአብሔር የአማኙ የልብ ታዛዥነት ባልታከለባቸው መሥዋዕቶች ደስ አለመሰኘቱን የሚያሳይ ነው። የትኛውም ያህል መሥዋዕት ታዛዥነትን ሊተካ አይችልም። (1ኛ ሳሙ. 15:22፤ መዝ. 51:16-17፤ ኢሳ. 1:11፥ 19፤ ኤር. 6:19-20፤ ሆሴዕ 6:6፤ አሞፅ 5:20-21)።

ኢየሱስ የመጣው የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም ነው። ይህም ብሉይ ኪዳንን በአዲስ ኪዳን መተካቱ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው አማካኝነት የመጀመሪያውን ኪዳን አስወግዶ፥ ሁለተኛውን መሥርቷል። የዚህ መልእክት አንባቢያን የነበሩት ዕብራውያን ምን ለማለት እንደተፈለገ ከእነዚህ ጥያቄዎች መልሱን ሳያገኙ አልቀሩም። ወደተሻረው ኪዳን ለምን ትመለሳላችሁ? ፋይዳ ቢስ ወደሆኑት መሥዋዕቶች ለምን ትሄዳላችሁ?

ሐ. <u>የተሻለው መሥዋዕት ውጤታማነት</u> (ዕብ. 10:10)። አንድ ጊዜ ለዘላለም በቀረበው የክርስቶስ ሰውነት አማኞች ተለይተዋል («ተቀድሰዋል»)። የብሉይ ኪዳን መሥዋዕት ያንን ሊያደርግ

አይችልም። የብሉይ ኪዳን አምላኪ በተደጋጋሚ ከሥርዓታዊ እርኩሰቶች መንጻት አለበት። የአዲስ ኪዳን ቅዱስ ግን ሙሉ ለሙሉ ተለይቷል።

## 2. የክርስቶስ መሥዋት መደገም አያስፈልገውም (10፡11–18)

አሁንም ጸሐፊው የብሉይ ኪዳንን ሊቀ ካህናት ታላቁ ሊቀ ካህናችን ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያነጻጽራል። ክርስቶስ ሥራውን ከጨረሰ በኋላ ወደ ሰማይ ዐርጎ ከአብ ቀኝ መቀመጡ የሥራውን ፍጻሜ የሚያመለክት ነው (1፡3፥ 13፤ 8፡1)። ካህናት በመገናኛው ድንኳንና በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያካሂዱት አገልግሎት ግን በአንዴ ተከናውኖ የሚያልቅ ስላይደለ ሠርክ ለውጥ ሳይኖረው የሚደጋገም ነበር። ዕለት በዕለት ያንኑ መሥዋዕት ነበር የሚያቀርቡት። ይህም ድግግሞሽ መሥዋዕቶቻቸው ኃጢአትን እንደማያስተሰርዩ የሚያረጋግጥ ነበር። በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ መሥዋዕቶች ያልቻሉትን፥ ክርስቶስ በአንድ መሥዋዕት ተግባራዊ ሊያደርግ ችሏል!

«ተቀመጠ» የሚለው አሁንም ወደ መዝሙር (110)፡1 ይወስደናል። «እግዚአብሔር ጌታዬን፦ ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው።» ክርስቶስ አሁን የሚገኘው በክብርና በድል ስፍራ ነው። ዳግም በሚመለስበት ጊዜ ጠላቶቹን ሁሉ በማጥፋት የጽድቅ መንግሥቱን ይመሠርታል። እርሱን ያመኑት ሰዎች ለዘላለም ፍጹማን ስለተደረጉ (ዕብ. 10፡14) የሚያስፈራቸው ነገር አይኖርም። አማኞች በእርሱ ምሉዓን ናቸው (ቆላስይስ 2፡10)። ከኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመ ሥራ የተነሣ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹማን ሆነናል።

በእግዚአብሔር ፊት ፍጹማን መሆናችን በግላችን እንዴት እናውቃለን? መንፈስ ቅዱስ ይህንን በቃሉ አማካኝነት ይመሰክርልናል (ዕብ. 10፡15–18)። የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት በወልድ ሥራ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፥ የምንቀበለውም በመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት አማካኝነት ነው። ጸሐፊው ኤርምያስ 31፡33–34ን ጠቅሷል (ዕብ. 10፡16–17)። ይህም በዕብራውያን 8፡7–12 በከፊል የጠቀሰው ምንባብ ነው። የብሉይ ኪዳን አምላኪ «ሕሊናዬ ከኃጢአት ወቀሳ ነጻ ነው» ሊል አይችልም ነበር (10፡2)። የአዲስ ኪዳን አምላኪ ግን ኃጢአቶቹና በደሎቹ ከእንግዲህ እንደማይታሰቡ ያውቃል። ከእንግዲህ ለኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብም ሆነ (10፡18) ኃጢአትን ማስታወስ አይኖርም!

አንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር ቃል እውነት ጋር የሚስናኝ ትምህርት ካቀረበ አንድ ግሩም ክርስቲያን ሳይኪያትሪስት (የሥነ አእምሮ ምሑር) ጋር ኮንፍረንስ ተካፍዬ ነበር። ይህ ወንድም፥ «የሳይኪያትሪ ዋናው ችግር ከአእምሮ የጤና መታወክ ጋር ብቻ የተቆራኘ ነው። አንድ ሳይኪያትሪስት የበሽተኛውን የበደለኛነት ስሜቶች ሊያስወግድ ቢችልም፥ በደለኛነቱን ሊያስወግድለት አይችልም። ይህ ልክ የሞተሩን ጓጓታ ላለመስማት መኪናውን ከጭቃና ከተለያዩ አላስፈላጊ ነገሮች የሚጋርድብን መከላከያ እንደ ማላላት ነው። በሽተኛው ከበፊቱ የተሻለ ስሜት ሊሰማው ቢችልም፥ በቀድሞው ችግሩ ላይ ሌላ አንድ ችግር ደርቦ ይመለሳል! አንድ የነበረው ችግሩ ሁለት ይሆናል ብሎኛል።

አንድ ኃጢአተኛ በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ ኃጢአቶቹ ሁሉ ይቅር ይባሉለታል። የበደለኛነት ስሜቱ ይወገድና ጉዳዩ ለዘላለም እልባት ያገኛል።

## 3. የክርስቶስ መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰውን መንገድ ይከፍታል (10፡19–39)

በብሉይ ኪዳን ዘመን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት የሚደፍር አምላኪ አልነበረም። ሊቀ ካህናቱ እንኳ ወደዚህ ስፍራ የሚገባው በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር። ከቅድስተ ቅዱሳን የሚለየው ወፍራም መጋረጃ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል የቆመ መጋረጃ ነበር። ያንን መጋረጃ ቀዶ (ማር. 15፡38) እግዚአብሔር ወደሚገኝበት ወደ ሰማያዊ ቤተ መቅደስ መንገዱን ሊከፍት የሚችለው የክርስቶስ ሞት ብቻ ነበር።

*ሀ.* <u>የጸጋ ግብዣ</u> (ዕብ. 10፡19–25)። «እንቅረብ. . .እንጠብቅ. . .እርስ በርሳችን እንተያይ።» ይህ ሦስት ገጽታዎች ያሉት ግብዣ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት ባለን ድፍረት ላይ የተመሠረተ ነው። ይህም ድፍረት በአዳኙ የተፈጸመ ሥራ ላይ ያረፈ ነው። በስርየት ቀን ሊቀ ካህናቱ ደም ካልያዘ በስተቀር ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ መግባት አይችልም ነበር። (9፡7)። እኛ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ የምንገባው ግን ክርስቶስ ካፈሰሰልን ደም የተነሣ እንጂ በእንስሳት ደም አይደለም።

ይህ እግዚአብሔር ወደሚገኝበት ስፍራ የሚወስደን የተከፈተ መንገድ አዲስ ሲሆን፥ ካረጀውና ሊጠፋ ከተቃረበው አሮጌ ኪዳን የተለየ ነው (8፡13)። ክርስቶስ ለእኛ ለማማለድ ለዘላለም ስለሚኖር፥ ይህም መንገድ «ሕያው» ነው (7፡25)። ክርስቶስ አዲስና ሕያው መንገድ ነው! እኛም በእግዚአብሔር ቤት ሊቀ ካህናችን በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር እንቀርባለን (3፡6ን አንብብ።) ሥጋው በመስቀል ላይ ሲከፈልና ሕይወቱ መሥዋዕት

ሲደረግ እግዚአብሔር የቤተ መቅደሱን መጋረጃ ቀደደው። ይህም ለሚያምኑት ሁሉ አዲስና ሕያው መንገድ እንደተከፈተላቸው ያመለክታል።

በእነዚህ ማረጋገጫዎች ቤዛነት (ሕያው ሊቀ ካህናት ስላለንና በዚሁም ምክንያት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የመግባት ድፍረት ስላለን)፥ እግዚአብሔር ወደሚገኝበት ለመግባት ግብዣ ቀርቦልናል። የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚገባው በዓመት አንድ ጊዜ ሲሆን፥ እኛ ግን ሁልጊዜም እግዚአብሔር ባለበት የመኖር ግብዣ ቀርቦልናል! በዚህ ባለ ሦስት ደርብ ግብዣ ውስጥ የሚካተቱትን ነገሮች አስተውሉ።

እንቅረብ (10፡22)። በእርግጥም ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ በመንፈሳዊ ሁኔታ ራሳችንን ማዘጋጀት አለብን። የብሉይ ኪዳን ካህን በስርየት ቀን የተለያዩ የመታጠብ ሥርዓቶችንና ደም መርጨትን ማከናወን ነበረበት (ዘሌ. 16)። እንዲሁም፥ በመደበኛ ዕለታዊ አገልግሎታቸው ካህናት ወደ ቅድስት ከመግባታቸው በፊት በመታጠቢያ ሳህን ላይ የመንጻት ተግባር መፈጸም ነበረባቸው (ዘጸ. 30፡18-21)። የአዲስ ኪዳን ክርስቲያን በንጹሕ ልብና ሕሊና ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይኖርበታል። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ ንጽሕና አስፈላጊ ነው (1ኛ ዮሐ. 1፡5-2፡2)።

እንጠብቅ (ዕብ. 10፡23)። የዚህ መልእክት አንባቢያን ወደ ብሉይ ኪዳን ለመመለስ እና በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የነበራቸውን እምነት ለመተው ብርቱ ፈተና ገጥሞአቸው ነበር። የደኅንነት ዋስትናቸው በራሳቸው ሳይሆን በክርስቶስ የሚወሰን በመሆኑ፥ ጸሐፊው ደኅንነታቸውን እንዲጠብቁ አልመከራቸውም (7፡25)። ይልቁንም፥ የተስፋቸውን ምስክርነት እንዲጠብቁ መከራቸው። (በዚህ ስፍራ «እምነት» የሚል ቃል መኖሩን የሚያመለክት የግሪክ አዲስ ኪዳን ሰነድ የለም። የግሪኩ ቃል «ተስፋ» ነው።)

ቀደም ባለው ጥናታችን ላይ በዕብራውያን መጽሐፍ በአማኙ የከበረ ተስፋ ላይ ትኩረት እንደተሰጠ ገልጸናል። እንደዚሁም እግዚአብሔር ብዙ ልጆችን ወደ ክብር እንደሚያመጣቸውም ተመልክተናል (2፡10)። አማኞች የሰማያዊ ጥሪ ተካፋዮች በመሆናቸው (3፡1)፥ በተስፋ ደስ ሊሰኙ ይችላሉ (3፡6)። ተስፋ ከዕብራውያን 6 ዐበይት ጭብጦች አንዱ ነው (ቁ. 11-12፥ 18-20)። የክርስቶስን መመለስ እየተጣበበቅን ስንሆን (9፡28)፥ ከሰማይ የምትመጣውን ከተማ እንሻለን (13፡14)።

የአንድ አማኝ ተስፋ፥ በክርስቶስ ላይ ሲያርፍና በእግዚአብሔር ታማኝነት ላይ ሲደገፍ፥ ወላዋይነት ሊያውከው አይችልም። አይሁዶች

ብዙ ጊዜ እንዳደረጉት ወደኋላ ሳናይ፥ የጌታን ምጽአት ወደፊት አሻግረን ልንመለከት ይገባል።

እርስ በርሳችን እንተያይ (10:24–25)። ከእግዚአብሔር ጋር የምናደርገው ኅብረት በራስወዳድነት ላይ የተመሠረተ መሆን የለበትም። በአጥቢያ ቤተክርስቲያናችን ከሌሎች አማኞችም ጋር ኅብረት ማድረግ አለብን። እዚህ ላይ ትኩረት የተሰጠው አማኙ ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት ከሚያገኘው ጥቅም ይልቅ እርሱ ሊያበረክት በሚችለው ነገር ላይ ነው። ከቤተ ክርስቲያን አለመቅረት ሌሎችንም የሚያበረታታ ከመሆኑም በላይ ለፍቅርና ለመልካም ሥራ ያነሣሣል። በታማኝነት እንድንመላለስ ከሚያነሣሡን ጠንካራ ምክንያቶች አንዱ የኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት መቅረብ ነው። እንዲያውም፥ «መሰብሰብ» የሚለው ቃል ከዕብራውያን 10:25 በተጨማሪ የተጠቀሰበት ሌላው የአዲስ ኪዳን ክፍል 2ኛ ተሰሎንቄ 2:1 ላይ ብቻ ነው። እዚህም ላይ ይህ ቃል ከክርስቶስ ምጽአት ጋር በማዛመድ በሚናገረው ክፍል ውስጥ የሚገኝ ነው።

በዚህ ስፍራ ሦስቱ ታላላቅ ክርስቲያናዊ ፍሬዎች ተገልጸዋል። እምነት (ዕብ. 10:22)፥ ተስፋ (ቁ. 23) እና ፍቅር (ቁ. 24)። እነዚህ ቃላት ከእግዚአብሔር ጋር በሰማያዊ ቤተ መቅደስ ኅብረት የማድረጋችን ፍሬዎች ናቸው።

ለ. ጠንካራ ምክር (10:26–31)። ይህ በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ከሚገኙ አምስት ምክሮች አራተኛው ነው። ክፍሉ የተጻፈው ለአማኞች ሲሆን፥ ሌሎች ምክሮችን ተከትሎ የሚመጣ ነው። ከቃሉ የሚያፈነግጥ አማኝ (2:1–4) ብዙም ሳይቆይ ቃሉን ይጠራጠራል (3:7–4:13)። ከዚያም ቃሉ ይሰለቸዋል (5:11–6:20)። ቃሉ የሚሰለቸው ከሆነ ደግሞ መንፈሳዊ ሕይወቱ ስንፍና የጎላበት ይሆናል። ይህም ቃሉን እንዲንቅ ያደርገዋል። ጸሐፊው በዚህ ክፍል ውስጥ ያተኮረው በዚሁ ጭብጥ ላይ ነው።

ይህ ንቀት የሚገለጸው ሆን ተብሎ በሚፈጸም ኃጢአት ነው። የጊዜ አመልካቹ እንደሚያሳየው፥ ዕብራውያን 10:26፥ «በፈቃደኝነት ኃጢአት መሥራታችንን ከቀጠልን. . .» ተብሎ ሊነበብ ይገባል። ይህ ምክር ያተኮረው በአንድ የተወሰነ ኃጢአት ላይ ሳይሆን፥ ወደ ተደጋጋሚ አለመታዘዝ በሚመራው አመለካከት ላይ ነው። በብሉይ ኪዳን ሆን ተብለው በድፍረት ለሚፈጸሙ ኃጢአቶች የሚቀርቡ መሥዋዕቶች አልነበሩም (ዘጸ. 21:12–14፤ ዘኁል. 15:27–31)። የሙሴን ሕግ ንቀው ኃጢአት የሚፈጽሙ ሰዎች በሞት ይቀጡ ነበር (ዘዳግ. 17:1–7)። ለዚህ ነው ዳዊት በመዝሙር (51) ያለውን እንደዚያ ዓይነት

ጸሎት የጸለየው። በሥልጣኑ በመጠቀም ሆን ብሎ ኃጢአትን ስለፈጸመ፥ በሞት መቀጣት ይገባው ነበር። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን ለመነ። እርሱም ብዙ መሥዋዕቶችን ማቅረብ እንደማያድነው ያውቅ ነበር። ስለሆነም፥ ሊያቀርብ የሚችለው ነገር ቢኖር የተሰበረ ልብ ነበር። (መዝ. 51፡16–17)።

ዕቡይ ልብ አንድ አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚጎዳው እንዴት ነው? ይህ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደመርገጥ፥ ያዳነውን ውድ ደም እንደማርከስና መንፈስ ቅዱስን እንደመሳደብ ነው። ይህ በዕብራውያን 10፡19–25 የቀረበው ምክር ተገላቢጦሽ ነው! ወደኋላ የተመለሰ አማኝ እምነቱን፥ ተስፋውንና ፍቅሩን አጥብቆ ከመያዝ ይልቅ በአኗኗሩ የክርስቶስንና የቤተ ክርስቲያንን ስም ያሰድባል።

እንዲህ ዓይነት ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ምን ሊጠብቅ ይችላል? እንዲህ ዓይነቱ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ዘንድ ሊጠብቅ የሚችለው ኃይለኛ ቅጣትን ነው። (ቅጣት የዕብራውያን ምዕራፍ 12 ጭብጥ ነው።) እንደ ፍርድና ኃይለኛ ቁጣ (10፡27)፥ ወይም «የሚብስ ቅጣት» (ቁ. 29) የመሳሰሉትን ቃላት ቀለል አድርገን ልናይ አይገባም። ከግብጽ በበጎች ደም ድነው ከወጡት እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር የገቡ ሰዎች ብዙዎች አለመሆናቸውን እናውቃለን። ሁሉም በምድረ በዳ ላይ ሞተው ቀርተዋል ማለት ይቻላል። ይህም ወደሞት የሚያደርስ ኃጢአት እንዳለ ያሳየናል (1ኛ ዮሐ. 5፡16)። አንዳንድ የቆሮንቶስ አማኞች ሆን ብለው ኃጢአት በመሥራታቸው ምክንያት ተቀጥተዋል፤ ለሞትም ተዳርገዋል (1ኛ ቆሮ. 11፡30)።

እግዚአብሔር ሁልጊዜም የዓመፀኛ ክርስቲያንን ሕይወት ባያጠፋም፥ መቅጣቱ ግን የማይቀር ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡ ለሆኑት እስራኤላውያን፥ «በቀል የእኔ ነው» ሲል ተናግሯል። እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እንደሚፈርድም የዕብራውያን ጸሐፊ (10፡30) ዘዳግም 32፡35ንም ጠቅሶ አስረድቷል። ስለዚህ «በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ እጅግ የሚያስፈራ ነው» (ዕብ. 10፡31)።

የዕብራውያን መልእክት ዋንኛ ጭብጥ፥ «እግዚአብሔር ለተናገረው ቃል ምላሽ የምትሰጡት እንዴት ነው?» የሚል ነው። እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ቃል አምነው ለመታዘዝ ባለመፈለጋቸው፥ እግዚአብሔር ቀጥቷቸዋል። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በድፍረት የሚፈጸም ኃጢአት እንዳያደርጉ ለማስጠንቀቅ ይህንኑ እውነት ገልጾላቸዋል (1ኛ ቆሮ. 10፡1–12)። በዚህ ምንባብ ውስጥ የቀረቡት ምሳሌዎች ሆን ብለው በድፍረት ኃጢአት በመፈጸማቸው

የሞቱትን ሰዎች እንደሚያካትቱ አስተውሉ። በዕብራውያን ምዕራፍ 12 ላይ ስለ ቅጣት በምናጠናበት ጊዜ እግዚአብሔር በልጆቹ ላይ ስለሚወስደው ስለዚሁ አስፈሪ እርምጃ ጠለቅ ብለን እንመለከታለን።

ይህ ቅጣት ዛሬ በክርስቲያኖች ላይ ተግባራዊ እንደሚሆን ነገር ግን ደኅንነትን እንደማያሳጣ ስገልጽ፥ ቅጣት ቀለል ተደርጎ መታየት አለበት ማለቴ አይደለም። እያንዳንዱ ክርስቲያን መታዘዝና በሁሉም ነገሮች እግዚአብሔርን ማስደሰት ይጠበቅበታል። የቀድሞው የሙዲ የመጽሐፍ ቅዱስ ተቋም ፕሬዚዳንት የነበሩት ዶክተር ዊሊያም ካልበርትሰን፥ «ይቅርታ የተደረገላቸው ኃጢአቶች ስለሚያስከትሏቸው አሳዛኝ መዘዞች» ያስጠነቅቁ ነበር። እግዚአብሔር የዳዊትን ኃጢአቶች ይቅር ቢልም፥ ለብዙ ዓመታት በአሳዛኝ መዘዞች ሲሠቃይ ኖሯል (2ኛ ሳሙ. 12፡7–15)። ዳዊት የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በመናቁ (12፡9)፥ እግዚአብሔር ቀጥቶታል።

በመንፈሳዊ ጥርጣሬና ስልቹነት ውስጥ ተደፍቆ በፈቃዱ የእግዚአብሔርን ቃል በመናቅ ላይ የሚገኝ አማኝ፥ ከዚህ መንገድ ይመለስ ዘንድ ምን ማድረግ ይኖርበታል? ምሕረትንና ይቅርታን ያገኝ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለበት። የክርስቶስ መሥዋዕት ለኃጢአታችን ሁሉ በቂ በመሆኑ፥ ለኃጢአት ሌላ መሥዋዕት ማቅረቡ አስፈላጊ አይደለም። ለቅጣቱ በእግዚአብሔር እጅ መውደቁ እጅግ አስፈሪ ሲሆን፥ ለመንጻትና ለመመለስ ከእርሱ እጅ መውደቁ ግሩም ነው። ዳዊት የምሕረቱን ታላቅነት በመገንዘብ ከእግዚአብሔር እጅ መውደቅን መርጧል (1ኛ ዜና 12፡13)።

ሐ. አበረታች ማጽኛ (ዕብ. 10፡32–39)። አንባቢያን ምክሩን በተሳሳተ መንገድ እንዳይረዱት ጸሐፊው የማበረታቻና የማጽኛ ቃላት ያስከትላል። አንባቢያኑ እውነተኛ ክርስቲያኖች መሆናቸውን በበቂ መረጃ አስመስክረዋል። ስለሆነም፥ ጸሐፊው የእግዚአብሔርን ቃል በመናቅ ቅጣቱን እንደሚቀበሉ አይጠብቅም! እንዲያውም፥ እንደ ዕብራውያን 6 ሁሉ ጸሐፊው ተውላጠ ስሞችን ከ«እኛ» (10፡26) ወደ «እርሱ» (ቁ. 29) እና «እነርሱ» (ቁ. 39) ለውጧል።

ቀደም ሲል አንባቢያን ንብረታቸውን እስኪያጡ ድረስ ነቀፋንና መከራን ለመቀበል ፈቃደኞች ነበሩ። ራሳቸው ባይሰደዱም፥ የሌሎችን ክርስቲያኖች መከራና እስራት ተካፍለዋል። በዚያን ጊዜ ከፍተኛ እምነትና ተስፋ የነበራቸው ሲሆን፥ አሁን ግን እምነታቸውን ጥለው ወደ አሮጌው ሃይማኖታቸው ለመመለስ ያስቡ ነበር።

የድል ምሥጢር ያለው በእምነታቸውና ትዕግሥታቸው ውስጥ ነበር። የነዚህን ጸጋዎች ጥምረት በዕብራውያን 5፡12 እና 15

ተመልክተናል። እዚህ ላይ ጸሐፊው የዕብራውያን መልእክት የተመሠረተበትን ምንባብ ያቀርባል። ይህም «ጻድቅ በእምነት ይኖራል» የሚለው ነው (10:38)። ጥቅሱ የተወሰደው ከዕንባቆም 2:4 ሲሆን፥ በሮሜ 1:17 እና ገላትያ 3:11ም አገልግሏል። የሮሜ መልእክት በጽድቅ ላይ ሲያተኩር፥ የገላትያ መልእክት በሕይወት የመኖርን ጉዳይ ያብራራል። የዕብራውያን መልእክት ደግሞ «በእምነት» ላይ አጽንኦትን ይሰጣል። ከኃጢአታችን በእምነት መዳናችን ብቻ በቂ አይደለም። በእምነት መኖርም አለብን። ይህ የዕብራውያን 11-13 ጭብጥ ነው።

በእምነት የሚኖር አማኝ ወደ ፍጹምነት ይሄዳል (6:1)። በማየት የሚመላለስ አማኝ ግን ወደኋላ ያፈገፍጋል (10:39)። «ማፈግፈግ» በዚህ ዓውደንባብ ውስጥ ምን ማለት ነው? ማፈግፈግ ተብሎ የተተረጎመው የዕርዕ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ 20 ያህል ጊዜ አገልግሏል። ይህ የግሪኩ ቃል ከተገለጸባቸው የተለያዩ ፍችዎች መካከል «መጥፋት» (የሐዋ. 8:20)፥ «መሞት» (የሐዋ. 25:16)፥ «መጥፋት» (ሮሜ 9:22) እና «ማባከን» (ማቴ. 26:16) ይገኙባቸዋል። ይህ ቃል ዘላለማዊ ፍርድን ሊያመለክት ቢችልም፥ በሁሉም አገባቦቹ ውስጥ ይህንን አሳብ የግድ አያሳይም። በእኔ አመለካከት፥ በ10:39 ያገለገለው «ማባከን» በሚለው ፍችው ነው። በእምነት የማይመላለስ አማኝ ወደ አሮጌ መንገዶቹ በመመለስ ሕይወቱን ያባክናል።

ሕይወትን ማዳን፥ የማባከን ተቃራኒ ነው። በእምነት መመላለስ ማለት የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝ ለኢየሱስ ክርስቶስ መኖር ነው። ለእርሱ ስንል ሕይወታችንን ብንተው መልሰን እናገኘዋለን እንጂ አናጠፋውም። እንዲያውም ሕይወታችንን እናድናለን! (ማቴ. 16:25-27)። በራሴ የመጋቢነት አገልግሎት፥ ጀርባቸውን ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመስጠታቸው እንደ እስራኤል ለዓመታት በመባከን በረሃ ውስጥ ሲቅበዘበዙ የኖሩ ሰዎች አጋጥመውኛል።

እኛ ግን በእምነት ልንመላለስ እንችላለን! በእምነት በምንመላለስበት ጊዜ፥ ታላቁ ሊቀ ካህናችን ሊመራንና ፍጹም ሊያደርገን አብሮን ይሆናል!

# 10

# እምነት – በዓለም ታላቁ ኃይል

**ዕብራውያን 11**

ይህ ምዕራፍ የመልእክቱን የመጨረሻ ክፍል ይከፍታል (ምዕ. 11–13)። ይህንንም «ከፍተኛ የእምነት መርህ» ብዬ ዋለሁ። ክርስቶስ ከፍ ያለ ማንነት ያለው (ምዕ. 1–6) እና ከፍተኛ የክህነት አገልግሎት ያለው መሆኑ (ምዕ. 7–10)፥ እምነታችንን በእርሱ ላይ እንድንጥል ሊያበረታታን ይገባል። የዚህ መልእክት አንባቢዎች ወደ ይሁዲነት በመመለስ እምነታቸውን በሙሴ ላይ ለመጣል ይፈተኑ ነበር። የሚተማመኑት በማይታዩ የእግዚአብሔር እውነታዎች ሳይሆን፥ በዚህች ዓለም ተጨባጭ ነገሮች ነበር። ወደ ፍጹምነት (ብስለት) መገስገስ ሲኖርባቸው ወደ ኋላ ወደ ጥፋት ያፈገፍጉ ነበር (6፡1 እና 10፡39)።

ይህ አሥራ አንደኛው ምዕራፍ ክርስቲያኖች ሁሉ በእምነት እንዲመላለሱ ጥሪ ያቀርባል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፥ ጸሐፊው ከእምነት ጋር የተያያዙትን ሁለት ዐበይት ጉዳዮች ያነሣል።

## 1. እምነት ምንድን ነው? (11፡1–3)

ይህ እምነት ምን እንደሆነ ለማብራራት የተሰጠ ትርጉም፥ እምነት ምንን እንደሚያደርግና እንዴትስ እንደሚሠራ የሚያመለክት ገለጻ ነው። እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ጭፍን የሆነ ተምኔት ወይም ራሳችን የምንፈጥረው፥ «ተስፋ አደርጋለሁ» ዓይነት ስሜት አይደለም። በተጨማሪም፥ እምነት አስተምህሮን በአእምሮ የመቀበል እሺታ አይደለም። ደግሞም እምነት ከማስረጃ ውጭ ማመን አይደለም! ይህ እምነት ሳይሆን አጉል አምልኮ ነው።

እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ከሁኔታዎችና ከውጤቶቻቸው ባሻገር ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኘውን አሳብ እንደገና በማንበብ በአእምሮአችሁና በልባችሁ ውስጥ እንዲሰርፅ አድርጉ።

ይህ እምነት የሚሠራው በቀላሉና ባልተወሳሰበ መንገድ ነው። እግዚአብሔር ሲናገር ድምፁን እንሰማዋለን። ሁኔታዎቻቸውና ውጤቶቻቸው ምንም ዓይነት ይዘት ይኑራቸው ቃሉን አምነን ተግባራዊ እናደርገዋለን። ሁኔታዎች የማይሞከሩ ሊሆኑ ይችላሉ። ተግባራችን የሚያስከትላቸው መዘዞችም እጅግ አስፈሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር

ግን የእግዚአብሔርን ቃል በማመን እርሱ ትክክለኛውንና ከሁሉም የሚሻለውን እንደሚያደርግ እንተማመናለን።

ምናልባትም ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙም እምነት ተግባራዊ ሲሆን ባለመመልከቱ ምክንያት ሊሆን ይችላል፥ ያልዳነው ዓለም እውነተኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት አይገነዘብም። በእግዚአብሔር ሕልውና የማያምነው ተጠራጣሪው ኤዲተር ወይም አርታዒ ኤች.ኤል. ሜንኪን እምነት «ሊሆን የማይችል ነገር ይሆናል ብሎ በጭፍኑ ማመን» እንደሆነ አድርጎ ገልጾታል። ዓለማውያን የእምነት ዋጋ የሚለካው፥ እምነቱ ባረፈበት አካል እንደሆነና የእምነታችንም ማረፊያ እግዚአብሔር እራሱ እንደሆነ መገንዘብ ይሳናቸዋል። እምነት እኛ እንዳሻን የመረጥነው የሆነ «ስሜት» ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ለገለጸው አሳብ የምንሰጠው አጠቃላይ ምላሻችን ነው።

በዕብራውያን 11፥1–3 ውስጥ የሚገኙ ሦስት ቃላት፥ እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት ምን እንደሆነ ጠቅለል ያለ አሳብ ይሰጡናል። እነዚህም ማስረገጥ (substance)፥ ማስረዳት (evidence) እና መመስከር (witness) ናቸው። በዚህ ክፍል «ማስረገጥ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል በቁሙ «ምርኩዝ መሆን፥ መደገፍ» ማለት ነው። እምነት ለክርስቲያን እንደ ቤት መሠረት ነው። በመሆኑም፥ የሚቆምበትን መተማመኛና እርግጠኝነትን ይሰጠዋል። ስለሆነም፥ «እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ. . . ነው» ማለት ይቻላል። እምነት እግዚአብሔር የገባውን ተስፋ እውን እንደሚያደርግ የምናስረግጥበት መንገድ ነው።

ማስረዳት ማለት ግንዛቤንና መረዳትን ያመለክታል። ይህም አንድ ሰው እግዚአብሔር ተስፋ የሰጠውን ነገር እንደሚያገኝ ውስጣዊ መረዳትን የሚያገኝበት መንገድ ነው። በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ከእግዚአብሔር የተሰጠ እምነት መኖሩ፥ እግዚአብሔር ቃሉን እንደሚጠብቅ ለማስገንዘብ በቂ ነው።

ምስክር፥ (ኪጀቪ በተባለው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ «መልካም ሪፖርት ያገኙት») በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አስፈላጊ ቃል ነው። ይህ ቃል በቁጥር 2 ብቻ ሳይሆን በቁጥር 4ም ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል። እንዲሁም በቁጥር 5 እና 39ም ላይ ተጽፎአል። በዕብራውያን 12፥1 የሚገኘው ማጠቃለያ ይህንኑ የእምነት ሰዎች ዝርዝር፥ «እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን» ሲል ገልጾአል። እግዚአብሔር ለእነሱ ስለመሰከረ እነሱ ለእኛ ምስክሮች ናቸው። እግዚአብሔር ለተጠቀሱት ሰዎች ሁሉ

መስክሮላቸዋል። ይህም ምስክርነት ሕይወታቸውና አገልግሎታቸው መለኮታዊ ተቀባይነት እንዳገኘ ዋስትና የሚሰጣቸው ነው።

የማያምኑ ሰዎች ስለ እምነት ምንም ዓይነት ነገር ይናገሩ፥ እምነት ተግባራዊ ነገር መሆኑን የዕብራውያን ጸሐፊ በግልጽ ጽፎታል (ቁ.3)። እምነት እግዚአብሔር የሚሠራውን ለመረዳትና የማያምኑት ሊያዩ የማይችሉትን ማየት እንድንችል ያደርገናል። (11፡7፥ 13፥ 27 አንብብ)። ከዚህም የተነሣ፥ እምነት የማያምኑ ሰዎች ሊያደርጓቸው የማይችሏቸውን ነገሮች እንድናደርግ ያስችለናል! እነዚህ የእምነት ሰዎች በእምነት ተግባራዊ እርምጃዎችን በወሰዱባቸው ጊዜያት ሰዎች ተሳልቀውባቸዋል። እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ ጋር ስለነበረ ለክብሩ ታላላቅ ድሎች እንዲቀዳጁ ረድቷቸዋል። ዶክተር ጄ. ኦስዋልድ፥ «እምነት የምታምን ነፍስ የወደፊቱን እንደ አሁን ጊዜ፥ የማይታየውን እንደሚታይ አድርጋ እንድትወስድ ያስችላታል» ሲሉ ግሩም አድርገው አስቀምጠውታል።

በእምነት ለማደግ ከሁሉም የበለጠው መንገድ ከታመኑት ጋር መመላለስ ነው። የዚህ ምዕራፍ ቀሪ ክፍል በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩትን የእምነት ጀግኖች ሕይወትና አገልግሎት ይዘክራል። በእነዚህ የእምነት ጀግኖች ሕይወት ውስጥ ተመሳሳይ የእምነት አላባውያንን (መሠረታውያን) ታገኛላችሁ። 1. እግዚአብሔር በቃሉ አማካኝነት ተናግሯቸዋል፤ 2. ውስጣዊ ማንነታቸው በተለያዩ መንገዶች ተነቃቅቷል፤ 3. እግዚአብሔርን ታዘዋል፤ 4. እርሱም ስለ እነርሱ ምስክርነት ሰጥቷል።

## 2. የእምነት ማሳያ (11፡4–40)

ሀ. <u>አቤል – እምነት በአምልኮ ላይ ሆኖ</u> (11፡4)። ይህ አሳብ የተመሠረተበት ታሪክ የሚገኘው በዘፍጥረት 4፡1–10 ውስጥ ነው። አቤል በእምነቱ ምክንያት የጸደቀ ሰው ነበር (ማቴ. 23፡35)። እግዚአብሔር ለአዳምና ለዘሮቹ እውነተኛውን የአምልኮ መንገድ አሳይቷቸው ስለነበር፥ አቤል በእምነት ለእግዚአብሔር ታዘዘ። እንዲያውም፥ ታዛዥነቱ ሕይወቱን አሳጥቶታል። ቃየን ሃይማኖተኛ ቢሆንም እምነት ስላልነበረው የእግዚአብሔር ልጅ አልነበረም (1ኛ ዮሐ. 3፡12)። የመጀመሪያው የእምነት ሰማዕት የሆነው አቤል የእምነትን ዋጋ ያሳየናል።

ለ. <u>ሄኖክ – እምነት ሲመላለስ</u> (ዕብ. 11፡5–6)። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በምናደርግበት ጊዜ እምነታችን እያደገ ይሄዳል። በእምነት በምንመላለስበት ጊዜ እርሱን የማስደሰት ፍላጎትና እርሱን የመፈለግ ትጋት ሊኖረን ይገባል። በዚህ ጉዟችን እንደ ጸሎት፥ ቃሉን ማሰላሰል፥

አምልኮና ራስን መግዛት የመሳሰሉት ነገሮች ከፍተኛ እገዛ ያደርጉልናል። የጥፋት ውኃ ከመምጣቱ በፊት በነበረው ኃጢአተኛ ዓለም ውስጥ፥ ሄኖክ ከእግዚአብሔር ጋር ስለተመላለሰ ሕይወቱን በንጽሕና ለመጠበቅ ችሏል። ከዚያም አንድ ቀን ሄኖክ ወደ ሰማይ ተወሰደ። ከዚያ በኋላ በምድር ላይ አልታየም። አቤል በአሰቃቂ ሁኔታ ሲገደል፥ ሄኖክ ግን ሞትን አልቀመሰም። ይህ የሚያሳየን እግዚአብሔር ለሚያምኑት ሁሉ የተለያዩ ዕቅዶች እንዳሉት ነው። አንዳንዶች የሄኖክን ወደ ሰማይ መወሰድ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም በሚመለስበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የምትነጠቅበትን ሁኔታ ለማሳየት እንደሚያገለግል ምሳሌ አድርገው ይጠቀሙበታል (1ኛ ተሰ. 4፡13–18)።

ሐ. <u>ኖኅ – እምነት በሥራ ላይ ሆኖ</u> (ዕብ. 11፡7)። የኖኅ እምነት ሁለንተናውን ያካተተ ነበር። አእምሮው የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ አስተውሎ ልቡ በፍርሃት ተናወጠ። ፈቃዱም እግዚአብሔር ለተናገረው አሳብ ታዘዘ። በዚያን ጊዜ ማንም ሰው የጥፋትን ውኃ አይቶ ስለማያውቅ፥ ሰዎች በኖኅ ሥራ ሳይገረሙና ሳይሳለቁበት አልቀሩም። የኖኅ እምነት በቤተሰቡ ሁሉ ላይ ተጽእኖ በማሳደሩ ሁሉም ሊድኑ ችለዋል። እንዲሁም፥ እምነቱ ሰዎች አለማመናቸውን እንዲረዱ በማድረግ መላውን ዓለም ኮነነ። ዓለም ቢሳለቅበትም የመጣው የውኃ ጥፋትና በወቅቱ የታዩት ክስተቶች ኖኅ ትክክል እንደነበር አረጋግጠዋል! ኢየሱስም ወደ ጥፋት ውኃ በማመልከት ሰዎች ለምጽአቱ እንዲዘጋጁ አስጠንቅቋል (ማቴ. 24፡36–42)። በኖኅ ዘመን፥ ሰዎች በዕለት ተግባራቸው ከመጠመዳቸው የተነሣ፥ የኖኅን ምስክርነት መስማት ሳይችሉ ቀርተዋል (2ኛ ጴጥ. 2፡5)።

መ. <u>የእምነት አባቶች – እምነት በተስፋ ሲጠባበቅ</u> (ዕብ. 11፡8–22)። በዚህ ስፍራ ትኩረት የተሰጠው በእግዚአብሔር የተስፋ ቃልና ለእስራኤል ሕዝብ በወጠናቸው ዕቅዶች ላይ ነው (ቁ. 9፥ 11፥ 13፥ 17)። የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ የሚጀምረው ከአብርሃም መጠራት ነው። እግዚአብሔር አብርሃምና ሣራ ልጅ እንደሚወልዱ ቢነገራቸውም፥ 25 ዓመታት መታገሥ ነበረባቸው። 25 ዓመታት ከጠበቁ በኋላ የተወለደው ይስሐቅ ኋላ ያዕቆብንና ዔሳውን ወለደ። ያዕቆብ አሥራ ሁለት ልጆችን በመውለድ የእስራኤልን ሕዝብ መሠረተ። ዮሴፍ ሕዝቡን በግብጽ ምድር ሲታደግ፥ ሙሴም በኋላ በእግዚአብሔር መሪነት ከግብጽ ባርነት አርነት አወጣቸው።

መጠበቅ በሕይወቴ በጣም ፈታኝ ከሚሆኑብኝ ሥነ ሥርዓቶች አንዱ ነው። እውነተኛ እምነት ግን የእግዚአብሔር ዓላማዎች እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜያት እስኪፈጸሙ ድረስ በትዕግሥት

ይጠባበቃል። ነገር ግን በምንጠባበቅበት ጊዜ እግዚአብሔርን ከመታዘዝ መቆጠብ የለብንም። «አብርሃም. . . በእምነት ታዘዘ» (11፡8)። አብርሃም የታዘዘው የሚሄድበትን በማያውቅበት ወቅት ነበር። (11፡8–10)። በምድር ላይ እንግዳና መጻተኛ ስለነበርና እግዚአብሔር በሚያዘው ጊዜ ሁሉ መንቀሳቀስ ስለነበረበት፥ ድንኳን እንጂ ቤት አልነበረውም። ዛሬም ክርስቲያኖች እንግዶችና መጻተኞች ናቸው። (1ኛ ጴጥ. 1፡1፤ 2፡11)። አብርሃም ዓይኖቹን በሰማያዊቷ ከተማ ላይ አሳርፎ በወደፊት የጊዜ ሰሌዳ እየተመራ ይኖር ነበር።

በተጨማሪም፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዴት እንደሚፈጸም በማያውቅበት ጊዜም ታዟል (ዕብ. 11፡11–12)። አብርሃምም ሆነ ሣራ ልጅ ለመውለድ ከሚችሉበት ዕድሜ ውጭ እስኪሆኑ ድረስ ቢያረጁም፥ ሁለቱም እግዚአብሔር ተአምር እንደሚሠራ ያምኑ ነበር (ሮሜ 4፡13–25)። አለማመን፥ «ይህ እንዴት ይቻላል?» ብሎ ሲል ይጠይቃል (ሉቃስ 1፡18–20)። እምነት ግን፥ «ይህ እንዴት መሆን አለበት?» ብሎ ይጠይቃል (ሉቃስ 1፡34–35)።

አብርሃም እግዚአብሔር የተስፋ ቃሎቹን መቼ እንደሚፈጽም በማያውቅበት ጊዜ ታዟል። (ዕብ. 11፡13–16)። የእምነት አባቶች ከርቀት አሻግረው አዩ እንጂ፥ ማናቸውም የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ሙሉ ለሙሉ ሲፈጸሙ አልተመለከቱም። ታላቅ የስኮትላንድ ሰባኪ የሆኑት ዶክተር ጆርጅ ሞሪሰን አንድ ጊዜ «ዋናው ነገር የምንኖርበት ሳይሆን፥ ወደፊት በተስፋ የምንመለከተው ነው» ሲሉ ተናግረዋል። ምንም እንኳ እነዚህ የእምነት ሰዎች በድንኳኖች ውስጥ የኖሩ ቢሆኑም፥ ሰማያዊት ከተማ ተዘጋጅታ እንደምትጠብቃቸው ያውቁ ነበር። ውሎ አድሮ እግዚአብሔር ለሚያምኑበት የተስፋ ቃሎቹን ይፈጽማል።

በመጨረሻም፥ አብርሃም እግዚአብሔር ለሚያደርገው ነገር ምክንያቱ ምን እንደሆነ ሳይገባው በእምነት ታዟል (11፡17–19)። የእስራኤል የወደፊት ተስፋዎች ሁሉ በይስሐቅ ውስጥ ተጠቃለው ሳለ፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ ከሰጠው በኋላ መልሶ እንዲሠዋለት የሚጠይቀው ለምንድን ነው?። ከእግዚአብሔር ጋር በምንመላለስበት ጊዜ የእምነት ፈተናዎች ይበልጥ አስቸጋሪዎች እየሆኑ ይሄዳሉ። ሽልማቶቹ ደግሞ በዚያው ልክ አስደናቂዎች ይሆናሉ! የታዳጊ ወጣቱን (የይስሐቅን) ታዣዥ የሆነ እምነት ቸል ልንል አይገባም (ዘፍጥ. 22)።

በአብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብና ዮሴፍ ውስጥ አራት የእምነት ትውልዶችን እናገኛለን። እነዚህ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ቢሰናከሉም፥

መሠረታዊ ባሕርያቸው እምነት ነበር። ፍጹማን ባይሆኑም፥ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ራሳቸውን የሰጡ ሰዎች ነበሩ። ይስሐቅ የተስፋ ቃሎቹንና በረከቶቹን ወደ ያዕቆብ ሲያስተላልፍ (ዘፍጥ. 27)፥ ያዕቆብ ደግሞ ለ12 ልጆቹ አጋርቷቸዋል (ምዕ. 48 እና 49)። ያዕቆብ መጻተኛ ነበር፤ በሚሞትበት ጊዜ እንኳ በመጻተኛነት በትሩ ላይ ተመርኩዞ ነበር።

ዮሴፍ ከቤተሰቡ ያንን ያህል መከራ ከደረሰበት በኋላ በእምነቱ ይጸናል ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነበር። ነገር ግን ዮሴፍ እምነቱን ከመተው ይልቅ እያደገና እየበረታ ሄደ። ፍሪሃ–እግዚአብሔር በሌለበት በግብፅ እየኖረ በዙሪያው ያየው ነገር በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት ሊያዳክም አልቻለም። ዮሴፍ ቤተሰቡን፥ ሥራውን ወይም የነበረበትን ሁኔታ በእግዚአብሔር ላለማመን ማመኻኛ አድርጎ አልተጠቀመም። ምክንያቱም ዮሴፍ ያመነውን ያውቅ ነበር። ይኸውም አንድ ቀን እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት ነፃ እንደሚያወጣቸው ነበር (ዘፍጥ. 50፡24–26)። በተጨማሪም፥ ዮሴፍ ስፍራውን ያውቅ ነበር። የእርሱ ስፍራ ከነዓን እንጂ ግብጽ እንዳልነበረች ተረድቶ፥ ዓፅሙን ወደዚያ ይዘውት እንዲሄዱ ቃል አስገባቸው። እነሱም ይህንኑ አድርገዋል! (ዘጸአት 13፡19 እና ኢያሱ 24፡32 አንብብ)።

የእምነት አባቶች እምነት የሚደነቅ ነው። ምክንያቱም ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ባይኖራቸውም፥ እምነታቸው ጠንካራ ነበር። ስለዚህ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው አስተላልፈዋል። ከድካማቸው ባሻገር እነዚህ የእምነት ሰዎች በእግዚአብሔር አምነው ነበርና እርሱም ለእምነታቸው መሰከረ፟ል። እንግዲህ፥ እኔና አንተ ከዚህ ምን ያህል የተሻለ እምነት ሊኖረን ይገባል!

ሠ. <u>ሙሴ – እምነት በውጊያ ላይ</u> (ዕብ. 11፡23–29)። ሙሴ አማኝ ወላጆች ማግኘቱ የመታደል ያህል ነበር። ለእነዚህ ወላጆች የባለሥልጣናትን ትእዛዝ በመተላለፍ ልጃቸውን ለመደበቅ መሞከራቸው የእምነት እርምጃ ነበር። የዚህ ታሪክ ዝርዝር በዘጸአት 2፡1–10 ይገኛል። የሙሴ ወላጆች አምለምና ዮካቤድ ይባሉ ነበር (ዘጸ. 6፡20)። ምንም እንኳ መንፈሳውያን ወላጆች ለልጆቻቸው እምነትን እንደ ቤተሰባዊ ባሕርይ ሊያስተላልፉ ባይችሉም፥ በቤት ውስጥ የእምነትን ድባብ በመፍጠር ለልጆቻቸው የእምነት ምሳሌዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ቤተሰብ ለልጆች የመጀመሪያው የእምነት ትምህርት ቤታቸው ሊሆን ይገባል።

በሙሴ ሕይወት ውስጥ ሦስት ከእምነት ጋር የሚዛመዱ ታላላቅ ጭብጦች ተመልክተዋል። መጀመሪያ፥ የእምነት እምቢተኝነት፥ (ዕብ. 11፡24–25)። የግብጽ ንጉሥ ልጅ ስላሳደገችው፥ ሙሴ በቤተመንግሥቱ ውስጥ ምቹ ሕይወት ለመምራት ይችል ነበር። ነገር ግን እምነቱ እንዲህ ዓይነቱን ሕይወት እንዳይቀበል አስቻለው። ስለሆነም፥ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ። እውነተኛ እምነት ሰዎች ትክክለኛ እሴቶችን ሰጥተው ትክክለኛ ውሳኔዎችን እንዲያሳልፉ ይረዳቸዋል። «በኃጢአት የሚገኝ ደስታ» ምኞትንና ሌሎች ታላላቅ ኃጢአቶችን ብቻ ሳይሆን፥ ዛሬ ሰዎች «ስኬታማነት» ብለው የሚጠሩትን የሕይወት ዘይቤ ጭምር ሊያመለክት ይችላል። ይህም ሥልጣን፥ ክብር፥ ኃይል፥ ባለጸግነትና ከችግሮች ነፃ መሆንን የሚያሳይ ነው።

የሙሴ እምቢተኝነት በእምነቱ እንዲነቀፍ አደረገው (11፡26)። አንዲት በአሜሪካ ውስጥ የምትገኝ ትልቅ ከተማ ከንቲባ የሆነች ሴት፥ የአናሳዎችን፥ ከማኅበረሰቡ ተገልለው በመንገድ ላይ የሚኖሩትንና የድሆችን ችግሮችና ፍላጎቶች ለማሳየት ስትል አደገኛና የፈራረሱ ቤቶች ወደሚገኙበት አካባቢ ተዛወረች። ነገር ግን ይህች ከንቲባ ብዙም ሳትቆይ ያንኑ የድሆች ሰፈር ጥላ በመውጣት ወደ ቀድሞው ውብ አፓርትመንቷ ተመለሰች። ይህችን ከንቲባ ለቆራጥነቷ ብናመሰግናትም፥ ለሙሴ የምንሰጠው አክብሮት ከዚያ የላቀ መሆኑ ግልጽ ነው። ሙሴ ቤተ መንግሥቱን ትቶ ከወጣ በኋላ ወደ ኋላ አልተመለከተም! የእምነት ሰዎች ብዙውን ጊዜ ነቀፋንና መከራን ለመጋፈጥ ይገደዳሉ። ሐዋርያት ለእምነታቸው መከራን ተቀብለዋል። ዛሬም መከራ በመቀበል ላይ የሚገኙ ክርስቲያኖች ነቀፋን መሸከም ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያውቃሉ።

በመጨረሻም፥ *የእምነት ብድራት* አለ (11፡26–29)። እግዚአብሔር ሁልጊዜም እውነተኛ እምነትን ያከብራል! ብድራትንም ይከፍላል። ቅፅበታዊ ባይሆንም እንኳ ይህ የኋላ ኋላ የማይቀር ነው። ሙሴ ከግብጽ ባለጠግነት ይልቅ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመለከተ። ዶክተር ቫንስ ሄቭነር እንዳሉት፥ «ሙሴ የማይጠፋውን መርጧል! የማይታየውን አይቷል! የማይቻለውንም አድርጓል።» የሙሴ እምነት ፈርዖንን ሳይፈራ እንዲጋፈጥና ጠላቱን ለመግጠም በእግዚአብሔር እንዲታመን አድርጎታል። ሙሴ የማመንታት ባሕርይ ስለነበረው፥ የሙሴ ጽናት ተፈጥሯዊ ስጦታ አይደለም። ይህ ጽናትና ቆራጥነት የእምነቱ ሽልማት ሆኖ የተሰጠው ነው።

የሙሴ እምነት እሱና ሕዝቡ እንዲለቀቁ አድርጓል። (አስደሳቹን የፋሲካ በዓል ታሪክ ከዘጸአት 11–13 አንብብ።) እምነት ያወጣናል

(ዕብ. 11፡28)፤ ያሻግረናል (ቁ. 29)፤ መልሶም ያመጣናል (ቁ. 30)። በእግዚአብሔር በምንታመንበት ጊዜ እግዚአብሔር ሊያደርግ የሚችለውን ማየት እንችላለን። በራሳችን በምንታመንበት ጊዜ ግን በፍጥረታቸው ደካማ የሆኑ ሰዎች ሊያደርጉ ከሚችሉት በላይ አንሻገርም። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ማለት ሁኔታዎችና የሚያስከትሏቸው መዘዞች ሁሉ ምንም ዓይነት ቢሆኑ፥ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ማለት መሆኑን የሙሴ ሕይወት በግልጽ ያሳያል።

ይህንን ምዕራፍ የጻፍነው እኔና አንተ ብንሆን ኖሮ ቀጣዩን ክፍል የሚቅበዘበዝ እምነት ብለን እንጠራው ነበር። ጸሐፊው ግን ስለ እስራኤል ውድቀትና ስለ ባከኑት 40 ዓመታት አንዳች ነገር ሲያነሳ አናይም። ለምን? ምክንያቱም ያ ያለማመን እንጂ የእምነት ገጠመኝ አልነበረም! የዕብራውያን ጸሐፊ ይህንን ክፍል በምዕራፍ 3 እና 4 አንባቢያኑ የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይጠራጠሩ ለማስጠንቀቅ ተጠቅሞበታል። በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ውስጥ ግን ባለማመን ሳቢያ ስለተከሰተው ውድቀት የተጠቀሰ አሳብ አይገኝም። እምነት የሚመዘግበው ድሎችን ብቻ ነው።

ረ. <u>ኢያሱና ረዓብ – እምነት ድል ሲነሳ</u> (11፡30–31)። የኢያሪኮ መወገር ታሪክ በኢያሱ 2–6 ተገልጾአል። ኢያሱ ሙሴን ተክቶ እስራኤላውያንን በሚመራበት ወቅት የሙሴን አምላክ በመተማመኑ አገልግሎቱን ሊያበረክት በቅቷል። እግዚአብሔር ሠራተኞቹን እንጂ የሥራ መርሆዎቹን አይቀይርም። ስለሆነም፥ እግዚአብሔር እምነትን ሲባርክ፥ ባለማመን ላይ ግን ይፈርዳል።

ከሰብአዊ እይታ አንጻር፥ ኢያሪኮ የማትደፈር ከተማ ነበረች። የኢያሱ የመጀመሪያው የእምነት ተግባር ግን የከተማይቱ መሸነፍ ሳይሆን፥ የሕዝቡ ዮርዳኖስን መሻገር ነበር። የቀድሞው ትውልድ ቀይ ባሕርን እንደተሻገረ፥ አሁንም ሕዝቡ በእምነት ዮርዳኖስን ተሻገረ። ይህም እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ኃይል ወደፊት በመጓዝ ላይ መሆናቸውን በማመልከት ለከነዓናውያን ምስክርና ማስጠንቀቂያ ሰጣቸው።

ረዓብ በእስራኤል አምላክ ታምናለች ብሎ ለማሰብ በሚያስቸግር ሁኔታ ውስጥ የምትገኝ ጋለሞታ ሴት ነበረች! ሌሎች የከተማይቱ ነዋሪዎች ለመሞት ስለተወሰኑ፥ ይህች ሴት በጸጋ ድናለች። እግዚአብሔር በምሕረቱና በጸጋው ረዓብ በሕይወት እንድትኖር ፈቀደ። ነገር ግን የዳነችው በእምነት ነበር። ይህች ሴት ስለ እግዚአብሔር የምታውቀው ነገር በኢያሱ 2፡8–14 ተገልጾአል። ያህዌ እስራኤላውያንን ከግብጻውያን እጅ እንዳዳነና ቀይ ባሕርን ከፍሎ

እንዳሻገራቸው ታውቅ ነበር። ይህ የሆነው ግን ከ40 ዓመታት በፊት ነበር! እንዲሁም ደግሞ እስራኤላውያን በምድረ በዳ ውስጥ በሚጓዙበት ወቅት እግዚአብሔር ሌሎች አገሮችን እንዳሸነፈ ታውቅ ነበር። «አምላካችሁም እግዚአብሔር በላይ በሰማይ በታችም በምድር እርሱ አምላክ ነውና» (ኢያሱ 2፡11)። የእምነት ምስክርነቷ ይህ ነበርና እግዚአብሔርም አከብሮላታል።

*መልካም ሥራን ለማድረግ ዳነች።* እምነት ሁልጊዜም በሰናይ ምግባራት ራሱን መግለጥ አለበት (ያዕ. 2፡20–26)። ይህች ሴት ሰላዮቹን በመደበቅ፥ እንደታዘዘችው ጨርቁን ከመስኮቱ ላይ በማኖር (ኢያሱ 2፡15–21)፥ ምናልባትም ቤተሰቧን ወደ እግዚአብሔር በመመለስ (2፡13፤ 6፡25)፥ በሁሉም መንገድ እግዚአብሔርን ታዛለች። በዚህም ረዓብ ከፍርድ ማምለጥ ብቻ ሳይሆን፥ የሕዝበ እስራኤል አካልም ሆናለች። ሳልሞንን በማግባት በንጉሥ ዳዊት የዘር ሐረግ ውስጥ የነበረውን ቦዔዝን ወልዳለች (ማቴ. 1፡4–6)። አረማዊቷ ሴት የኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ አካል መሆኗ ምን ያህል አስደናቂ እንደሆነ አስተውለሃል? ይህ እምነት ሊሠራ የሚችለው ተግባር ነው!

ረዓብ በክርስቶስ ላለማመናቸው ማመኻኛ ለሚያቀርቡ ዓለማውያን ተግሣጽ ነች። ብዙውን ጊዜ፥ «ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙም አላውቅም» የሚል ማመኻኛ እንሰማለን። ረዓብ ብዙ መንፈሳዊ እውነትን ባታውቅም፥ በምታውቀው እውነት ላይ ተመሥርታ ተግባራዊ እርምጃ ወስዳለች። «ሥራዬ ለደኅንነት የማያበቃኝ ክፉ ሰው ነኝ» የሚሉም አሉ። ረዓብም ማኅበረሰቡ የኮነናት አረማዊት ጋለሞታ ነበረች! «ቤተሰቤ ምን ይል ይሆን?» የሚሉ ሞልተዋል። የረዓብ የመጀመሪያው ስጋት ቤተሰቧን ማዳን እንጂ መቃወም አልነበረም። ስለሆነም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት ታላላቅ የእምነት ሴቶች ጎን ተሰልፋለች።

ሰ. <u>የተለያዩ የእምነት ጀግኖች</u> (ዕብ. 11፡32–40)። እምነት የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማትና ፈቃዱን ለመፈጸም በሚደፍር በማንኛውም ሰው ሕይወት ውስጥ ሊሠራ ይችላል። እዚህ በጣም የተለያዩ የእምነት ጀግኖች ተዘርዝረዋል! ጌዴዎን እምነቱ ከመቅጽበት የበቀለ አልነበረም። ይልቁንም ፈሪ ገበሬ ነበር (መሳ. 6፡11–7፡25)። በሲሣራ ላይ ድልን የተቀዳጀው ነቢይቷ ዲቦራ በሰጠችው ማረጋገጫ ተበረታቶ ነበር። (መሳ. 4፡1–5፡31 አንብብ።) ጌዴዎንም ሆነ ባርቅ በእምነታችን ለደከምን ክርስቲያኖች ማበረታቻዎች ናቸው።

የሳምሶን ታሪክ ብዙዎቻችን የምናውቀው ነው (መሳ. 13–16)። ሳምሶን ለሥጋዊ ምኞቱ ያደረ ሰው በመሆኑ፥ መንፈሳዊ ሰው ነበር

ለማለት እንደፍርም። ሳምሶን ናዝራዊ፥ ማለትም ለእግዚአብሔር የተሰጠ ስለሆነ፥ ራሱን መላጩት ወይም የወይን ፍሬ መቅመስ አይገባውም ነበር። (ናዝራዊነትና የናዝሬት ከተማ ነዋሪነት የተለያዩ ነገሮች ናቸው።) ሳምሶን ይረዳው ዘንድ በእግዚአብሔር ከመታመኑም በላይ፥ በመጨረሻው ጠላቶቹን ለማሸነፍ ሲል የራሱን ሞት መርጧል። ይሁንና ዛሬ ክርስቲያኖች ሁለት ዓይነት ሕይወት እየኖሩ የእግዚአብሔርን በረከት እንደሚያገኙ ሊጠብቁ አይገባም።

የዮፍታሔ ታሪክ አስገራሚ ነው (መሳ. 11፡1–12፡7)። ዮፍታሔ ብቸኛ ሴት ልጁን እንደሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ እንደሠዋት ማሰቡ አያስኬድም። ምክንያቱም ይህ በእስራኤል የተከለከለ ተግባር ነበር። ምናልባትም በስዕለት ሕግጋት መሠረት ለእግዚአብሔር አሳልፎ ሰጥቷት ይሆናል (ዘሌ. 27)። ይህም ድንግላዊት ሆና እንድትኖር የሚያደርግ ይሆናል (መሳ. 11፡34–40)።

እዚህ ላይ እያንዳንዱን የእምነት ምሳሌ መመርመሩ የሚቻል አይደለም። የዕብራውያን ጸሐፊ እንኳ ታላላቅ የእምነት ሰዎች የነበሩትን ዳዊትንና ሳሙኤልን ከጠቀሰ በኋላ፥ የስም ዝርዝሩን አቁሟል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ በዕብራውያን 11፡33–35 የተጠቀሱትን ድሎች ያገኙ ወንዶችና ሴቶች ነበሩ። ዳዊት መንግሥታትን በመግዛት ጽድቅን አስፍኗል። የዳንኤል እምነት የአንበሶችን አፍ ዘግቷል (ዳን. 6)። ሦስቱ ዕብራውያን ወጣቶች የእሳቱን እቶን ኃይል አሳጥተውታል (ዳን. 3፡23–28)። በዕብራውያን 11፡35 የተጠቀሱት የእምነት ሴቶች ታሪክ በ1ኛ ነገሥት 17፡17–24 እና 2ኛ ነገሥት 4፡18–37 ውስጥ ይገኛል።

በዕብራውያን 11፡35 ውስጥ የሚገኘው የመሸጋገሪያ አሳብ ልብ ሊባል የሚገባው ነው። የእምነት ሰዎች ሁሉ በተአምር አልዳኑም። ስለዚህ አንዳንዶቹ ለሥቃይ ተዳርገው ሞተዋል! በቁጥር 36 «ሌሎች» ተብሎ የተተረጎመው ቃል፥ «ሌሎች ወገኖች» ማለት ነው። እነዚህ ሌሎችም እምነት ነበራቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር ለሙሴ፥ ለጌዴዎንና ለዳዊት ያደረገውን በእነርሱ አላደረገም።

ሆስፒታል ውስጥ በሽተኞችን በምጎበኝበት ጊዜ፥ በአልጋ ከተኙት መሃል አንዲት ሴት ስታለቅስ ተመለከትሁ። «ምን ሆንሽ?» ስል ጠየቅኋት። ጥያቄዬን በመመለስ ፋንታ በዚያን ቀን በፖስታ ቤት በኩል የተላከላትን መጽሐፍ ሰጠችኝ። መጽሐፉ ስለ መለኮታዊ ፈውስና የእምነት ኃይል ያትታል። አንድ ያልታወቀ ሰው በመጽሐፉ ላይ፥ «ይህንን መጽሐፍ አንብቢ! ለፈውስ የሚሆን እምነት ይሰጥሻል» የሚሉ ቃላት አስፍሮ ነበር። በሽተኛዋ በመከራዋ መካከል

እንኳ በእግዚአብሔር የምታምን የተሰጠች ክርስቲያን ነበረች። መጽሐፉን የላከላት ሰው ያልተገለጸው ሰውዬ ግን ሰዎች ሁሉ በተአምር መፈወስ እንዳለባቸው ያስብ ነበር።

እኔ ራሴ ብዙ ሰዎች እንደምሞት እርግጠኛ ሆነው ካበቁ በኋላ በእግዚአብሔር ተአምር ተዳስሼ ድኛለሁ። እግዚአብሔር ሊፈውስ እንደሚችል አውቃለሁ። ነገር ግን እግዚአብሔር እምነት እንዳለኝ ለማረጋገጥ ሲል የመፈወስ ግዴታ እንዴሌለባት አምናለሁ። የዕብራውያን ጸሐፊ (11፡36–38) ብዙ ስማቸው ያልተጠቀሰ የእምነት ሰዎች ከአስቸጋሪ ሁኔታዎቻቸው እንዳላመለጡ ገልጾአል። ነገር ግን እግዚአብሔር እምነታቸውን አክብሮላቸዋል። እንዲያውም፥ ከማምለጥ ይልቅ ለመታገሥ የበለጠ እምነት ያስፈልጋል። እንደነዚያ የዕብራውያን ወጣቶች *ባያድነንም እንኳ* እግዚአብሔርን መታዘዝ አለብን (ዳን. 3፡16–18) ብለው በቆራጥነት ጸንተዋል።

ሰዎች ለነዚህ የእምነት ጀግኖች ዝቅተኛ ግምት ስለነበራቸው፥ በማሳደድ፥ በማሰር፥ በማሠቃየትና አንዳንዴም በመግደል ለመከራ ዳርገዋቸዋል። የእግዚአብሔር ግምት ግን ሙሉ በሙሉ ከዚህ የተለየ ነበር። ስለሆነም፥ ዓለም ለእነርሱ እንደማትገባ ተናግሯል! ሐዋርያው ጳውሎስ ለዚህ እውነት ጥሩ ምሳሌ ነው። ጳውሎስ በፌስጦስ ዘንድ እንዳበደ (የሐዋ. 26፡24)፥ በአይሁዶች ደግሞ በሕይወት ሊኖር እንደማይገባ የተቆጠረበት ጊዜ ነበር (የሐዋ. 22፡22)። ራሱ ጳውሎስም ሰዎች እንደ ዓለም ቆሻሻና የሁሉም ጥራጊ አድርገው የሚመለከቱት ሰው እንደነበር ተናግሯል (1ኛ ቆሮ. 4፡13)። ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ የተመረጠ ሐዋርያ የነበረው ጳውሎስ ምናልባትም በምድር ከኖሩት ክርስቲያኖች ሁሉ የበለጠ ሳይሆን አይቀርም!

እምነት የሰዎችን ድጋፍ ትተን የእግዚአብሔርን ድጋፍ እንድንሻ ያደርገናል። እግዚአብሔር ሕዝቡን በማዳን የሚከብር ከሆነ ያድናቸዋል። ነገር ግን ከገቡበት ችግር ሳያወጣቸው ቢቀር ባለማዳኑ የሚከብር ከሆነ፥ አያወጣቸውም። ሁኖም አንድ ክርስቲያን ከአንድ አደጋ አላመለጠም ማለት እምነት የለውም ወደሚል ድምዳሜ እንዳያደርሰን መጠንቀቅ አለብን።

እምነት ወደፊት አሻግሮ ይመለከታል። ከሁሉም የሚልቁ ሽልማቶች ያሉት እዚያ ነውና። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተዘረዘሩትም ሆኑ ያልተዘረዘሩ ሰዎች የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙም (ዕብ. 11፡13)። ነገር ግን አንድ ቀን ብድራታቸውን እንደሚከፍላቸው እግዚአብሔር ስለ እምነታቸው መስክሮላቸዋል። ዓላማው የብሉይንም ሆነ የአዲስ ኪዳን ቅዱሳንን የሚያጠቃልል ነው። እውነተኛ ቅዱሳን

ሁሉ በእምነት የጠበቋትን ሰማያዊት ከተማ አንድ ቀን ሁላችንም በጋራ እንወርሳለን።

በአስቸጋሪ ጊዜያት ታማኞች ሆነው የኖሩትን የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ልናመሰግናቸው ይገባል። ለእነርሱ ተስፋ የተገባላቸውን የተሻለውን በረከት ያገኘነው እኛ ነን። እነርሱ እነዚህን በረከቶች በርቀት ቢመለከቱም (ዮሐ. 8፡56 አንብብ)፥ እኛ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት የበረከቶቹ ተካፋዮች ሆነናል። የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን እግዚአብሔርን አምነው ፈቃዱን ባይፈጽሙ ኖሮ፥ እስራኤል የምትባል አገር በጠፋችና መሢሑም ባልተወለደ ነበር።

«ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም» (ዕብ. 11፡6)። ነገር ግን ቃሉን ስንሰማና (ሮሜ 10፡17) በአምልኮና በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ስናደርግ እምነታችን እየጠነከረ ይሄዳል። እምነት በሁሉም ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ ሁሉም አማኞች ሊኖራቸው የሚችሉት ነው። ለጥቂት ምርጥ ቅዱሳን የተሰጠ የተለየ ብፅዕና ሳይሆን፥ ለሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝብ መሠረታዊ ና አስፈላጊ ነገር ነው።

ጌታ ሆይ፥ እምነትን ጨምርልን!

# 11

# ሩጫህን ቀጥል

## ዕብራውያን 12

ሐዋርያው ጳውሎስ ዛሬ በሕይወት ቢኖር ኖሮ ምናልባት ከጋዜጦች በቅድሚያ የስፖርት ገፆችን በማንበብ የተለያዩ ቡድኖችንና አትሌቶችን እንቅስቃሴዎች ይከታተል ነበር። ለምን? ምክንያቱም በመልእክቶቹ ውስጥ ስለ አትሌቲክስ የጻፋቸው አሳቦች ስፖርትን እንደሚወድ ያመለክታሉ። በርግጥ ግሪኮችም ሆኑ ሮማውያን ለአትሌቲክስ ውድድሮች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጡ ነበር። ይህንንም የሚያደርጉት ለአካላዊ ጤንነታቸው በማሰብ ብቻ ሳይሆን፥ ለከተሞቻቸውና ለአገሮቻቸው ክብር ጭምር ነበር። ጥሩ አትሌት ሆኖ ለአገር ክብር ማምጣት የአገር ወዳድነት ምልክት ነበር።

የዕብራውያን ጸሐፊ በዚህ በ12ኛው ምዕራፉ የአትሌቲክስንና የዜግነትን ጭብጦች አጣምሮ አቅርቧል። ከክፍሉ የምንመለከተው የሩጫ ውድድርን ገለፃ ነው። ሯጮቹ የሥልጠና መሣሪያዎቻቸውን ወደ ጎን አድርገው ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ የሚጥሩበት ሁኔታ በዓይነ ሕሊናችን ይታየናል። አንዳንዶች ደክመው ሲዝሉ፥ ሌሎች ግን እስከ መጨረሻው በመጽናት የተዘጋጀውን ሽልማት ይቀበላሉ። ጸሐፊው መጀመሪያ ውድድሩን ይገልጽና (ዕብ. 12፡1-13)፥ ከዚያ በኋላ የሰማያዊቷን ከተማ ዜግነት አጽንኦት ሰጥቶ ያብራራል (12፡14-29)። በመሆኑም፥ በአንባቢያን አእምሮ ውስጥ እነዚህ ሁለት ነገሮች አብረው ይሄዳሉ። ምክንያቱም አንድ ሰው የአገሪቱ ዜጋ ሳይሆን በብሔራዊ ውድድሮች ሊሳተፍ ስለማይችል ነው።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምንመለከተው አንድ ጭብጥ ጽናት ነው። (12፡1፥ 2፥ 3፥ 7፤ በተጨማሪም 10፡32፥ 36 ተመልከት።) ይህን መልእክት የተቀበሉት የአይሁድ ክርስቲያኖች በእምነታቸው ደክመው ወደኋላ ለመመለስ ዳር ዳር እያሉ ነበር። ጸሐፊው ግን ተወዳዳሪ አትሌቶች በጽናት እንደሚሮጡት እነርሱም በክርስትና ሕይወታቸው ወደፊት እንዲገፉ አበረታቷቸዋል። (ፊልጵስዩስ 3፡12-14 አንብብ።) ለዚህም አንድ ክርስቲያን በሕይወቱ እንዳይበረታ የሚያውኩ ችግሮች በሚገጥሙት ጊዜ የሚያግዙትን ሦስት መለኮታዊ አጋዥ ነጥቦች ዘርዝሯል።

## 1. የእግዚአብሔር ልጅ ምሳሌ (12፥1-4)

የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ሳለሁ፥ እኔን አትሌት የማድረግ ቅናት የነበረው አሠልጣኝ ነበረኝ። በክፍሉ፥ ምናልባትም በትምህርት ቤቱ ውስጥ ከሁሉም ያነሰ የአትሌቲክስ ችሎታ እንደነበረኝ የታወቀ ስለነበረ፥ ሁሉም ተማሪ ሰውዬው ጊዜውን እያባከነ እንደነበረ ሳያስቡ አልቀሩም። ነገር ግን ትምህርት ቤታችን ለሚገኝባት ከተማ የመሰናክል ሩጫ እንድወዳደር አደረገኝ። በዚህ ጊዜ የግራ እግር ቁርጭምጭምቴን በመሰበሬና በውድድሩ ዝቅተኛ ውጤት በማምጣቴ፥ ስፖርት የሚባል ነገር እርግፍ አድርጌ ተውሁ። (ይህ ከሆነ ብዙም ሳይቆይ አሠልጣኙ የጦር ሠራዊት አባል ሆነ። ምናልባትም እኔው እሆናለሁ ወደዚሁ መስክ እንዲገባ ያደረግሁት።)

አሠልጣኜ ዎከር የተቻለኝን ሁሉ እንዳደርግ ለማገዝ አያሌ ዘዴዎች ተጠቅሟል። ከማበረታቻዎቹም መካከል፥ «ሌሎች ተማሪዎች እየቻሉት አንተን ሊያቅትህ አይችልም. . .ይህ ለአካላዊ ጤንነትህ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አስበው. . . ሌሎች ልጆች እንዴት እንደቻሉ ተመልከት» የሚሉ ይገኙባቸዋል። እነዚህ ሦስቱ ተመሳሳይ መንገዶች በክርስቲያናዊ ጉዟችን ያበረታቱን ዘንድ በዚህ አንቀጽ ውስጥ ተጠቅሰው መገኘታቸው አስደነቀኝ።

ሀ. <u>ሌሎች አሸናፊዎችን ዘወር ብለህ ተመልከት</u>! (12፥1)። በምዕራፍ 11 እንደ ደመና ያሉ እጅግ ብዙ ምስክሮች ቀርበውልናል። እነዚያ የእምነት ጀግኖች ናቸው። ይህ ማለት ግን እነዚህ የእምነት ጀግኖች እንደ ስታድዩም ተመልካቾች ሩጫችንን በሰማይ ተቀምጠው እየተመለከቱ ናቸው ማለት አይደለም። ምስክሮች የሚለው ቃል «ተመልካቾች» የሚል ፍች አይሰጥም። «ሰማዕት» የሚለው ቃል «ምስክር» ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ነው። እነዚህ ሰዎች የእኛን ጉዞ እየተመለከቱ ሳይሆን እግዚአብሔር ሊረዳን እንደሚችል እየመሰከሩልን ናቸው። እግዚአብሔር ስለመሰከረላቸው (ዕብ. 11፥2፥ 4-5፥ 39)፥ እነሱም አሁን ለእኛ በመመስከር ላይ ናቸው።

አንድ ጊዜ አንድ አማኝ፥ «ከመዝሙረ ዳዊትና መጽሐፈ ምሳሌ በቀር ብዙም ብሉይ ኪዳንን አላነብም» አለኝ።

«እንግዲያውስ፥ ትልቅ መንፈሳዊ ሀብት እያጎደልህ ነው ማለት ነው ስል መለስሁለትና፥ ሮሜ 15፥4ን ጮክ ብሎ እንዲያነብ ጠየቅሁት። «በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና።»

ከዚያም፥ ትዕግሥት ማለት መጽናት፥ መጽናናት ማለት ደግሞ መበርታት ማለት እንደሆነ ገለጽሁለት። ለመጽናናታችን እና ለመበርታታችን ለማሳደግ ከሚያግዙን እጅግ ጠቃሚ መንገዶች አንዱ የእምነትን ሩጫ ሩጠው ያሸነፉትን የብሉይ ኪዳን ሰዎች ማወቅ ነው። የቤተሰብ ችግር ካለብህ ስለ ዮሴፍ አንብብ። ሥራህ ከዓቅምህ በላይ መስሎ የሚታይህ ከሆነ የሙሴን ታሪክ አጥና። የበቀል ስሜት ካደረብህ፥ ዳዊት ይህንን ችግር እንዴት እንደተቋቋመ ተመልከት።

ለ. <u>ራስህን ተመልከት</u>! (ዕብ. 12፡2)። አትሌቶች ለውድድር ይረዳቸው ዘንድ ክብደት ያላቸውን ነገሮች ጨምረው ልምምዶቻቸውን ያካሂዱ ነበር። በውድድሩ ጊዜ ግን እነዚያን ሸክሞች ያስቀምጡ ነበር። ለዚህም ምክንያቱ ብዙ ክብደት ጉልበትን የሚያዝል መሆኑ ነው።

እኛስ በውድድሩ ለማሸነፍ ልናስወግዳቸው የሚገቡን ሸክሞች የትኞቹ ናቸው? ዕድገታችንን የሚያደናቅፉትን ነገሮች ሁሉ ማስወገድ አለብን። እነዚህ ነገሮች በሌሎች ሰዎች ዓይኖች ጥሩ ነገሮች ሊመስሉ ይችላሉ። አሸናፊ አትሌት ምርጫ ማድረግ ያለበት ጥሩ ባልሆነና በጥሩ መካከል ሳይሆን፥ በሚሻልና ምርጥ በሆነው ነገር መካከል ነው።

ቶሎ የሚከበንን ኃጢአትም ማስወገድ አለብን (12፡1)። ጸሐፊው የተወሰነ ኃጢአት በስሙ ጠቅሶ ባይናገርም፥ ለመጥቀስ የፈለገው ያለማመንን ኃጢአት ሳይሆን አይቀርም። እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዳይገቡ የከለከላቸው አለማመን ነበር። እኛም በክርስቶስ ያለንን ርስት እንዳንካፈል የሚያግደን አለማመን ነው። በምዕራፍ 11 ውስጥ «በእምነት» የሚለው ቃል 21 ጊዜያት ተደጋግሟል። ይህም እንድንጸና የሚያደርገን በክርስቶስ ላይ ያለን እምነት መሆኑን ያመለክታል።

ሐ. <u>ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከት</u>! (12፡2-4)። እርሱ የእምነታችን ራስ (መሥራች) እና ፈጻሚ ነው። «መመልከት» ማለት «ማመን» በመሆኑ፥ የዳንነው ወደርሱ በመመልከት ነው። ለሞት ያጣጥሩ የነበሩ አይሁዶች ከፍ ብሎ የተሰቀለውን የነሐስ እባብ በሚመለከቱበት ጊዜ ይፈወሱ ነበር። ይህም በክርስቶስ በማመን ለመዳናችን ምሳሌ የሚሆን ነው (ዘኁል. 21፡4-9፤ ዮሐ. 3፡14-16)። ወደ ክርስቶስ መመልከት የእምነት ምልክታ እንጂ ተራ እይታ አይደለም።

ጌታችን በምድር ላይ ሲመላለስ የኖረው በእምነት ነበር። የመለኮታዊና ሰብአዊ ባሕርያቱ ምሥጢር ከእኛ ግንዛቤ በላይ ቢሆንም፥ በዕለት ተዕለት አኗኗሩ በሰማይ የሚኖረውን አባቱን ይታመን እንደነበረ እንረዳለን። የዕብራውያን ጸሐፊ ጌታችን፥ «እኔ በእርሱ እታመናለሁ» ማለቱን ጠቅሷል (2፡13)። ጥቅሱ የተወሰደው

ከኢሳይያስ 8፡17 ነው። ኢየሱስ በምድር ሲመላለስ ወደ አብ መጸለዩን ያመለክታል።

ጌታችን በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ከተዘረዘሩት ከየትኞቹም የእምነት ጀግኖች በላይ በመከራ ጸንቷል። ስለሆነም፥ ልንከተለው የሚገባን ፍጹም ምሳሌያችን ነው። *የመስቀል ላይ ምትን መከራ ታግሦአል!* ይህም ኃፍረትን፥ *ሥቃይን*፥ የኃጢአተኞችን ተቃውሞና በአብ ለጊዜው መተውን ይጨምር ነበር። በመስቀል ላይ ለዓለም ሁሉ ኃጢአቶች በሙሉ መከራ ተቀብሏል! ነገር ግን በትዕግሥት አብ የሰጠውን ሥራ ፈጽሟል (ዮሐ. 17፡4)። ምንም እንኳ የዕብራውያን መልእክት አንባቢዎች የስደትን መከራ የተቀበሉ ቢሆኑም፥ ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወሙም ነበር (ዕብ. 12፡4)። ከእነሱ መካከል ለሰማዕትነት የተዳረገ አልነበረም። ኢየሱስ ግን ኃጢአትን በመቃወም ደሙን አፍስሷል።

ጌታችን የመስቀል ሥቃዩን ችሎ እንዲጸና ያደረገው ምንድነው? ጌታችን በምድር ላይ ያገለግል በነበረበት ወቅት መለኮታዊ ኃይሉን ለግሉ ጥቅሙ እንዳላዋለ አስተውል። ሰይጣን ይህንኑ እንዲያደርግ ቢፈትነውም (ማቴ. 4፡1–4)፥ ኢየሱስ ግን ፈቃደኛ አልሆነም። እንዲጸና ያደረገው እምነቱ ነበር። የእምነት ዓይኖቹን በፊቱ ካለው ደስታ ላይ አኖረ። መቃብሩን ፈንቅቅሎ እንደሚወጣ ከመዝሙር 16፡8–10 ያውቅ ነበር። (ጴጥሮስ በዕለተ በዓለ ኀምሳ በሰበከው ስብከት ውስጥ ይህንን መሢሐዊ መዝሙር ጠቅሷል። የሐዋ. 2፡24–33።) በዚህ መዝሙር ውስጥ (16፡11) ዳዊት በእግዚአብሔር መገኘት ስለሚያገኘው የተትረፈረፈ ደስታ ይናገራል። እንዲሁም ከመዝሙር (110)፡1 እና 4 ኢየሱስ በክብር ወደ ሰማይ እንደሚያርግ ያውቅ ነበር። (ጴጥሮስ ይህንንም መዝሙር ጠቅሷል። የሐዋ. 2፡34–36።) ስለሆነም፥ በፊቱ የነበረው ደስታ ኢየሱስ የአብን ፈቃድን መፈጸሙን፥ ትንሣኤውን፥ ዕርገቱንና ለአብ አማኞችን በክብር መወከሉን ያካትታል (ይሁዳ 24)።

በዚህ መልእክት ውስጥ ጸሐፊው *ስለ ወደፊቱ ተስፋ* አስፈላጊነት አጽንኦት ሰጥቶ ገልጾአል። አንባቢዎቹ *ወደ ኋላ ለመመልከትና ወደኋላ ለመመለስ* ያስቡ ነበር። ነገር ግን የክርስቶስን ምሳሌነት ተከትለው በእምነት ወደፊት አሻግረው እንዲመለከቱ ያበረታታቸዋል። በቀደመው ምዕራፍ ውስጥ የተዘረዘሩት የእምነት ጀግኖች በወደፊት የጊዜ ሰሌዳ ተመርተው በመኖራቸው ሊጸኑ ችለዋል። (ዕብ. 11፡10፥ 14–16፥ 24–27)። እንደ ጴጥሮስ ዓይኖቻችንን ከአዳኙ በምንነቅልበት ጊዜ፥ መስመጥ እንጀምራለን! (ማቴ. 14፡22–33)።

ክርስቶስ የእምነታችን ራስና ፈጻሚ ስለሆነ፥ በእርሱ ስንተማመን ወደ ሕይወታችን ይፈስሳል። የአንድን ታላቅ አትሌት ምሳሌነት ለዓመታት ስለተከተልኩ የዚያን አትሌት ድል የግድ አያጎናጽፈኝም። ነገር ግን በወጣትነት ዘመኔ ያ አትሌት በቅርቢ ሆኖ ምሥጢሩንና ችሎታውን ቢያጋራኝ ኑሮ፥ ያ ለአሸናፊነት ሊያበቃኝ በቻለ ነበር። ክርስቶስ ምሳሌያችን ብቻ ሳይሆን ኃይል የሚያስታጥቅ አዳኛችንም ነው! በቃሉ ውስጥ እርሱን ስንመለከትና ራሳችንን ለመንፈሱ አሳልፈን ስንሰጥ፥ እምነታችንን በመጨመር ሩጫችንን እንድንቀጥል ያስችለናል።

## 2. የእግዚአብሔር ፍቅር ዋስትና (ዕብ. 12፡5–13)

በዚህ ክፍል ቁልፉ ቃል *ቅጣት* የሚለው ነው። ቅጣት ተብሎ የተተረጎመው (የግሪኩ) ቃል፥ «ልጆችን ማሠልጠን፥ ማስተማር፥ ሥርዓት ማስያዝ» የሚል ፍች አለው። የግሪክ ልጆች ከብስለት ደረጃ ላይ እስኪደርሱ ድረስ በጂሚናዚዩም ውስጥ እንዲሠለጥኑ ይደረግ ነበር። ይህ ለጎልማሳነት ሕይወት የሚደረግ ዝግጅት አካል ነበር። ጸሐፊው አማኙ በክርስትና ሕይወት የሚገጥሙት መከራዎች እንዲያድግ የሚያግዙት መንፈሳዊ ዲስፕሊኖች እንደሆኑ ያመለክታል። ስለሆነም፥ ከእነዚህ ችግሮች ለመሸሽ ከመፍጨርጨር ይልቅ በሕይወታችን እናድግ ዘንድ «ልንለምዳቸው» ያስፈልጋል (12፡11)።

መከራ በምንቀበልበት ጊዜ እግዚአብሔር እንደማይወደን ማሰቡ ይቀናናል። ስለሆነም፥ ጸሐፊው ቅጣት አፍቃሪው አባት ከፍቅሩ የተነሣ በሕይወታችን የሚያመጣው መሆኑ ለማሳየት ሦስት መረጃዎችን ያቀርባል።

ሀ. ቅዱሳት መጻሕፍት (12፡5–6)። ጥቅሱ የተወሰደው ከምሳሌ 3፡11–12 ሲሆን፥ አንባቢዎቹ የሚያውቁትና አሁን ጊዜ የዘነጉት ነው። (ቃሉን መስልቸት ከሚያስከትላቸው አሳዛኝ መዘዞች አንዱ ይኼ ነው። ዕብ. 5፡11–12 አንብብ።) ይህ ጥቅስ (12፡5–6) በቀጥታ ሲተረጎም «ማበረታቻ» የሚል ፍች ያለው ምክር ነው። አንባቢዎቹ ቃሉን በመርሳታቸው፥ ማበረታቻውንም ረስተው ወደ ኋላ ለመመለስ እየተፈተኑ ነበር!

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ቁልፍ ቃላት፥ «ልጅ» እና «ልጆች» የሚሉ ናቸው። እነዚህ ቃላት በዕብራውያን 12፡5–8 ውስጥ ስድስት ጊዜ አገልግለዋል። ሕጻን ልጁን በተደጋጋሚ የሚቀጣ አባት እንደ ጨካኝ ሊታይ ይችላል። እኛ ግን በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ በማደጎነት አድገን የአዋቂነት ደረጃ ስለተሰጠን የምንቀጣውም እንደ አዋቂ ልጆች ነው (ሮሜ 8፡14–18፤ ገላ. 4፡1–7 አንብብ።) አብ እኛን መቅጣቱ

በሕይወታችን እየበሰልን መሆናችንን የሚያመለክት ሲሆን፥ ይበልጥ እየበሰልን የምንመጣውም የእግዚአብሔርን ቅጣት በመቀበል ነው።

ቅጣት የእግዚአብሔር አባታዊ ፍቅር መግለጫ ነው። ሰይጣን በሕይወታችን ውስጥ ችግሮች መከሰታቸው እግዚአብሔር እኛን ባለመውደዱ ምክንያት እንደሆነ ሊያሳምነን ቢሞክርም፥ እውነቱ ግን የዚህ ተገላቢጦሽ መሆኑን እናስተውል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር እኛን የሚቀጣው፥ በሚናገረን የተግሳጽ ቃልና በሕይወታችን እንዲከሰቱ በሚፈቅዳቸው ሁኔታዎች ነው። ሌላ ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔር በአካላዊ ሥቃይ ውስጥ እንድናልፍ በማድረግ ይቀጣናል። በምንም ዓይነት ሁኔታ ብናልፍ የቅጣት እጁ በአፍቃሪ ልቡ የሚገዛ እንደሆነ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። እርሱ የሚፈልገው ሞልቃቃ ሕጻናት እንድንሆን ሳይሆን፥ የሕይወትን ኃላፊነቶች ለመሸከም የምንችልና ለአደራ የምንበቃ በሳል ልጆቹ እንድንሆንለት ነው።

ለ. የግል ተሞክሮ (ዕብ. 12፥7-11)። ሁላችንም ምድራዊ አባት አለን። ይህ አባት ታማኝ ከሆነ፥ ልጆቹን የመቅጣት ኃላፊነት እንዳለበት እናውቃለን። ልጅ ሳይቀጣ ስድ ከተለቀቀ ዱርዬ ይሆናል። ጸሐፊው ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት (ቁ. 7-8)፥ አባት የሚቀጣው የራሱን ልጆች ብቻ መሆኑን ሲሆን፥ ይህ ደግሞ ልጆቹ የእርሱ መሆናቸውን ያረጋግጣል። የጎረቤቶቻችንን ልጆች ለመቅጣት ብንፈልግ እንኳ ሥልጣኑ የለንም። እግዚአብሔር እኛን ሲቀጣ ልጁ መሆናችንን ማስተማመኛ እየሰጠን ነው።

በአገልግሎት ዘመኔ ተቀጥተው የማያውቁ ክርስቲያን ነን ባዮች አጋጥመውኛል። እግዚአብሔርን ሳይታዘዙ ቀርተው እንኳን ከቅጣት አምልጠዋል። እኔ ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየተቃወምሁ ካልተቀጣሁ አልጻንሁም ብዬ እፈራለሁ። የእግዚአብሔር እውነተኛ ልጆች ሁሉ ቅጣቱን ይቀበላሉ። ድነናል እያሉ የማይቀጡት ግን ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደሉም።

መልካም ምድራዊ አባቶች ልጆቻቸውን የሚቀጡት ለምንድነው? የሚቀጡት ልጆቻቸው እንዲያከብሯቸውና ትእዛዛቸውን እንዲፈጽሙላቸው ነው። የሰማዩ አባታችንም የሚቀጣን ለዚሁ ማለትም እንድናከብረውና ፈቃዱን እንድንታዘዝ ነው። ለበላይ መገዛትን ያልተማረ ልጅ ጠቃሚና አዋቂ ሰው ወደመሆኑ ደረጃ ሊደርስ አይችልም። በሥልጣኑ ላይ የሚያምፁ የእግዚአብሔር ልጆች ራሳቸውን ከሞት አደጋ ሥር ይጥሉታል! «እንዴትስ ይልቅ ለመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛና በሕይወት ልንኖር በተገባን?» (12፥9)።

የጸሐፊው መልእክት ለእግዚአብሔር ካልታዘዝን በሕይወት የመኖር እድላችንን ልንነጠቅ እንችላለን የሚል ነው። ለሞት የሚያደርስ ኃጢአት እንዳለ አንዘንጋ (1ኛ ዮሐ. 5፡16)።

አሁን ይህ 12ኛ ምዕራፍ በመጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙ አምስት ምክሮች ጋር እንዴት እንደሚዛመድ እንመለከታለን። አንድ ክርስቲያን ከቃሉ ሲንሸራተትና ወደ ኋላ ሲመለስ፥ ሰማያዊ አባት የሳተውን ልጁን ወደ መገዛትና ታዛዥነት ይመልሰው ዘንድ ይቀጣዋል። በእግዚአብሔር የቅጣት ሥነ ሥርዓት ያላለፈ ሰው እውነተኛ ዳግም ልደት እንዳገኘ ሊቆጠር አይችልም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመቃወም ከጸና፥ ምናልባትም እግዚአብሔር በሞት ሊቀጣው ይችላል። ይህም ሕይወትን ይበልጥ እንዳያበላሽና እግዚአብሔርንም እንዳያሰድብ ለማድረግ ሲል ነው። እግዚአብሔር በሺዎች የሚቆጠሩ ዓመፀኞች እስራኤላውያንን በምድረበዳ ላይ በሞት ከቀጣቸው (1ኛ ቆሮ. 10፡1–12)፥ በእኛ ላይ ይህን እንዳያደርግ ማን ያግደዋል? ምንም እንኳ ይህ የተለመደ የእግዚአብሔር የቅጣት መንገድ ባይሆንም፥ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ግን መደረጉ የማይቀር ነው። ስለሆነም፥ የሚቀጣን ቅዱስ ባሕርዩን እንካፈል ዘንድ ለራሳችን ጥቅም እንደሆነ ተረድተን፥ እግዚአብሔርን ልንፈራና ልናከብር ይገባል።

ሐ. <u>የተባረኩ ውጤቶች</u> (ዕብ. 12፡11–13)። የትኛውም ቅጣት ለወላጅም ሆነ ለልጅ አስደሳች አይደለም። ውጤቶቹ ግን ጠቃሚዎች ናቸው። ወላጆቻቸው፥ ስለ ፍትሕ ስቀጣህ የሚሰማህ ሕመም ለአንተ ከሚሰማህ የጠለቀ ነው ሲሉ፥ ልጆቻቸው እንደማያምኗቸው እርግጠኛ ነኝ። ነገሩ ግን እውነት ነው። አባቱ ልጆቹን በመቅጣቱ አይደሰትም። ነገር ግን በኋላ ቅጣቱ የሚያመጣቸው መልካም ፍሬዎች ቅጣቱ የፍቅሩ መገለጫ እንደሆነ ያስመሰክራሉ።

የቅጣት መልካም ፍሬዎች ምን ዓይነት ናቸው? በመጀመሪያ ደረጃ፥ «የሰላም ፍሬ እርሱም ጽድቅ» ነው። ከቅጣት በኋላ ልጅ ልክ የሆነውን ነገር ለማድረግ ጥረት ያደርጋል! በጠበኝነት ፈንታ ሰላማዊ ይሆናል። አመጸኝነት አብቅቶ ልጁ ከአባቱ ጋር የፍቅር ኅብረት ዳግም ይመሠርታል። በተጨማሪም፥ ቅጣት ልጁ በቃለ እግዚአብሔር፥ በጸሎት፥ በማሰላሰል፥ ምስክርነትና በመሳሰሉት መንፈሳዊ ተግባራት እንዲተጋ ያበረታታዋል። ይህ ሁሉ አዲስ የሆነ ደስታን ወደልቡ ያመጣለታል። ጳውሎስ፥ «. . . ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ. . .» (ሮሜ 14፡17) ሲል ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚገባ በኅብረት መኖር የሚያመጣልንን ፍሬ መግለጹ ነው።

አንድ የእግዚአብሔር ልጅ ለቅጣቱ ምላሽ የሚሰጥበት መንገድ በጣም ወሳኝ ነው። ቅጣቱን ማቃለል ወይም በድካም መዛል (ዕብ. 12፡5) ተገቢ ምላሽ አይደለም። ቅጣቱን ለመንፈሳዊ ተግባር እንደሚያገለግል ጠቃሚ መሣሪያ ተጠቅሞ፥ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሱን በማስገዛት አክብሮቱን ማሳየት አለበት (ቁ. 11 እና 1ኛ ጢሞ. 4፡7–8)። በቁጥር 12 እና 13 የሚገኙት ትእዛዛት አሠልጣኝ ለቡድኑ የሚሰጣቸውን ትእዛዛት ይመስላሉ። እጆቻችሁን አጽኑ! ጉልበቶቻችሁን አበርቱ! (ኢሳ. 35፡3)። የእግርህን መንገድ አቅና! (ምሳሌ 4፡26)። እናም ወደፊት ገስግሱ! የሚሉት ናቸው።

የእግዚአብሔር ልጅ ምሳሌና የእግዚአብሔር ፍቅር ማረጋገጫ አስቸጋሪውን ክርስቲያናዊ ሩጫ እንድንቀጥል ሊያበረታቱን ይገባል። ሌላም ሦስተኛ አጋዥ ነጥብ አለ።

## 3. የእግዚአብሔር ጸጋ ማስቻል (ዕብ. 12፡14–29)

ክርስቲያናዊ ሩጫን ስንሮጥ ከፊት ለፊታችን የተቀመጠው ግብ ምንድን ነው? ጸሐፊው በቁጥር 14 ላይ እንደገለጸው፥ ግቡ ከሰዎች ሁሉ ጋር ሰላምን መከተል ና በእግዚአብሔር ፊት በቅድስና መመላለስ ነው። (ሰላማዊ የጽድቅ ፍሬ፥ ቁ. 11።) እነዚህ ሁለት የዓላማ ግቦች የጌታችንን ሊቀ ካህናዊ አገልግሎት ማለትም የሰላምና የጽድቅ ንጉሥ የመሆኑን እውነታ ያስገነዝቡናል (7፡1–2)። ከእግዚአብሔር ጸጋ ሳንወድቅ (12፡15) የተሳካ ሩጫ መሮጥ ትጋትን የሚጠይቅ ነገር ነው። የእግዚአብሔር ጸጋ የሚያልቅ ወይም የሚነጥፍ ባይሆንም፥ እኛ ግን በራሳችን ድክመት በጸጋው ሳንጠቀም ልንቀር እንችላለን። በምዕራፉ መጨረሻ ላይ በጸጋ ላይ ተጨማሪ ትኩረት ተሰጥቷል (ቁ. 28)።

በዚህ ክፍል፥ ጸሐፊው አንባቢያኑ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ እንዲደገፉ አበረታቷል። ይህንንም ያደረገው በእምነት ወደ ሦስት አቅጣጫዎች እንዲመለከቱ በማስገንዘብ ነው።

ሀ. <u>ወደ ኋላ ተመልከቱ – የዔሳው መጥፎ ምሳሌነት</u> (12፡15–17)። ዔሳው የእርሱ ሊሆን ይችል የነበረውን የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመጠቀም ሳይችል ቀርቷል። ታሪኩ በዘፍጥረት 25፡27–34 እና 27፡30–45 ተገልጾአል። ዔሳው «ለዓለም የሚመች» ተራና ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለዓለም የሚኖር ሰው ነበር። («ለዓለም የሚመች» ለሚለው ሐረግ የዋለው የእንግሊዝኛ ቃል ዱፕርሆፍ ን ዲ ሲሆን፥ በቀድሞው ትርጉም «ከቤተ መቅደስ ውጭ» ወይም «የእግዚአብሔር ያልሆነ» የሚል ፍች ተሰጥቶታል። ዔሳው የብኩርና መብቱን ንቆ ለያዕቆብ በመሸጡ፥ በረከትን አጥቷል።

(በረከቱ ለያዕቆብ እንደሚሰጥ የተነገረ ቢሆንም፥ ያዕቆብ በማታለል መቀበሉ ተገቢ አልነበረም። ዘፍጥረት 25፡19–26 አንብብ።) ከዚያ በኋላ፥ ዔሳው የአባቱን የይስሐቅን አሳብ ለማስለወጥ ቢሞክርም፥ አንዱ ስላመለጠው እንባውን እያፈሰሰ ብኩርናውን መልሶ ለማግኘት ያደረገው ሙከራ ሊሳካለት አልቻለም።

የማስቻል ኃይል የሚሠጠንን የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚቀሙን የትኞቹ ኃጢአቶች ናቸው? በዚህ ክፍል ላይ እንደምንመለከተው፥ የመንፈሳዊ ትጋት ጉድለትና በሌሎች ላይ መራራ መሆን (ዘዳግ. 29፡18 አንብብ)፥ እንዲሁም ወሲባዊ እርኩሰት፥ ለዓለምና ለሥጋ መኖር ጸጋችንን ይቀማሉ። አንዳንድ ሰዎች ለዓለም የተመቸ ሰው ማለት ተሳዳቢና በግብሩ የጎደፈ ሰው እንደሆነ ያስባሉ። ነገር ግን ዔሳው ጥሩ ባሕርይ የነበረው አዳኝና አባቱን የሚወድ ሰው ነበር። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ጥሩ ጎረቤት ሊሆን የሚችል ግሩም ሰው ቢሆንም፥ ለእግዚአብሔር ነገር ደንታ አልነበረውም።

የእግዚአብሔር ጸጋ አስተማማኝ ቢሆንም፥ እኛ ግን በጸጋው ላይ ባለመደገፍ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ረገድ ጎደሎዎች ልንሆን እንችላለን። ዔሳው ለተራ ነገሮች እንዳንኖር ማስጠንቀቂያ ይሆነናል።

ለ. ወደላይ ተመልከት – የሰማያዊቷ ከተማ ክብር (12፡18–24)። የዕብራውያን ጸሐፊ የሲናን ተራራና የሕጉን መሰጠት፥ ከሰማያዊቷ የጽዮን ተራራና በቤተ ክርስቲያን የጸጋ በረከቶች ጋር ያነጻጽራል። (ዘጸ. 19፡10–25፤ 20፡18–21፤ ዘዳግ. 4፡10–24 አንብብ።) ጸሐፊው ሕጉ በተሰጠበት ጊዜ የነበሩትን አስፈሪ ክስተቶች ፍርሃቶችና አስገዳጅ ሁኔታዎችን ሽብሮች ሳይቀሩ ገልጾአል (ዕብ. 12፡18–21)። በዚያን ጊዜ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ድምፅ ለመስማት ፈሩ። ሙሴም እንኳ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ውስጥ ነበር። እግዚአብሔር በተራራው ዙሪያ ድንበር አድርጎ ነበርና በዚያ በኩል የሚያልፍ ሰውም ሆነ እንስሳ እንዲገደል ወስኖ ነበር። እግዚአብሔር የሕጉን ታላቅነት በሕዝቡ አእምሮ ውስጥ ማስረጽ ነበረበት። ይህም እኛ ለልጆቻችን ልናደርግ የሚገባው ነገር ነው። ይህ የሆነው እስራኤል ገና ለጋ በነበረችበት ወቅት ነበር። እንደሚታወቀው፥ ልጆች ሽልማትና ቅጣትን ምን ማለት እንደሆኑ አሳምረው ያውቃሉ።

ከሲና ተራራ ወደ ጽዮን ተራራ መሸጋገር ምንኛ እፎይታ የሚሰጥ ነገር ነው! ሲና አሮጌውን የሕግ ቃል ኪዳን፥ ጽዮን ግን በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘውን የአዲስ ኪዳን ጸጋ ታመለክታለች። (ገላ. 4፡19–31 አንብብ።) ሰማያዊቷ ከተማ የእግዚአብሔር ጽዮን ተራራ (መዝ. 110፡1–2፥ 4 እና መዝ. 2 አንብብ።) እና የእምነት አባቶች በእምነት

የተጠባበቋት ከተማ ናት (ዕብ. 11፥10፥ 14-17)። ምድራዊቷ ኢየሩሳሌም በሮማውያን መፈራረሷ የማይቀርላት ሲሆን፥ ሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ግን ለዘላለም ትኖራለች።

ጸሐፊው የዚህች ከተማ ነዋሪዎች የሆኑት ዜጎች እነማን እንደሆኑ ገልጾአል። ስፍር ቁጥር የሌላቸው መላእክት በዚያ ይኖራሉ። አማኞች የሰማይ ዜጎች ስለሆኑና (ፊልጵ. 3፥20) ስማቸው በሰማይ ስለተጻፈ (ሉቃስ 10፥20)፥ ቤተ ክርስቲያን እዚያ ትኖራለች። ብኩርና የትጋትና የደረጃ ማዕረግ ነው። ዔሳው የይስሐቅ የበኩር ልጅ ቢሆንም፥ በረከቱንና ብኩርናውን አጥቷል።

እግዚአብሔር፥ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን («ፍጹማንም ወደሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች») እና ደሙን ለእኛ ያፈሰሰውና የመካከለኛነትን አገልግሎት የሚሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ ይገኛሉ። አቤል አሁንም እየተናገረ መሆኑን ቀደም ብለን ተመልክተናል (ዕብ. 11፥4)። በሰማያዊቷ ከተማ ከአቤል ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደ ደም መርጨት እንደርሳለን (12፥24)። የአቤል ደም ከምድር ለፍትሕ ሲጮኽ (ዘፍጥ. 4፥10)፥ የክርስቶስ ደም ከሰማይ ሆኖ ለኃጢአተኞች ምሕረትን ያውጃል። የአቤል ደም ቃይን የበደለኝነት ስሜት እንዲሰማው በማድረግ በጭንቀት እንዲኮበልል ሲያደርግ (ዘፍጥ. 4፥13-15)፥ የክርስቶስ ደም ግን እኛን ከበደለኝነት ስሜት ነፃ በማውጣት ወደ እግዚአብሔር መገኘት መቅረብ እንድንችል መብት ሰጥቶናል። የአዲስ ኪዳን ደም ባይፈስ ኖሮ፥ ወደዚህች ሰማያዊት ከተማ ለመግባት አንችልም ነበር!

አንድ ወዳጄ፥ «ስለ መንግሥተ ሰማይ ብዙ ስብከትና ትምህርት የማይሰጠው ለምን ይሆን?» ሲል ጠየቀኝና ጥያቄውን ራሱ መለሰው። «ምድራዊ ሕይወት ስለተመቸን፥ ስለ መንግሥተ ሰማይ የምናስብ አይመስለኝም» ሲል ምዕራባውያንን አስመልክቶ ትክክለኛ አሳብ ተናግሯል።

ዘመናት ሲከፉና ለመጽናት ስንቸገር፥ ዓይኖቻችንን አንስተን የሰማዩን ክብር ማሰብ አለብን። ሙሴ ብድራቱን ትኩር ብሎ በመመልከቱ (ዕብ. 11፥27)፥ ያጋጠመውን መከራ በጽናት ተወጥቷል። የእምነት አባቶች እግዚአብሔር ከተማን እያዘጋጀላቸው መሆኑን ሲገነዘቡ በእምነታቸው ጸንተዋል። የእግዚአብሔርን ጸጋ በሕይወታቸው ለመለማመድ ከተጠቀሙባቸው መንገዶች አንዱ እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን ድንቅ የወደፊት ሕይወት በእምነት አሻግሮ መመልከት ነበር።

ሐ. <u>ወደፊት ተመልከት - የማይናወጥ መንግሥት</u> (12፡25-29)። ዛሬ እግዚአብሔር በቃሉና በዓለም ውስጥ በሚያካሂዳቸው መግቦታዊ ተግባራት እየተናገረን ነው። እኛም ብንሰማው ይበጀናል! እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ነገሮችን ካናወጠና ቃሉን ባልፈለጉ ሰዎች ላይ ፍርድ ከበየነ፥ ዛሬ የአዲስ ኪዳንን በረከቶች የተቀበልን እኛስ ምን ያህል ከባድ ኃላፊነት ተጥሎብናል! ዛሬም እግዚአብሔር ነገሮችን እያናወጠ ነው። (በመገናኛ ብዙሃን የምንሰማው ይሄንኑ ነው?) በዚህም የውሸት ተግባሮቻችንን ለማጋለጥና እውነተኛና ዘላለማዊ እውነታዎችን ለመግለጥ ይፈልጋል። ክርስቲያኖችን ጨምሮ ብዙ ሰዎች ሕይወታቸውን በፈራሽ-መሠረቶች ላይ ማነጻቸው የሚያሳዝን ነገር ነው።

ስለ መናወጥ የሚናገረው አሳብ የተገኘው ከሐጌ 2፡6 ሲሆን፥ ጌታ ዳግም ተመልሶ ቤቱን በክብር ስለሚሞላበት ጊዜ ይናገራል። ጊዜው እየቀረበ ሲሄድ በዓለማችን ውስጥ ተጨማሪ መናወጦችን እናያለን። ክርስቲያን ግን የማይናወጠውን መንግሥት ስለሚቀበል፥ በልበሙሉነት ሊመላለስ ይችላል። ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንግሥት አካል መሆኑ ብርታትን ይሰጠዋል።

ስለዚህ በሚናወጥ ዓለም ውስጥ የምንኖረው እኛ፥ እግዚአብሔር የሚናገረውን ስምተን ልንታዘዘው ይገባል። እርሱን በአክብሮትና በመንፈሳዊ ፍርሃት ማገልገል እንችል ዘንድ ዕለት በዕለት ጸጋውን ልንቀበል ያሻል። በዙሪያችን የምናያቸው ድንገተኛ ለውጦች ትኩረታችንን ሊያዛቡም ሆነ ሊያስፈራሩን አይገባም። አይታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ማረፍ አለበት፤ ሩጫውንም በጽናት መሮጥ አለብን። መመልከታችንን መቀጠል አለብን። አባታችን እንደሚወድን በማስታወስ የሚያስችል ጸጋውን ልንላበስ ይገባል።

ሌሎች በፍርሃት ሲናወጡ፥ አንተ ግን ታምነህ ልትሰማራ ትችላለህ!

## 12

# እምነታችሁ ፍሬ እያሳየ ነው

ዕብራውያን 13

ይህንን የመጨረሻ ምንባብ በምታነብበት ጊዜ፥ ደራሲው የሚያስተላልፋቸው የተለያዩ አሳቦች እንደነበሩትና ሁሉንም ለመጨረሻው ክፍል እንዳቆየ ልትገነዘብ ትችላለህ። በምዕራፍ 12 በጽዮን ተራራ ላይ ስላለው ደስታ እያወጋን ነበር። እዚህ ደግሞ እንደ እንግዳ ተቀባይነት፥ ጋብቻ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና እስረኞች በመሳሰሉት ዕለታዊ ጉዳዮች ላይ እንነጋገራለን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን በአስተምህሮና ግዴታን በመወጣት፥ በመገለጥና በኃላፊነት መካከል ልዩነት የለም። ሁልጊዜም ሁለቱ አብረው ይሄዳሉ። በዚህ የመጽሐፉ የመጨረሻ ክፍል ውስጥ ትኩረት የተሰጠው በእምነት በመኖር ላይ ነው። ጸሐፊው በምዕራፍ 11 የታላላቅ የእምነት ጀግኖችን ምሳሌዎች፥ በምዕራፍ 12 ደግሞ የእምነት ማበረታቻዎችን አቅርቧል። በምዕራፍ 13 በማየት ሳይሆን በእምነት በምንመላለስበት ጊዜ በሕይወታችን የሚከሰቱትን የእምነት መረጃዎች ገልጾአል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንደዚህ ዓይነት አራት ማስረጃዎች ተጠቅሰዋል።

### 1. በመንፈሳዊ ኅብረት ደስ መሰኘት (13፥1–6)

የመንፈሳዊ ኅብረት መሠረቱ፥ ወንድማዊ ፍቅር ነው። ክርስቲያን አማኞች እንደመሆናቸው፥ እነዚህ ዕብራውያን በማያምኑ ጓደኞቻቸውና ዘመዶቻቸው የተገለሉ መሆናቸው አያጠራጥርም። ነገር ግን የጠለቀው ኅብረት በዘር ወይም በቤተሰባዊ ግንኙነት ላይ ሳይሆን፥ በክርስቶስ ባለን መንፈሳዊ ሕይወት ላይ የተመሠረተ ነው። ለክርስቶስና ለእርስ በርስ ካለው ፍቅር ውጭ በሚገኝ በሌላ በማንኛውም ዓይነት ነገር ላይ፥ የተመሠረተ የቤተ ክርስቲያን ኅብረት ዕድሜ አይኖረውም። ስለ ወንድማማችነት ፍቅር፥ ሮሜ 12፥10፥ 1ኛ ተሰሎንቄ 4፥9–10፤ 1ኛ ጴጥሮስ 1፥22 እና 2ኛ ጴጥሮስ 1፥7 አንብብ።

እውነተኛ ክርስቲያናዊ ፍቅር በሰፈነበት ስፍራ እንግዳ ተቀባይነትም ይኖራል (ዕብ. 13፥2)። በስደት ምክንያት ብዙ ክርስቲያኖች ከቤታቸው ይፈናቀሉ ስለነበር እንግዳ ተቀባይነት በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አቢይ ስፍራ የሚሰጠው አገልግሎት ነበር። እንዲሁም ደግሞ፥ የማረፊያ ስፍራ የሚፈልጉ ተጓዥ አገልጋዮችም ነበሩ (3ኛ ዮሐ. 5–8)። ድሀ ክርስቲያኖች ለሆቴል የሚከፍሉት

ገንዘብ ስላልነበራቸውና አብያተ ክርስቲያናት የሚሰባሰቡት በግለሰብ ቤቶች ውስጥ ስለነበር (ሮሜ 16፡5)፥ የእንግዳው በተቀባዩ ቤት ማረፍ የተለመደ ነገር ነበር። በተለይ መጋቢያን እንግዳ ተቀባይነትን ሊወዱ እንደሚገባ የተገለጸ ሲሆን (ቲቶ 1፡8)፥ ቅዱሳን ሁሉ ይህንኑ ተግባር ልማዳቸው ሊያደርጉት ይጠበቅባቸዋል (ሮሜ 12፡13)።

ሙሴ (ዘፍጥ. 18) አብርሃም፥ ኢየሱስ ክርስቶስንና ሁለት መላእክትን በእንግድነት እንደተቀበለ ገልጾአል። አብርሃም እንግድነት በተቀበላቸው ጊዜ ማንነታቸውን አላወቀም ነበር። እንግዶቹ ምን ያህል የከበሩና ታላላቅ እንደሆኑ የተገነዘበው ገና ቆይቶ ነበር። ሊሆን አይችልም ባይባልም፥ እኔና አንተ መላእክትን በእንግድነት አንቀበልም ይሆናል። ነገር ግን በጌታ ፍቅር የምንቀበለው ማንኛውም እንግዳ፥ ለእኛ የበረከት መልእክተኛ ሊሆን ይችላል። (መልአክ መልእክተኛ ማለት ነው።) ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ሆነው የተገኙትን እንግዶች በቤታችን ሳናስተናግድ አልቀረንም ይሆናል።

ፍቅር ለሌሎች በማሰብም ይገለጻል (ዕብ. 13፡3)። ክርስቲያኖች ለእምነታቸው ተይዘው መታሰር አዲስ ነገር አይደለም። ከእነዚህ እስረኞች ጋር አብሮ መሆኑና እገዛ መስጠቱ አደገኛ ሊሆን ቢችልም፥ ለእነዚህ ወገኖች እናገለግል ዘንድ የክርስቶስ ፍቅር ያስገድደናል። ክርስቲያንን በክርስቶስ ስም ማገልገል፥ ክርስቶስን ራሱን ማገልገል ነው (ማቴ. 25፡36፥ 40)። ነፃ በሆኑ አገሮች ውስጥ የሚኖሩ ምዕራባውያን በእምነታቸው ምክንያት አይታሰሩም። በሌሎች የዓለም ክፍሎች ግን ክርስቲያኖች በእምነታቸው ምክንያት ይታሰራሉ። ስለሆነም፥ ክርስቶስ በረዳን መጠን ለእነዚህ ወገኖች መጸለይና መከራቸውን መካፈል አለብን!

ክርስቲያናዊ ፍቅር ተግባራዊ የሚሆንበት የመጀመሪያው ስፍራ ጋብቻ ነው (ዕብ. 13፡4)። ክርስቲያናዊ ጋብቻ በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመሠረት ነው። ይህም የታማኝነትንና የንጽሕናን አስፈላጊነት ያጎላል። ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸም ወሲብ ኃጢአት ና አጢፊም ነው። በጋብቻ ውስጥ የሚካሄድ ወሲብ ግን ተጋቢዎቹን የሚያረካ ና እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሊሆን ይችላል። ሴሰኝነትና መዳራት ባላገቡት ሰዎች የሚፈጸም ሲሆን፥ አመንዝራነት ባገቡት ዘንድ የሚፈጸም ኃጢአት ነው። (በአዲስ ኪዳን ግን ሴሰኝነት የተለያዩ ወሲባዊ ኃጢአቶችን ሊያመለክት ይችላል። የሐዋርያት ሥራ 15፡20 እና 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡18 አንብብ።)

እግዚአብሔር በሴሰኞችና አመንዝራዎች ላይ የሚፈርደው እንዴት ነው? አንዳንድ ጊዜ በሥጋዎቻቸው ይፈረድባቸዋል (ሮሜ 1፡24-27)።

በመጨረሻው የፍርድ ጊዜም ይፈረድባቸዋል (ራእይ 21፡8፤ 22፡15)። እነዚህን ኃጢአቶች የሚፈጽሙ ክርስቲያኖች ይቅርታን ሊያገኙ ቢችሉም፥ በሰማይ ሽልማቶች ይቀሩባቸዋል፤ (ኤፌ. 5 ከቁጥር 5 ጀምሮ)። ዳዊት ለኃጢአቱ ይቅርታ ቢያገኝም፥ መዘዞቹ ለዓመታት አልለቀቁትም ነበር። ስለዚህ የገዛ ልጆቹ አበሳ አብዝተውበታል።

ወሲባዊ ኃጢአቶች በፊልምና በቴሌቪዥን ላይ እንደ መዝናኛ በሚስተጋቡበት በአሁኑ ወቅት ቤተ ክርስቲያን ለጋብቻ ንጽሕና ጠንካራ አቋም መውሰድ ይኖርባታል። ለእግዚአብሔር የተሰጠ ክርስቲያናዊ ቤተሰብ በምድር ላይ ለሰማይ እጅግ የቀረበ ሲሆን፥ ይህም የሚጀምረው በክርስቲያናዊ ጋብቻ ነው።

እግዚአብሔርንና ሌሎችን እንደሚገባን ብንወድ፥ በቁሳዊ ነገሮች ልባችን አይወሰድም (ዕብ. 13፡5-6)። የመከራ ጊዜያት የአገልግሎት ወይም የራስወዳድነት ጊዜያት ሊሆኑ ይችላሉ። «የገንዘባችሁን ንጥቂያ በደስታ» (10፡34) መቀበል ቀላል አይደለም። ነገር ግን ዛሬ በዓለማችን ውስጥ ካለው የኢኮኖሚና የአካባቢ ችግር ሳቢያ፥ በጸሎት የሚኖሩ ክርስቲያኖች እንደ መሠረታዊ ነገሮች የሚቆጥሯቸውን አንዳንድ ምቾቶች መተው ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

ክርስቲያን የሆኑ ባልና ሚስት በምሥራቅ አውሮፓ በኮምዩኒዝም አገሮች ውስጥ በማገልገል ላይ ነበሩ። እነዚህ ባልና ሚስት ለአማኞቹ ክርስቲያናዊ ሥነ ጽሑፎችን፥ ብርድ ልብሶችንና ሌሎች ጠቃሚ ነገሮችን ያድሉዋቸው ነበር። አንድ ቀን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባለትዳሮቹ አሜሪካውያን በምሥራቅ አውሮፓ ለሚገኙ አማኞች እንደሚጸልዩ ነገሩአቸው።

በዚህ ጊዜ አንድ አማኝ ተነሥቶ፥ «ስለ እኛ መጸለያችሁ ደስ ይለናል። ነገር ግን በአሜሪካ የሚገኙ ክርስቲያኖች ከእኛ በላይ ጸሎት የሚያስፈልጋቸው ይመስለናል። እኛ እዚህ በምሥራቅ አውሮፓ እየተሠቃየን ነው፤ እናንተ ግን በምቾት ትኖራላችሁ። ሁልጊዜም በምቾት በምንኖርበት ጊዜ ጥሩ ክርስቲያን መሆኑ አስቸጋሪ ነው» ሲል ልብ የሚነካ ነገር ተናገረ።

ምኞት የገንዘብ ፍቅርን የሚያመለክት ቃል ነው። ነገር ግን የትኛውንም ነገር በተጨማሪ ለማግኘት የሚደረገውን ሩጫ ሊያመለክት ይችላል። አንድ ሰው የናጠጠውን ባለጸጋ በርናርድ ባሮክን፥ «ሀብታም ሰው ምን ያህል ገንዘብ ቢያገኝ ይረካል?» ብሎ ቢጠይቀው ባሮክ፥ «ካለው በላይ የአንድ ሚሊዮን ጭማሪ ብቻ» ሲል መልሶለታል። ምኞት አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝም ባይገኝም ተጨማሪ ነገሮችን መፈለግ ነው።

ቁሳዊ ነገሮች የሰውን ልብ ስለማይሞሉ፥ ሊያረኩ አይችሉም። እርካታን የሚሰጠን እግዚአብሔር ብቻ ነው። «የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ፤ ከመጎምጀትም ሁሉ ተጠበቁ» (ሉቃስ 12፡15)። እግዚአብሔር ካለን የሚያስፈልገን ሁሉ አለን ማለት ነው። ቁሳዊ ነገሮች ሊበላሹ ወይም ሊሰረቁ ይችላሉ። እግዚአብሔር ግን ምን ጊዜም አይጥለንም፤ አይተወንምም። ኢያሱ ሙሴን በተካው ጊዜ ይህ የተስፋ ቃል ተሰጥቶት ነበር (ዘዳግ. 31፡7-8፤ ኢያሱ 1፡5፥ 9)። ለእኛም በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጽሞልናል (ማቴ. 28፡20፤ የሐዋ. 18፡9-10)።

በዕብራውያን 13፡6 ላይ የሚገኘው የእምነት ማጽኛ ከመዝሙር (118)፡6 የተወሰደ ነው። ይህ መሢሐዊ መዝሙር በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጻሚነትን ስላገኘ፥ ለራሳችን እንደ ተሰጠ የተስፋ ቃል አድርገን ልንጠቀምበት እንችላለን። ለቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች ሰዎችን ከመፍራት ነፃ መሆናቸውን ማወቃቸው ታላቅ የሰላም ምንጭ ነበር። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ማንም ምንም ሊያደርጋቸው አይችልምና። ሰዎች ሀብቶቻቸውን ሊነጥቁአቸው ቢችሉም፥ እግዚአብሔር ግን የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ያሟላላቸዋል።

አንዲት ሴት ለዲ. ኤል. ሙዲ፥ «በምፈራበት ጊዜ የሚረዳኝን የተስፋ ቃል አግኝቻለሁ። ይህም በመዝሙር 56፡3፥ ሐእኔ ግን ፈራሁ፤ በአንተም ታመንሁመ የሚለው ነው» ስትል ተናዘዘች።

ሙዲም፥ «እኔ ከዚያ የተሻለ የተስፋ ቃል አለኝ! በኢሳይያስ 12፡2፥ ዮበእርሱ ታምኜ አልፈራምመ የሚል ቃል አለ» ሲሉ መለሱላት።

ሁለቱም የተስፋ ቃሎች እውነት ሲሆኑ፥ ሁለቱም ከሕይወታችን ጋር የሚዛመዱበት መንገድ አላቸው። ዋናው ነገር ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታችንና እንደ ረዳታችን ማወቃችንና በቁሳዊ ነገሮች አለመታመናችን ነው። የረኩ ክርስቲያኖች ቅድሚያ የሚሰጧቸው ነገሮች ያሏቸው ሲሆኑ፥ ቁሳዊ ነገሮች በእነሱ መዝገብ ውስጥ የቀዳሚነቱን ሚና አይጫወቱም።

## 2. ለመንፈሳዊ አመራር መገዛት (ዕብ. 13፡7-9)፥ 17፥ 24።

ጸሐፊው «ዋኖቻችሁ» የሚለውን ቃል ሦስት ጊዜ ደጋግሞታል። ይህ ቃል የሚያመለክተው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ መሪዎች ነው። ቤተ ክርስቲያን አካል ብትሆንም፥ ድርጅትም ነች። አንድ አካል ካልተደራጀ ይሞታል! ጳውሎስ በሄደባቸው ስፍራዎች ሁሉ አብያተ ክርስቲያናትን ከመሠረተ በኋላ፥ ይመሯቸው ዘንድ ብቃት ያላቸውን ክርስቲያኖች ይሾም ነበር። (የሐዋ. 14፡23፤ ቲቶ

1፥6)። ኤጲስ ቆጶሳት፥ ዲያቆናትና ቅዱሳን (ፊልጵ. 1፥1) በአዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት አባልነትና አመራር ተጠቃልለዋል።

እያንዳንዱ ክርስቲያን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ለሚገኙ መንፈሳዊ መሪዎች ሦስት ኃላፊነቶች አሉት።

ሀ. አስቧቸው (ዕብ. 13፥7–9)። «አስቡ» የሚለው ቃል እነዚህ መሪዎች እንደ ሞቱ፥ ምናልባትም እንደ ተገደሉና መዘንጋት እንደሌለባቸው የሚያመለክት ይሆናል። በሥራዎቻቸውና በመሥዋዕቶቻቸው ዛሬ እንድናገለግል ያስቻሉትን የቀድሞ ቀራጥ ክርስቲያኖች መዘንጋቱ ቀላል ነው። ሰዎችን ማምለክና ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን ክብር መስጠት ልክ አይደለም። በታማኝነት ስላከናወኗቸው ተግባራት ምስጋና ልንነፍጋቸው አይገባም (1ኛ ተሰ. 5፥12–13)።

ምናልባትም የመልእክቱን አንባቢዎች ወደ ክርስቶስ ያመጧቸው እነዚሁ መሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ምክንያቱም እነዚህ መሪዎች ለሰዎቹ የእግዚአብሔርን ቃል ተናግረዋልና። በዚያን ጊዜ ብዙ ክርስቲያኖች የግል መጽሐፍ ቅዱስ እንዳልነበራቸው ስትገነዘብ፥ እንዲህ ዓይነቱ ቃሉን የማገልገል ተግባር ምን ይህል ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ጉዳይ እንደነበር ልትረዱ ትችላላችሁ። ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስን ራሳችን ልናጠና፥ የሬድዮና የቴሌቪዥን፥ እንዲሁም የካሴት ስብከቶችን ልንከታተል እንችላለን። ቃሉን በቀላሉ ማግኘት መቻላችን ቃሉን እንደዋዛ እንድንመለከት እየተፈታተነን ነው።

አማኞቹ በሞት የተለዩአቸው መሪዎች ሲናገሩ ሊሰሙ ባይችሉም፥ እምነታቸውንና ፍሬውን ወይም ፍጻሜውን ሊከተሉ ይችሉ ነበር። ይህም ከመሪዎቻቸው አንዳንዶቹ በሰማዕትነት መገደላቸውን ሊያመለክት የሚችል አሳብ ነው። እኔ እንደማምነው፥ የእነዚህ መሪዎች «የእምነት ፍሬ (13፥7)» በቁጥር 8 ተመልክቷል! «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።» ሕይወታቸው ወደ ክርስቶስ ያመለክታል! የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይመጣሉ! ይሄዳሉም። የእምነታችንም እምብርት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ግን ዛሬም ለዘላለም ያው ነው።

ለረዥም ዓመታት ሳገለግል ከቆየሁባት ቤተ ክርስቲያን ለመልቀቅ እንዳሰብኩ ለሃላፊው ስገልጽ፥ «ያለ አንተ እንዴት እንደማደርግ አላውቅም! ለመንፈሳዊ እርዳታ አንተ ላይ በጣም እደገፍ ነበር» ሲል ገለጸልኝ።

የእኔ ምላሽ ግን የጠበቀው አልነበረም። «እንደዚያ ከሆነ፥ እኔ ከቤተ ክርስቲያን ቶሎ ብለቅ ይበጅሃል። ፈጥነህ በጌታ ላይ መደገፍን

ትማራለህ ማለት ነው። ሕይወትህን በምንም ዓይነት በአገልጋይ ላይ አትመሥርት። ሕይወትህን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ መሥርት። እርሱ ከቶውንም አይለወጥም።»

በርግጥ ሁልጊዜም በተለያዩ እንግዳ በሆኑ ትምህርቶች የመወሰድ አደጋ ያጋጥማል (13፡9)። የመንፈሳዊ አገልግሎት ዓላማ ሰዎች በአደገኛ አስተምህሮዎች እንዳይወሰዱ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ መመሥረት ነው (ኤፌ. 4፡11–14)። ከዕብራውያን መልእክት ተቀባዮች አንዳንዶቹ የምግብ ሥርዓቶች ወደሚገኙባቸው የአይሁድ ሕግጋት ለመመለስ ያስቡ ነበር። ጸሐፊው እነዚህ ሥርዓቶች እንደማይጠቅሟቸው በመግለጽ ያስጠነቅቃቸዋል! የምግብ ሕግጋት ለሰዎች መንፈሳዊ ነገሮችን መስለው ቢታዩም ቢያስደንቁም፥ ነገር ግን አሁን በክርስቶስ ያገኘነውን እውነታ የሚያመለክቱ ጥላዎች ብቻ ነበሩ። (ቆላስይስ 2፡16–23ን በጥንቃቄ አንብብ።)

አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መጋቢዎችን በሚለውጡበት ጊዜ አስተምህሮዎችን ወይም አስተምህሮአዊ ትኩረቶችን የመለወጥም አደጋ ሲከሰት ይታያል። ነገር ግን ከተጻፈው ከእግዚአብሔር ቃል አልፈን እንዳንሄድ መጠንቀቅ አለብን። እንዲሁም ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ መሠረት እንዳንለውጥ መጠንቀቅ አለብን። መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የብርታትና የዕድገት ምንጭ ሆኖ ሳለ ዛሬ በዶክትሪናዊ ትምህርት ላይ ትኩረት አለመሰጠቱ አሳዛኝ ነገር ነው። ታዋቂ የብሪታኒያ ኮንግሪጌሽናል ሰባኪ የሆኑት ዶክተር አር. ደብልዩ. ዴይል፥ «በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች ላይ ተከታታይ ትምህርት ለአማኞች መስጠት ጀምሬአለሁ» ሲሉ ለአንድ ወዳጃቸው ነገሩዋቸው። ወዳጃቸውም፥ «እንዲህ ዓይነቱን ትምህርት አይቀበሉም» ሲሉ መለሱ። ዴይል፥ «ባይወዱም ይቀበሉታል!» ሲሉ ትክክለኛ ምላሽ ሰጥተዋል።

ለ. አክብሯቸው (ዕብ. 13፡17)። የእግዚአብሔር አገልጋይ የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማረ በፈቃዱ በሚመላለስበት ጊዜ፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊገዛለትና ሊታዘዘው ይገባል። ይህ ማለት ግን መጋቢዎች አምባገነኖች መሆን አለባቸው ማለት አይደለም። ማኅበሮቻቸውን በኃይል መግዛት የለባቸውም (1ኛ ጴጥ. 5፡3)። አንዳንድ ምእመናን የመጋቢነትን ሥልጣን እንደ ዋዛ ያዩታል። ይህ ደግሞ አደገኛ ነው። አንድ ቀን እያንዳንዱ መጋቢ ስለ አገልግሎቱ ለእግዚአብሔር ምላሽ ለመስጠት ይገደዳል። እያንዳንዱ መጋቢ በደስታ ይህንን ምላሽ ለመስጠት ይፈልጋል። በዚያን ጊዜ ለመታዘዝ የማይፈልግ ክርስቲያን የእምቢተኝነቱ ውጤቶች የሚጎዱት መጋቢውን ሳይሆን ራሱን እንደሆነ ይገነዘባል።

እውነቱን ለመናገር መንጋውን ከመጠበቅ ይልቅ (ሕዝ. 3፡16–21) ነፍሳትን ወደጌታ ማምጣት በጣም ቀላል ነው። አንዲት ቤተ ክርስቲያን እየተስፋፋች በምትሄድበት ጊዜ ለበጎቹ እንክብካቤ ማድረጉ ይበልጥ አስቸጋሪ እየሆነ ይሄዳል። አንዳንድ አገልጋዮች በስብከትና «ፕሮግራሞችን በማካሄድ» ላይ ብቻ ጊዜያቸውን መጨረሳቸው አሳዛኝ ነገር ነው። ይንከባከቧቸው ዘንድ የተሰጧቸውን ነፍሳት ዞር ብለው አይመለከቱም። አንዳንዶች እንዲያውም ለገንዘብ ብቻ የሚሠሩ «ቅጥረኞች» በመሆናቸው፥ አደጋ ሲመጣ የሚሸሹ ናቸው (ዮሐ. 10፡11–14)። ነገር ግን አንድ እረኛ በታማኝነት ነፍሳትን በሚንከባከብበት ጊዜ፥ በጎቹ እሱን መታዘዛቸው አስፈላጊ ነው።

ሐ. *ሰላምታ አቅርቡላቸው* (ዕብ. 13፡24)። አይሁዶች፥ «ሻሎም – ሰላም!» በመባባል ሰላምታ የመለዋወጥ ልማድ ነበራቸው። ግሪኮች ደግሞ የ«ጸጋ» ሰላምታ የመለዋወጥ ልማድ ነበራቸው። ጳውሎስ እነዚህ ሁለቱን በማቀላቀል፥ «ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን» ብሏል (ከ1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ እና ከቲቶ በቀር በመልእክቶቹ ሁሉ፥ እንዲሁም በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡3፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 1፡2 ጳውሎስ ለመጋቢዎች ሲጽፍ፥ «ጸጋ፥ ሰላምና ምሕረት» እንዲሆንላቸው መመኘቱ ለምን ይሆን?)

የዕብራውያን ጸሐፊ ሰላምታውን የሚያስተላልፈው ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበር። ይሁንና፥ ይህ ሁላችንም ልንከተለው የሚገባን መልካም ምሳሌ ነው። እያንዳንዱ ክርስቲያን ከመጋቢው ጋር ሰላማዊ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል። በልብህ ውስጥ ምንም ዓይነት መራርነት እንዲኖር አትፍቀድ (ዕብ. 12፡15)። ይህ አንተን ከመመረዝና ቤተ ክርስቲያንን ከመጉዳት ያለፈ ሚና አይኖረውም።

እያንዳንዱ የአጥቢያ አካል የሚያከናውነው ጠቃሚ ተግባር እንዳለው የሚታወቅ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር መንፈሳዊ መሪዎችን ለቤተ ክርስቲያን እንደሾመም መገንዘብ ይኖርብናል። በበኩሌ፥ በአሜሪካ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የመስበክ ዕድል አግኝቻለሁ። ከዚህ ልምድ እንደተገነዘብሁት፥ ሕዝቡ መጋቢዎች ወይም ሽማግሌዎች እንዲመሩት በሚፈቅድበት ጊዜ፥ ባብዛኛው በረከትና ዕድገት እንደሚከሰት ተረድቻለሁ። ይህን የምለው በራስወዳድነት መንፈስ ወደ አምባገነንነት ስለሚከንፉት መሪዎች ሳይሆን፥ ስለ እውነተኛ መንፈሳዊ መሪዎች ነው። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የወጠነው የአሠራር መንገድ ይህ ነው።

## 3. መንፈሳዊ አምልኮን መካፈል (13፡10–16፥ 18–19)

የአዲስ ኪዳን ክርስቲያን የመገናኛውን ድንኳን ወይም የቤተ መቅደሱን ሥርዓቶች ባያካሂድም፥ እነዚህ ሥርዓቶች የሚያመለክቷቸውን በረከቶች መቀበሉ ግን ግልጽ ነው። በአሮጌው ኪዳን ሥር የሚገኝ አይሁዳዊ በቤተ መቅደሱ ሊመካም ሆነ፤ ሊያመለክት ይችላል። ክርስቲያን ግን ከቶውንም የማትጠፋ ሰማያዊት ቤተ መቅደስ አለችው። አይሁዶች በኢየሩሳሌም ከተማ ይኩራሩ ነበር፤ ክርስቲያን ግን ዘላለማዊት የሆነች አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከተማ አለችው። የብሉይ ኪዳን አማኝ በሚጠቀምባቸው ጊዜያዊናምድራዊ ዕቃዎች አንፃር የአዲስ ኪዳን አማኝ ሰማያዊና ዘላለማዊ አቻዎች አሉት።

«መሠውያ አለን» (13፡10) ሲል በምድር ላይ ቁሳዊ መሠውያ እንዳለን አያመለክትም። ምክንያቱም ይህ መንገድ የመልእክቱን ጠቅላላ ሃሳብ ይቃረነዋል። በብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደስ፥ የነሐስ መሠውያ የደም መሥዋዕቶች የሚቀርቡበት ስፍራ ነበር። ከመጋረጃው ፊት የሚገኘው የወርቅ መሠውያ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር የሚያርግ ጸሎት ምሳሌ የሆነው የዕጣን ማጠኛ ነበር (መዝ. 141፡2)። የአዲስ ኪዳን ክርስቲያን መሠውያ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። መንፈሳዊ መሥዋዕቶቻችንን ወደ እግዚአብሔር የምናቀርበው በእርሱ በኩል ነው። (ዕብ. 13፡15፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡5)። በቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎቻችን ውስጥ ስፍራዎችን ለይተን መሠውያዎች ልንል ብንችልም፥ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አተረጓጎም መሠውያዎች አይደሉም። ለምን? ምክንያቱም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የክርስቶስ መሥዋዕት ተፈጽሟል። ለእግዚአብሔር የምናመጣቸው ስጦታዎች ተቀባይነት የሚያገኙትም በምድራዊ መሠውያ ምክንያት ሳይሆን፥ ሰማያዊ መሠውያ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ምክንያት ነው።

ይህ ክፍል የሚያተኩረው ከሙት ሃይማኖት ተለይቶ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነቀፋን መካፈል እንደሚያስፈልግ ነው። አሳቡ የተወሰደው ከስርየት ቀን ነው። የኃጢአት መሥዋዕቱ ከሰፈር ውጭ ተወስዶ ሙሉ በሙሉ ይቃጠል ነበር። (ዘሌ. 16፡27)። እንደዚሁም ፍጹም የኃጢአት መሥዋዕታችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ የተቀበለውና የሞተው ከኢየሩሳሌም በር ውጭ ነበር። እውነተኛ ክርስቲያኖች ሁሉ ወደርሱ መሄድ አለባቸው። ይህም በመንፈሳዊ አገላለጽ የነቀፌታና በሰው የመገለል ስፍራ ነው። ጸሐፊው፥ «ኢየሩሳሌም ከተማችሁ እስካልሆነች ድረስ ለምን በዚያ ትቆያላችሁ? ክርስቶስ ካስወገደው በኋላ ለምን ከብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳን ጋር ትተባበራላችሁ?» ሲል ይጠይቃል።

የዚህ መልእክት ተቀባዮች ከማያምኑ አይሁዶች የሚመጣውን ስደት እየሸሹ ክርስቲያን እንደሆኑ መቀጠል የሚችሉበትን መንገድ በመፈለግ ላይ ነበሩ። ጸሐፊው ግን ይህ ሊሆን እንደማይችል ይነግራቸዋል። «ኢየሩሳሌም ጠፍታለች። ከአይሁድ የሃይማኖት ሥርዓት ውጡና ለእናንተ ከሞተው አዳኝ ጋር ተባበሩ።» ማመቻመች የሚቻልበት ስፍራ አይኖርም።

ጸሐፊው እንደ ክርስቲያኖች ልናቀርባቸው የሚገቡንን ሁለት መሥዋዕቶች ጠቅሷል (ዕብ. 13፡15–16)። መንፈሳዊ ነገር የቁሳዊው ተቃራኒ ሆኖ እንደ ተገለጸ ከዚህ ክፍል መመልከት ይቻላል። ምክንያቱም ቁሳዊ ስጦታዎችን እግዚአብሔር እንደ መንፈሳዊ መሥዋዕቶች ሊቀበላቸው ይችላል። (ፊልጵ. 4፡10–20 አንብብ።) «መንፈሳዊ» የሚለው ቃል መንፈስ ቅዱስ ለመንፈሳዊ ዓላማዎች ይጠቀምበት ዘንድ መንፈሳዊ ባሕርይ ያለው ማለት ነው። ለእግዚአብሔር የቀረበ የአማኝ ሰውነት መንፈሳዊ መሥዋዕት ነው (ሮሜ 12፡1–2)።

የመጀመሪያው መንፈሳዊ መሥዋዕት ባለማቋረጥ እግዚአብሔርን ማመስገን ነው (ዕብ. 13፡15)። ከልባችን የሚመጡ የምስጋና ቃላት በመሠውያ ፊት እንደ ቀረበ ግሩም ፍሬ ይጥማሉ። መከራ ለሚቀበሉ ክርስቲያኖች ማጉረምረሙ እንዴት ቀላል ነው! ነገር ግን መከራ የሚቀበሉ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረባቸው እጅግ አስፈላጊ ነው።

ሁለተኛው መንፈሳዊ መሥዋዕት መልካም ማድረግና ለሌሎች ማካፈል ነው (ቁ. 16)። ይህ በቁጥር 2 እና 3 የተጠቀሱትን የእንግዳ ተቀባይነትና እስረኞችን የመጠየቅ ተግባራት እንደሚያጠቃልል አይጠረጠርም። «መልካም ማድረግ» ብዙ የአገልግሎት ዘርፎችን ሊያካትት ይችላል። ከእነዚህም መካከል ለድሆች ምግብን ማካፈል፥ የመጓጓዣ አገልግሎት መስጠት (ወደ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ወደ ሌሎች ስፍራዎች)፥ ገንዘብን ማካፈል፥ ምናልባትም ጥሩ ጎረቤት ብቻ መሆን ሊጠቀሱ ይችላሉ። አንድ ጊዜ አንድ ሰውዬ የሣር ማጨጃ ማሽን በመበላሸቱ ምክንያት የእኔን ማሽኑ ስላዋስሁት ወደ ክርስቶስ ሲመጣ ተመልክቻለሁ።

ከዚያም ጸሐፊው ለጸሎት አስፈላጊነት ትኩረት ሰጥቷል (ቁ. 18–19)። አንባቢያኑን በአካል ለመጎብኘት ባይችልም፥ የጸሎት እገዛቸውን ይጠይቃል። አንዳንድ ጠላቶቹ ስለ እርሱ ውሸትን ስለ ተናገሩ፥ እውነተኛነቱን ያረጋግጥላቸዋል። የዕብራውያን ጸሐፊ ማን እንደ ነበር በርግጠኝነት አናውቅም። ብዙዎች ጳውሎስ እንደ ሆነ ይገምታሉ።

በቁጥር 23 የጢሞቴዎስ ስም መጠቀሱና በቁጥር 25 የጸጋ ቡራኬ መስጠቱ ይህንን አሳብ የሚያጠናክር ይመስላል። (2ኛ ተሰሎንቄ 3፡17–18 አንብብ።) አንዳንድ ምሁራን ጴጥሮስ የዕብራውያንን መልእክት ጳውሎስ እንደጻፈ ጠቁሞአል ይላሉ (2ኛ ጴጥ. 3፡15–16)። ያ አሳብ ግን ጳውሎስ በሮሜ መልእክት ውስጥ የጻፋቸውን ነገሮችም የሚመለከት ሊሆን ይችላል። ስለሆነም፥ ይህንን መጽሐፍ ማን እንደጻፈው አናውቅም። የጸሐፊውን ስም ማወቃችንም አስፈላጊ አይደለም።

## 4. መንፈሳዊ ጌትነት (ዕብ. 13፡20–21)

ይህ የማሳረጊያ ቡራኬ እንደ ሰላም፥ የክርስቶስ ትንሣኤ፥ ደም፥ ቃል ኪዳን፥ መንፈሳዊ ፍጹምነት (ብስለት)፥ እግዚአብሔር በአማኝ ሕይወት ውስጥ የሚሠራው ሥራ ያሉትን ዐበይት የዕብራውያን መልእክት ጭብጦች ጠቅለል አድርጎ የሚያቀርብ ይመስላል። እንደ መልካም እረኛ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ለበጎቹ ሞቷል (ዮሐ. 10፡11)። እንደ ታላቅ እረኛ፥ ዛሬ ለበጎቹ እየሠራ በሰማይ ይኖራል። እንደ ዋና እረኛ፥ በዳግም ምጽአት ለበጎቹ ይመጣላቸዋል (1ኛ ጴጥ. 5፡4)። ከዚህ በፊት፥ አሁንም ሆነ ወደፊት እረኞችን ለበጎቹ ያስባል። እርሱ ትናንት፥ ዛሬና ለዘላለም ያው ነው!

ታላቁ ሊቀ ካህናችን ታላቁ እረኛችንም ነው። በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ታላቅ የደኅንነት ተግባር አከናውኖልናል (ዮሐ. 17፡4)። አሁንም በሰማይ ሆኖ በፈቃዱ እንድንኀለብትና ወደ መንፈሳዊ ፍጹምነት እንድንደርስ ለማድረግ በውስጣችን ይሠራል (1ኛ ዮሐ. 2፡28–3፡3)። ነገር ግን እርሱ እስኪመለስ ድረስ ከዚያ ደረጃ ላይ ልንደርስ አንችልም (1ኛ ዮሐ. 2፡28–3፡3)። ጸሐፊው የእርሱን መምጣት እየተጠባበቅን እንድናግ ይመክረናል።

«ፍጹማን ያድርጋችሁ» (ዕብ. 13፡21) «ካታርቲዞ» (katartidzo) የሚለው የግሪክ ቃል ትርጉም ነው። በሕክምና መስክ፥ ይህ ቃል «የተሰበረውን አጥንት መጠገን» የሚል ፍች ይሰጣል። ለዓሣ አጥማጆች፥ «የተቀደደ መረብ መጠገን» የሚል ፍች ይሰጣል። (ማቴ. 4፡21 አንብብ።) ለመርከበኞች፥ «መርከብን ለጉዞ ተስማሚ ማድረግ» ማለት ነው። ለወታደሮች፥ «ሠራዊትን ለጦርነት ማዘጋጀት» የሚል መልእክት ያስተላልፋል።

በሰማይ ያለው አዳኛችን በምድር ላይ ላለው ሕይወት ብቁ ሊያደርገን ይፈልጋል። ፍሬያማ ሕይወት እንመራ ዘንድ፥ አዳኛችን በሕይወታችን ውስጥ የተሰበሩ አጥንቶችን ለመጠገን ይፈልጋል። የመረቦቹን ቀዳዳ በመጠገን ዓሦችን እንድንይዝና ሰዎችን ለእርሱ

እንድናጠምድ ይሻል። በሕይወት ማዕበሎች እንዳንዝል ለውጊያው ብቁ ሊያደርገን ይፈልጋል። በአጭሩ፥ ደስ የሚያሰኘውንና ፈቃዱን የሚፈጽመውን ተግባር በእኛ ውስጥና በእኛ አማካኝነት ያካሂድ ዘንድ ጠንካሮች እንድንሆንለት ይሻል።

የሚያስታጥቀን እንዴት ነው? በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህንኑ ካታርቲዞ የተሰኘ ቃል የሚገኝበትን ክፍል በማጥናት፥ እግዚአብሔር ልጆቹን ለማስታጠቅና በሳሎች ለማድረግ የሚጠቀምባቸውን መሣሪያዎች ልናውቅ እንችላለን። እግዚአብሔር በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት ውስጥ (ኤፌ. 4፡11-12)፥ ቃሉን (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17) እና ጸሎትን (1ኛ ተሰ. 3፡10) ይጠቀማል። እንዲሁም ግለሰብ ክርስቲያኖችን ይጠቀማል (ገላ. 6፡1)። በመጨረሻም፥ እግዚአብሔር ልጆቹን ፍጹማን ለማድረግ መከራን ይጠቀማል። ይህም በዕብራውያን ምዕራፍ 12 ውስጥ ከተማርነው ጋር ይዛመዳል።

ዕብራውያን 13፡20-21ን በየቀኑ ግላዊ ብናደርግ፥ በሕይወታችን ውስጥ ምን ያህል ታላቅ ለውጥ ይከሰት ይሆን? «ጌታ ሆይ፥ ፈቃድህን አደርግ ዘንድ በመልካም ነገር ሁሉ ፍጹም አድርገኝ። በፊትህ ደስ የሚያሰኘውን በሕይወቴ ውስጥ አድርግ። ይህንን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት በሕይወቴ ፈጽም። ክብሩንም እርሱ ይውሰድ።»

የዚህ ድንቅ ሥራ መሠረቱ የዘላለማዊ ቃል ኪዳን ደም ነው (ቁ. 20)። ይህም በምዕራፍ 8 ውስጥ የተመለከትነውና በዕብራውያን ምዕራፍ 10 ውስጥ በቀረበው መሥዋዕት ላይ የተመሠረተ አዲስ ኪዳን ነው። ይህ አዲስ ቃል ኪዳን የእግዚአብሔር ዘላለማዊ የደኅንነት ዕቅድና የዘላለምን ሕይወት ዋስትና ስለሚሰጥ፥ «ዘላለማዊ ቃል ኪዳን» ተብሏል። ነገር ግን ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በዚህ ታላቅ ቡራኬ ውስጥ የቀረቡትን በረከቶች ልንቋደስ አንችልም።

ከቡራኬው መጨረሻ ላይ የሚገኘው «አሜን» የዕብራውያን መልእክቱን የሚቋጭ ነው። በቀረው ጸሐፊው ሰላምታና የግል መረጃዎችን አክሏል።

ጸሐፊው በረዥም መልእክቱ ውስጥ አንዳንድ መሠረታዊና ጥቅል አስተምህሮዎችን አቅርቧል። ስለሆነም፥ አንባቢያኑ ይህንን የምክር ቃል እንዲታገሡ ያበረታታቸዋል። ይህ ለኛ ረዥም መልእክት ቢመስልም፥ ጸሐፊው ግን «ጥቂት ቃል» ይለዋል። ይህንን መልእክት አንዳንዶች እንደተቃወሙትና ሌሎች ግን ደግፈው ተግባራዊ እንዳደረጉት አያጠራጥርም። ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ቃል እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለብን ይነግረናል (1ኛ ተሰ. 2፡13)። ይኸውም

ቃሉን በጥንቃቄ አንብበን ተግባራዊ ማድረግ እንዳለብን ይነግረናል (1ኛ ተሰ. 2፡13)። ይህንን ጥቅስ በጥንቃቄ አንብበህ ተግባራዊ አድርገው።

ጢሞቴዎስ ከመልእክቱ ተቀባዮች ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት እንደ ነበረው አናውቅም። በወቅቱ ታላቅ አገልጋይ ስለ ነበር አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ወይም በግል ባያውቁት እንኳ በዝና ስለርሱ ሊሰሙ እንደሚችሉ መገመት እንችላለን። እንዲህ ዓይነቱ ግላዊ ትስስር እግዚአብሔር የተባበሩትን ብቻ ሳይሆን ግለሰቦችንም በተናጠል እንደሚፈልግ ያስገነዝበናል።

«ከኢጣሊያ የሆኑቱ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል» (ቁ. 24)። ይህም ጸሐፊው ኢጣሊያ እንደ ነበረ፥ ወይም ከኢጣሊያ የመጡ ቅዱሳን ከእርሱ ጋር እንደነበሩና ለሚጽፍላቸው ወገኖች ሰላምታ ለማስተላለፍ እንደ ፈለጉ ሊያመለክት ይችላል።

እነዚህ ከደብዳቤው መጨረሻ ላይ የሚገኙ የግል ማጣቀሻዎች አሁን ልንመልሳቸው የማንችላቸውን ጥያቄዎች ያስነሣሉ። ነገር ግን የዕብራውያን መልእክት፥ «እየታወከ ባለው ዓለም ውስጥ እንዴት በእምነቴ ልጸና እችላለሁ?» የሚለውን ዋንኛ ጥያቄ ይመልሳል። መልሱም፥ የሚበልጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እወቅ፤ የሚበልጥ ሊቀ ክህነቱን እመን፤ በሚበልጠው የእምነት መርህ ተመላለስ የሚል ነው። መቼም ቢሆን ሊናወጡ በማይችሉ ሰማያዊ ነገሮች ላይ ሕይወትህን መሥርት።

በማየት ሳይሆን በእምነት ተመላለስ! ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አዳኝ ነው!

## የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አንድ

# የሚሰማ ሰው አለ?

ዕብራውያን 1፥1–3

1. በመስማትና በትክክል በማዳመጥ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

2. «በክርስትና ሕይወት፥ ወደፊት ካልገሰገስክ ወደኋላ መሄድህ አይቀርም። ለዘለቄታው ባለህበት ልትረግጥ አትችልም» ከሚለው አሳብ ጋር ትስማማለህ?

3. እግዚአብሔር ልጆቹ እንዲበላሹ አይፈቅድም ብለናል። የተበላሸ ክርስቲያን ባሕርያት ምንድን ናቸው?

4. ዛሬ ከእግዚአብሔር ይልቅ የምንታመንባቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?

5. ዌርዝቢ የዕብራውያን መልእክት የፍተሻ መጽሐፍ ነው ብለዋል። እምነታችን ምኑ ጋ እንዳለ እንድንመረምር ይረዳናል። አንዳንድ ጊዜ ሕይወታችንን እንዳንመረምር የሚያደርገን ምንድን ነው?

6. አብርሃም ዋጋ ሊሰጣቸው የሚገቡ ነገሮችን የሚያውቅ ሰው ስለነበር ጥቅም ፍለጋ ከመሮጥ ታቅቧል። በሌላ በኩል፥ ሎጥ ለጊዜያዊ ጥቅም ራሱን ሰጥቷል። በዛሬው ዓለም የአብርሃምና የሎጥ ምሳሌዎች ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን ዘርዝር።

7. የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ፥ ክርስቶስ ሰው ብቻ እንዳልሆነ ለማረጋገጥ ሞክሯል። ክርስቶስ ተራ ሰው ወይም ነቢይ ብቻ መሆኑን ብታውቅ በሕይወትህ ውስጥ ምን ዓይነት ነገር ሊከሰት የሚችል ይመስልሃል?

8. ዘፍጥረት 1፥26ን፣ ዮሐ. 1፥1–14ን እና ቆላስይስ 1፥13–17 አንብብና ክርስቶስ ከትስእብት በፊት ምን ሚና እንደነበረው ግለጽ።

9. ቶዘር፥ «እያንዳንዱ ሰው የራሱን ዓለም መምረጥ አለበት» ብሏል ይባላል። አንዳንድ ጊዜ ከምድራዊ መንግሥት ይልቅ ሰማያዊ መንግሥትን መምረጥ ፈታኝ የሚያደርጉብን ነገሮች ምንድን ናቸው?

# ምዕራፍ ሁለት

## ከመላእክት በላይ

ዕብራውያን 1:4–2:18

1. ዛሬ መላእክት በዓለማችን ውስጥ ምን ዓይነት ተግባራትን የሚያከናውኑ ይመስልሃል?
2. አንድ ትንሽ ልጅ፥ «ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ከሆነ፥ እንዴት የእግዚአብሔር ልጅ ሊሆን ይችላል?» ብሎ ቢጠይቅህ እንዴት ትመልስለታለህ?
3. አንተ ወይም ሌሎች ሰዎች ደካማነታችሁን ችል ያላችሁት እንዴት ነው?
4. አንዳንድ ጊዜ የሚገባንን ያህል ለእግዚአብሔር ቃል ትኩረት የማንሰጠው ለምንድነው?
5. መልአክ ከመሆን ይልቅ ሰው መሆን የሚሻለው በምን መልኩ ነው? ሰው ከመሆን መልአክ መሆን የሚሻለውስ በምን መልኩ ነው?
6. እግዚአብሔር ወሰን የለሽ በሆነው ጥበቡ እኛን ለማዳን ሌላ መንገድ ሊመርጥ ሲችል ሰው ሆኖ ወደ ዓለም ለመምጣትና ለእኛ ለመሞት የመረጠው ለምን ይመስልሃል?
7. ዕብራውያን 4:15ን አንብብና ኢየሱስ ልክ እንዳንተ በምድር ላይ እንደተመላለሰ ማወቁ ምን ዓይነት ትርጉም እንደሚሰጥህ ግለጽ።
8. ፊልጵስዩስ 2:5–11 አንብብ። አሳባችን እንደ ክርስቶስ ቢሆን፥ ሕይወታችን ምን ይመስላል?

# ምዕራፍ ሦስት

## ከሙሴ የሚበልጥ

ዕብራውያን 1፡1–3

1. ዘጸአት 3፡1–13 እና ዮሐንስ 14፡6–14 አንብብ። ኢየሱስ ክርስቶስና ሙሴ ጥሪያቸውን በተቀበሉባቸው ሁኔታዎች መካከል ያሉትን ልዩነቶች ዘርዝር።

2. በአዲስ ሰማይና ምድር ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብረን ገዢዎች ስንሆን፥ ምን ዓይነት ተግባራት የምናከናውን ይመስልሃል?

3. የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ወደ እግዚአብሔር የጸጋ ዙፋን በድፍረት እንድንቀርብ ያስችለናል። ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት መንገድ ይኼ ነው? ካልሆነ፥ ወደኋላ የሚይዘን ምንድን ነው?

4. ቄርዝቢ፥ «ጸሐፊው እነዚህ መከራ የሚቀበሉ ቅዱሳን መታገሥ ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ ገጠመኞቻቸው ደስ እንዲሰኙበት መክሯቸዋል» ብለዋል። በሚያልፍባቸው መንገዶች ሊደሰት ሲገባው ጥርሱን ነክሶ ለመታገስ የሚሞክር ሰው ምልክቶች ምንድን ናቸው?

5. በመንፈሳዊ ሕይወትህ የምትደናቀፈው ከመውደቅ፥ ከመጠራጠር ነው ወይስ ካለማመን የተነሣ ነው?

6. እስራኤላውያን አገራቸውን በእጃቸው ለማስገባት ብዙ ጦርነቶችን ተዋግተዋል። ለነዚህ ጦርነቶች የአሁኑ ዘመን አቻዎች ሊሆኑ የሚችሉ ትግሎች ምንድን ናቸው?

7. በመንፈሳዊ ሕይወትህ ተጨማሪ «ዕረፍት» ለማግኘት የምትፈልገው እንዴት ነው?

8. የክርስቶስ ሞት በከነዓን እንድናርፍ አድርጎን ሳለ፥ በምድረ በዳ የምንቅበዘበዘው ለምንድን ነው?

9. ከዚህ ዓለም ተገላግለህ በመንግሥተ ሰማያት ያለውን እረፍት እንድትናፍቅ የሚያደርግህ ነገር ምንድን ነው?

## ምዕራፍ አራት

# ኢየሱስ ከሊቀ ካህናቱ አሮን ይበልጣል

ዕብራውያን 4፡14–5፡10

1. ዕረፍት ስለስፈነበት ሁኔታ ስታስብ፥ ወደ አእምሮህ የሚመጣው ምስል ምንድነው?
2. ፍጹም የሆነ ካህን እንዲኖርህ ብትፈልግ፥ ባሕርዩ ምን እንዲመስል ትፈልጋለህ?
3. ዘጸአት 30፡1–10ን አንብብ። የክርስቶስ የሊቀ ካህንነት ሚና ከመሥዋዕቱ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?
4. ዘጸአት 26፡31–35 እና ማቴዎስ 27፡50–51 አንብብ። የተቀደደው የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከዕለት ተዕለታዊ ሕይወትህ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ አንዳንድ ምሳሌዎችን ጥቀስ።
5. ቄርዝቢ፥ «እግዚአብሔር በምሕረቱ እንደሚገባን አይከፍለንም። በጸጋው ደግሞ የማይገባንን ይሰጠናል» ብለዋል። የእግዚአብሔር ምሕረትና ጸጋ በሕይወትህ የተገለጡት እንዴት ነው?
6. የክርስቶስ ካህንነትና በንጉሥነት ላንተ ሕይወት ያለውን ትርጉም ግለጽ።
7. ራሳችንም ኃጢአት እየሠራን አንዳንድ ጊዜ ለሌሎች ምሕረትን ለማድረግ የምንቸገረው ለምንድን ነው?
8. ከእግዚአብሔር የተለየህ ወይም የራቅህ መስሎ የተሰማህን ጊዜያት አስታውስ። ለክርስቶስ በመስቀል ላይ ከእግዚአብሔር መለየት ምን ይመስል እንደነበር ግለጽ።
9. ክርስቶስ ሞትን እንደቀመሰው ላላጠፋህበት ጉዳይ መቀጣት ምን ዓይነት ስሜት ያሳድራል?
10. ክርስቶስ ሊቀ ካህንህ ሆኖ ካቀረበው መሥዋዕት ልብህን በጣም የሚነካው የትኛው ነው?

## ምዕራፍ አምስት

# መጻተኞች ወደ ፊት በመገስገስ ዕድገት ማሳየት አለባቸው

**ዕብራውያን 5፡11–6፡20**

1. በመንፈሳዊ ሕይወትህ እያደግህ መሆንህን ወይም አለመሆንህን እንዴት ታውቃለህ?

2. ለራሳችን መንፈሳዊ ዕድገት ኃላፊነት ልንወስድ የምንችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

3. ብዙውን ጊዜ ራሳችንን ጭራሽ ወድቀን እስከምንገኝ ድረስ፥ ከእግዚአብሔር ቃል ምን ያህል እንደራቅን አናውቅም። የእግዚአብሔርን ቃል ወደመስልቸት የሚያደርሱትን የመጀመሪያ ደረጃዎች እንዴት ትገልጻቸዋለህ?

4. በእግዚአብሔር ቃል ጠንካራ ምግብነት ማለትም «አጥንትነት»ና ወተትነት መካከል ስላለው ልዩነት በራስህ ቃላት ግለጽ።

5. በግብጽና በከነዓን፥ በስቅለትና በፋሲካ መካከል እንድንዋዥቅ፥ ማለትም በጸጋው የዳንን ሆነን በትንሣኤው ሕይወት ደስ እንዳንሰኝ የሚያደርገን ምንድን ነው?

6. በእምነታቸው ጠንካሮች እንደነበሩና በኋላ ግን እንደወደቁ የምታውቃቸውን ሰዎች አስብ። እነዚህ ሰዎች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከቃሉ እንደወደቁ ከተገለጹት ሰዎች ጋር እንዴት ይመሳሰላሉ? አንተስ ደኅንነታቸውን ትጠራጠራለህ?

7. ያለ ምንም ቅድመሁኔታ መወደድህን ማወቅህ ምን ዓይነት ስሜት ያሳድርብሃል?

8. ደኅንነትህን እንደምታጣ ብታስብ፥ በሕይወትህ ውስጥ ምን ለውጥ ይኖራል?

9. ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንተ መልሕቅ የሆነባቸውን አንዳንድ መንገዶች ዘርዝር።

10. ከእግዚአብሔርና ከቃሉ እንድትወድቅ የሚያደርጉ ነገሮች ምንድን ናቸው?

# ምዕራፍ ስድስት

## ምሥጢራዊ መልከ ጼዴቅ

ዕብራውያን 7

1. ዘፍጥረት 14፡17-20 እና መዝሙር 110፡4-5ን አንብብ። ስለ መልከ ጼዴቅ ከእነዚህ ጥቅሶች ላይ ምን ዓይነት ዝርዝር አሳቦችን ልትገነዘብ ትችላለህ?
2. በራስህ ሕይወት፥ በጽድቅና ሰላም መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ያየኸው እንዴት ነው?
3. ሕግ ለሙሴ ከመሰጠቱ በፊት ሕዝቡ ለእግዚአብሔር አሥራት የከፈሉበትን ምክንያት ስታስብ ያንተ አመለካከት ምንድን ነው?
4. ሌዋውያን ካህናት የነበሩት በባሕርያቸው ሳይሆን በዘር ሐረጋቸው ነበር። ይህ ሁኔታ ቤተ መቅደስ ላይ ምን ዓይነት ችግሮችን ያስከትል ነበር?
5. ክርስቶስ ሕግን ያስወገደው ለምን ይመስልሃል? የሕጉ አስፈላጊነት ስላበቃ ነበር?
6. ባሕርያችን ለብሉይ ኪዳን ሕግጋት የማይገዛ ከሆነ፥ ታዲያ በምን ይገዛል?
7. ኢየሱስ ክርስቶስ የማይሞት ለመሆኑ ያለንን ዋስትና ግለጽ።
8. ኢየሱስ ክርስቶስ ባስወገደው ብሉይ ኪዳንና ባስገኘው «የተሻለ ኪዳን» መካከል ያሉት ልዩነቶች ምን ምንድን ናቸው?
9. ክርስቶስ በእኛ ምትክ ለእግዚአብሔር እንደሚማልድልን ብንገነዘብ፥ ሕይወታችን ከሚለወጥባቸው መንገዶች አንዳንዶቹን ጥቀስ።

# ምዕራፍ ሰባት

# የሚሻል ቃል ኪዳን

ዕብራውያን 8

1. ሥነምግባራዊ ንጽሕና ያለው ሰው ምን ዓይነት ባሕርይና አኗኗር ይኖረዋል?
2. ክርስቶስ እኛን የማዳን ሥራው ስለተጠናቀቀ እነሆ በሰማይ ተቀምጧል። እኛስ እርሱ የሰጠንን መዋጀት ለመቀበል ድርሻችንን የምንወጣው እንዴት ነው? ከእኛስ ምን ይጠበቃል?
3. እንደ አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ምን ቃል ኪዳን ገብተሃል?
4. ዘፍጥረት 17፡1–12 እና ቆላስይስ 3፡10–18 አንብብ። እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ የእርሱ ድርሻ እንደሆነ ተስፋ የገባልን ነገር ምንድን ነው?
5. አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር በገባው ቃል ኪዳን ውስጥ ግርዛት የነበረው አስተዋጽኦ ምን ነበር?
6. በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ያሉትን ልዩነቶች ግለጽ።
7. የእግዚአብሔር ጸጋ በክርስቶስ በኩል መገለጡ፥ ብሉይ ኪዳንን የለወጠው እንዴት ነው?
8. ማቴዎስ 5፡27–32 አንብብ። ክርስቶስ ለአድማጮቹ በውጪአዊና በውስጣዊ ማስረጃዎች አማካኝነት ስለ አዲስ ኪዳን የተናገራቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
9. በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔርን ፍቅርና ይቅርታ የምትቀበልበት መንገድ፥ አንድ እስራኤላዊ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ይቅርታ ከሚቀበልበት መንገድ የሚለየው እንዴት ነው?
10. ይህ አዲስ ኪዳን ሊታደስ ወይም በሌላ ሊለወጥ የማያስፈልገው ለምንድን ነው?

# ምዕራፍ ስምንት

# የሚበልጥ ቤተ መቅደስ

ዕብራውያን 9

1. በምድራዊና በሰማያዊ ቤትህ መካከል ሚዛን ለመጠበቅ አስቸጋሪ የሚሆንብህ ለምንድን ነው?
2. የዕብራውያን የመገናኛ ድንኳን በነበረበት ወቅት፥ እግዚአብሔር በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ይኖር ነበር። ዛሬ ግን እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ይኖራል። ከዚህ አንጻር፥ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ከእስራኤላውያኑ የሚለይባቸውን አንዳንድ ተግባራዊ መንገዶች ዘርዝር።
3. እንደ እግዚአብሔር የመኖሪያ ስፍራ፥ የመገናኛው ድንኳን ውስንነቶች አለመብቃት ምን ምን ነበሩ?
4. እንደ እግዚአብሔር የመኖሪያ ስፍራ፥ የሕይወታችንና የልባችን ውስንነቶች አለመብቃት ምን ምንድን ናቸው?
5. የምሕረት መቀመጫው ለእስራኤላውያን ኃጢአታቸውን ለመሸፈን የፈሰሰውን ደም ያስገነዝብ ነበር። በክርስቶስ ደም ስላገኘኸው ምሕረት የሚያስገነዝቡህ ነገሮች ምንድን ናቸው?
6. የክርስቶስ ደም ኃጢአታችንን ከመሸፈን ይልቅ ያስወግደዋል። ኃጢአትህ ከመወገድ ይልቅ ተሸፍኖ ቢሆን ኖሮ ሕይወትህ የተለየ ሊሆን ይችል እንደነበር ይሰማሃል?
7. የዕብራውያን ክርስቲያኖች፥ ክርስቶስ ካሳያቸው አዲስ መንገድ ወደ አይሁዳዊ የሃይማኖት ሥርዓት ለመመለስ ተፈትነው ነበር። እግዚአብሔር እንድታደርገው ያላዘዘህ ሆኖ ሳለ፥ ይበልጥ ስለሚመቹህ ልታደርጋቸው ዝንባሌ የሚያሳድሩብህን አንዳንድ ነገሮች ዘርዝር።
8. በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ይገኙ የነበሩትን የአምልኮ ዕቃዎች ዘርዝር። እግዚአብሔር በነዚህ ዕቃዎች አማካኝነት ለእስራኤላውያን ምን ዓይነት ትምህርት ለማስተላለፍ የፈለገ ይመስልሃል?

# ምዕራፍ 9

# ከፍተኛ መሥዋዕት

### ዕብራውያን 10

1. የክርስቶስ የደኅንነት ተግባር «የተፈጸመ ሥራ» መሆኑን እንዳንቀበል የሚያደርገን ምንድን ነው?
2. ቄርዝቢ፥ «ኃጢአተኞች የሆንነው ኃጢአትን ስለምንሠራ አይደለም። ይልቁንም ኃጢአተኞች ስለሆንን ኃጢአትን እንሠራለን» ብለዋል። ከዚህ አሳብ ጋር የምትስማማባቸውን ወይም የማትስማማባቸውን መንገዶች ዘርዝር።
3. የኃጢአት መሥዋዕቶች ኃጢአትን ለማስወገድ ሳይሆን፥ ለሕዝቡ ኃጢአታቸውን ለማስታወስ አገልግለዋል። በዕለታዊ ሕይወትህ ኃጢአተኛ ሰው መሆንህን የሚያሳዩ ምን ምን ነገሮች ያጋጥሙሃል?
4. ደም የመሥዋዕት አስፈላጊ ክፍል የሆነው ለምንድን ነው?
5. ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት የምትናፍቃቸውን አንዳንድ ነገሮች ዘርዝር።
6. እግዚአብሔር «ቀጥቶኛል» ብለህ ስላመንህበት ጊዜ አስብ። ከዚያም በሕይወትህ ላይ የተከሰተውን ሁኔታ እንዴት ተገነዘብህ?
7. ዕንባቆም 2፥4፥ «ጻድቅ በእምነት ይኖራል» ይላል። ለአንተ «በእምነት መኖር» ማለት ምን ማለት ነው?
8. በእምነት ያለመኖር አንዳንድ ምሳሌዎች ምንድን ናቸው?
9. በዚህ ሳምንት የሚያጋጥሙህንና እምነትህን ሊጠይቁ የሚችሉትን ነገሮች ዘርዝር።

# ምዕራፍ አሥር

## እምነት—በዓለም ታላቁ ኃይል

ዕብራውያን 11

1. በእምነት የምትቀበላቸው የማይታዩ ነገሮች ምንድን ናቸው?
2. ቄርዝቢ ቃየን ሃይማኖተኛ እንጂ ጻድቅ እንዳልነበረ ገልጸዋል። በእነዚህ ሁለት ነገሮች መካከል ያሉትን ልዩነቶች አብራራ።
3. አንድ ሁኔታ ምን እንደሚያስከትል ሳታውቅ ለመጠበቅ የተገደድህባቸውን ጊዜያት አስብ። ያ በእምነትህ ላይ ተጽእኖ ያሳደረው እንዴት ነው?
4. ረዓብ ስለ እግዚአብሔር የተናገረችውን (ኢያሱ 2፡8–14) እስራኤላውያን ከተናገሩት (ዘዳግ. 1፡27–28) ጋር አነጻጽር። በረዓብና በእስራኤላውያን እምነት መካከል የነበረውን ልዩነት እንዴት ትገልጸዋለህ?
5. በቁጥር 36 ለእምነታቸው ተአምራት ወይም ነፃ የመውጣት ዕድል ስላላገኙት «ሌሎች» አስብ። እነዚህ ሰዎች መከራ ተቀብለው ሞተዋል። ከመከራህ የምትወጣበትን መንገድ ባያዘጋጅ እንኳ በእምነትህ መጽናት የተከበረ ተግባር የሚሆነው ለምንድን ነው?
6. አንድ ሰው እግዚአብሔር እንደሚፈውሰው አምኖ እየጸለየ ሳይፈወስ ቢቀር፥ ምክንያቱ ምንድነው ትላለህ? ከራስህና ከመጽሐፍ ቅዱስ ምክንያቶችን ጥቀስ።
7. በዓለማችን ውስጥ ብዙ ሰዎች ለእምነታቸው የሚሰደዱት ለምንድን ነው?
8. የአንድ ሰው እምነት ሁኔታውን ሲለውጥ የተመለከትህበትን ሁኔታ ግለጽ።
9. «ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም።» ለዚህ እውነት ያንተ ምላሽ ምንድነው?

# ምዕራፍ አሥራ አንድ

## ሩጫህን ቀጥል!

ዕብራውያን 12

1. መንፈሳዊ ሕይወትህ ከአትሌቲክስ ውድድር ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?
2. ሩጫህን ለመሮጥ ተስፋ በምታደርግበት መንገድ፥ እንዲሮጡ የምታስባቸው ሌሎች ሰዎች እነማን ናቸው?
3. በመንፈሳዊ ሕይወትህ ወደኋላ የሚጎትቱህን ነገሮች ዘርዝር።
4. ወደኋላ የሚጎትቱንን ነገሮች እንዳንጥል የሚያግደን ምንድን ነው?
5. ከኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፥ በመንፈሳዊ ሕይወትህ እንዴት ወደፊት መሄድ እንዳለብህ እንድታውቅ የሚረዱህ ነገሮች የትኞቹ ናቸው?
6. ሯጮች የፍጻሜውን መስመር ወደፊት አሻግረው በማየት የሚያገኟቸውን ሽልማቶች (ቁሳዊ ማቴሪያል ወይም ሌላ) ተስፋ ያደርጋሉ። እኛስ ይህንን የክርስትና ሕይወት ሩጫ ጨርሰን፥ ለማግኘት የምንፈልገው ነገር ምንድን ነው?
7. እግዚአብሔር ሊቀጣን የሚችልባቸውን አንዳንድ መንገዶች ግለጽ።
8. በወደፊት ተስፋ ላይ ማተኮር ወደ ኋላ ከመመልከት እንዴት እንደሚለይ ከራስህ ሕይወት አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ።
9. በእምነት ሩጫህ ውስጥ፥ የእግዚአብሔር ጸጋ ለውጥን የሚያመጣው እንዴት ነው?
10. ወደፊት ለመመልከትና ሩጫውን ለመጨረስ እርስ በርሳችን እንዴት ልንረዳዳ እንችላለን?

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት

# እምነታችሁ ፍሬ እያሳየ ነው

ዕብራውያን 13

1. እንደ ቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ዛሬም በአብያተ ክርስቲያናቶቻችን ውስጥ እንግዶችን መቀበል አስፈላጊ የሚሆነው እንዴት ነው?
2. በምቾት የታጠረ ክርስትና የሚያስከትላቸው አደጋዎች ምንድን ናቸው?
3. ሁልጊዜም በአሳባቸው ባንስማማም እንኳ፥ ዛሬ መንፈሳዊ መሪዎቻችንን ልናከብር የምንችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?
4. ከመንፈሳዊ መሪዎች መልካም ነገርን በመማርና፥ እንደዋና መሪ አድርጎ በከፍተኛ ደረጃ በእነርሱ ላይ ያለአግባብ በመደገፍ መካከል ያለውን ሚዛን እንዴት ልንጠብቅ እንችላለን?
5. እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመኖር ከአሁኑ ዘመን ሃይማኖታዊ ሥርዓት መውጣት እንደሚያስፈልግ የምታስባቸውን መንገዶች ዘርዝር።
6. ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት እንዳንሰጥ ከፊታችን የሚቆመው መሰናክል ምንድን ነው?
7. ያለንን ለሌሎች ማካፈል ለወንጌል አገልግሎት ያለውን ድርሻ ግለጽ።
8. እግዚአብሔር ወደ መንፈሳዊ ብቃት የሚያደርሰን እንዴት ነው?
9. በዘላለማዊ ቃል ኪዳን ከእግዚአብሔር ጋር የምንተባበረው ወይም የምንቆራኘው እንዴት ነው?
10. እምነትህ በሚናወጥ ዓለም ውስጥ ጸንተህ እንድትቆም የሚያስችልህ እንዴት ነው?

## ወደ አማርኛ ተተርጉመውና ታትመው በስርጭት ላይ ያሉ በዋረን ዌርዝቢ የተጻፉ የ«. . . ሁን» ተከታታይ መጻሕፍት፥

1. ለጌታ የተገዛህ ሁን (የማቴዎስ ወንጌል)
2. ርኅሩኅ ሁን (ሉቃስ 1–13)
3. የበረታህ ሁን (ሉቃስ 14–24)
4. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተመላለስ (የሐዋርያት ሥራ 1–12)
5. ደፍረህ መስክር (የሐዋርያት ሥራ 13–28)
6. ጠቢብ ሁን (1ኛ ቆሮንቶስ)
7. ተጽናና (2ኛ ቆሮንቶስ)
8. አርነት መውጣት (ገላትያ)
9. ፍለጋ የሌለውን ባለጸግነት ውረስ (ኤፌሶን)
10. ደስተኛ ሁን (ፊልጵስዩስ)
11. ፍጹም ሁን (ቆላስይስ)
12. ለምጽአቱ ተዘጋጅ (1ኛ እና 2ኛ ተሰሎንቄ)
13. ታማኝ ሁን (1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ፥ ቲቶ፥ ፊልሞና)
14. በማየት ሳይሆን በእምነት ተመላለስ (ዕብራውያን)
15. ንቃ! (2ኛ ጴጥሮስ፥ 2ኛ ና 3ኛ ዮሐንስ፥ ይሁዳ)
16. እውነተኛ ሁን (1ኛ ዮሐንስ)
17. በብስለት ማደግ (የያዕቆብ መልእክት)
18. ድል አድራጊ ሁን (የዮሐንስ ራእይ)